# የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር

የዜግነት ክብር በኢትዮጵያችን ፀንቶ፣
ታዬ ሕዝባዊነት ዳር እስከዳር በርቶ::
ለሰላም፣ ለፍትህ ለሕዝቦች ነፃነት፣
በእኩልነት በፍቅር ቆመናል ባንድነት::
መሠረተ ፅኑ ሰብዕናን ያልሻርን፣
ሕዝቦች ነን ለሥራ በሥራ የኖርን::
ድንቅ የባህል መድረክ የአኩሪ ቅርስ ባለቤት፣
የተፈጥሮ ፀጋ የጀግና ሕዝብ እናት፣
እንጠብቅሻለን አለብን አደራ፣
ኢትዮጵያችን ኑሪ እኛም ባንቺ እንኩራ::

## ይህን መፅሐፍ በጥንቃቄ ያዝ/ያዥ




- ይህ መጽሐፍ የትምህርት ቤትህ/ቤትሽ ንብረት ነው::
- መጽሐፉ እንዳይበላሽ ወይንም እንዳይጠፋ በጥንቃቄ ያዝ/ያዥ::
- ቀጥሎ መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ የሚረዱ 10 ነጥቦች ቀርበውልሃል/ቀርበውልሻል::

1. መጽሐፉን እንደ ኘላስቲክ፣ ጋዜጣ ወይንም መሰል ወረቀቶች በመጠቀም ሸፍን/ሸፍኝ::
2. ምንጊዜም መጽሐፉን በንፁህ እና ደረቅ ቦታ አስቀምጥ/አስቀምጪ::
3. መጽሐፉን በምትጠቀምበት/በምትጠቀሚበት ወቅት እጆችህ/እጆችሽ ንፁህ መሆን አለባቸው::
4. በመጽሐፉ ሽፋን ላይ ወይንም በውስጥ ገጾች ውስጥ አትፃፍ/አትፃፊ::
5. ለመጽሐፉ የገፅ ማስታወሻ መያዝ ሲያስፈልግ ቁራጭ ወረቀት ተጠቀም/ተጠቀሚ::
6. ከመጽሐፉ ውስጥ ገጾችን ወይንም ስዕሎች በፍፁም ቀደህ/ቀደሽ አታውጣ/አታውጪ::
7. የተቀደዱ ገጾች ሲኖሩ በማጣበቂያ ወይንም በኘላስተር ጠግን/ጠግኝ::
8. መጽሐፉን ከትምህርት ቤት ቦርሳህ/ቦርሳሽ ውስጥ በምታስገባበት/በምታስገቢበት እና በምታስወጣበት/በምታስወጪበት ጊዜ ጥንቃቄ ውሰድ/ውሰጂ::
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው በምታቀብልበት/በምታቀብይበት ወቅት ጥንቃቄ አድርግ/አድርጊ::
10. አዲስ መፅሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ በምትጠቀምበት/በምትጠቀሚበት ወቅት በመጀመሪያ መጽሐፉን በጀርባው አስቀምጥ/አስቀምጭ:: ቀጥሎ በአንድ ጊዜ ጥቂት ገፆችን ብቻ ግለጥ/ግለጭ:: መጽሐፉ የሚታጠፍበት ገፅ ላይ በዝግታ ጫን በማድረግ አስተካክል/አስተካክይ:: ይህም ሽፋኑ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዲቆይ ይረዳል::

# የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት

## የተማሪ መጽሐፍ

## 8ኛ ክፍል


**ፀሐፊዎች፡-**

1. አቶ ሸዋቀና ቸርነት
2. አቶ ቦጋለ ስብሃቱ
3. አቶ አሰግደው ተስፋዬ
4. አቶ ተስፋዬ ከፋለ
5. አቶ ጌታቸው በለጠ
6. ወ/ሮ ፀሐይ መላኩ
7. ወ/ሮ ውዳላት ገዳሙ
8. ወ/ሮ የዝና ወርቁ
9. ወ/ሮ አጋረደች ጀማነህ
10. አቶ ብቃለ ሥዩም
11. አቶ የሻው ተሰማ

**አዘጋጆችና አርታኢአን፡-**

አቶ ግርማ አለማየሁ
አቶ ዳንኤል አበበ
አቶ ቱጁባ በቃና



© MoE FDRE Ethiopia
Not to be republished



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

AL GHURAIR
PRINTING AND PUBLISHING LLC

© ትምህርት ሚኒስቴር
የመጀመሪያ እትም 2003 ዓ.ም

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

© MoE, FDR Ethiopia
Not to be republished

ISBN 978-99944-2-056-8

# ማውጫ

ገፅ


ምዕራፍ አንድ፡- ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ........................................ 1
ምዕራፍ ሁለት፡- የሕግ የበላይነት ........................................ 13
ምዕራፍ ሦስት፡- እኩልነት ........................................ 25
ምዕራፍ አራት፡- ፍትሐዊነት ........................................ 36
ምዕራፍ አምስት፡- የሀገር ፍቅር ........................................ 48
ምዕራፍ ስድስት፡- የኃላፊነት ስሜት ........................................ 62
ምዕራፍ ሰባት፡- ጠንካራ የሥራ ባህል ........................................ 71
ምዕራፍ ስምንት፡- ራስን መቻል ........................................ 82
ምዕራፍ ዘጠኝ፡- የቁጠባ ባህል ........................................ 94
ምዕራፍ አሥር፡- ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ........................................ 103
ምዕራፍ አሥራ አንድ፡- ዕውቀትን መሻት ........................................ 114


© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

# ምሥጋና

*ይህ መጽሐፍ ጥራቱ የተጠበቀ ሆኖ እንዲወጣ በርካታ ሰዎች ያልተቆጠበ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል። Ms. Myra Murphy ለመጽሐፉ አዘጋጆች ተማሪ አሳታፊና ምቹ የሆነ የመጽሐፍ አዘገጃጀት ሥልጠና በመስጠት ከፍተኛ ድጋፍ አድረገዋል። Ms. Myra Murphy በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ወጪያቸውን የሸፈነው የአውሮፓ ዩኒየን በመሆኑ ከፍተኛ ምሥጋና ይገባዋል።*

*በመጽሐፉ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉትን የተለያዩ ምስሎች በመለገስ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ፕሬስ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ባህልና ቱሪዝም ኮሚሽን፣ በወቅቱ የነበረው የማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበርና የኢትዮጵያ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ላደረጉት ድጋፍ ምሥጋና ሊቸራቸው ይገባል።*

*በአጠቃላይ ትምህርት የሥርዓተ ትምህርት መመሪያ ውስጥ የሚገኘው የመማሪያ ማስተማሪያ አዘገጃጀት ዩኒት መጽሐፉን ለማሣተም የሚያስችል የጨረታ ሰነድ በማዘጋጀትና ለዓለም ባንክ በመስጠት ላደረገው አስተዋጽኦ ሊመሰገን ይገባዋል።*

*በተለይም የቪኤሶ ኢትዮጵያ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አባል የሆኑት Mrs. Helen Papworth መጽሐፉን ከወትሮ ለየት ባለመልኩ ፎርማት በማድረግ ልዩ አድናቆት የሚሰጠው ተግባር በማከናወናቸው ሊመሰገኑ የሚገባ ሲሆን፣ የቪኤሶ ኢትዮጵያም የበጎ ፈቃደኞች ወደሚኒስቴር መሥሪያ ቤታችን በመምጣት ሙያቸውን እንዲያካፍሉን በማድረጉ ከፍተኛ ምሥጋና ስናቀርብ በከፍተኛ ደስታ ነው።*

# ምዕራፍ አንድ
# ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤**

- የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታን ምንነት ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ፡፡
- የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ትረዳለህ/ትረጃለሽ፡፡
- የዴሞክራሲ ተቋማትን አስፈላጊነት ትገነዘባ ለህ/ትገነዘቢያለሽ፡፡
- ልዩነቶችን አቻችሎ በሰላም አብሮ የመኖር ጠቀሜታን ትረዳለህ/ ትረጃለሽ፡፡
- የፌደራልና የክልል መንግሥታትን አንድነትና ልዩነት ታውቃለህ/ታውቂያለሽ፡፡

## 1.1 የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፤

### 1.1..1. የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ምንነት፣



ሥዕል 1.1 የሥነዜጋና ሥነምግባር ክበብ አባላት በሥልጠናው ላይ በንቃት ሲሳተፉ

✓ *እዚህ በላይ ያለውን ሥዕል መሠረት በማድረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግለጹ፡፡*

የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሲባል ዴሞክራሲ እንዲሰፍን እና እንዲዳብር የሚረዱ ተግባሮች መኖራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የዴሞክራሲ ሥር ዓት ግንባታ በዋናነት ዴሞክራሲያዊ ዜጋን የመ ቅረጽ እና የዴሞክራሲ ባህልን የማዳበር ወሳኝ ተግባሮች የማከናወን ሂደትን ያካትታል፡፡ ዴሞክ ራሲያዊ ዜጋ መቅረጽ የሚከተሉት መገለጫዎች ያሉት ዜጋ ማፍራት ማለት ነው፣

ሀ. የዜጐችን ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ የሚያከብርና የሚያስ ከብር፣ ግዴታዎቹን በሚገባ የሚያውቅና በተገቢው መንገድ የሚወጣ፣
ለ. ልዩነቶች የዴሞክራሲ ሥርዓትን ለመገን ባት ጠቃሚ መሆናቸውን አምኖ የተቀበለ፣
ሐ. የዴሞክራሲ መሠረታዊ ዓላማና የሚያስገ ኘው ጥቅም በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በአመለካከት ወዘተ ልዩነት ያላቸው ሕዝቦች ልዩነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በጋራ ዓላማ ዙሪያ ተቻችለው በሰላምና በፍቅር መኖርን ማስቻል መሆኑን ጠንቅቆ የሚያውቅ፣
መ. በህግ የበላይነት የሚያምን፣
ሠ. የሥራ ተነሳሽነትና የሀገር ፍቅር ያለው፡፡

*የዴሞክራሲ ባህልን ማዳበር በርካታ መገለጫ ዎች አሉት፡፡ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-*

1. ሰዎች በአመለካከትም ሆነ በፍላጐት ልዩነቶች እንዳሏቸው በሚገባ በማወቅ የሌሎችን ሃሳ ብና አመለካከት ማክበር ወይም በትዕግሥት መቀበል፣
2. አለመግባባቶችን በሠላማዊ መንገድ፣ በውይ ይትና በመተማመን መፍታት፣
3. በውይይት ሊፈቱ የማይችሉ ግጭቶች ሲያጋ ጥሙ ለዳኝነት ማቅረብና የብዙሃኑን ውሳኔ በፀጋ ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረግ፡፡

**ጠይጠጀ 1**

❓ ***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማለት ምን ማለት እንደሆነ አራት ምሳሌዎችን በማቅ ረብ አስረዱ፡፡
2. ዴሞክራሲያዊ ዜጋን ለመፍጠር የሚቻለው እንዴት ነው? ተወያዩበት፡፡
3. የዴሞክራሲ ባህልን ለማዳበር የሚቻለው እንዴት ነው? ተወያዩበት፡፡

የዴሞክራሲ ሥርዓት የዜጎች ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች እንዲሁም የብሔሮች፣ የብሔረሰቦች እና የሕዝቦች የእኩልነት መብት የሚከበርበት ሥርዓት ነው:: ሕዝቡ በመረጣቸው መሪዎች የሚመራበት፣ በመረጣቸው መሪዎች ላይ እምነት ባጣ ጊዜ በሰላማዊ መንገድ የሚያወርድበት፣ ሌሎችን የሚመርጥበት እና የሚተካበት ነው:: በመሆኑም የዴሞክራሲ ሥርዓት የሥልጣን ባለቤት ሕዝቡ ራሱ መሆኑ የሚረጋገጥበት ነው::

***የቡድን ሥራ፣***

*የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን በተመለከተ በሀገራችን እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን ከተለያዩ ምንጮች መረጃ በመሰብሰብ ከሁለት ገፅ ባልበለጠ ፅሑፍ አቅርቡ::*

### 1.1.2 የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረቶች፣




ሥዕል 1.2 የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረቶች

- ✓ *ከዚህ በላይ ካለው ሥዕል ምን ተገነዘባችሁ?*
- ✓ *የዴሞክራሲ ሥርዓትን ለመገንባት እንደ መሠረት ወይም እንደ ማዕዘን ድንጋይ ሆነው የሚያገለግሉ ዋና ዋና ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝሩ::*

የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረቶች በርካታ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

#### ሀ. ለሕግ የበላይነት መገዛት፣

ለሕግ የበላይነት የመገዛት መርህ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ዋነኛው መሠረት ነው:: ይህን ለማለት የሚያስችሉ በርካታ ምክንያቶች ሲኖሩ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፣ መርሁ ሥልጣን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ብቻ እንዲያዝ ዋስትና ስለሚሰጥ ነው:: ለሕግ የበላይነት የመገዛት አስተሳሰብ ተግባራዊ ሲሆን ሥልጣን በነፃ የፖለቲካ ውድድር፣ ያለምንም ጫናና ማጭበርበር በሕዝብ ፍላጎትና ነፃ ምርጫ መሠረት መያዝ ይቻላል::

ሌላው ምክንያት መርሁ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲሁም የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች የእኩልነት መብቶች እንዲከበሩ ዋስትና ስለሚሰጥ ነው::

#### ለ. የሕዝቦች በመፈቃቀድ መኖርና የዜጎች መብቶች መጠበቅ፣

የሕዝቦች መፈቃቀድ በሌለበት የዴሞክራሲ ሥርዓት ሊገነባ አይችልም:: ምክንያቱም የሕዝቦች መፈቃቀድ ሲኖር ብቻ ነው በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በአመለካከት እና በመሳሰሉት ልዩነት ያላቸው ሕዝቦች ልዩነቶቻቸውን አቻችለው በሰላም ና በፍቅር መኖር የሚችሉት::

ልዩነቶችን ለመፍታትም ሆነ በልዩነቶች ውስጥ በአንድነት ተቻችሎ ለመኖር ተቀራርቦ መነጋገር፣ መወያየት፣ ሃሳብን በነፃ መግለፅ ያስፈልጋል:: ለዚህ ደግሞ የግድ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ይኖርባቸዋል:: የእነዚህ መብቶች መከበር ልዩነቶችን ለመፍታት ወይም ለመቻቻል ወሳኝ ሚና ይጫወታል::

#### ሐ. የእኩልነት መብቶች መከበር፣

የተለያዩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች በአንድ ላይ በሚኖሩባቸው ሀገራት የእኩልነት መብት መከበር መፈቃቀድ እንዲኖርና ሰላምና ፍቅር እንዲሰፍን ይጠቅማል:: የእኩልነት መብት መከበር ልዩነቶችን ለመፍታትም ሆነ በልዩነቶች ውስጥ በአንድነት ተቻችሎ ለመኖር ይረዳል::

#### መ. የመምረጥና የመመረጥ መብት መከበር፣

የዚህ መብት መከበር ሕዝቡ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በሚከተሉት ወሳኝ ተግባራት ውስጥ በንቃት እንዲሳተፍና የሥልጣን ባለቤት እንዲሆን ያስችለዋል::

ሀ. ማንኛውም ዕድሜው ለመምረጥና ለመመረጥ የደረሰ ጤነኛ ዜጋ በፆታ፣ በብሔረሰብ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት ወዘተ ምክንያት ልዩነት ሳይደረግበት በነፃነት እንዲሳተፍ፣
ለ. ህዝብ እራሱ በመረጣቸው እንደራሴዎች እንዲተዳደር፣
ሐ. በፖለቲካ ሥርዓቱ ውስጥ በራሱ ወይም እንደራሴዎቹ አማካኝነት እንዲሳተፍ፣ ያስችለዋል ::

ሕዝቡ ያለምንም ልዩነት ለመምረጥም ሆነ ለመመረጥ፣ የቀረቡትን አማራጮች አመዛዝኖ መወሰን ከሌሎች ወገኖች ጋር መወያየትና መከራከር

ከቻለ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታው እየጎለበተ መሄዱን የሚያመለክት ነው:: ምክንያቱም እነ ዚህ ተግባሮች የዴሞክራሲ ባህል መገለጫዎች በመሆናቸው ነው::

### ሠ. በራስ ቋንቋ የመጠቀም መብት መከበር፣

በራስ ቋንቋ የመጠቀም መብት መከበር የዴሞ ክራሲ ሥርዓት መሠረት የሆነበት ምክንያት ሕዝቡ የራሱን ጉዳይ በመወሰን ረገድ አስተ ርጓሚ ሳያስፈልገው ራሱ ማከናወን እንዲችል ስለሚያደርገው ነው:: ሕዝቡ በቋንቋው ከተጠ ቀመ ባህልና ታሪኩ ከተከበረለት ከሌሎች ጋር በውዴታ ተግባብቶ፣ ተፈቃቅዶና ተከባብሮ በጋራ ለመኖር ይችላል:: ይህም ዴሞክራሲያዊ ሀገራዊ አንድነት ለመፍጠር ያስችላል:: በራስ ቋንቋ የመ ጠቀም መብት መከበር ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ወሳኝ የሆነውን ሌላ መሠረት የዜጐች ንቁና ጠንካራ ተሳትፎን ለመፍጠርም ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታል::

### ረ. የዜጐች ንቁና ጠንካራ ተሳትፎ ማድረግ፣

ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ከዜጎች ንቁና ጠንካራ ተሳትፎ ውጭ በጥቂቶች ጥረት ብቻ ሊገነባ አይችልም:: የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታው እን ዲፋጠን ከተፈለገ መላው ኅብረተሰብ በዴሞክ ራሲ ሥርዓት ግንባታ እንቅስቃሴው ውስጥ በሥፋትና በንቃት መሳተፍ አለበት:: ለዚህም በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ በቀጥታ ተሳ ታፊ መሆንና ከታሳትፎው የበለጠ መማር፣ ጉድለቶችን እያስተካከሉና ጠንካራ ጎኖችን እያጎለ በቱ መሄድ የዴሞክራሲ ሥርዓቱን የበለጠ እያጐ ለበተው ይሄዳል::

### ሰ. የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ የመናገርና የመፃፍ መብቶች መከበር፣

የእነዚህ መብቶች መከበር ጠንካራ ፓርቲዎች እንዲፈጠሩና በንቃት መንቀሳቀስ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል:: የተለያዩ ጠንካራ ፓርቲ ዎች ከኖሩና በንቃት መንቀሳቀስ ከቻሉ ሕዝቡ የተለያዩ አማራጮች እንዲቀርቡለት እድል ያገ ኛል:: የእውነተኛ ዴሞክራሲ ገፅታ ብዙሃን ፓር ቲዎች የሚሳተፉበት ሥርዓት መሆኑ ነው:: ፓርቲዎች የሕብረተሰቡን ልዩ ልዩ ክፍሎች አመለካከቶችና ፍላጎቶችን መሠረት በማድረግ የሚቋቋሙ የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው:: እነሱም ተመሳሳይ አመለካከትና ፍላጎት ያላቸውን ዜጐች በአባልነት ይይዛሉ:: ፕሮግራማቸውን ቀርፀው ቢመረጡ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ለሕብ ረተሰቡ ያሳውቃሉ:: በዚህም ለሕዝቡ የተሻለ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ ወዘተ አማራ ጮች እንዲቀርቡ ያደርጋሉ:: ይህም የዴሞክራሲ ሥርዓቱ የበለጠ እንዲጐለብት ያደርጋል::

**መልመጃ ሥ**


***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. የዜጎች መብቶች መጠበቅና የሕዝቦች መፈ ቃቀድ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠ ረቶች ናቸው የሚባልበት ምክንያት ምንድ ነው? በምሳሌ አስረዱ::
2. የመሰብሰብ የመናገርና የመፃፍ መብቶች የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረቶች ናቸው የሚባልበት ምክንያት ምንድነው? ተወያዩበት::

***የቡድን ሥራ፣***

*ከላይ በተማራችሁት ርዕስ ሥር የተዘረዘሩት የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረቶች በሀገ ራችን በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ከተለያዩ ምንጮች መረጃ በመሰብሰብ ገምግሙና አቅርቡ:*

## 1.2 የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ስማስፈን የሚያስችሉ ዴሞክራሰያዊ ተቋማትና አስፈላጊነታቸው፤




ሥዕል 1.3 ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ስማስፈን የሚያስችሉ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት

- ✓ *ከዚህ በላይ የቀረበውን ሥዕል መሠረት በማድረግ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለማስፈን የሚያስችሉ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ምን ጠቀሜታ እንዳላቸው ግለፁ::*

**ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥበቃ ማድረግ ያስፈለገባቸው በርካታ ዓላማዎች አሉ:: ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፣**

ሀ. ሕገመንግሥቱ እውቅና የሰጣቸው መብቶች በአተረጓጐም ሒደትም ሆነ በሌሎች የተለያዩ መንገዶች ሳይሸራረፉ በአግባቡ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ፣

ለ. መብቶች በየትኛውም ቦታ በሚገኝ ማህበረሰብ ልማዳዊ አሠራር እንዳይጣሱ ማናቸውም ልማዳዊ አሠራሮች ከሕገመንግሥቱ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረኑ ከሆኑ ተፈፃሚነት እንዳይኖራቸው ለማድረግ ነው::

እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለማስፈን የሚያስችሉ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት መኖር አስፈላጊ ነው:: የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለማስፈን የሚያስችሉ ተቋማትን መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ በማለት ከፍሎ ማየት ይቻላል:: መንግሥታዊ የሆኑ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ፍርድ ቤቶች፣ ፖሊስ ጣቢያ፣ እምባ ጠባቂ ተቋም፣ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን፣ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ እና በመንግሥት ይዞታ ሥር የሚገኙ መገናኛ ብዙኃኖችን ያካትታሉ:: በሀገራችን ውስጥ የሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ዓለም ዓቀፍ የሲቪክ ማሕበራት፣ ሀገር በቀል ሲቪክ ማህበራትና በግል ይዞታ ሥር ያሉ መገናኛ ብዙኃኖችን ያጠቃልላሉ::
በአጠቃላይ ጠንካራ የሆኑ ዲሞክራሲያዊ ተቋማት የሕዝቡ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተከብረው ሕዝቡም የእነዚህ መብቶች ዋነኛ ተጠቃሚ መሆን የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር ስለሚያስችሉ በጣም አስፈላጊ ናቸው::

**ፍርድ ቤቶች:-** ፍርድ ቤቶች ከሌላው ከማንኛውም የመብቶች አስከባሪ ተቋማት በግንባር ቀደምትነት የሕግ የበላይነትን ሊያስከብሩ የሚችሉ ተቋማት ናቸው:: ፍርድ ቤቶች በተከራካሪ ወገኖች መካከል የሚነሱትን ክርክሮች ተመልክተው፣ ሕግን መሠረት በማድረግ ከማንኛውም አድልዎ ወይም ጥላቻ ውጭ ሚዛናዊ ዳኝነት እንዲሰጡ በሕገመንግሥት የሚቋቋሙ ናቸው:: የዳኝነት መሠረቱ ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው የሚለው ሐረግ ነው:: በፍርድ ቤቶች አሠራር በዘር በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ እና በመሳሰሉት ልዩነት አይደረግም::

**ፖሊስ:-** ፖሊስ በሕገመንግሥቱ የተረጋገጡትን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሳይሸራረፉ በማክበርና በሌሎችም እንዲከበሩ በማድረግ የሕዝብን ሰላምና ደህንነት የሚያረጋግጥ ተቋም ነው:: የፖሊስ ዋና ዓላማ የሀገሪቱን ሕገመንግሥትና ሌሎች ሕጎችን በማክበርና የሕዝቡን ተሳትፎ መሠረት አድርጐ ወንጀልን በመከላከል የሕዝብን ሰላማዊ ኑሮና ፀጥታ ማስጠበቅ ነው::

**የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን:-** የሰብዓዊ መብቶች እንዳይጣሱ ከመከላከል በተጨማሪ የሰብዓዊ መብታችን ተደፍሯል ብለው አቤቱታ የሚያቀርቡ ግለሰቦችን ቅሬታ ተቀብሎ ከመረመረ በኋላ ውሳኔ የሚሰጥ መብት አስከባሪ ተቋም ነው:: በመንግሥት የሚወጡ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ከዜጎች ሰብዓዊ መብቶች ጋር የማይቃረኑ መሆናቸውን ያረጋግጣል:: በፍ/ቤት በመታየት ላይ ካሉ ጉዳዮች በስተቀር የሰብዓዊ መብት መጣስን በተመለከተ አቤቱታዎችን ያለምንም ክፍያ ይመረምራል::

**የእምባ ጠባቂ ተቋም:-** የእምባ ጠባቂ ተቋም በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በደል ደርሶብናል በማለት ቅሬታ የሚያቀርቡ ግለሰቦችን አቤቱታ እየመረመረ ውሳኔዎችን የሚሰጥ መብት አስከባሪ ተቋም ነው:: ይህ ተቋም ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች ተግባራቸውን በሕጉ መሠረት ማከናወናቸውን ወይም ሥልጣናቸው ከሚፈቅድላቸው በላይ አልፈው መሥራታቸውን የሚከታተል ተቋም ነው:: የተቋሙ ዋና ዓላማ በሕግ የተደነገጉ የዜጎች መብቶች እና ጥቅሞች በአስፈጻሚው አካላት መከበራቸውን በማረጋገጥ የሕግ የበላይነትን መሠረት ያደረገ ጥራት፣ ቅልጥፍናና ግልፅነት ያለው መልካም የመንግሥት አስተዳደር እንዲሰፍን ማድረግ ነው::

**የፌደራል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣** በመልካም ሥነ ምግባር የታነፀ፣ ሙስናን የሚፀየፍ እና በንቃት የሚዋጋ ኅብረተሰብ ለመፍጠር የሚንቀሳቀስ ተቋም ነው:: ተቋሙ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርቶችን የማስፋፋት፣ የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሠራርን የመከላከል፣ የማጋለጥ፣ የመመርመርና እና የመክሰስ የመሳሰሉትን ተግባራት ያከናውናል::

**ሲቪክ ማኅበራት:-** ከመንግሥት አደረጃጀት ውጭ ያሉ ንቁና ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጐች በራስ ተነሳሽነትና በፈቃደኝነት የሚያቋቁሟቸው ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ ተቋማት ናቸው:: የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህሕላዊ ድርጅቶች፣ ወዘተ በሲቪክ ማህበራት እንደ አብነት የሚጠቀሱ ናቸው:: ሲቪክ

ማህበራት ግልፅነትን፣ ተጠያቂነትንና የሕዝብ ተሳታፊነትን በማጎልበት ኅብረተሰቡ የራሱን ችግር በራሱ መፍታት የሚያስችለው ሁለንተ ናዊ አቅም እንዲኖረው ከመርዳታቸው ባሻገር ኅብረተሰቡ በመንግሥት አሠራር ላይ ቁጥጥር እንዲያደርግ አቅሙን ይገነቡለታል::

*መገኛኛ ብዙኃን:-* በጥቅሉ ነፃና ሚዛናዊ ሆነው ያለውን ተጨባጭ እውነታ ለሕዝብ ማሳወቅና ማስተማር እንዲሁም በማንኛውም የሀገር ጉዳይ ላይ ሕዝቡ በእውቀት ላይ የተመሠረተ ውሳኔ ለመስጠት እንዲችል ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ የሚያቀርቡ ተቋማት ናቸው:: ከዚህም ባሻገር መገናኛ ብዙኃን በኅብረተሰቡ ውስጥ ባሉት በመንግሥትና በሌሎችም ድርጅቶች አሠራር ላይ እንደ እንባ ጠባቂ ሆነው ሕዝብን ለማገል ገል የሚሠሩ ተቋማት ናቸው::

የራዲዮና የቴሌቪዥን ሥርጭቶች የጋዜጣ እና የመጽሔት ሕትመቶች እየተስፋፉ ሲሄዱ የዜ ጎች መብቶች እንዲከበሩ ለማድረግ የሚጫወ ቱት ሚና ከፍተኛ እየሆነ ይሄዳል::

በአጠቃላይ የመብቶች ጥሰት በማወቅም ሆነ ባለ ማወቅ በተለያዩ ወገኖች ሊፈፀም ይችላል:: የመ ንግሥት ባለሥልጣናት ሥልጣናቸውን መከታ በማድረግ የዜጐችን መብቶች ሊጥሱ ይችላሉ:: ግለሰብ ዜጐችም በግጭት ወይም በሌላ ምክ ንያት የሌሎች ግለሰብ ዜጐች መብቶችን ሊጥሱ ይችላሉ:: ኅብረተሰቡም በኋላቀር ልማዳዊ አሠ ራር መብትን ሊጥስ ይችላል::

ዜጐችም ከእውቀት ማነስ የተነሳ ለመብቶቻቸው መደፈር ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ:: መብቴ ተነ ክቷል፣ መብቴ ተጥሷል ብሎ የመጠየቅ አቋም ከዕውቀትና ከግንዛቤ የሚገኝ በመሆኑ ይህ ዕው ቀት ከሌለ መብቶች መጣሳቸውን መገንዘብ አይቻልም::

ስለዚህ ይህን ሁሉ ችግር ለማቃለልና የዜጎች መብቶች በሚገባ የሚከበሩበትን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ለማፋጠን የሰብዓዊና የዴሞክ ራሲያዊ መብቶችን ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ተቋ ማት ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ::

**መልመጃ 3**

***የሚከተሉን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥበቃ የሚደረግላቸው ለምንድነው? ተወያዩበት?
2. በአካባቢያችሁ ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር የሚሠሩ ተቋማት ካሉ: ዝርዝራቸውንና ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለማስከበር እያንዳንዳቸው የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በፅሑፍ አቅርቡ::

***በቡድን በቡድን ሆናችሁ ቀጥሎ የቀረበውን ተግባር ሥሩ::***

*ከላይ በተማራችሁት ርዕስ ሥር የተዘረዘሩትን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለማስፈን የሚያስችሉ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ውስጥ ለቡድናችሁ በዕጣ የደረሳችሁ ተቋም በሀገራችን በኢትዮጵያ በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንደ ሚገኝ (ተቋሙ በአካባቢያችሁ ካለ ወደ ተቋሙ በመሄድ፣ ከሌለ ደግሞ ከተለያዩ ምንጮች መረጃ በመሰብሰብ) ገምግሙና አቅርቡ::*

## 1.3 ልዩነቶች (አለመግባባቶች) በሰላም የሚፈቱባቸው መንገዶች፤



ሥዕል 1.4 የጓደኛሞቹ ውይይት

- ✓ ከላይ ያለውን ሥዕል በማየት ተማሪዎቹ ምን እያደረጉ እንደሆነ ገምቱ::
- ✓ ከጓደኞችሁ ጋር በሃሳብ ብትለያዩ ወይም አለ መግባባት ቢፈጠር ልዩነቱን ወይም አለመ ግባባቱን በሰላም ለመፍታት ምን ታደርጋ ላችሁ?

### ሦሥቱ ጓደኞሞች

የ8ኛ «ለ» ክፍል ተማሪ የሆኑት ሐዋ፣ አስማ ረች እና አልማዝ ከክፍል ጓደኝነት ያለፈ ይቀራ ረባሉ:: የሚኖሩትም አንድ ሠፈር ነው:: ቅዳሜ እና እሁድ አንድ ላይ የሚያጠኑበት ፕሮግራም ለማውጣት ተስማሙ:: ፕሮግራሙን ለማዘ ጋጀት እርሳስና ወረቀት ይዘው ቁጭ አሉና መነ ጋገር ጀመሩ:: ሆኖም የሶስቱም ፍላጐት የተ ለያየ በመሆኑ ሶስቱም የሚስማሙበት ፕሮግ ራም ማዘጋጀት አቃታቸው::

መጀመሪያ ምን እናጥና? የሚለውን ለማስፈር አብርኸት ሂሳብ ስትል፣ ኩለኒ እንግሊዝኛ ትላለች፣ አስማረች ደግሞ የለም ሳይንስ ነው መሆን ያለበት ትላለች:: በዚህ ዓይነት ለቅዳሜ እና እሁድ የሚሆን የጥናት ፕሮግራም ማዘጋጀት ቀርቶ ወደ ፀብ እንዳይሄዱ ያሰጋል::

**ጠ|ጠጀ 4**

*በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሥሩ::*

1. እናንተ በሦሥቱ ጓደኛሞች ቦታ ብትሆኑ ይህን ልዩነት እንዴት ትፈቱታላችሁ?
2. ሦሥቱንም ሊያስማማ የሚችል የጥናት ፕሮግራም እንዴት ልታዘጋጁ ትችላላችሁ?

**ልዩነቶችን ወይም አለመግባባቶችን በሰላም ለመፍታት የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው::**

**ሀ. ውይይት:-**

ውይይት ማንኛውም ዓይነት አለመግባባት ወይም ልዩነት ሲፈጠር በጋራ ወደሚያስማማ ውሳኔ ላይ መድረስ በጣም አስፈላጊ ነው:: ውይይት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ወገኖች እርስ በርሳቸው ተቀራርበው በመካከላቸው ያለውን ልዩነት፣ አለመግባባት ወይም ግጭት ሊያስነሳ የሚችልን ጉዳይ በሁሉም ወገኖች ተቀባይነት ያለውን መፍትሔ ለመስጠት ጥረት የሚያደርጉበት ሂደት ነው:: ውይይት ለአለመግባባቶች መፍትሔ ለማፈላለግና ስምምነት ለመፍጠር ሲባል የሚከናወን ተግባር በመሆኑ ተወያዮቹ የየራሳቸውን አቋም ከመግለፅ ባሻገር የሌላውን ወገን በፅሞና ማዳመጥ ይጠበቅባቸዋል::

ውይይት የታለመለትን ግብ እንዲመታ ማለትም ልዩነትን ወይም አለመግባባትን በሁሉም ወገኖች ተቀባይነት ያለውን መፍትሔ አቅርቦ በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት ደግሞ መቻቻል እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው::

**ለ. መደማመጥ፣**

መደማመጥ ተወያይ ወገኖች አንዱ የሌላውን ሃሳብ በጥሞና፣ በትዕግሥት፣ በትህትና፣ በቅንነት ማድመጥ፣ መናገር የፈለገውን ተናግሮ ሳይጨርስ ጣልቃ ገብቶ ከማቋረጥ መታቀብና የመሳሰሉትን ያካትታል::

**ሐ. መቻቻል፣**

መቻቻል ደግሞ ተወያይ ወገኖች ጥሩ የመግባባትና የጓደኝነት መንፈስ በመፍጠር፣ እርስ በርስ በመከባበር፣ ግትርነትን፣ ኃይለኝነትንና ቁጡነትን ማስወገድን ያመለክታል:: ከዚህም ባሻገር መቻቻል አቋምን አለዝቦ ስምምነት ላይ ለመድረስ ዝግጁ መሆንን፣ አንዱ የሌላውን ስሜት እና አመለካከት ለመረዳት መሞከርን፣ ሁለቱም ወገኖች ድርቅ ካለ ክርክርና መወነጃጀል ርቀው በጋራ የሚረኩበት ስምምነት ላይ ለመድረስ የሚረዱ መፍትሔዎችን ለማፍለቅ መጣርን ወዘተ... ያካትታል::

**ጠ|ጠጀ 5**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

1. በተለያዩ ጊዜና ቦታ የሚፈጠሩ ልዩነቶችን ወይም አለመግባባቶችን በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት ምን ማድረግ ይጠበቅባችኋል? ተወያዩበት::
2. መወያየት፣ መደማመጥ፣ እና መቻቻል ልዩነቶችን ወይም አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚጫወቱትን ሚና ምሳሌዎችን በማቅረብ ማብራሪያ ስጡ::

## 1.4 የፌደራልና የክልል መንግሥታት፤

### 1.4.1 አንድነትና ልዩነት፣

- ✓ የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን አንድነት የሚያሳዩ ጉዳዮችን ግለፁ::

**አንድነት:-** የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግሥትና በክልሎች በጋራ መዋቀሩ ዋናው የፌዴራልና የክልል መንግሥታት አንድነት መገለጫ ነው:: ሌላው አንድ የሚያደርጋቸው ነጥብ የሥልጣን አካላት አወቃቀራቸው ተመሳሳይ መሆኑ ነው:: ይኸውም የፌደራል መንግሥት የራሱ የሆነ ሕግ አውጭ፣ ሕግ አስፈጻሚና ሕግ ተርጓሚ አካላት ሲኖረው በተመሳሳይ መልኩ የክልል መንግሥታትም የራሳቸው የሆነ የሕግ አውጭ፣ የሕግ አስፈጻሚና የሕግ ተርጓሚ አካላት አላቸው::

ሌላው የፌዴራል መንግሥትና የክልል መንግሥታት አንድነት መገለጫ ሁለቱም መንግሥታት የፌደራሉን ሕገመንግሥት ማክበርና መጠበቅ ዋነኛው ተግባራቸው መሆኑ ነው::

**ልዩነት:-** የፌዴራል መንግሥትና የክልል መንግሥታት የመመሳሰላቸውን ያህል ልዩነትም አላቸው:: የመጀመሪያው ልዩነት በክልሎች የሌለ ነገር ግን በፌዴራል መንግሥት ደረጃ ከሶስቱ የሥልጣን አካላት ጋር የማይመደብ የፌዴሬሽን ምክር ቤት መኖሩ ነው:: ምክር ቤቱ በሀገሪቱ

የሚገኙትን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሚወክሉ አባላት የሚገኙበት ነው:: ሌላው መሠረታዊ ልዩነት የፌዴራል መንግሥቱ ሀገር አቀፍ ጉዳዮችን (ገንዘብን፣ መከላከያ ኃይልን የውጪ ግንኙነትን ወዘተ) የሚያስፈፅም ሲሆን ክልሎች ደግሞ ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ሥልጣን አላቸው::

**መልመጃ 6**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው::*

1. የፌዴራልና የክልል መንግሥታት አንድነት መገለጫዎች ምንድን ናቸው?
2. የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ልዩነት መገለጫዎች ምን ምን ናቸው?

### 1.4.2 የጋራ ሥልጣን፣

✓ *የፌደራል መንግሥትና የክልል መንግሥታት የጋራ ሥልጣን ናቸው ብላችሁ የምትገምቱትን ጥቀሱ::*

በፌዴራል መንግሥት እና በክልል መንግሥታት መካከል የሥልጣን ክፍፍል ቢኖርም የጋራ ሥልጣንም አላቸው:: በዚህም መሠረት የፌዴራል መንግሥትና የክልል መንግሥታት በሕገመንግሥቱ በምዕራፍ 11 አንቀፅ 98 መሠረት የሚከተሉት የጋራ ሥልጣን አላቸው:-

1. የፌዴራል መንግሥትና ክልሎች በጋራ በሚያቋቁሟቸው የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይስ ታክስ በጋራ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ::
2. በድርጅቶች የንግድ ትርፍ ላይ እና በባለ አክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክስ በጋራ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ::
3. በከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና በማንኛቸውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች ላይ የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በጋራ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ::

**መልመጃ 7**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

1. የፌደራልና የክልል መንግሥታት የጋራ ሥልጣኖችን ዘርዝሩ::
2. እነዚህ ሥልጣናት የፌደራልና የክልል መንግሥታት የጋራ የሆኑት ለምንድነው? ተወያዩበት::

### 1.4.3 የከተማ አስተዳደሮች ዋና ዋና ተግባራት፣

✓ *ተጠሪነታቸው ለፌዴራሉ መንግሥት የሆኑ ሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች እነማን ናቸው?*

የፌዴራል መንግሥትን ከመሠረቱት ዘጠኙ የክልል መንግሥታት በተጨማሪ ሁለት የከተማ አስተዳደሮች አሉ:: እነሱም የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ናቸው:: ሁለቱም የከተማ አስተዳደሮች የሚያከናውኗቸው በርካታ ተግባራት አሏቸው:: የከተማ አስተዳደሮቹ ዋና ዋና ተግባራት (በአዋጅ ቁጥር 87/1999 ዓ.ም የአዲስ አበባ ቻርተር ዓዋጅ እና አዋጅ ቁጥር 416/1996 ዓ.ም የድሬዳዋ ቻርተር ዓዋጅ ላይ እንደተገለፀው) የሚከተሉት ናቸው:-

ሀ. በተሰጧቸው የገቢ ምንጮች ዙሪያ ግብርና ቀረጥ የመጣልና የመሰብሰብ፣
ለ. የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ልማት ፕሮግራሞችን የማቀድና የማስፈጸም፣
ሐ. የራሳቸውን በጀት የማጽደቅና የማስተዳደር እንዲሁም ከሀገር ውስጥ ምንጮች የመበደር፣
መ. በከተማዎቹ አስተዳደር ክልል ወስጥ የሚገኘውን መሬትና የተፈጥሮ ሀብት የማስተዳደር፣
ሠ. የከተማዎቹን ሕዝብ ሠላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ የሚያስችል የፖሊስ ኃይል የማቋቋም፣
ረ. የከተማዎቹን አስተዳደር መንግሥታዊ መሥሪያቤቶችና ተቋሞች እንዲሁም የልማት ድርጅቶች የማቋቋምና ሥልጣንና ተግባራቸውን የመወሰን፣
ሰ. የከተማዎቹን አስተዳደር ሠራተኞች አስተዳደርና የሥራ ሁኔታ የመወሰን፣
ሸ. በሥልጣናቸው ክልል ሥር በሚገኙ ጉዳዮች ላይ ደንቦችና መመሪያዎችን የማውጣትና የማስፈጸም፣
ቀ. ከውጭ ሀገራት እህት ከተሞች ጋር ቴክኒካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባሕላዊ የፕሮቶኮል ስምምነቶችን ማድረግ፣
በ. ከፌዴራሉ መንግሥት አካላትና ተቋማት እንዲሁም ከሀገሪቱ ክልላዊ መንግሥታት ጋር ቀጥታ ግንኙነት መመሥረትና ስምምነት ማድረግ::

**መልመጃ 8**

*የሚከተሉን ጥያቄዎች መልሱ::*

1. ከከተማዎች አስተዳደር ዋና ዋና ተግባራት ውስጥ አምስቱን ዘርዝሩ::
2. የዘረዘራችኋቸው የከተማዎች አስተዳደር ተግባራት ከክልል መንግሥታት ተግባራት ጋር የሚመሳሰሉበትን እና የሚለያዩበትን ነጥብ በመለየት ተወያዩበት::

## 1.5 የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት፤

### 1.5.1 ኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት፣



ሥዕል 1.5 ኢትዮጵያ ከተለያዩ የዓለም ሀገራት ጋር መልካም ግንኙት አላት

✓ ከላይ ያለውን ካርታ በማየት ኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት ጋር በምን በምን ጉዳዮች ላይ ግንኙነት ልታደርግ እንደምትችል ጥቀሱ::

ኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ነው:: እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1945 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሲቋቋም መሥራች ከነበሩት ሀገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ነበረች:: በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ይህ ግንኙነት በመጠናከር ላይ ነው:: ለምሳሌ ያህል የመካከለኛው ምሥራቅ፣ የእሲያ፣ የአውሮፓና የአሜሪካ ባለሃብቶች በኢትዮጵያ በተፈጠሩት ምቹ የኢንቨስትመንት አማራጮች በመጠቀም በሀገሪቱ ውስጥ በርካታ የልማት ተግባራትን እያካሄዱ ነው::

የእሲያ ሀገራትን በተመለከተ ከህንድ፣ ከቻይና እና ከጃፓን ጋር ያለው የትብብር እንቅስቃሴ አበረታች ነው:: ከምስራቅና ደቡብ ምስራቅ እስያ ሀገራት ጋር ያለውን ግንኙነት የማጠናከሩ ጉዳይ የንግድና የኢንቨስትመንት ተግባራትን የማስፋትና የማጠናከር ጉዳይ ስለሆነ ትኩረት ተሰጥቶታል:: በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ከአለም ሀገራት ጋር ባላት ግንኙነት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታዋንና ልማቷን ለማፋጠን በመደጋገፍ ላይ የተመሠረተ ትብብር በማድረግ ላይ ትገኛለች::

**መልመጃ 9**

? *የሚከተሉን ጥያቄዎች መልሱ::*

1. ኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት ውስጥ የላቀ ግንኙነት ያላት ከየትኞቹ ሀገራት ጋር ነው?
2. ኢትዮጵያ ከጠቀሳችኋቸው የዓለም ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? ምሳሌዎች በማቅረብ አስረዱ::

### 1.5.2 ኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት ጋር ባላት ግንኙነት የምታገኘው ጥቅም፣

✓ ኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት ጋር በምታደርገው ግንኙነት ምን ጥቅም ታገኛለች?

የኢትዮጵያ አንዱ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ዓላማ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን በማጠናከር ፈጣን ልማትን እውን ለማድረግ የሚያስችል የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር ነው:: ለዚህም ዋነኛ ምክንያቱ የሀገሪቱ የውጭ ግንኙነት መነሻም መድረሻም ልማትና ዴሞክራሲን እውን ማድረግ ነው:: ለልማትና ለዴሞክራሲ እውን መሆን የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር ሲባል የገበያ፣ የኢንቨስትመንት፣ የብድር፣ የዕርዳታ እና የቴክኒክ ድጋፍ ለማግኘትና ለመጠቀም ይረዳል::

ከዚህ አንፃር ኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት ጋር ባላት የውጭ ግንኙነት ልማትን እውን ለማድረግ የሚያስችል ሰፊ የገበያ ዕድል፣ ኢንቨስትመንትና ቴክኒካዊ ድጋፍ ለማግኘት ይጠቀማታል:: እንደዚሁም ዴሞክራሲን ለማስፈን የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ተቋሞችን ለመፍጠርና ለማጠናከር የሚረዳ ሰፊ የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ለማግኘትም ያስችላል::

**መልመጃ 10**

? *በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::*

1. ኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት ጋር ባላት ግንኙነት በምታገኛቸው ጥቅሞች ላይ ተወያዩ::
2. በቡድን በቡድን በመሆን የተለያዩ የዓለም ሀገራትን በመውሰድ ኢትዮጵያ ከነዚህ ሀገራት ጋር ግንኙት በማድረጓን ያገኘችውን ጥቅም በክፍል ውስጥ አቅርቡ::

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የዴሞክራሲ ሥርዓት የዜጐች ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች እንዲሁም የብሔሮች፣ የብሔረሰቦች እና የሕዝቦች የእኩልነት መብት የሚከበርበት ሥርዓት ነው፡፡ የግንባታው ሂደት የዴሞክራሲ ሥርዓት እንዲሠፍንና እንዲዳብር የሚረዱ ዴሞክራሲያዊ ዜጎችን ለመፍጠር እና የዴሞክራሲ ባህልን ለማዳበር የሚያግዙ ወሳኝ ተግባሮችን ማከናወንን የሚጠይቅ ነው፡፡ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በጥቅሉ ዴሞክራሲያዊ ዜጋን በመፍጠር እና የዴሞክራሲ ባህልን በማዳበር ለሀገርና ለሕዝብ የሚበጅ እና የሚስማማ አስተዳደር ማስፈን ነው፡፡

የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መሠረቶች የሕግ የበላይነት መስፈን፣ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር፣ የሕዝቦች መፈቃቀድ መኖርና ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መብቶች የእኩልነት፣ በራስ ቋንቋ የመጠቀም፣ የመም ረጥና የመመረጥ መብቶች መከበር ናቸው ፡፡

የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለማስፈን የሚያስችሉ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ መንግሥታዊ የሆኑ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ፍርድ ቤቶች፣ ፖሊስ፣ እምባ ጠባቂ ተቋም፣ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን፣ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ እና በመንግሥት ይዞታ ሥር የሚገኙ መገናኛ ብዙኃን ናቸው፡፡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ደግሞ አለም አቀፍ እና ሀገር በቀል ሲቪክ ማህበራት፣ እንዲሁም በግል ይዞታ ሥር ያሉ መገናኛ ብዙኃኖች ናቸው፡፡

ልዩነቶችን ወይም አለመግባባቶችን በሰላም ለመፍታት የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነገሮች ውይይት፣ በውይይት ወቅት መደማመጥ እና መቻቻል ናቸው፡፡

የፌዴራልና የክልል መንግሥታት አንድነት መገለጫ አንዱ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌደራል መንግሥትና በክልሎች በጋራ መዋቀሩ ነው፡፡ ሌላው ሁለቱም የራሳቸው የሆነ ሕግ አውጭ፣ ሕግ አስፈጻሚና ሕግ ተርጓሚ አካላት ያላቸው መሆኑ ሲሆን በተጨማሪም የሁለቱም ዋነኛ ሥልጣን ከሆኑት ውስጥ ሕገመንግሥቱን መጠበቅና መከላከል መሆኑ አንድነታቸውን ያሳያል፡፡

ልዩነታቸው ደግሞ የማዕከላዊ መንግሥት ሥልጣን ሀገር አቀፍ ጉዳዮችን (ገንዘብን፣ መከላከያ ሃይልን፣ የውጭ ግን ኙነትን) የሚመለከት ሲሆን የክልሎች ሥልጣን በዋነኛነት ራሳቸውን ማስተዳደርን የሚመለከት ነው፡፡

የጋራ ሥልጣናቸው ደግሞ የፌዴራል መንግሥትና ክልሎች በጋራ በሚያቋቁሟቸው የልማት ድርጅቶች እና በከፍተኛ የማዕ ድን ሥራዎችና በማንኛቸውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች፣ የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይስ ታክስ፣ የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በጋራ መጣልና መሰብሰብ ነው፡፡

የከተማ አስተዳደሮች ዋና ዋና ተግባራት በተሰጣቸው የገቢ ምንጮች ዙሪያ ግብርና ቀረጥ መጣልና መሰብሰብ፣ በከተ ማዎቹ አስተዳደር ክልል ወስጥ የሚገኘውን መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ማስተዳደር፣ የሕዝቡን ሠላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ የሚያስችል የፖሊስ ኃይል ማቋቋም፣ በሥልጣናቸው ክልል ሥር በሚገኙ ጉዳዮች ሳይ ደንቦችና መመሪያዎችን ማውጣትና ማስፈጸም፣ ከውጭ ሀገራት ከተሞች ጋር ቴክኒካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባሕላዊ የፕሮቶኮል ስምምነቶችን መፈራረም ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ ከተለያዩ የዓለም ሀገራት ጋር ያላት ግኙነት በመጠናከር ላይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት ጋር ባላት ግን ኙነት ልማትን እውን ለማድረግ የሚያስችል ሰፊ የገበያ ዕድል፣ የልማት እንቅስቃሴዋን የሚያግዝ፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን ለማጐልበትና ለማስፈን የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ተቋሞችን ለመፍጠርና ለማጠናከር የሚረዳ የብድርና የርዳታ እንዲሁም ቴክኒካዊ ድጋፍ ለማግኘት እንድትችል ረድቷታል፡፡ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት የሀገሪቱን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በማጠናከርና ፈጣን ልማትን በማረጋገጥ ረገድ ጥሩ ውጤት እያስገኘ በመሄድ ላይ ነው፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**የፕሮቶኮል ስምምነት፣** በሀገሮች መካከል የሚደረግ የትምህርት፣ የባህል፣ የኢኮኖሚ ስምምነት፣ ውስታ፣ ውል።

**የፖለቲካ ፓርቲ፣** የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በአንድነት ተሰባስበው ነፃነትን፣ ወይም ማህበራዊና ኢኮኖሚ ጥቅማጥቅሞችን ለማስጠበቅና ለዚህም እንዲረዳ በነፃ ውድድር የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ የሚያቋቁም ድርጅት ነው።

**የሮያሊቲ ክፍያዎች፣** አንድ ደራሲ (የመፅሐፍ፣ የሙዚቃ፣ የቅርፃቅርፅ ወዘተ) ስአዘጋጃቸው የሥራ ውጤቶች በተ ሸጡ ወይም እንደገና በቀረቡ ቁጥር የሚከፈለው ክፍያ።

© MoE, FDR Ethiopia
Not to be republished

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

***ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ::***

**I *የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ::***

1. የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዲሞክራሲያዊ ዜጋን መፍጠር እና የዴሞክራሲ ባህልን ማዳበር ነው።
2. የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረቶች የሕዝቦች መፈቃቀድና የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ናቸው።
3. ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ከሌላው ከማንኛውም የመብቶች አስከባሪ ተቋማት በማንባር ቀደምትነት የሕግን የበላይነትን የሚያስከብር ተቋም ነው።
4. ኢትዮጵያ ከሌሎች የዓለም ሀገራት ጋር የምታደርገው ሠላማዊ ግንኙነት ለልማትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚያስፈልጋትን ማንኛውንም ድጋፍ ለማግኘት ጠቅሟታል::
5. በከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና በማንኛቸውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች ላይ የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች መጣል የፌደራል መንግሥት ሥልጣን ነው::

**II *በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ::***

**ሀ**

1. ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሳይሸራረፉ እንዲከበሩ የሚሠራ ተቋም፣
2. ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ከዜጎች ሰብዓዊ መብቶች ጋር የማይቃረኑ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ተቋም፣
3. በሕግ የተደነገጉ የዜጎች መብቶች እና ጥቅሞች በአስፈጻሚው አካላት መከበራቸውን የሚከታተል ተቋም፣
4. ግልፅነትን፣ ተጠያቂነትንና የሕዝብ ተሳትፎን ለማጎልበት የሚሠራ ተቋም፣
5. ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ ለሕዝቡ የሚያቀርብ ተቋም፣

**ለ**

ሀ) መገኛኛ ብዙኃን ::
ለ) የእምባ ጠባቂ ተቋም::
ሐ) ሲቪክ ማኅበራት::
መ) የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን::
ሠ) የፌደራል የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን::
ረ) ፖሊስ::

**III *ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ::***

1. ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ዋነኛው መሠረት ለሕግ የበላይነት መገዛት መርህ ነው የሚባልበት ምክንያት ምንድነው?
   ሀ) መርሁ ሥልጣን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ብቻ እንዲያዝ ዋስትና ስለሚሰጥ፣
   ለ) መርሁ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ዋስትና ስለሚሰጥ፣
   ሐ) የብሔር፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች የእኩልነት መብቶች እንዲከበሩ ዋስትና ስለሚሰጥ፣
   መ) ሁሉም መልስ ነው።
2. ከሚከተሉት ውስጥ የዴሞክራሲያዊ ዜጋ ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ) የዜጐችን ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ጠንቅቆ ያውቃል፣
   ለ) ልዩነቶች የዴሞክራሲ መሠረቶች መሆናቸውን አያምንም፣
   ሐ) የዜጐችን ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች በሚገባ ያከብራል፣ ያስከብራል፣
   መ) መልሱ አልተሰጠም።

© MoE FDRE Ethiopia not to be republished

3. የዴሞክራሲ ባህል ዳብሯል ለማለት የሚቻለው መቼ ነው?
   ሀ) ልዩነቶችን እና የሌሎችን ሃሳብና አመለካከቶችን ማክበርና መቀበል ሲቻል፣
   ለ) አለመግባባቶችን በሰላማዊ ውይይትና በመተማመን መፍታት ሲቻል፣
   ሐ) በውይይት ሊፈቱ የማይችሉ ግጭቶች ሲያጋጥሙ ለዳኝነት ማቅረብና የብዙሃኑን ውሳኔ በፀጋ ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረግ ሲቻል፣
   መ) ሁሉም መልስ ነው።

## IV *የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::*

1. ከመንግሥት አደረጃጀት ውጭ ያሉ ንቁና ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች በራስ ተነሳሽነት የሚያቋቁሟቸው ተቋማት ---------------- ተብለው ይጠራሉ::
2. በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በኩል ጉዳት ደርሶብናል በማለት ቅሬታ የሚያቀርቡ ግለሰቦችን አቤቱታ እየመረመረ ውሳኔዎችን የሚሰጥ መብት አስከባሪ ተቋም ----------------ይባላል::
3. ልዩነቶችን ወይም አለመግባባቶችን በሰላም ለመፍታት የሚያስፈልጉ ሦስቱ መሠረታዊ ነገሮች ------------፣ --------------- እና --------------- ናቸው::

## V *የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ::*

1. ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መሠረቶች ውስጥ ሦስቱን ጥቀሱና እያንዳንዳቸው መሠረት መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ አቅርቡ::
2. ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ከሚሠሩ ተቋማት ውስጥ ቢያንስ ሁለቱን በመጥቀስ ዓላማቸውን ግለፁ::
3. የፌደራል መንግሥትንና የክልል መንግሥታትን አንድነትና ልዩነት አብራሩ::

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

# ምዕራፍ ሁለት
# የሕግ የበላይነት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤**

- በፌዴራል ሕገመንግሥትና በክልል ሕገ መንግሥት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ታወቂያለሽ/ታውቃለህ፡፡
- የሥልጣን ገደብን አስፈላጊነት ትረጂያለሽ/ትረዳለህ፡፡
- የሚጠበቅብሽን/የሚጠበቅብህን ሥነምግባር ታውቂያ ለሽ/ታውቃለህ፡፡
- ሙስና የሚያስከትላቸውን ችግሮች ትረጂያለሽ/ትረዳለህ፡፡


## 2.1 ሕገመንግሥት፤

### 2.1.1 የኢፌዴሪ ሕገመንግሥትና የክልል መንግሥታት ሕገመንግሥቶች አንድነትና ልዩነት፣

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት መግቢያ**

እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም፣ ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገታችን እንዲፋጠን፣ የራሳችንን ዕድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን፣ በነፃ ፍላጐታችን፣ በሕግ የበላይነት እና በራሳችን ፈቃድ ላይ የተመሠረተ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ በጋራ ለመገንባት ቆርጠን በመነሣት፣ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ፣ የግለሰብና የብሔር/ብሔረሰብ መሰረታዊ መብቶች መከበራቸው፣ የፆታ እኩልነት መረጋገጡ፣ ባሕሎችና ሃይማኖቶች ካለአንዳች ልዩነት እንዲራመዱ የማድረጉ አስፈላጊነት ፅኑ እምነታችን በመሆኑ፣ ኢትዮጵያ ሀገራችን የየራሳችን አኩሪ ባህል ያለን፣ የየራሳችን መልክዓ ምድር አሰፋፈር የነበረንና ያለን፣ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በተለያዩ መስኮችና የግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረን አብረን የኖር ንባትና የምንኖርባት ሀገር በመሆንዋ፣ ያፈራነው የጋራ ጥቅምና አመለካከት አለን ብለን ስለምናምን፣

ይህ ሕገመንግሥት ከዚህ በላይ ለገለፅናቸው ዓላማዎችና እምነቶች ማሰሪያ እንዲሆነን እንዲወክሉን መርጠን በላ ክናቸው ተወካዮቻችን አማካይነት በሕገ መንግሥት ጉባኤ ዛሬ ኀዳር 29 ቀን 1987 አፅድቀነዋል፡፡



ሥዕል 2.1. ሕገመንግሥቶች

- በሥዕሉ የተመለከቱት ሕገመንግሥቶች አንድነትና ልዩነት ምን ይመስላችኋል?

ከዚህ ቀጥሎ ከፌዴራል ሕገመንግሥት እና ከደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገመንግሥት መግቢያ ውስጥ የተወሰዱ ከፊል ሃሳቦች ቀርበዋል። በቡድን በቡድን ሆናችሁ ሃሳቦችን በማነፃፀር ከግርጌው ለቀረቡት ጥያቄዎች በፅሁፍ መልሳችሁን አቅርቡ፡፡

**በ1994 ዓ.ም. ተሻሽሎ የወጣው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገመንግሥት መግቢያ**

**እኛ የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕዝቦች፡-**

ለዘመናት ተንሰራፍቶ የቆየው ጨቋኝ ሥርዓት ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻችንን አፍኖና በተዛባ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፖሊሲዎች ለድህነትና ለኋላ ቀርነት ዳርጎን መቆየቱን በጠቅላላ እድገታችን ላይ ያደረሰውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለማስወገድ በመሻት፤

በአብዛኞቹ የአገራችን ብሔር-ብሔረሰቦች ላይ ሲፈፀም በቆየው አስከፊ ብሔራዊ ጭቆና ምክንያት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የጉዳቱ ሰለባዎች ሆነን መቆየታችን በማያዳግም ሁኔታ መታረም እንዳለበት በማመን፤

መላ የአገራችን ብሔር-ብሔረሰቦችና ህዝቦች ለዘመናት ካካሄዱት አኩሪ ተጋድሎ የነበረው ኋላ ቀርና አፋኝ ሥርዓት ተገርስሶ አገራችን ኢትዮጵያ የግለሰቦችንና የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠልን ጨምሮ የሁሉም ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሰብአዊና ዲሞክ ራሲያዊ መብቶች በሙሉ የተከበሩባትና በአጠቃላይ የሕግ የበላይነት የሰፈነባት ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊት ሪፑብሊክ መሆኗ ለጋራ እድገ ታችን መፋጠን ያለውን ጠቀሜታ በመገንዘብ፤

እኛ በአማራ ብሔራዊ ክልል የምንገኝ ህዝቦች ለተፋጠነ ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ ለዘላቂ ሰላምና ለዳበረ ዲሞክራሲ የምንበቃው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገመንግስት መሰረት ያደረገ፣ ከክልላችን ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር የተገናዘበና የብሔራዊ ክልሉ ህዝቦች የተከበሩልንን ሕገመንግስታዊ መብቶች ባልተሸራረፈ ሁኔታ በስራ ላይ ለማዋል የሚያስችለን የራሳችን ሕገመንግስት ሲኖረን እንደሆነ አጥብቀን በማመን፤

ከዚህ በመነሳት በቀጥተኛ ተሳትፏችን በዲሞክራሲያዊ አግባብ ከመ ካከላችን መርጠን በላክናቸው የክልሉ ምክር ቤት መስራች ጉባዔ ተወካዮቻችን አማካኝነት እስካሁን ድረስ ፀንቶ የሚሰራበትን ክልላዊ ሕገመንግስት ሰኔ 15 ቀን 1987 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ መክረን ያፀደቅነው መሆኑን እያስታወስን፣ ይኸው በስራ ላይ ያለው ሕገመንግስታችን/ አስቀድሞ እንደተሻሻለ/ ግልፅ አሰራርን የሚከተል፣ ስመረጥነው ህዝብ ተጠያቂ የሆነና ብቃት ያለው መንግስታዊ አደረጃጀትን በሚያሳይ አግባብ ጥልቅ ክለሳ ተደርጎበትና የምንገኝበት ሁኔታ በሚጠይቀው መጠን እንደገና ተሻሽሎ መውጣት የሚገባው መሆኑን በውል በመረዳት፣

እነሆ ዛሬ ጥቅምት 26 ቀን 1994 ዓ.ም. በባሕር ዳር ከተማ ባካሄድነው የክልሉ ምክር ቤት ሶስተኛ መደበኛ ጉባዔ ለዚህ ዓላማ በተሰየመው አካል ተረቅቆ በቀረበው የተሻሻለ ሕገመንግስት ላይ መክረንና በአንቀጾቹ ላይ በዝርዝር ተወያይተን ሰነዱን በሙሉ ድምፅ አፅድቀነዋል፡፡

**መልመጃ 1**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. በቀረቡት የሁለቱ ሕገመንግሥቶች መግቢያ ላይ ያለውን አንድነት በዝርዝር ግለፁ::
2. የክልሉ ሕገመንግሥት የፌዴራሉን ሕግ መንግሥት መነሻ ማድረጉና እንዲሁም የማይቃረን መሆኑን የሚያሳዩ ሃሳቦችን በማነፃፀር አሳዩ::
3. በዚሁ መልክ ያሳችሁበትን ክልል ወይም ሌላ አንድ ክልል መርጣችሁ መግቢያውን ከፌዴራሉ ሕገመንግሥት ጋር በማነፃፀር አንድነትና ልዩነታቸውን በቡድን በመሆን አሳዩ::

የፌዴራል ሕገመንግሥት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መርጠው በላኳቸው ተወካዮቻቸው አማካኝነት ተመክሮበት የፀደቀ እንደመሆኑ በሀገሪቱ ያሉ ሕጎች ሁሉ መነሻና የበላይ ሕግ ነው:: የክልል ሕገመንግሥታትም የክልሉ ሕዝቦች በመረጧቸው ተወካዮቻቸው አማካኝነት በየክልሉ ምክር ቤት የጸደቁ ናቸው:: በመሆኑም በክልሉ ውስጥ ያሉ ሕጎች ሁሉ የበላይ ሕጎች ናቸው:: ከዚህም በመነሳት ሁለቱም (የፌደራል ሕገመንግሥትና የክልል ሕገመንግሥት) ሕዝቦች በመረጧቸው ተወካዮቻቸው አማካኝነት ተመክሮባቸው የፀደቁ መሆናቸውን እንገነዘባለን::

የፌዴራል ሕገመንግሥት ዋነኛ ዓላማ የመንግሥትን የተለያዩ ክፍሎች ሥልጣንና ሃላፊነት መወሰን፣ ዜጎች ያሏቸውን መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች መደንገግ ሲሆን፣ የክልል ሕገመንግሥት ዓላማ ደግሞ በክልል መንግሥቱ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ክፍሎች ሥልጣንና ኃላፊነት መወሰን፣ በክልሉ ያሉ ሕዝቦች ያሏቸውን መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶችን መደንገግ ነው:: ሌሎች ሕጎችና ደንቦች አሠራሮች ሁሉ የበላይ ከሆነው የፌዴራል ሕገመንግሥቱ ጋር እንዳማይቃረኑ ሁሉ በክልሎች ወስጥ የሚወጡ ሕጎች፣ ደንቦችና አሠራሮችም ከክልሉ ሕገመንግሥት ጋር የሚቃረኑ አይሆኑም::

ስለዚህ ሁለቱም ሕጎች በሕዝቦች ሙሉ ፍቃድ የፀደቁ በየደረጃቸዉ የበላይ ሕግ መሆናቸዉ አንድ ዓይነት ባህርይ እንዳላቸው ያመለክታል:: ይህም ማለት የፌዴራሉ ሕገመንግሥት በሀገር ደረጃ የበላይ ሕግ ሲሆን፣ የክልል ሕገመንግሥቶች ደግሞ በክልሎች የበላይ ሕጎች ናቸው:: ልዩነታቸው ደግሞ የፌዴራሉ ሕገመንግሥት በሀገሪቱ በሙሉ የበላይ ሕግ ሲሆን፣ የክልል ሕገመንግሥቶች ደግሞ የበላይ ሕግ የሚሆኑት በክልላቸው ደረጃ መሆኑ ነው:: ይህ በመሆኑም የፌዴራል ሕገመንግሥቱን የሚቃረን ሕገመንግሥት ወይንም ሕግ በክልሎች ሊወጣ አይችልም::

**መልመጃ 2**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ በቀረበው ማስታወሻ ላይ በመመሥረት መልሱ::***

1. የፌዴራል እና የክልል ሕገመንግሥት የሚፀድቁት በምን ዓይነት መንገድ ነው?
2. የፌዴራል ሕገመንግሥትና የክልል ሕገመንግሥት ከሕጐች ሁሉ የበላይ መሆናቸው በምን መልክ እንደሆነ ግለፁ::
3. የፌዴራል እና የክልል ሕገመንግሥቶች የሚመሳሰሉባቸውንና የሚለያዩባቸውን ነጥቦች ዘርዝሩ::

## 2.2 ሥነምግባር

### 2.2.1 በሀገር ደረጃ ከተማሪዎች የሚጠበቅ ሥነምግባር፣

በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚገኙ የሥነ ምግባር መርሆዎች፣

ሐቀኝነት፣ ታማኝነት፣ ቅንነት፣ ሚስጢርን መጠበቅ፣ ለሕዝብ ጥያቄ ምላሽ መስጠት፣ ተጠያቂነት፣ አድሎ አለመፈጸም፣ ሕጋዊ በሆነ ሥልጣን በአግባቡ መገልገል፣ ሕግን ማክበርና አርአያነት ናቸው::

✓ እነዚህን መርሆዎች ሠራተኞች እንዲያዉቋቸዉ መደረጉ ምን ጥቅም የሚሰጥ ይመስላችኋል?

**እወስዳለሁ**

እናቴ እኔን እንደያዘች ተቀምጣ ተራዋን እየተጠባበቀች ነው::
"ለመሆኑ ምንሽን አሞሽ ነው ሐኪም ቤት የመጣሽው?" አልኳት ድንገት።
"ለመሆኑ ማነህ አንተ?" ብላ ጠየቀችኝ::
"ልጅሽ ነኛ:: ማን መስልኩሽ?" አልኳት፣ በደብልጥ ላሣምናት ፊልጌ ማህፀኗ ውስጥ መሆኔን እንድታረጋግጥ ሁለት ጊዜ ገልበጥ ገልበጥ አልኩ::
"ታሪኩን መስማት መብቴ ነው፣ የመጣሽበትን::"

"አንተን ለማስወረድ!"
"እንዳልወለድ?"
"አዎ"
"እወለዳለሁ አልኳት ጮክ ብዬ"

ኧረ እወለዳለሁ ሀገሬንና ወገኔን ለመልካም ፍጻሜ የሚያደርስ ራዕይ አለኝ:: ሰዎች ሁሉ ክፉዎች ናቸው የሚል እምነት የለኝም:: የእርኩሳኑን ያህል ደጋጐችም አሉ፣ ለወሽካታው እውነተኛ፣ ለከዳተኛው ታማኝ፣ ለትዕቢተኛው ትሑት፣ ለክፉው ጥሩ፣ ለሱሰኛው ጨዋ፣ ለባለጌው ጭምት፣ ለመሰሪው ሰው ወዳድ፣ ለሰባቂው አስታራቂ፣ ተፈጥሯል:: ስለዚህ ጥሩ ሰው ማየት ካሁኑ ይናፍቀኛል:: በተለይ ጥሩ ጓደኛ ጓደኛውን በቅናትና ምቀኝነት የማይተበትብ፣ የሚች ጓደኛውን ድንቅ ሥራ የኔ ነው የማይል፣ ለችግር ጊዜ የሚደርስ፣ አፈጮማ ሳይሆን በተግባር የሚያምን የልብ ጓደኛ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ::

ለሀገሩ በሐቅ የሚሰራ፣ ቢሮክራሲ ያላጠየመው፣ የማይመዘብር፣ ሙስናን ተዋግቶ የሚያዋጋ፣ ለወገኖቹ እድገት፣ ብልፅግናና ደህንነት ሳይታክት የሚሠራ፣ በፈረንጅ አስተሳሰብ ያልተበረዘ፣ የሕዝቦችንም የራሱንም ባህል የሚያዳብር ጥሩ ኢትዮጵያዊ ለማየት ቸኩያለሁ፣ አርአያነቱንም ለክፉዎች አሳይቼ ከስህተታቸው እንዲማሩ ለማድረግ እሻለሁ:: ብዙ ታላላቅ ሰዎችን እንዳናጣ ውርጃን አወግዛለሁ::

አመጣጥና በመውለድ ግን አምናለሁ፣ ጥሩ ትጉህ የሀገር መሪና ሀገርን ከጠላት የሚያድን ጀግና ወታደር ማየት እፈልጋለሁ:: ስለዚህ እወለዳለሁ::

*(መስፍን ሃብተማርያም፣ እፍታ፣ 1993 ለማስተማሪያ እንዲሆን በከፊል የተወሰደ)*

**መልመጃ 3**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

?

1. በምንባቡ ውስጥ ከተጠቀሱት ሐሳቦች ውስጥ ከተማሪዎች የሚጠበቁት የትኞቹ ይመስሉአችኋል? ምክንያታችሁን ግለጹ::
2. በምንባቡ ውስጥ ከተጠቀሱት ሐሳቦች ተማሪዎች ሊያስወግዷቸው ይገባል የምትሏቸውን ለዩና ምክንያታችሁን ግለጹ::

ለሕግ የበላይነት መገዛት ሁሉም መብቶችና ጥቅሞች የሚከበሩበት ሥርዓት የሚቆምበት ምሰሶ ነው:: መልካም ሥነምግባር ደግሞ ለሕግ የበላይነት ለመገዛት ቁልፍ ነው፤ በመሆኑም በሀገር ደረጃ ከተማሪዎች ብዙ መልካም ሥነምግባር ይጠበቃል::

እያንዳንዱ ዜጋ የራሱ መብት በመከበሩ እንደሚረካ ሁሉ የሌላውም ዜጋ መብት ሲከበር እንደሚረካ በመገንዘብ የሌላውን መብት ማክበርና ማስከበርን የህይወት መመሪያው ማድረግ አለበት:: እንዲሁም መብቱን በጉልበትና በኃይል ሳይሆን ሕግን አክብሮ ብቻ መጠቀም እንዳለበት ከልቡ ማመንና መተግበር አለበት:: ሕግ ይቀጣኛል ወይንም የተለየ ጥቅም አገኛለሁ ብለው ሳያስቡ ሕግን አክብሮ መንቀሳቀስ ከፍተኛ የሥነምግባር መገለጫ ነው::

የተለያዩ ቋንቋዎች፣ እምነቶች፣ ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች ያሉዋቸው ማህበረሰቦች በአንድ ላይ እንደየእምነታቸው፣ ባህላቸውና አኗኗራቸው በጋራ ተስማምተውና ተባብረዉ የሚኖሩት በመቻቻል ነው:: ስለዚህ የመቻቻል መርህ ከተማሪዎች የሚጠበቅ ሥነምግባር ነው:: ወጣት ተማሪዎች በሀገራዊም ሆነ በአካባቢ ጉዳይ ላይ ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ የሀገር ፍቅር ሊኖራቸው ይገባል:: ይህ ካልሆነ በጥቂቶች ጥቅማቸው ሊነጠቅ መብታቸው ሊረገጥ መቻሉ አይቀሬ ነው:: በመሆኑም በማንኛውም ሀገራዊም ሆነ አካባቢያዊ ጉዳይ ላይ ያለጐትጓች መሳተፍ ተገቢ ነው::

ሀገር ወጣት ዜጐቿ ሀቀኞች እንዲሆኑላት ትፈልጋለች:: ሀቀኝነት በሚነገርና በሚደረግ መካከል ልዩነት አለመኖር ሲሆን ልዩ ልዩ መገለጫዎች አሉት:: ከነዚህም መካከል አለመዋሸት፣ አለማጭበርበር፣ አለመስረቅ ወዘተ ይገኙበታል፣ በመሆኑም ወጣቶች ሀቀኛ እንዲሆኑ ይጠበቃል::

በመጨረሻም ወጣት ተማሪዎች የሥራ ፍቅርና ከበሬታ ሊኖራቸው ይገባል "በሥራቸው የረኩ ሰዎች በህይወታቸው የረኩ ሰዎች ናቸው" እንደሚባለው መታፈር ያለበት ሥራ ባለመሥራት እንጂ በምንሠራው የሥራ ዓይነት መሆን የለበትም፤ ሥራ አማርጦ መናቅ የኋላቀርነት መገለጫ መሆኑን መረዳት ይገባል:: ስለሆነም ማንም ሰው በሚያከናውነው ተግባር የሥራ ሥነምግባር ሊኖረው ይገባል::

በአጠቃላይ ልዩነትን አምኖ በመቀበል ተቻችሎ መኖር፣ ማንኛውንም ተግባር በሕግ መሠረት ማካሄድ፣ ሀገርን መውደድ፣ እውነትን ማራመድ፣ ሌሎችን ጎድቶ የተለየ ጥቅም ለማግኘት አለመሻት፣ ትምህርትን በርትቶ በመማር ያስቡት

ግብ ላይ መድረስ ለሀገርና ለወገን የሚበጁ ተግባራትን ማከናወን ከተማሪዎች የሚጠበቁ ጥሩ የሥነምግባር መገለጫዎች ናቸው::

**መልመጃ 4**

***የሚከተሉትን ተግባራት ሥሩ::***

?

*ሀቀኛ* | *የሀገር ፍቅር* | *መብትን* | *የማክበርና የማስከበር* | *ትዕግሥተኛ* | *የሥራ ፍቅር* | *መቻቻል*

ሀ) ከላይ በሣጥኑ ውስጥ የተሰጡትን የሥነምግባር መገለጫዎች ከዚህ በታች በቀረቡት ዐረፍተነገሮች ዉስጥ ይበልጥ ተስማሚ ናቸው በምትሉዋቸው ቦታዎች አስገቡ::

1. የእነ ስምስም ሰፈር ወጣቶች የተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች ቢሆኑም በ ___ አብረው ይኖራሉ::
2. እነተኮላ የራሳቸው የሆነውን አያስነኩም፤ የሌሎችንም አይነኩም እንዲያውም የሌሎች መብት ያለአግባብ ሲደፈር ዝም አይሉም በመሆኑም በሰፈሩ _____ ምሳሌዎች ናቸው::
3. ዳንቻ ወጣት ነጋዴ ቢሆንም ለሕገ ወጥ ትርፍ ብሎ ቃሉን አያጥፍም ስለዚህ በሰፈሩ ______________ በመባል ይታወቃል::
4. ወጣቷ ብዙ ውጣ ውረዶችን ታግሳ ለቁም ነገር በመብቃቷ የሰፈሯ ሰዎች እንደ ስምሽ _______ ነሽ ይሏታል::
5. ዛሬ ትንሽ የምትመስለዋን ሥራ ሳይንቁ የሰሩ ______________ ያላቸው ወጣቶች ነገ ባለኩባንያ ሆነው ብዙዎችን የሚያስተዳድሩ ዜጐች እንደሚሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው::
6. _______ ያለው ወጣት በመከባበርና በእኩልነት የሚኖርባትን ሀገር ጥቃት ለመመከት ቀስቃሽ አያስፈልገውም::

ለ) በሀገር ደረጃ ከተማሪዎች ከሚጠበቁ የሥነምግባር መገለጫዎች መካከል የተወሰኑትን በመጥቀስ አብራሩ::

## 2.3 የሥልጣን ገደብ

### 2.3.1 የሥልጣን ገደብ አለመኖር የሚያስከትላቸው ችግሮች

- ✓ በአንድ መሥሪያ ቤት ያለ ባለስልጣን የተሰጠውን ሥልጣን ያለገደብ እንዲጠቀምበት ቢደረግ ምን ዓይነት ችግር ሊፈጠር ይችላል?

**ነውር ነው**

አቶ ሺበሺ ከግቢያቸው ጐን ባለው ክፍት ቦታ ሱቅ ለመስራት አሰቡና ጐረቤታቸው የሆነውን አንድ ደንብ አስከባሪ አማከሩ::

እሱም ችግር የለም፣ ይፍረስ ቢባል እንኳ እኔ አለሁ አላቸው:: እሳቸውም ሱቁን ሠሩ:: ይሁን እንጂ ሶስት ወርም ሳይጠቀሙበት ቦታው መንገድ የሚወጣበት ስለሆነ እንዲያፈርሱት ተነገራቸው:: እሳቸው ግን የደንብ አስከባሪውን አስፈቅጄ ነው የሰራሁት በማለት አላፈርስም አሉ:: እንዲያውም አንድ ለሚያውቁት ባላሥልጣን ጉቦ ሰጥተው የደንብ ማስከበሪያ ኮሚቴ አባላትን አሳሰሩዋቸው::

***የቡድን ሥራ፣***

*በዚህ ጉዳይ ላይ ጥፋተኛው ማን እንደሆነ፣ ሥልጣኑንም ያለገደብ የተጠቀመው ማን እንደሆነና በዚህ ምክንያት የተከሠተውን ችግር እንዲሁም መሆን የነበረበትን ትክክለኛ አሠራር ተወያዩና የቡድናችሁን ሃሳብ በፅሁፍ አቅርቡ::*

የሕግ የበላይነት መገለጫዎች ከሆኑት ጉዳዮች መካከል አንዱ የመንግሥትን ሰፊ ሥልጣን ለመገደብና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥልት መኖር ነው:: የሥልጣን ገደብ ከሌለ ሕግ እየተጣሰና ሁሉም ከሕግ በላይ እየሆነ የሕግ የበላይነት ትርጉም ያጣና በርካታ ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ::

የሥልጣን ገደብ ከሌለ ሥርዓት አልበኝነት ይነግሥና የዜጐች መብቶች በሕገወጥ አሠራር ሊጣሱ ይችላሉ:: አገልግሎት ሰጪ አካላት የሥልጣን ገደብ ካልተደረገባቸው የተገልጋዩ መብቶችና ግዴታዎች ይጣሳሉ:: ከዚህም የተነሳ ተገልጋዩ መብቱን ለማስከበር ከሕጋዊ መንገድ ይልቅ ጉቦና አማላጅ የመሳሰሉትን መንገዶች አማራጭ ያደርጋል፤ በዚህም ሙስና ይንሰራፋል::

የሥልጣን ገደብ በማይኖርበት ጊዜ ግልፅነትና ተጠያቂነት አይኖርም:: በመሆኑም ባለሥልጣናት ሕግን መተላለፋቸውና አለመተላለፋቸው በግልፅ አይታወቅም:: ስለዚህ የተበደለ ሰውም መበደሉን በግልፅ የሚያውቅበት ሕግና አግባብ አይኖረውም፤ ተበድያለሁ ብሎ እንኳን ቢያስብ ቅሬታውን ሊያቀርብ የሚችልበት ሁኔታ አይፈጠርም::

እንዲሁም በሥልጣን ላይ ገደብ አለመደረጉ የተለያዩ የመንግሥት አካላትና ሠራተኞች በዘፈቀደ

እንዲሰሩ በማድረግ ለዜጐች መብት መጣስ ምክንያት ይሆናል:: ለምሳሌ ማንም ሰው ሊቀጣ የሚችለው በግልፅ የተከለከለና ሕግን ሲጥስ እና በአግባቡ ተከሶና ፍርድ ቤት ቀርቦ ሲፈረድበት ብቻ ነው:: ይሁን እንጂ የሥልጣን ገደብ ከሌለ አንድ ሰው ሕግ ሳይጥስ፣ በአግባቡ ክስ ሳይቀርብበትና ሳይፈረድበት በባለስልጣናት ገደብ የለሽ ትዕዛዝ ብቻ ሊታሠርና ሊቀጣ ይችላል:: የእንዲህ ዓይነት አሠራር መኖር የዜጎችን ፍትህ የማግኘት መብት የሚጥስ ሲሆን ዞሮ ዞሮ ሀገርንም ይጎዳል:: ስለዚህ የሥልጣን ገደብ መኖር እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው::

**መልመጃ 5**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::***

1. የሥልጣን ገደብ አስመኖር የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ እንቅፋት የሚሆነው እንዴት ነው?
2. የሥልጣን ገደብ ከሌለ ሲደርስ የሚችለው ችግር ምንድን ነው?
3. ዜጐች መበደል አስመበደላቸውን የማያውቁበት ሁኔታ የሚከሰተው ምን ዓይነት አሠራር ሲኖር ነው?
4. በኢትዮጵያ ሕገመንግሥት አንቀፅ 12 ላይ የተደነገገውን በማንበብ ሥልጣንን ስመገደብ ያለው አስተዋፅኦ ምን እንደ ሆነ ግለጹ::

## 2.4 ሚስጥር

### 2.4.1 ሚስጥር ስመጠበቅ መደረግ ያሳባቸው ጥንቃቄዎች፣

- ✓ ሚስጥር መጠበቅ እንዳለበት የሚገልጹና በአካባቢያችሁ የሚነገሩ አባባሎች አሉ? ካሉ እስቲ ግለጹዋቸዉ::
- ✓ ሚስጥር ለመጠበቅ ሊደረጉ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች ምንድናቸዉ?

**ማንጉዳይ**

አቶ ማንጉዳይ የአንድ መሥሪያ ቤት ሠራተኛ ናቸው:: አንድ ፀሐፊና አንድ ቢሮ የሚያፀዳ ሠራተኛ ተመድቦላቸው ይሠራሉ:: እሳቸውም ብዙውን ጊዜ ለሻይ እረፍት ሲወጡ ቢሮአቸውን አይዘጉም:: እንዲሁም አንድ ነገር ለመፃፍ ረቂቅ የሚያወጡባቸውን ወረቀቶች ሳይቀዱ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ መጨመር ያዘወትራሉ:: ፀሐፊያቸውም ኮምፒውተሩን ሳታጠፋ መውጣት ታዘወትራለች:: እንዲሁም ኮምፒዩተሩን ከውጭ የሚመጡ ጓደኞቿ ይጠቀሙበታል:: ታዲያ በአንድ ወቅት አቶ ማንጉዳይ አዲስ ለሚቀጠሩ ሠራተኞች ፈተና እንዲያወጡ ታዘው ነበር:: ይሁን እንጂ ፈተናውን ያልተጠበቀ ሰው ሙሉ በሙሉ በመድፈኑ ፈተናው ሳይወጣ አይቀርም የሚል ጥርጣሬ ተፈጥሯል::

**መልመጃ 6**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. ፈተናው እንዴት ሊወጣ ቻለ?
2. ፈተናው ሊወጣ የሚችልበት ሁኔታ ካለ ሁኔታው እንዳይፈጠር ምን ጥንቃቄ መደረግ እንደነበረበት በሪፖርት መልክ ጽፋችሁ አቅርቡ::

ሚስጥር የሆኑ ጉዳዮች ሚስጥራዊነታቸው ካልተጠበቀ በግለሰብ፣ በቤተሰብና በሀገር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ:: በመሆኑም ሚስጥርን ለመጠበቅ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል:: ብዙ ጊዜ ሚስጥርን አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የሚያባክኑ ሰዎች፣ ሚስጥሩ በመወጣቱ ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት እያዩ ምነው ባልተናገርኩና፣ ምነው አፌን በቆረጠውና በማለት በከፍተኛ ፀፀት ውስጥ ሲወድቁ ይታያል:: ለመሆኑ ሚስጥርን ለመጠበቅ ምን ዓይነት ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል?

ሚስጥርን ለመጠበቅ መደረግ ከሚገባቸው ጥንቃቄዎች የመጀመሪያው ሚስጥር የሆኑ ጉዳዮችን ለይቶ ማወቅ ነው:: ሚስጥር የሆኑ ጉዳዮችን ለይቶ ካለማወቅ የተነሳ ሚስጥሮች ሊወጡ ይችላሉ:: በየመሥሪያ ቤቱ ሚስጥር የሚባሉ ጉዳዮች በሥነምግባር ደንቦች ላይ ተዘርዝረው የሚቀመጡትም ለዚህ ነው::

ሚስጥርን ለመጠበቅ መልካም ሥነምግባር ያስፈልጋል:: መልካም ሥነምግባር ያላቸው ሰዎች ሚስጥር የሆኑ ጉዳዮችን ለመጠበቅ ታማኞች ናቸው:: ባንፃሩም መልካም ሥነምግባር የሌላቸው ሰዎች ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ሚስጥር ሊያባክኑ ይችላሉ:: ስለዚህ ሚስጥርን ለመጠበቅ መልካም ሥነምግባርን መገንባት አስፈላጊ ነው::

አንዳንዶች ደግሞ በቸልተኝነት ሚስጥርን ሲያባክኑ ይታያሉ:: ለምሳሌ ሚስጥር ያለበትን ቢሮ ሳይዘጉ በመሄድ፣ ሚስጥር የተፃፈበትን ኮምፒዩተር ሳይዘጉ መሄድ፣ ወይም ሌሎች እንዲጠቀሙበት በመፍቀድ፣ ሚስጥር የሆኑ ጉዳዮችን ለጓደኞቻቸው በመንገር፣ አንድ መሥሪያ ቤት ከለቀቁ በኋላ ቀደም ሲል በሥራ አጋጣሚ ያወቁትን ሚስጥር ኃላፊነት በጎደለዉ ሁኔታ ሲያባክኑ ይታያል:: በመሆኑም ቸልተኝነትን ማስወገድ ሚስጥርን ለመጠበቅ ከሚደረጉ ጥንቃቄዎች ዋነኛው ነው::

**መልመጃ 7**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብባችሁ መልሱ።***

1. ሚስጥር የሆኑ ጉዳዮች በሥነምግባር ደንብ ላይ መገለፃቸው ሚስጥርን ለመጠበቅ እንዴት ይጠቅማሉ? ተወያዩበት።
2. መልካም ሥነምግባር መገንባት ሚስጥርን ለመጠበቅ እንዴት ይጠቅማል?
3. በቸልተኝነት ምክንያት ሚስጥር የሚባክን ባቸውን ሁኔታዎች እንዴት ማስወገድ ይቻ ሳል?

***የቡድን ሥራ***

***ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ሠርታችሁ ሪፖርት አቅርቡ።***

1. *በትምህርት ቤታችሁ ሚስጥር የሚባሉት ጉዳዮች የትኞቹ ናቸው? ሚስጥሮቹንስ ለመጠበቅ ምን ዓይነት ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል?*
2. *በአካባቢያችሁ ካሉት መሥሪያ ቤቶች አን ዱን ምረጡና በዚያ መሥሪያ ቤት ሚስ ጥር የሚባሉት ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ፣ ሚስጥሮቹን ለመጠበቅ ምን ምን ጥንቃቄ ዎች እየተደረጉ እንደሆነ ጠይቃችሁ በጽ ሁፍ ሪፖርት አቅርቡ።*

### 2.4.2 ሚስጥርን አለመጠበቅ በሀገር ላይ የሚያስከትላቸው ችግሮች፣

- ✓ ሚስጥርን ባለመጠበቅ በሀገር ላይ ምን ጉዳት ሊደርስ ይችላል?

በሥራ ላይ ሚስጥርን አለመጠበቅ በርካታ ጉዳቶች ሊያስከትል ይችላል። የሀገር ዳር ድን በር የሚጠበቁባቸው ቁልፍ የሆኑ ሚስጥሮች ሾልከው ከጠላት እጅ ውስጥ ከገቡ ሀገር በቀላሉ ልትደፈር ትችላለች። ለዚህ ነው በጦርነት ወቅት ሀገሮች ሰላዮቻቸውን ወደ ባላጋራዎቻ ቸው ልከው ሚስጥር ፈልፍለው ለማወቅ ጥረት የሚያደርጉት።

በሌላ በኩል ደግሞ ሚስጥር ባለመጠበቁ ምክን ያት ስፍር ቁጥር የሌለው የሀገር ሀብትና ንብ ረት ሊባክን፣ ሊዘረፍና ሊወድም ይችላል። ለም ሳሌ አንድ ከፍተኛ ገንዘብ በሙስና የዘረፈ ሰው ጥቆማ እንደቀረበበት ካወቀ ሳይያዝ ሀገር ጥሎ ሊጠፋ ይችላል። ስለዚህ ጥቆማ አቅራቢውም ሆነ ተቀባዩ ሚስጥሩን መጠበቅ አለባቸው።

እንዲሁም በፍርድ ቤት በፖሊስ የተያዙ ሚስ ጥሮች በቀላሉ የሚባክኑ ከሆነ ወንጀለኞች ሊያ መልጡ በዚህም ዜጐች በመንግሥታቸው ላይ አመኔታ ሊያጡ ይችላሉ። ከዚህም የተነሳ ሀገር ሲዘረፍ፣ ሲወድም ዜጎች ምን ቸገረኝ ብለው ሊያልፉና የሀገር ሀብት ሊባክን ይችላል።

**መልመጃ 8**

***የሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።***


1. ሚስጥር ባለመጠበቅ በሀገር ላይ ምን ዓይ ነት ችግር ሊከተል ይችላል?
2. ሀገራችንን ሊጐበኝ የመጣ አንድ ፈረንጅ ድንገት ተዋወቀሁና የባጥ የቆጡን ሳወራ ለት ጓደኛዬ ስምቶ ተቆጣኝ። ምነው ብዙ የሀገር ሚስጥር አኮ ነግረኸዋል፣ ተገቢ አይደለም አለኝ። እኔ ደግሞ የውጭ ሀገር ዜጋ ስለሆነ ምንም ችግር አያመጣም የሚል ሃሳብ አለኝ፣ እውነት ምን ችግር አለው? እናንተ ምን ትላላችሁ?

***የቡድን ሥራ፣***

1. *ከላይ ከቀረቡት ሚስጥርን አለመጠበቅ ከሚ ያስከትሉት ጉዳቶች መካከል አንዱን መርጣ ችሁ ሚስጥር ባለመጠበቅ በሀገር ላይ ሊከ ሰት የሚችለውን ችግር መርምሩና በቡድን ሆናችሁ ሪፖርት አቅርቡ።*

## 2.5 ሙስናን የመከላከያ መንገዶች፤

### 2.5.1 ሙስናን የሚከላከሉ ዲሞክራሲያዊ ተቋማት አስፈላጊነት፣




ሥዕል 2.2 ሙስናን ለመከላከል
የፀረ ሙስና ተቋሚት ከፈተኛ ሚና አላቸው

- ወጥመዱና ድመቱ ምንን የሚወክሉ ይመስ ላቸኋል?
- በቀረበው የካርቱን ሥዕል ውስጥ የምስ ሎቹን ውክልና ከገለፃችሁ በኋላ ሙስናን በመከላከል ረገድ ያለውን ተምሳሌትነት አስ ረዱ።

## ማን ይሆን ትክክል?

ኡስማን ሙስናን ከመከላከል አንፃር የፖሊስ ኃይል በቂ ነው የሚል አቋም ያለው ሲሆን ምህረት ደግሞ ከዚህ የተለየ አቋም አላት፡፡ አንዱ ሌላውን ለማሳመን ያደረጉት ውይይት ቀጥሎ ቀርቧል፤

**ምህረት፣** የሙስና ወንጀል ከተለመዱት ወንጀሎች የተለየ መሆኑን ትገነዘባለህ?

**ኡስማን፣** ምን የተለየ ግንዛቤ ያስፈልገዋል? ወንጀል ወንጀል ነው፣

**ምህረት፣** እሱን ማን ካደው? የሙስና ወንጀል ከሌሎች ወንጀሎች ጋር ሲነፃፀር ግን የተለዩ ባህሪያት ስላሉት የተለየ ትኩረት ያሻዋል፡፡

**ኡስማን፣** በጀ! ምንድናቸው እነዚህ የተለዩ ባህሪያት?

**ምህረት፣** የሙስና ወንጀል በአፈፃፀም ሥልቱ በአብዛኛው ስሜታዊነት እና ግብታዊነት አይታይበትም፤ ድርጊቱ በሚገባ ታስቦበት እና በጥንቃቄ የሚፈፀም ነው፡፡ በመሆኑም ከሌሎች የተለመዱት ወንጀሎች ጋር ሲነፃፀር ውስብስብ እና ጉዳቱም እጅግ የከፋ ነው፡፡ ስለዚህ ድርጊቱን ለመከላከል የተደራጀ አሠራርን ይጠይቃል፡፡

**ምህረት፣** ሌላም ልጨምርልህ፣

**ኡስማን፣** እሺ ቀጥይ ልስማሽ!

**ምህረት፣** ቀደም ሲል ከጠቀስኩልህ በተጨማሪ በሙስና ወንጀል ተጐጂው መላው ሕብረተሰብ ነው፡፡ በወንጀሉ እኔ ተጐድ ቻለሁ ለጉዳዩ ባለቤት ነኝ ባይ ብዙ ጊዜ ቶሎ አይቀርብም፡፡ በተለመዱት ወንጀሎች ግን የሚጐዳው ግለሰብ/ቤተሰብ ሊሆን ይችላል፡፡

ተበዳዩ ግለሰብ ወይም ቤተሰብ ጉዳዩን ለፍትህ አካላት ቢያቀርብ ለወንጀሉ መፍትሄ ሊገኝለት ይችላል፡፡ ሌሎች ነጥቦችንም ማንሳት ይቻላል፡፡ ታዲያ እነዚህ ነጥቦች የሙስናን ወንጀል ልዩ አያደርጉትም ትላለህ?

**ኡስማን፣** ነገሩ እንዲህ ከሆነማ የሰጠሽኝ ማብራሪያ ጥሩ ነው፡፡ ቢሆንም አሁንም ያለኝን አቋም የሚያስቀይረኝ አይደለም፡፡

**ምህረት፣** በነዚህና በሌሎችም ጉዳዮች የኔ አቋም ግን ሙስና በባህሪው ለየት ስለሚል ጉዳዩን በባለቤትነት ሊከታተሉ የሚችሉ የፀረ ሙስና ተቋማት መቋቋም አስፈላጊና ወሳኝ ነው የሚል ነው፡፡ ተረዳኸኝ

**ኡስማን፣** በእርግጥ የተረዳሁት ነገር ቢኖር ይኼ አሁን የነገርሽኝ ነገር የአንቺ አመለካከት መሆኑን ነው፡፡

### መልመጃ ፱

❓ *ከላይ የቀረበውን ውይይት መሠረት በማድረግ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡*

1. እናንተስ የማን ሀሳብ ትክክል ነው ትላላችሁ? ምክንያታችሁን እየሰጣችሁ ተወያዩበት፡፡

ሙስናን አምርሮ መዋጋትና ከሥር መሠረቱ በማስወገድ ከሙስና የፀዳ ሕብረተሰብ መፍጠር ለነገ የማይባል ጉዳይ ነው፡፡ ሙስናን መታገልና ማስወገድ አስፈላጊ የሆኑባቸው በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም በዋናነት የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ሙስና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትንና መልካም አስተዳደርን የሚያናጋ ነው፡፡ በሙስና ውስጥ የሚገቡ ኃይሎች የግልፅነትና የተጠያቂነት አሠራር ሥርዓት እንዲኖር አይፈልጉም፡፡ ምክንያቱም የሚያጋልጣቸውና ተጠያቂ የሚያደርጋቸው ስለሚሆን ነው፡፡ የግልፅነትና የተጠያቂነት ሥርዓት ከሌለ ደግሞ ለሕግ የበላይነት መገዛት ይጠፋል፡፡ የሕግ የበላይነት ካልኖረ የዜጎች መብቶች ያለአግባብ ይረገጣሉ፡፡ በመሆኑም ሙስናን ለመከላከል የግልፅነትና የተጠያቂነት ሥርዓት መኖር አማራጭ የለውም፡፡

ሙስና የሀገር ልማትን ወደኋላ የሚያስቀር ለሕዝብ እድገትና መልካም ኑሮ ፀር የሆነ ወንጀል ነው፡፡ ይኸው የእድገት ጠንቅ የሆነው የሙስና ወንጀል በተለይ የደሀ ሀገሮች ህዝቦችን በእጅጉ ይጐዳል፡፡ ምክንያቱም መንግሥት ከዜጐች ሰብስቦ ቅድሚያ ለሚሰጠው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት የሚያውለውን ገንዘብ ጥቂት ስግብግብ ባለስልጣናት ዘርፈው በማስቀረት ልማት እንዳይፋጠን ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም ሙስና ሊዋጉት የሚገባ የልማት እንቅፋትና አስከፊ ወንጀል ነው፡፡

የሙስና ወንጀል ውስብስብና በአብዛኛው ደግሞ የሚፈፀመው በባለሥልጣናት መሆኑ ወንጀሉን ከሌሎች ወንጀሎች የተለየ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ሙስናን አዋጅ በማውጣትና ደንቦችን በመቅረፅ ብቻ መከላከልና መግታት አይቻልም፡፡ ስለዚህ ሀገራትና መንግሥታት ይህን ከባድ ወንጀል የሚታገሉበት ተቋማት ያቋቁማሉ፡፡

በሀገራችን የፌዴራልና የክልል ሥነምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽኖች ሙስናን ለመከለከል በአዋጅ የተቋቋሙ መሥሪያ ቤቶች ናቸው፡፡ ተቋማቱ የሥነምግባር ትምህርትን በመስጠት፣ በየመሥሪያ ቤቱ ለሙስና የሚያጋልጡ አሠራሮችን በማስተካከል፣ እንዲሁም ሙስና የሚፈፅሙ ወንጀለኞችን ለፍርድ በማቅረብ ሙስናን ይከላከላሉ፡፡

**መልመጃ 10**

***?***


***ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብባችሁ ተወያዩባቸው::***

1. ሙስና የመልካም አስተዳደር ጠንቅ የሚሆነው እንዴት ነው?
2. ሙስና የልማት እንቅፋት የሚሆነው እንዴት ነው?
3. የሙስና ወንጀልን ለመከላከል ብርቱ ትግል የሚያስፈልገው ለምንድነው?
4. በሀገራችን ሙስናን ለመከላከል የተቋቋሙት ተቋማት ተግባራቸው ምን ምንድ ነው?

### 2.5.2 ሙስናን በመከላከል ረገድ የፍትሕ አካላት ሚና፣




ሥዕል 2.2.1 ሙስናን እንከላከል




ሥዕል 2.2.2 ሙስናን በማስወገድ ፍትሕን እናስፍን

- *እያንዳንዱ ሥዕል የሚያስተላልፈውን መልእክት አብራሩ::*
- *ሙስናን በመከላከል ረገድ የፍትህ አካላት ሚናን አስመልክቶ የሥዕሎቹን ተምሳሌነት አብራሩ::*

እንደ ፖሊስ፣ ፍርድ ቤት፣ አቃቤ ሕግ የመሳሰሉት ሙስናን በመከላከል ረገድ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለባቸው የፍትህ አካላት ናቸው:: እነዚህ የፍትህ አካላት ከሕግ ውጭ የሆኑ ወንጀለኞችን ተከታትለው በማስተካከልና በመቀጣት የሕግ የበላይነት እንዲከበር ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ:: ሙስናም ወንጀል እንደመሆኑ መጠን ሙሰኛ የሆነን ማንኛውንም ግለሰብ እነዚህ የፍትህ አካላት ተከታትለው ሕጉ በሚያዘው መሠረት የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳሉ::

በሀገራችንም ሙስና ወንጀል መሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ውስጥ ተደንግጓል:: በመሆኑም እንደ ፖሊስ፣ ፍርድ ቤትና አቃቤ ሕግ ያሉት የፍትህ አካላት ወንጀለኛን የመያዝ፣ ወደ ፍርድ የማቅረብ ከዚያም በሕጉ መሠረት መቅጣት የሚችሉ አካላት ናቸው::

**መልመጃ 11**


***?***

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. የፍትህ አካላት የሚባሉት ተቋማት እንዴት ያሉ ናቸው?
2. የፍትህ አካላት ሙስናን የሚከላከሉባቸው መንገዶች ምን ምን ናቸው?

### 2.5.3 ሙስናን በመከላከል ረገድ የሕብረተሰቡ ሚና፣

- ✓ ሕብረተሰቡን ያላሳተፈ የፀረ-ሙስና ትግል የሚፈለገውን ውጤት የሚያስገኝ ይመስላችኋል?
- ✓ ሕብረተሰቡን በፀረ ሙስና ትግሉ ውስጥ እንዴት ነው ማሳተፍ የሚቻለው?




ሥዕል 2.3 ሙስናን መዋጋት የዜጐች ሁሉ ኃላፊነት ነው::

*ከዚህ በላይ የቀረበውን ሥዕል መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

- *እያንዳንዱ ሥዕል የሚያስተላልፈው መልእክት ምን ይመስላችኋል?*
- *988 የሚለው ቁጥር የምን ይመስላችኋል? ጥቅሙስ ምንድን ነው?*
- *ሥዕሎቹ ከሚያስተላልፉት መልእክት አንፃር ሙስናን ለመከላከል የሕብረተሰቡ ሚና ምን ሊሆን ይገባል ትላላችሁ?*

### ዳዲ አባ መስጠት

የኩርቱሜ ሰፈር ነዋሪ የሆነው መሐመድ በአምስት መቶ ብር በአንድ መሥሪያ ቤት ንብረት ክፍል ውስጥ ተቀጥሯል። ታዲያ በተቀጠረ በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሱን ከመቀየር አልፎ ችግረኛ ቤተሰቦቹ የተንደላቀቀ ኑሮ እንዲኖሩ አድርጓቸዋል። ለታናሽ ወንድሙ ሚኒባስ ገዝቶ ለታል፤ በሠፈሩ ያሉ ችግረኞችንና አዛውንቶችን ሁሉ ይረዳል። በዓመት በዓል ወቅት በሠፈሩ ላሉ አቅመ ደካሞች በግና ዶሮ ይገዛል። በዚህም ምክንያት በጣም ተወዳጅ ሆኗል።

ጓደኞቹንም አይተውት የማያውቁት ሆቴል እየወሰደ ያዝናናል፤ ከሠፈሩ ልጆች ሁሉ እንደሱ ተወዳጅ የለም። ታዲያ አንዳንዶች ይሄ ነገር ሙስና ሳይሆን አይቀርም፣ ልጁን መምከር አለብን ሲሉ ሌሎች ደግሞ ለፀረ ሙስና አካላት መጠቆም አለብን ይላሉ። በሦስተኛ ወገን ያሉ ደግሞ ምንም ይስራ ምንም እንዲህ መልካም የሚያደርግ ልጅን መመረቅ እንጂ መውቀስ አይገባም ባይ ናቸው።

### *የቡድን ሥራ*

*ከዚህ በላይ የቀረበውን ጉዳይ መሠረት በማድረግ በቡድን በቡድን በመሆን እራሳችሁን በመሐመድ ቦታ አድርጉና ማድረግ የሚገባችሁን በጽሁፍ ሪፖርት አቅርቡ።*

ሙስና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን የሚያናጋና መልካም አስተዳደርን የሚያዳክም፣ ፍትህን የሚያዛባና የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገትን የሚያጓትት በመሆኑ ኅብረተሰቡ አምርሮ ሊታገለው የሚገባ ጉዳይ ነው። ከዚህ አንፃር ኅብረተሰቡ በርካታ ሚና ሊጫወት ይችላል።

ሙስናን የሚፈፅሙ ሰዎች ተቸግረው ሳይሆን ከስግብግብነታቸው ከመነጨ ፍላጎትና ፈጥኖ ለመክበር ሲባል ሥልጣንና ኃላፊነትን ተገን በማድረግ የሚፈፀሙት ታላቅ ወንጀል መሆኑን ኅብረተሰቡ በሚገባ መገንዘብ አለበት። ስለዚህ ሙስና ኅብረተሰብን ለአደጋ የሚያጋልጥ ቀንደኛ ጠላት መሆኑን ተገንዝቦ ለመዋጋት ቁርጠኛ መሆን ከኅብረተሰቡ ይጠበቃል።

ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የሚገኙ ጥቅሞች ትንሽም ይሁኑ ብዙ ሙስና ናቸውና የትኛውንም ዓይነት ጥቅም ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ለማግኘት አለማሰብ፤ እንዲያውም መጠየፍ ከኅብረተሰቡ ይጠበቃል።

ሙስና የዲሞክራሲ፣ የመልካም አስተዳደርና የእድገት ጠንቅ በመሆኑ በዚህ የተሳተፉ ሰዎች በሕግ እንዲጠየቁ በማድረግ በኩል ኅብረተሰቡ ከፍተኛ ኃላፊነት አለበት። እንዲሁም የሙስና ተግባራትን በማንኛውም ጊዜና ቦታ በመዋጋት ሙሰኞች እንዲጋለጡ ለተገቢው አካል መጠቆም ከኅብረተሰቡ የሚጠበቅ ተግባር ነው።

በመጨረሻም በምንሄድባቸው ቦታዎች ሁሉ ለሙስና ምክንያት ይሆናሉ ብለን የምንገምታቸውን ብልሹ አሠራሮች እንዲስተካከሉ መጠቆም ከኅብረተሰቡ የሚጠበቅ ሌላው ጉዳይ ነው። ድር ቢያብር አንበሳ ያስር እንደሚባለው ኅብረተሰቡ ከተባበረ ሙስናን ሊገታ እንዲሁም ከሥር መሠረቱ ሊያጠፋው የሚችልበት ሁኔታ ስላለ ሙስናን ማቆም ይቻላል።

**መልመጃ 12**

### *የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በቡድን በመሆን ተወያዩባቸው።*

1. ሙስናን በመከላከል ረገድ የኅብረተሰቡ ሚና ምን እንደሆነ ተወያዩበት።
2. ሙስናን ማቆም ይቻላል ወይስ መቀነስ ይቻላል በሚሉት ሁለት ሀሳቦች ላይ በቡድን ተወያዩባቸው።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የኢፌዴሪ ሕገመንግሥትና የክልል ሕገመንግሥቶች ሕዝቦች መርጠው በላኳቸው ተወካዮቻቸው አማካኝነት የፀደቁ ሰነዶች ናቸው:: የፌዴራሉ ሕገመንግሥት በሀገሪቱ ያሉ ሕዝቦች መርጠው በላኳቸው ተወካዮቻቸው ተመክሮበት የፀደቀ ሲሆን የክልል ሕገመንግሥቶችም በየክልሉ ያሉ ሕዝቦች በመረጧቸው የክልል ምክር ቤት አባላት ተመክሮባቸው የፀደቁ ሰነዶች ናቸው::

ለሕግ የበላይነት መረጋገጥ መልካም ሥነምግባር ቁልፍ እንደመሆኑ በሀገር ደረጃ ከተማሪዎች በርካታ መልካም ሥነምግባሮች ይጠበቃሉ:: ከነዚህም መካከል *መደማመጥ*፣ መቻቻል፣ ልዩነትን በሰላማዊ መንገድ መፍታት፣ ሀገርን *መውደድ* የመሳሰሉት ይገኙበታል::

*ሥ*ልጣንን መገደብ ለሕግ የበላይነት መረጋገጥ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንዳለው ሁሉ የሥልጣን ገደብ አለመኖር የሕግ የበላይነት እንዳይኖር በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል:: በተለይም የሥልጣን ገደብ አለመኖር የግልፅነትና የተ ጠያቂነት አሠራር እንዳይኖር በማድረግ *ኃላፊዎች* ከሥልጣናቸው *ውጭ* በመውጣት እንዲሰሩና የዜጎች መብቶች እንዲጣሱ ምክንያት ሲሆኑ ይችላሉ::

ሚስጥርን አለመጠበቅ በሀገር ደረጃ በርካታ ችግሮች ስለሚያስከትል ሚስጥርን ለመጠበቅ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል:: ከሚወሰዱ ጥንቃቄዎች መካከልም ሚስጥር የሆኑትን ጉዳዮች ለይቶ ማወቅና በታማኝነትና በጥንቃቄ መጠበቅ ዋና *ዋ*ናዎቹ ናቸው::

ሙስና የሕግ የበላይነት ጠንቅ *ነው*:: ስለሆነም ኅብረተሰቡ አምርሮ ሊታገለው የሚገባው ሲሆን በሌላ በኩልም ሙስናን የሚከላከሉ ተቋማትና የፍትህ አካላት ያስፈልጋሉ:: የሥነምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን ሙስናን የሚከላከል ተ ቋም ሲሆን ፖሊስ፣ አቃቤ ሕግና ዳኞች ደግሞ ሙስናን የሚከላከሉ የፍትህ አካላት ናቸው:: እነዚህ ተቋማትና የፍትህ አካላት ብቻ ሙስናን ለመከላከል በቂ ናቸው ማለት አይቻልም:: በመሆኑም ኅብረተሰቡ ሙሰኞችን በመጠቆምና በማግለል ወዘተ የራሱን የዜግነት ኃላፊነት ሊወጣ ይገባዋል::

© MoE, Not to be re...

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

***ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ::***

**I** ***የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ::***

1. ሙሰናን ለመከላከል ፖሊሶች ብቻ በቂ ናቸው::
2. የሀገር ሚስጥር የሚጠበቀው በከፍተኛ ባለሥልጣናት ብቻ ነው::
3. የሥልጣን ገደብ በማይኖርበት ጊዜ ግልፅነትና ተጠያቂነት አይኖርም::
4. በትምህርት ቤት ደረጃ እንጂ በሀገር ደረጃ ከተማሪ የሚጠበቅ ሥነምግባር የለም::
5. የፌዴራልና የክልል ሕገመንግሥቶች በቅርፅም በይዘትም ምንም ልዩነት የላቸውም::

**II** ***በ "ለ" ሥር የተዘረዘሩትን "ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ::***

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርትን ማስፋፋት፣ | ሀ. አቃቤሕግ። |
| 2. ወንጀለኛን መያዝ፣ | ለ. የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን። |
| 3. ወንጀለኛን በሕግ መሠረት መቅጣት፣ | ሐ. ፍርድ ቤት። |
| 4. የአሠራር ሥርዓት ጥናት ማድረግ፣ ለተግባራዊነቱም ክትትል ማድረግ፣ | መ. ፖሊስ። |
| 5. ወንጀለኛን ወደ ፍርድ ማቅረብ፣ | |

**III** ***ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ::***

1. የፌዴራል ሕገመንግሥቱን ትክክለኛ መጠሪያ የያዘው የቱ ነው?
   ሀ. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት፣
   ለ. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሕገመንግሥት፣
   ሐ. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት፣
   መ. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት።
2. ትክክለኛውን ሃሳብ የያዘው የቱ ነው?
   ሀ. የክልል ሕገመንግሥቶች የሀገሪቱ ሕጐች ሁሉ የበላይ ሕጐች ናቸው፣
   ለ. የክልል ሕገመንግሥት በክልሉ ውስጥ ያሉ ሕጐች ሁሉ የበላይ ነው፣
   ሐ. የክልል ሕገመንግሥት በሀገሪቱ ሕዝቦች ተወካዮች የፀደቀ ነው፣
   መ. የክልል ሕገመንግሥት አልፎ አልፎ ከፌዴራል ሕገመንግሥቱ ጋር ይቃረናል።
3. ሥልጣን የመገደብ ጥቅምን የሚያሳየው የትኛው ነው?
   ሀ. የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ፣
   ለ. የግልፅነትና የተጠያቂነት አሠራር ለማስፈን፣
   ሐ. ሥርዓት - አልበኝነት እንዳይነግሥ ለማድረግ፣
   መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ።
4. ቀጥለው ከቀረቡት መካከል የሙስና መከላከያ መንገድ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ሙሰኞችን መምከር ወይም ማስወገድ፣
   ለ. ለሙስና የሚያጋልጡ ብልሹ አሠራሮችን ማስተካከል፣
   ሐ. ሙሰኞችን ለፍርድ ማቅረብ፣
   መ. ሁሉም መልሶች ይሆናል።

© Not to be republished FDRE Ethiopia

## IV የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ፡፡

- የፀረ ሙስና ተቋማት
- የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን
- የክልሎች የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽኖች
- የክልል ሕገመንግሥት
- የፌዴራል ሕገመንግሥት
- የሕግ የበላይነት
- ሙስና
- ፍርድቤቶች

1. በክልል ምክር ቤት የሚፀድቀው የ________________ ሕገመንግሥት ነው፡፡
2. ሙስናን የሚከላከሉ የፍትህ አካላት ___________ ይባላሉ፡፡
3. ________________ሙስናን ለመከላከል በአዋጅ የተቋቋመ ሃገራዊ ተቋም _________ ይባላል፡፡
4. የፍትሕ አካላት ከሕግ ውጭ የሆኑ ሰዎችን በማስተካከልና በመቅጣት________________ እንዲቀበል ያደርጋሉ፡፡
5. ________________ ወንጀል ነው፡፡

## V የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. የሥልጣን ገደብ በማይኖርበት ጊዜ ግልፅነትና ተጠያቂነት አይኖርም ማለት ምን ማለት ነው?
2. ለሙስና ሊያጋልጡ ከሚችሉ አሠራሮች ሦስቱን ጥቀሱ፡፡
3. ሚስጥርን ለመጠበቅ መደረግ ከሚገባው ጥንቃቄ መካከል የመጀመሪያው ሚስጥር የሆኑ ጉዳዮችን ለይቶ ማወቅ ነው ሲባል ምን ማለት ነው?

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

# ምዕራፍ ሦስት
# እኩልነት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤**

- በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት የተደነገጉ የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን መብቶች ታውቃለህ/ታውቂያለሽ፡፡
- የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብት አለመከበር የሚያስከትለውን ጉዳት ትረዳለህ/ትረጃለሽ፡፡
- ሴቶችና ወንዶች በማንኛውም ሁኔታ እኩል መሆናቸውን ታውቃለህ/ ታውቂያለሽ፡፡
- የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበር እንዳለባቸው ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ፡፡

## 3.1 የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች አካባቢያቸውን የማስተዳደር መብት፤

### 3.1.1 የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች አካባቢያቸውን የማልማትና ከልማቱም እኩል የመጠቀም መብት አስፈላጊነት፣

✓ *የህዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በሀገራችን መከበሩ ምን ምን ጥቅሞች የሚሰጥ ይመስላችኋል?*

በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ የሕዝቦች የእኩልነት መብቶች እውቅና ተሰጥቷቸው ይከበራሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር መቻላቸው አንዱ የዴሞክራሲ ሥርዓት መገለጫ ነው፡፡ በሀገራችን በመገንባት ላይ በሚገኘው የዴሞክራሲ ሥርዓት የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች መብቶች ሊረጋገጡ ችለዋል፡፡ በመሆኑም ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች ሊሳተፉና የመንግሥት ሥልጣን ባለቤት ሊሆኑ ችለዋል፡፡

ይህም በአካባቢያቸውም የልማት እንቅስቃሴዎች በባለቤትነት ስሜት እንዲሳተፉ አስችሏቸዋል፡፡ የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት መረጋገጡ የዴሞክራሲ ሥርዓቱን የበለጠ የሚያጠናክር ሲሆን በዜጎችም መካከል እኩልነት እንዲሰፍን ያደርጋል፡፡

**መልመጃ 1**

**?** ***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. የሕዝቦች የእኩልነት መብቶች እውቅና የሚያስገኛቸውን ጥቅሞች ግለጹ ፡፡
2. የሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት ባይከበር ኖሮ በሀገራችን ምን ችግር ይፈጠር ነበር?





ሥዕል 3.1 ሕዝቦች በጋራ የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ ተቋማት

- *ሥዕሎቹ ምንን ያመለክታሉ?*
- *በአካባቢያችሁ የሚገኙ የልማት ተቋማትን በመዘርዘር ግለፁ፡፡*
- *በእነዚህ የልማት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ህዝቡ እንዴት ባለ ሁኔታ እየተጠቀመባቸው ይገኛል?*

### የቀበሌው ህዝብ የልማት ጥያቄ፤

አቶ ሺበሺ በሚኖሩበት ቀበሌ ንጹህ ውሃ፣ መብራትና የስልክ አገልግሎቶች በበቂ ሁኔታ ለሕዝቡ አልተዳረሱም:: ያሉትም የተወሰኑ አገልግሎቶች ለሕዝቡ የሚዳረሱት መድሎ ባለበትና ግልፅነት በጎደለው አሰራር ነው:: በዚህም የተነሳ አብዛኛው ሕዝብ ስለደረሰበት ከፍተኛ በደል እየተማረረ ይገኛል:: የቀበሌው ሥራ አስፈፃሚም ቢሆን በሕገ መንግሥቱ መሠረት የተጣለበትን ግዴታ አልተወጣም:: ሕዝቡ ግን በልማት ሂደቱ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታትና ንቁ ተሳታፊ ለመሆን ከፍተኛ ፍላጐት አለው::

በዚሁ መሠረት የሕዝቡ ተወካዮች ችግራቸውን ለመስተዳድሩ አካላት በተደጋጋሚ ገልፀዋል:: እነዚህን የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትም በቀበሌው ሕዝብ አቅም ለማልማትና በእኩልነት ለመጠቀም ጥያቄ አቅርበዋል:: ይሁንና አጥጋቢ ምላሽ አላገኙም:: እንደውም የቀበሌው ሃላፊዎች እኛ እናንተን የምንወክል ስለሆንን ይጠቅማል የምንለውን ስራ እንሰራለን፤ እናንተም እኛ የምንለውን በመቀበል ማስፈጸምና መጠቀም አለባችሁ በማለት ገለጹላቸው::

**መልመጃ 2**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::*

1. አቶ ሺበሺ የሚኖሩበት ቀበሌ ኃላፊዎች ለሕዝቡ የልማት ጥያቄ የሰጡት መልስ አግባብነት አለው ትላላችሁ? ለምን?
2. ሕዝቡ በቀጣይ ችግሩን ለመቅረፍ ምን ማድረግ አለበት ትላላችሁ? ተወያዩበት::
3. ሕዝቡ ቀበሌው ባለው አቅምና በራሱ በሕዝቡ ድጋፍ በጋራ እንጠቀም ብሎ ጥያቄ ማቅረቡ ስህተት ነውን? ለምን?
4. በአካባቢያችሁ እንዲህ ያለ ሁኔታ አለ? ካለስ ለወደፊቱ ምን መስራትና መለወጥ ታስባላችሁ? ተወያዩበት::

### 3.1.2. ክልሎችን ከሀገር ልማት እኩል ተጠቃሚ ለማድረግ፣ ሰላምን ለማስፈንና ዕድገትን ለማፋጠን፤

የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች እኩልነት መከበር የብዙኃን ተጠያቂነት ስለሚረጋገጥ ዜጐች ክልላቸውን ለማልማት እንዲነሳሱ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው:: የሕዝቦች የእኩልነት መብቶች ከተረጋገጡ ሕዝቦች በጋራና በመቻቻል የሚኖሩበት ሁኔታ ይፈጠራል:: ይህ ሲሆንም ሕዝቦቹ ከሀገራቸውም ሆነ ከክልላቸው ሀብት እኩል ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ:: ከልማት እኩል ተጠቃሚነትም ሲኖር ዜጐች ድህነትና ኋላቀርነትን ለማስወገድ በሙሉ ልባቸው በጋራ ይረባረባሉ::

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከክልላቸውም ሆነ ከሀገራቸው ሀብትና ልማት እኩል ተጠቃሚ መሆናቸው የሀገር አንድነትን ያጠናክራል:: ለጋራ ዕድገት በጋራ ለመሥራትም የበለጠ ያነሳሳል:: ልማትን ያፋጥናል:: ፈጣን ልማት ሲረጋገጥም ከጦርነት ይልቅ ሰላም፣ ከመበታተን ይልቅ አንድነት፣ ከኋላቀርነት ይልቅ ዕድገት ዕውን ይሆናል::

**መልመጃ 3**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

1. ሕዝቦች ከአካባቢያቸው ልማት እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማህበረሰቡም ሆነ ከእናንተ ምን ይጠበቃል?
2. ለጋራ እድገት በጋራ መሥራት የሚያስገኛቸውን ፋይዳዎች ዘርዝሩ::
3. የእኩል ተጠቃሚነት በሌለበት ሀገር ውስጥ ምን ሊከሰት ይችላል?

## 3.2 እኩል ተጠቃሚነት ካልኖረ የሚያስከትለው ጉዳት፤

✓ የእኩል ተጠቃሚነት መብት ካልተከበረ ምን ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ግለጹ::

በዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ሥርዓት መብት በመብትነቱ መከበር አለበት:: መብትን አለማክበር በዜጐች መካከል የበላይና የበታችነትን ያስከትላል:: ይህም በሕብረተሰቡ ውስጥ ቅራኔ እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል:: በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ መብቱ ያልታወቀለትና ያልተከበረለት ሕዝብ መብቱን ለማስከበር ለመታገል ይገደዳል:: በዚህም ጦርነት ሊቀሰቀስና ሰላምም ሊደፈርስ ይችላል:: ይህም እድገት ሳይሆን ጥፋት እንዲከተል ያደርጋል::

በተለይ እንደ እኛ ባለ ብዙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባሉበት ሀገር ውስጥ የሕዝቦች የእኩል ተጠቃሚነት መብት ካልተከበረ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት አይቻልም:: በመሆኑም የሕዝቦችን መብት ማወቅና ማክበር የዜጎችን ሁሉንም ዓይነት መብት ማክበር ነው::

ተደጋግፎ ለማደግና፣ እድገትንም ቀጣይነት ያለው ለማድረግ መብቶች ሳይሸራረፉ መከበር አለባቸው:: ይህም የዜጎችን የእኩልነት መብትና ጥቅም ለማስከበር ይጠቅማል::

**መልመጃ 4**

***በሚከተሉት ሃሳቦች ላይ ተወያዩባቸው::***

1. ያለ እኩልነት ዴሞክራሲ፣ ያለዴሞክራሲ ሠላም፣ ያለሠላም ሥራ፣ ያለ ሥራ ልማት፣ ያለልማት ብልፅግና አይገኝም:: ይህ አባባል ትክክል ስለመሆኑ ተወያዩበት::
2. ሕዝቦች ለጋራ ልማትና እድገት በጋራ እን ዲያስቡ የእኩል ተጠቃሚነት መብት ያለውን ፋይዳ በማብራራት አስረዱ::
3. በሀገራችን የተጠናከረ ዴሞክራሲያዊ ሥር ዓት ለመገንባት ከመንግሥትና ከእያንዳንዱ ዜጋ ምን ይጠበቃል?
4. የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦችን የእኩ ልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶችን አለ መቀበልና አለማክበር ምን ምን ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል?

## 3.3 የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች እኩልነት፤

### 3.3.1 የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቋንቋዎችና ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች መከ በራቸው የሚኖረው ጠቀሜታ፣



*ሥዕል 3.2 ኢትዮጵያ የተለያዩ ሕዝቦች መገኛ ሀገር*

- *ከሥዕሉ የተገነዘባችሁትን ለክፍል ጓደኞቻ ችሁ ግለጹላቸው::*

የሕዝቦች የእኩልነት መብት መገለጫ ከሆኑት መካከል አንዱ የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕ ዝቦች ቋንቋዎች፣ እንዲሁም ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች መከበር ነው:: የሕዝቦች የማንነት መገለጫ የሆነው ቋንቋቸው፣ ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች ወዘተ የአንዱ ከሌላው ሊያንስ ወይም ሊበልጥ የሚችልበት ምንም ምክንያት የለም:: ሁሉም እንደየባህላቸው በእኩልነት ለጋራ አላማ ተባብረው መኖር ይችላሉ:: ይህም እውን የሚሆነው በመቻቻልና በመተሳሰብ መርህ ላይ ሲመሠረት ብቻ ነው::

በዚሁ መሠረት በሀገራችን የተለያዩ ቋንቋ ዎችና፣ ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች መኖራ ቸው እንደ ችግር ሳይሆን እንደ ውበት መገለጫ ዎች ስለሆኑ እንደ መታደል ተቆጥሮ መቀ በሉ ተገቢ ነው::

እያንዳንዱ ሰው በራሱ ቋንቋ መገልገል፣ በራሱ ባህል መኩራትና ባህሉን ማሣደግ እንደሚችል ሁሉ የሌላውንም ሰው መብት መቀበልና ማክ በር የሥልጣኔ መገለጫ ነው:: ይህንን ነፃነትና መብት በማንኛውም ሁኔታ መገደብም ሆነ አስገ ድዶ መከልከል የማይቻል ነው:: ይህም በሕገመ ንግሥቱ አንቀፅ 27 ላይ በግልፅ ሰፍሮ ይገኛል::

ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የህሊናና የሃይማኖት ነፃነት ስላለው አንዱ የሌላውን መብት አክብሮ የራሱንም መብት ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅ በታል:: ማንም ሰው አንዱ የበላይ ሌላው ደግሞ የበታች እንደሆነ ሊቆጠር አይገባም:: ሁሉም እኩል ናቸው:: በአጠቃላይ የዜጎች የቋን ቋና ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች እኩልነት ካልተከበረ አድሎ ይከተላል:: ይህ የአድሎና የጭቆና ሁኔታ ደግሞ የዜጎችን አጠቃላይ መብት የሚጎዳ ነው::

በመሆኑም የቋንቋና፣ የሌሎችም ባህላዊ መገለ ጫዎች መብቶች እኩልነት መከበር ለዴሞክ ራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ለጠንካራ አንድነት ምሥረታ እጅግ አስፈላጊ ነው:: ስለሆነም ማንኛ ውም ዜጋ የራሱ ባህላዊ መገለጫዎች እንዲከ በሩለት የሚፈልገውን ያህል የሌላውን ማክበርና ለእኩልነታቸውም በፅናት መቆም ይኖርበታል::

**መልመጃ 5**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::***

1. ቋንቋም ሆነ ሌላ ባህላዊ መገለጫ በእኩ ልነት ይከበር ሲባል ምን ምን ጉዳዮችን ያካትታል?
2. የተለያዩ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች መኖራቸው የአንድነ ታችን መገለጫዎች ናቸው ሲባል ምን ማለት ነው?

## 3.4 የፆታ እኩልነት፤

### 3.4.1 የፆታ እኩልነት የሚሰጠው ጥቅም፣

- ✓ *የፆታ እኩልነት መከበር ምን ምን ጥቅሞችን ያስገኛል?*

**"አዲሱ የቤተሰብ ረቂቅ ሕግ"**

አንድ የክልል ምክር ቤት አዲስ የቤተሰብ ሕግ በማርቀቅ ላይ ይገኛል:: የረቂቁ ሕግ አንዱ ዓላማም የቤተሰብን ንብረት ሕጋዊ ወራሽ የሚመለከት ነው:: በዚህም መሠረት ከረቂቅ ሕጉ አንቀጾች አንዱ የውርስ መብትን ለወንድ ልጆች ብቻ እንዲፈፀም ይወስናል:: አብዛኞቹ የምክር ቤቱ አባላትም አካባቢያቸው ባህላዊ እሴት እንደ ሚፈቅደው በመቀበል ረቂቁን አንቀጽ ደግፈው ተከራክረዋል::

*ምንጭ: የሰብዓዊ መብት ትምህርት ማስፋፊያ፣ 1990 ዓ.ም*

**መልመጃ 6**

*ከላይ በቀረበው ምንባብ መሠረት የሚከተለውን ጥያቄ መልሱ::*

የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 35(7) ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው። በተለይ መሬትን በመጠቀም፣ በማስተላለፍ፣ በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው። እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው።

- የአንቀጽ 35(7) ሕገመንግሥታዊ አባባል ምን ማለት ነው? አብራሩ::

**መልመጃ 7**

*በሚከተለው ጥያቄ ላይ ተወያዩ::*

በኢፌዴሪ ሕገመንግሥት መሠረት ከላይ የተመለከተው አዲሱ የቤተሰብ ረቂቅ ሕግ ተቀባይነት ይኖረዋል? ለምን? ተወያዩበት::

የፆታ እኩልነት ሲባል በዴሞክራሲ መብቶች፣ በሰብዓዊ መብቶች፣ በሕግ ፊትና በሕገመንግሥቱ እውቅና ባገኙ ሌሎች መብቶች ሁሉ ሴቶች ከወንዶች እኩል ናቸው ማለት ነው:: የሴቶች እኩልነት ሴቶች ከወንዶች እኩል የመሰላቸውን አመለካከት የመያዝና የማራመድ፣ በትዳርና በንብረት ላይ እኩል የመወሰን፣ የመምረጥና የመመረጥ መብት፣ ስብዕናቸውን ከሚያንቋሽሽ ጎጂና ኋላቀር ድርጊት ነፃ የመሆን መብቶች አሏቸው::

የሴቶች እኩልነት ከተከበረ፣ ለሀገር እድገትና ብልፅግና ከወንዶች ያላነሰ የድርሻቸውን ማበርከት ይችላሉ:: በዚህም ምክንያት በሀገራችን የተፋጠነና ዘላቂ ልማትን አስተማማኝ ማድረግ ይቻላል:: ከሀገራችን ሕዝብ ግማሹ (50 በመቶ) ሴቶች ናቸው::

በመሆኑም የሁሉንም ዜጎች መብት የሚያከብር ሥርዓት አለ ለማለት የሚቻለው የሴቶች እኩልነት የተከበረ ሲሆን ብቻ ነው:: የኅብረተሰቡን ግማሽ ያህል ወገን መብት የረገጠ ሥርዓት ካለ ይህ ሥርዓት በምንም አይነት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊሆን አይችልም::

የሴቶች እኩልነት መብት ባለመከበሩ የሚጎዱት በተናጠል ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ፣ ሕብረተሰቡ በአጠቃላይ ነው:: ይህም የሚሆነው ኅብረተሰቡ ግማሽ አቅሙ (የሴቶችን ችሎታና አቅም) ስለሚጎዳና ስለሚባክን ነው:: በዴሞክራሲ የሴቶች መብት መከበር ያለውን ስፍራ በመረዳት ይህን ለማስቀረት በሕገመንግሥቱ ውስጥ የፆታ እኩልነት ጉዳይ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶታል:: በዚሁ መሠረት በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 35 ከሰፈሩት የሴቶች መብቶች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ::

ሀ. ሕገመንግሥቱ ያረጋገጣቸውን መብቶችና ጥበቃዎች ሁሉ ከወንዶች እኩል የመጠቀም፣
ለ. ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ፣
ሐ. ለእኩል ሥራ እኩል የመወዳደርና እኩል ክፍያ የማግኘት፣
መ. በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት የማግኘትና ጋብቻን በፍላጎቷ ብቻ የመመስረት፣
ሠ. ሴቶችን ከሚያንቋሽሽና ከሚጎዱ ኋላቀር ልማድና ድርጊቶች ነፃ የመሆን ወዘተ መብቶች::

ስለሆነም ሴቶችን በበታችነት የሚያይና መብቶቻቸውን የሚጎዳ ማንኛውም ሁኔታ ሲኖር ሴት ወንድ ብለው ሳይለዩ መቃወምና መታገል ተገቢ ይሆናል:: ሴቶች በማህበር የመደራጀት መብታቸውን በመጠቀም፣ ወንዶችም ከጎናቸው ቆመው ድጋፍ በማድረግ የሴቶችን እኩልነት የሚፃረር አመለካከትና ድርጊት በጋራ መታገል ይጠበቅባቸዋል::

**የሴቶችን የእኩልነት መብት ለማስከበር ወንዶችም ሃላፊነት አለባቸው::**

**መልመጃ 8**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የጋራ ድምዳሜ ላይ ድረሱ::*

1. የፆታ እኩልነት መብት ስንል ምን ምን ጉዳዮችን ያካትታል?
2. የሴቶችን መብት ማስከበር የኅብረተሰቡን መብት ማስከበር ነውና የሚባለው ከምን አንፃር ነው?
3. ለእኩል ስራ እኩል ክፍያን የሚለው አስተሳሰብ ምንን ያመለክታል?
4. ያለሴቶች ተሳትፎ የሚካሄድ የልማት እንቅስቃሴ «በአንድ እጅ ለማጨብጨብ እንደ መሞከር ነው ሲባል ምን ለማለት ነው?»

## 3.5 የአካል ጉዳተኝነት፤

### 3.5.1 የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበር የሚሰጠው ጠቀሜታ፣



ሥዕል 3.3 የአካል ጉዳተኞች ተገቢውን ድጋፍ ካገኙ ውጤታማ ተግባራትን ለማከናወን ይችላሉ

- ከሥዕሉ የተገነዘባችሁትን በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው::
- የአካል ጉዳቶኞች ሙሉ አካል እንዳላቸው ሰዎች ማንኛውንም ድርጊት ማከናወን የሚችሉ ይመስላችኋል?

**የተማሪ ምጥንና የአቶ ዘካርያስ ቃለ ምልልስ፣**

**ተማሪ ምጥን:-** ለዚህ ቃለመጠይቅ ፈቃደኛ ስለሆኑ ከልብ አመሰግናለሁ::

**አቶ ዘካሪያስ:-** እኔም እድሉን ስለሰጠሽኝ አመሰግናለሁ::

**ተማሪ ምጥን:-** የትውልድ ቦታዎ የት ነው? አስተዳዳግዎትስ?

**አቶ ዘካሪያስ:-** የተወለድኩት በቀድሞው አጠራር ወሎ ክፍለ ሀገር ይባል በነበረው በደሴ ከተማ ውስጥ ነው:: አስተዳደጌም በእናትና በአባቴ ቤት ውስጥ ከሁለት ወንድሞቼና ከሁለት እህቶቼ ጋር ነው::

**ተማሪ ምጥን:-** እንዴት ወደዚህ አሁን ወዳሉበት ስፍራ ሊመጡ ቻሉ?

**አቶ ዘካሪያስ:-** ወደዚህ የመጣሁት በልጅነቴ ሁለት እግሮቼን በድንገተኛ የመኪና አደጋ ካጣሁ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ተጨማሪ ህክምና መከታተል ስለነበረኝ ነው:: ከዚህ በላይ ግን ቤተሰቦቼም ሆኑ የአካባቢዬ ሕብረተሰብ ከተጎዳሁ በኋላ የነበራቸው አመለካከት የተዛባ ስለነበር አስቸጋሪ ሁኔታ ገጠመኝ:: ሰው እንዳያየኝና እንዳይጠቋቆምብኝ በማለት ቤት ውስጥ ይደብቁኝ ነበር::

**ተማሪ ምጥን:-** ወደዚህ ስፍራ ከመጡ በኋላ በሕብረተሰቡ ዘንድ ለአካል ጉዳተኞች የነበረው አመለካከት ምን ዓይነት ነበር?

**አቶ ዘካሪያስ:-** እውነቱን ለመናገር ከመጣሁበት አካባቢ የተሻለ ሆኖ አላገኘሁትም:: በአብዛኛው አካባቢዎች ተመሳሳይ ይመስለኛል:: በወቅቱ መጀመሪያ ላይ የሚያስጠጋኝ አጥቼ በየቤተክርስቲያኑ ደጃፍና በመንገድ ዳር ላይ በመተኛት ጭምር አሳልፌያለሁ:: ይህንን ስልሽ ግን በተቃራኒው ብዙ ደግ ሰዎች ያዝኑልኝና ይረዱኝ እንደነበር መግለጽ እፈልጋለሁ::

**ተማሪ ምጥን:-**በአሁኑ ጊዜ ምን እየሰሩ ይገኛሉ?

**አቶ ዘካሪያስ:-** አሁን ጡረታ ወጥቻለሁ:: ቀደም ሲል በአንድ የሹራብ ፋብሪካ ውስጥ ምርት ክፍል በሥራ ተሰማርቼ ከ30 ዓመታት በላይ አገልግያለሁ:: ማሽኖችንም በማንቀሳቀስና በመጠገን ሥራም ተሰማርቼ ሰርቻለሁ:: በሥራዬም እጅግ ከፍተኛ እርካታ አግኝቻለሁ:: ባለትዳርና የልጆች አባት ነኝ:: የራሴ መኖሪያ ቤት በመሥራቴም ኑሮዬ መልካም ሆኗል:: ያቅሜን ያህል ባልጥርና ሥራ ንቄ ልመናን ብመርጥ ኖሮ ይህን ሁሉ ባላገኘሁና ባላየሁም ነበር::

**ተማሪ ምጥን:-** እርስዎ የአካል ጉዳተኛ መሆንዎ ሳያግዶት ከባድ ሥራዎችን ሳይቀር በመስራት ውጤታማ ሆነዋል:: ለሌሎች ምን ይመክራሉ?

**አቶ ዘካሪያስ:-** እኔ ሥራ ስቀጥር ሳልንቅ በትንሽ ደሞዝ ነበር:: ከመለመንና የሰው እጅ ከማየት ይሻላል በማለት ራሴን አሳምኜ ነው:: ስለዚህ የአካል ጉዳተኛ ማለት ሥራ የማይሰራ ለማኝና ተመፅዋች ማለት አይደለም:: ይልቁንስ በራስ መተማመን ካዳበረ፣ አስተሳሰቡን ካስተካከለና ድጋፍ ከተደረገለት ለትውልድ የሚጠቅም ትልቅ ሥራ መስራት ይችላል:: ወደፊትም ሁኔታዎች እየተሻሻሉ ሊመጡ ስለሚችሉ በምንኖርበት አካባቢ ሆነን ሥራን ሳንንቅ ያቅማችንን መስራት አለብን::

**ተማሪ ምጥን:-** በትርፍ ጊዜዎት ምን ምን ተግባራትን ያከናውናሉ?

**አቶ ዘካሪያስ:-** እኔ አሁንም ቢሆን የምችለውን እሰራለሁ::ለምሳሌ በጓሮዬ አትክልት እተክላለሁ፣ ዶሮዎችን አረባለሁ፣ ጊዜ ሳገኝ መፃህፍትን አነባለሁ፣ ስፖርት በተለይ እግር ኳስ ስቴዲየም በመግባት ጭምር እከታተላለሁ::

**ተማሪ ምጥን:-** አመሰግናለሁ::

**አቶ ዘካሪያስ:-** እኔም አመሰግናለሁ::

**መልመጃ ፱**

***ከላይ በቀረበው ቃለ ምልልስ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ከአቶ ዘካሪያስ ሕይወት ምን ቁምነገር ተማራችሁ? ለጓደኞቻችሁ ግለጹላቸው፡፡
2. አቶ ዘካሪያስ የአካል ጉዳተኛ ማለት ለማኝና ተመጽዋች ማለት አይደለም ብለው ሲገልጹ ምን ማለታቸው ነው?
3. አቶ ዘካሪያስ ለአካል ጉዳተኝነት የተዳረጉት በምን ምክንያት ነበር? እንዲህ ያለ አደጋን ለመቀነስና ለማስቀረት ምን ማድረግ ይጠበቅባችኋል?

የአካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ሙሉ አካል እንዳለው ሰው ሠርተው መኖር፣ ራሳቸውን መለወጥ፣ ለልማትና እድገት ከፍተኛ አስተዋፆ ማድረግ ይችላሉ፡፡ በየወቅቱ በርካታ የአካል ጉዳተኞች ከሰው እጅ ጠባቂነትና ከተረጅነት ስሜት በመላቀቅና በመሥራት ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ከችግር በማውጣት ለሌሎች አርአያ ሲሆኑ ይስተዋላል፡፡ ስለሆነም የአካል ጉዳተኞች ሰው ሆነው በመፈጠራቸው ብቻ ሰብዓዊ መብቶቻቸው በተሟላ መልኩ ሊከበሩላቸው ይገባል፡፡

የአካል ጉዳተኞችን መብቶች በተሟላ መልኩ ማክበር የእኩልነትና የሀገር ፍቅር ስሜታቸውን ያዳብራል፡፡ የእኩልነትና የሀገር ፍቅር ስሜታቸው ሲጎለብት ደግሞ ለሀገር ልማት የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ እንዲያሳድጉ ያስችላቸዋል፡፡ ስለዚህም የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ማክበርና ማስከበር የሁሉም ዜጋ ሃላፊነት ሊሆን ይገባል፡፡

**መልመጃ 10**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. የአካል ጉዳተኞችን መብቶች በተሟላ መልኩ ማክበር የሚያስገኛቸውን ጥቅሞች ዘርዝሩ፡፡
2. በአካባቢያችሁ ለአካል ጉዳተኞች የሚደረጉ እንክብካቤዎችን በመለየት በፅሁፍ አቅርቡ፡፡
3. በአካባቢያችሁ በሥራ ላይ የተሰማሩ የአካል ጉዳተኞችን ፈልጋችሁ በማግኘትና ቃለመጠይቅ በማድረግ፣

ሀ. በምን ዓይነት የሥራ መስኮች እንደተሰማሩ፣

ለ. ስለቤተሰባቸው ሁኔታ፣

ሐ. ሲደረጉላቸው ስለሚገቡ ድጋፎችና ሲከበሩላቸው ስለሚገቡ መብቶች አጭር ፅሁፍ በማዘጋጀት በክፍላችሁ ውስጥ አቅርቡ፡፡

## 3.6 የሃይማኖት እኩልነት መብት አለመከበር የሚያመጣው ጉዳት

### ሀ. በግለሰብ ደረጃ፣

ማንኛውም ሰው የራሱ ሃይማኖት የሚያስደስተውን ያህል ሌላውም በራሱ ሃይማኖት እርካታ እንደሚያገኝ ማወቅ ይኖርበታል፡፡ የሌላውን ሃይማኖት አለማንቋሸሽና እኩል እንደሆነ መመልከትም ከያንዳንዱ ዜጋ ይጠበቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የራስን እምነት በሌላው ላይ በኃይል ለመጫን መሞከር ተገቢ አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም እያንዳንዱ ዜጋ ይህንን ተገንዝቦ የሌላውን የእምነት መብት ማክበርና ማስከበር ይጠበቅበታል፡፡ አንድ ዜጋ የራሱን ሃይማኖት ይዞ ከሌላው ጓደኛው ወይም ጎረቤቱ ጋር በአንድነትና በሰላም መኖር ይችላል፡፡ የሃይማኖት ልዩነት በራሱ ወደ ብጥብጥና አለመግባባት የሚያመራ ጉዳይ አይደለም፡፡ ሆኖም የአንድ ሃይማኖት ተከታይ የሌላውን ሃይማኖት ሲያንቋሽሽ፣ ሲዘልፍ፣ ዝቅ አድርጎ ሲመለከት ወዘተ አለመግባባት ይፈጥራል፡፡ ይህም ወደ ግጭት፣ ንትርክና ብጥብጥ በማምራት የግለሰቦችን የአብሮነት ኑሮ ሊያደፈርስ ይችላል፡፡ ስለሆነም የሃይማኖት እኩልነት መብትን አለማክበር ለግለሰቦችም ከፍተኛ ጉዳት አለው፡፡

### ለ. በሀገር ደረጃ፣

በሀገራችን ኢትዮጵያ ለረጅም ዘመናት መንግሥታዊ ሃይማኖት የነበረ በመሆኑ በሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች ላይ ጭቆና ያሳደረና በሀገሪቱ የሃይማኖት እኩልነት እንዳይሰፍን ያደረገ ጉዳይ ነው፡፡ ምንም እንኳን በወታደራዊው መንግሥት ወቅትም ሃይማኖትና መንግሥት እንዲለያዩ ቢደረግም በተለይ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት ከፀደቀበት ጊዜ አንስቶ ግን በኢትዮጵያ ውስጥ መንግሥትና ሃይማኖት በማያሻማ ሁኔታ ተለያይተው የየራሳቸውን የሥራ ድርሻ ይዘው እንዲቀጥሉ ተደርጓል፡፡ ይህን በተመለከተም በሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 11 ላይ:

1. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፡፡
2. መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም፡፡
3. መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ላይ ጣልቃ አይገባም፡፡ በሚል ተደንግጓል፡፡

አንዱ ሃይማኖት የተከበረና የበላይ፣ ሌላው ሃይማኖት ደግሞ የተናቀና የበታች ከሆነ፤ የዜጎች

መብት በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ይሆናል ማለት አይቻልም፡፡ የመብት መገፈፍ፣ አድሎና ጭቆና ካለ ደግሞ ዜጎች መብታቸውን አስገ ፍፊው መቀመጥ ስለማይችሉ ለመብታቸው ሲሉ ወደ ትግል ውስጥ ይገባሉ፡፡ በዚህም የእ ርስ በእርስ ጦርነት ይነግሣል፤ የሕዝቦች ሠላም ይናጋል፡፡ ግጭትና ጦርነት ባለበት የሀገር እድገትና ብልጽግና የማይታሰብ በመሆኑ ከድህ ነት ለመላቀቅ የማይቻል ይሆናል፡፡ ስለሆነም ዜጐች በዴሞክራሲ ግንባታና በልማት እንቅስ ቃሴ ውስጥ ጉልህ ተሳትፎ ያደርጉ ዘንድ የሃይማኖት እኩልነት ሊከበር ይገባዋል፡፡

## መልመጃ 11

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡*

?

1. የሃይማኖት እኩልነት መብት አለመከበር በግለሰብም ሆነ በሀገር ደረጃ ምን ጉዳት ያስከትላል?
2. የመንግሥትና ሃይማኖት አንዱ በሌላው ጣልቃ አለመግባት ምን ጥቅም ይሰጣል?

© MoE, FDR Ethiopia
Not to be republished

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የእኩልነት መብቶች እውቅና ማግኘታቸውና መከበራቸው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን ለማጠናከር ቁልፍ ጉዳይ ነው። በሀገራችን የሚገኙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብቶቻቸው መከበሩ እኩልነታቸውን ለማረጋገጥ ያስችላል። የእኩልነት መብቶች መረጋገጣቸው የጋራ ቃልኪዳን መተዳደሪያ በሆነው ሕገመንግሥት መሠረት የጋራ አንድነት ፈጥረው በመቻቻል ለመኖር ያስችላቸዋል። ችግሮችና አለመግባባቶችም ሲፈጠሩ በሠላም ለመፍታት ከመቻላቸውም በላይ በአካባቢያቸው ልማት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

ባለፉት ሥርዓቶች የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎችን አንዱን የበላይ ሌላውን የበታች አድርጎ መመልከት የተለመደ ነበር። ይሁንና አሁን በሀገራችን እየተገነባ ባለው የዴሞክራሲ ሥርዓት የሕዝቦች ባህላዊ መገለጫዎች በሕገመንግሥቱ እውቅና አግኝተዋል። የሀገራችን ማንኛውም ዜጋ በቋንቋው የመገልገል፣ የመሰለውን ሃይማኖት የመከተል መብት አለው። ከዚህ ጎን ለጎን የሌሎችንም ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎችን በተገቢው ሁኔታ ማክበር የሁሉም ዜጋ ግዴታ ነው። ይህ ሲሆን የሕዝባችን የልማትና የብልፅግና ተስፋ ብሩህ ይሆናል።

በቀደምት የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሥርዓቶች ሴቶች የበታች ወንዶች የበላይ ተደርገው ይታዩ ነበር። ነገር ግን ይህ ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ አድሎአዊና ጨቋኝ አመለካከት በአሁኑ ጊዜ እየተሻሻለ በመምጣት ላይ ይገኛል። ይህም የሆነው በሀገራችን ለሁሉም ወገኖች መብት እውቅና የሰጠ ዴሞክራሲያዊ ሕገመንግሥት ጸድቆ በሥራ ላይ ስለሚገኝ ነው። ስለ-ሆነም ሴቶች ከወንዶች እኩል ሙሉ ክብርና መብት የሚለው አስተሳሰብ በሕብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤው እየሰፋ መጥቷል። ይሁንና አሁንም ቢሆን የሴቶችን የእኩልነት መብቶች በተሟላ መልኩ ለማስከበር ከሴቶች፣ ከወንዶች፣ ከሕብረተሰቡና ከመንግሥት የሚደረገው ድጋፍ ተጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል።

የአካል ጉዳተኞች ማንኛውም የሰው ልጅ ያሉት መብቶችና ነፃነቶች ሁሉ አሏቸው። ስለሆነም የሰብዓዊ መብቶቻቸውና ነፃነቶቻቸው በተሟላ መልኩ መከበር አለባቸው።ሰብዓዊ መብቶቻቸውና ነፃነቶቻቸው ከተከበሩላቸው የአካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ሰው ሰርተው መኖር፣ ራሳቸውን በኑሮ ማሻሻልና ለሀገር ልማትና ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላሉ። ይህ በመሆኑም የአካል ጉዳተኞች መብቶች በተሟላ መልኩ እንዲከበር ማድረግ የሁሉም ዜጋ ሃላፊነት ነው።

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**መስተዳድር፣** የአንድን አካባቢ ሕዝብ የሚወክል ወይም የሚያስተዳድር አካል።

**ፋይዳ፣** ጠቀሜታ፣ አስተዋፆ።

**ሚና፣** ተግባር፣ ዓላማ።

**ተመፅዋቾች፣** ተረጂ፣ ተደጓሚ፣ ከሌሎች ፈላጊ።

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ፡፡*

I *የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ፡፡*

1. የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት መከበሩ የእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገለጫ ነው፡፡
2. ሕዝቦች ከአካባቢያቸውም ሆነ ከሀገራቸው ልማት በእኩልነት ተጠቃሚ ባይሆኑም በሙሉ ፈቃዳቸው ከሌሎች ሕዝቦች ጋር በአንድነት መኖር ይመርጣሉ፡፡
3. በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሴት ሀብት/ንብረትን የማፍራትና ባለቤት የመሆን፣ የማስተላለፍና የማውረስ መብቶች አሏት፡፡
4. የሴቶች የእኩልነት መብት ባለመከበሩ የሚጎዱት ሴቶች ብቻ ናቸው፡፡
5. የአካል ጉዳተኞችን መብቶች በተሟላ መልኩ ማክበር የእኩልነትና የሀገር ፍቅር ስሜትን ይቀንሳል፡፡

II *በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ "ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ፡፡*

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መስተዳደር፣ | ሀ. የጥቅምና ግዴታ እኩል ተካፋይነት መኖር፡፡ |
| 2. የእኩል ተጠቃሚነት አለመኖር፣ | ለ. ጥላቻና መራራቅን የሚፈጥር፡፡ |
| 3. የአንድነት መሠረቶች፣ | ሐ. የአንድን አካባቢ ሕዝብ የሚመራ ወይም የሚያስተዳድር፡፡ |

III *ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡*

1. ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እራሳቸውን በራሳቸው በማስተዳደራቸው ከሚያገኙት ጥቅም ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?
   ሀ. የራስን ዕድል የመወሰንና የራስን መንግሥት የመመስረት መብት፣
   ለ. የበላይና የበታች ተብሎ መጨቆንና ጥላቻ፣
   ሐ. በፈቃዳቸው እንደፈለጉት መወሰን፣
   መ. ሠላም፣ ልማትና ተከባብሮ መኖር።
2. ከሚከተሉት መካከል የእኩል ተጠቃሚነት መብት ባለመኖሩ ምክንያት የሚከሰተው ችግር፤
   ሀ. ድህነትና ኋላ ቀርነት ነው፣
   ለ. ብጥብጥና ጦርነት ነው፣
   ሐ. የእድገት መጓተት ነው፣
   መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡
3. ቀጥሎ ከቀረቡት መካከል ትክክለኛ ያልሆነው ዓረፍተ ነገር የቱ ነው?
   ሀ. የመቻቻልና የመተሳሰብ መርህ ሕዝቦች በእኩልነት እንዲኖሩ ትልቅ ፋይዳ አለው፣
   ለ. እኩልነት በሌለበት ሀገር ሠላምና እድገት ሊኖሩ ይችላሉ፣
   ሐ. አስተማማኝና ዘላቂ የሕዝቦች አንድነት እንዲመጣ ከተፈለገ የእኩል ተጠቃሚነትን መብት ማክበር የግድ ይላል፣
   መ. አንዱ ሃይማኖት የበላይ ሌላው የበታች ሃይማኖት የሚባል መኖር የለበትም፡፡
4. የሴቶችን መብት አስመልክቶ የተሳሳተ ሀሳብ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ያገባችም ሆነች ያላገባች ሴት እኩል መብት አላት፣
   ለ. በሀገራችን ሴቶች የሕብረተሰቡ ግማሽ ያህሉ ናቸው፣
   ሐ. የሴቶችን እኩልነት መብት ለማስከበር ወንዶች ሀላፊነት የለባቸውም፣
   መ. የሴቶችን መብት ማስከበር የሕብረተሰብን መብት ማስከበር ነው፡፡
5. የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበር የሚሰጠው ጠቀሜታ፤
   ሀ. በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርስን መድሎ ለማስቀረት ይረዳል፣
   ለ. ከተረጂነትና ከጠባቂነት ስሜት እንዲላቀቁ ያደርጋቸዋል፣
   ሐ. የእኩልነትና የሀገር ፍቅር ስሜትን በማዳበር ልማትን ያፋጥናል፣
   መ. ሁሉም ትክክል ነው፡፡

IV *የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግሙሉ፡፡*

1. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሥርዓት ______________ ብሔራዊ ክልላዊ አባል መንግሥታት አሉት፡፡
2. የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ልዩነትና የአንድነት ሕብረት ለሀገራችን ___________ ነው፡፡

**V *የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ።***

1. **በኢፌዴሪ ሕገመንግሥት ውስጥ የተደነገጉ የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች መብቶችን ዘርዝሩ።**
2. **የፆታ እኩልነት ምን ምን ጉዳዮችን ያካትታል?**
3. **የአካል ጉዳተኞች መብቶች እንዲከበሩ ከአንተ/አንቺ ምን ይጠበቃል? ከሕብረተሰቡና ከመንግሥትስ?**

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

# ምዕራፍ አራት

# ፍትሐዊነት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤**

- አድሎአዊ አሰራሮች መወገድ እንደሚገባቸው ትገነዘቢያለሽ/ትገነዘባለህ::
- የፍትሕ መጓደል የሚያስከትላቸውን ችግሮች ታውቃለህ/ታውቂያለሽ::
- የፍትሕ አካላት አሰራርን ትረጂያለሽ/ትረዳለህ::
- ማህበራዊ አገልግሎቶችን ሁሉም ዜጎች በፍትሐዊነት መጠቀም እንዳለባቸው ትገነዘቢያለሽ/ትገነዘባለህ::
- በሀገር ደረጃ የግብርን ጠቀሜታ ታውቂያለሽ/ታውቃለህ::

## 4.1 አድሎአዊነት፤

### 4.1.1 አድሎአዊነት አሰራሮች መወገድ የሚችሉባቸው መንገዶች፣

✓ በተለያዩ አካባቢዎች የሚፈጸሙ አድሎአዊ አሰራሮችን እንዴት መከላከል ይቻላል::

**ዋልካ ሜዳ፣ ለማን?**

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የዋልካ ሜዳ ነዋሪዎች በአካባቢያቸው በተቋቋመ ድርጅት ተደራራቢ ችግሮች እየደረሰባቸው ነው:: ችግራቸውን ለሚመለከታቸው የፍትሕ ተቋማት ቢያሳውቁም መፍትሄ ማግኘት ቀርቶ ትኩረት የሰጣቸው አንድም አካል የለም:: በነዋሪዎቹ ላይ ለደረሰው ችግር ዋና ምክንያት የኑሯቸውና የህይወታቸው መሰረት የሆነው ዋልካ ሜዳ በግለሰብ ቁጥጥር ስር መዋሉ ነው:: ዋልካ ሜዳ የእንስሳት መኖ የሚታጨድበት፤ የመጠጥ ውሃ የሚቀዳበት፣ የአትክልት ምርቶች ከዓመት ዓመት የሚሰበሰብበት ለምለም ስፍራ ነው:: ነዋሪዎቹ ተደራጅተው ሕጋዊ በሆነ መንገድ ለማልማት ያቀረቡት ተደጋጋሚ ጥያቄ ምላሽ ሳያገኝ መመሪያና ደንብን በጣሰና አድሏዊ በሆነ ሁኔታ በግለሰቡ መታጠሩ ብዙዎችን አሳዝኗል:: በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉን ነዋሪዎቹን በእጅጉ ያስቆጣው ጉዳይ ቀስ በቀስ ከመኖሪያቸው የማስለቀቅ ሴራም እንዳለ ማወቃቸው ነው:: እኔ ለሀገርና ለሕዝብ ስል ነው ገንዘብ የማፈሰው፣ ስለዚህ ማንም ሊናገረኝ አይገባምን የሚሉት ባለሀብት ከአካባቢው የፍትሕ አካላት ጋር በጥቅማ ጥቅሞች እንደተሳሰሩም ይነገራል::

አቶ እንግዳው፣ "እኛ ችግራችንን በአካባቢያችን ለሚገኙ ፍትሕ አካላት ብናቀርብ መፍትሄ ማግኘት አልቻልንም:: ወደፊትም ጉዳዩን ለከፍተኛ የፍትሕ አካል ብናመለክትም የተለየ ውሳኔ የምናገኝ አይመስለኝም:: ትርፉ በከንቱ መልፋትና መንገላታት ነው:: እሱ እንደ በደለን እኛም እንበቀለው:: በራሱም ላይ ሆነ በንብረቱ ላይ ጥቃት እንፈፅም:: ግፋ ቢል መታሰር ነው::"

አቶ ኡስማን፣ "አይ እንደሱ አይደለም የሚሻለው ገንዘብ አዋጥተን ለበላይ አካላት ጉቦ መስጠት ነው:: ይህንንም የሚያመቻችልን ሰው እንፈልግ:: ይህን ማድረግ ካልቻልን አርፎ መቀመጥና የሚመጣውን መጠበቅ ይሻላል::"

ወ/ሮ መኪያ፣ "ለጊዜው ባይሳካልንም ችግሩን ለተለያዩ የፍትሕ ተቋማት በማሳወቅ ላይ ነን:: አሁንም ቢሆን ተስፋ ሳንቆርጥ ችግሩን ለበላይ የፍትሕ አካላት ማሳወቅ ይኖርብናል::

ለዚህ የምናጠፋው ገንዝበ፣ ጉልበትና ጊዜ ሊቆጨን አይገባም:: ይሄን ካላደረግን ግን ነገ በእኛም ሆነ በሌሎች ላይ ከዚህ የከፋ በደል ይደርሳል::"

አቶ ይልቃል፣ "ግድ የለም እየደረሰብን ያለውን ችግር ባለሀብቱ በግልፅ እንዲረዳን እና ድርግ:: አንዴ ተሰባስበን ለማነጋገር እንሞክር፤ መቼም ህሊና አለው:: ከዚያ በኋላ በግልም ሆነ በቡድን ስለምንወስደው እርምጃ እንወስናለን::"

**መልመጃ 1**

*ከላይ ከሰፈሩት አማራጮች ችግሩን ለማስወገድ በተወሰኑ ነዋሪዎች የቀረቡ አማራጮችን ተመልክታችሁ ከታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች መልሱ::*

1.ትክክለኛ መንገድ ነው የምትሉት የትኛው ይመስላችኋል? ምክንያታችሁን ግለፁ::

2.ትክክል ያልሆኑት አማራጮችስ? ለምን ትክክል እንዳልሆኑ ማብራሪያ ስጡ?

3.የትኛቹ አማራጮች ለሠላም፣ ለፍትሕ፣ ለብልፅግና ጠቃሚነት አላቸው? እንዴት?

በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚፈፀሙ አድሎአዊ አሰራሮችን ለመከላከል ዜጎች ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው:: በዚህ ረገድ የሥራ ኃላፊዎች፣ ሰራተኞች እና ሕብረተሰቡ በአጠቃላይ ሊወጧቸው ከሚገቡት ኃላፊነቶች ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ::

**የሥራ ኃላፊዎችና የሠራተኞች ኃላፊነቶች:-**

- **በሕግ ብቻ መስራት፣** የመንግሥት ባለስልጣናትና ሠራተኞች ሕግን የሚያከብሩና ለሕግ የሚገዙ መሆን ይኖርባቸዋል:: የተሰጣቸውን ሥልጣን ለሥራቸው አገልግሎት ማዋል እንጂ ከገደብ በላይ መጠቀም አይገባቸውም:: የዚህ ዓይነት ድርጊቶች የአድሎአዊ አሰራሮች ዋና መንስኤዎች ናቸው:: ስለዚህ ኃላፊነታቸውን ሲወጡ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን መሠረት ባደረገ መልኩ መሆን አለበት:: ከዚህ በተጨማሪም ሰራተኞችና የስራ ኃላፊዎች ሕግ ሲጣስ እያዩ በዝምታ ማለፍ የለባቸውም:: በተቻለ መጠን ችግሩን ለሚመለከተው ክፍል ማሳወቅ ይኖርባቸዋል::
- **በቅንነትና በታማኝነት ሥራን ማከናወን:-** የአድሎአዊ አሠራሮች መከላከያ ከሆኑት መንገዶች መካከል ቅንነትና ታማኝነት በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ:: ቅንነት በፅኑ አቋም፣ በሐቀኛነት፣ እውነተኛ በሆኑ ድርጊቶች ይገለፃል:: በዚህ መሠረት ሰራተኞች ሙሉ ኃይላቸውን ለሥራ የሚያውሉ፣ ሥራቸውን የሚወዱ፣ ኃላፊነታቸውን በብቃትና በጥራት የሚወጡ ሊሆኑ ይገባል:: ለሀገራቸው፣ ለሥራቸውና ለተገልጋዩ ሕዝብ የሚታመኑና ቃላቸውን የሚያከብሩ መሆን አለባቸው::
- **ዜጎችን በእኩል ዓይን ማየት:-** አድሏዊነትን ለማስወገድ ሰራተኞች ተግባራዊ ሊያደርጓቸው ከሚገቡ መርሆዎች መካከል አንዱ ዜጎችን በእኩል ዓይን ማየት ነው:: ሰዎችን በእኩል ዓይን ማየት ማለት አለማዳላት ወይም በሰዎች መካከል ልዩነትን አለመፍጠር ማለት ነው::

**መልመጃ 2**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. የመንግሥት ሠራተኞች ሕብረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት ሲከተሏቸው ይገባሉ የምትሏቸውን መልካም ባህሪያት ዘርዝሩ::
2. ቤተሰቦቻችሁን ጠይቃችሁ በአካባቢያችሁ በሚገኙ የመንግሥት መሥሪያቤቶች ውስጥ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የሚታዩ ችግሮችን ዘርዝሩ::

## 4.2 የፍትሐዊነት መጓደል

### 4.2.1 የፍትሐዊነት መጓደል በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና በልማት ላይ የሚኖረው አሉታዊ ተፅእኖ፤

✓ በሀገር ደረጃ የፍትሐዊነት መጓደል ሊያስከትል ይችላል የምትሏቸውን ችግሮች ዘርዝሩ::

**“የዋንዛ ሜዳ፤ ፍትሕ አዛባ ሕዝብም ተጎዳ”**

በዋንዛ ሜዳ የታየው የፍትሕ መዛባት የተለያዩ ማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮችን ማስከተሉ አልቀረም:: ለአብነት ያህል፣ በይዞታ ውስጥ ከዋለው ሜዳ የሚወጣው ፍሳሽ እና ሽታ የሕብረተሰቡን ጤና እያወከና የቤት እንስሶችም ላይ ጉዳት እያደረሰ ነው:: ከዚህም በላይ የእንስሳት ውጤቶች እና የአትክልት ምርቶች በእጅጉ በመቀነሳቸው የነዋሪዎቹ የኑሮ መሠረት ተናግቷል:: የአትክልትና የእንስሳት ውጤቶች እጥረት በመፈጠሩ በአካባቢያቸው በምርቶቹ ላይ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ንረት እየታየ ነው::

በዚህ የተነሳም በአቅራቢያ የሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎችም የችግሩ ተቋዳሽ እየሆኑ ነው:: በፍትሕ አካላት በሚሰሩት አድሎአዊ ድርጊቶች ብዙዎቹ አዝነዋል:: የአካባቢው ነዋሪዎች በመንግሥት ተቋማት ላይ ያላቸው አመኔታ በእጅጉ ቀንሷል:: እንደቀድሞ በመንግሥት ተቋማት የሚተላለፉ መልእክቶችን

ለመቀበልም ሆነ ለማዳመጥ ብዙም ፍላጎት የላቸውም፡፡ ሕግን ማክበርና ለሕግ መገዛት እየተዳከመ ነው፡፡ ሠላምና ፀጥታ ከአካባቢው ርቋል፡፡ አንዳንዶች "ሕግ ስለሌለ የምንፈል ገውን በጉልበት እናስከብራለን" እስከ ማለት ደርሰዋል፡፡

## መልመጃ 3

*ከላይ በቀረበው ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

?

1. በዋንዛ ሜዳ በታየት አድሏዊ አሰራሮች ምክንያት ሊከሰቱ ይችላሉ የምትሏቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማሕበራዊ ችግሮች ዘርዝሩ፡፡
2. ነዋሪዎች ችግራቸውን ለበላይ አካላት አቅር በው መፍትሄ ካላገኙ ምን ማድረግ አለባ ቸው? ምን ዓይነት ጉዳትስ ሊከሰት ይችለል?

### *የፍትሐዊነት መጓደል የሚከተሉትን ችግሮች ያስከትላል፡፡*

**በዴሞክራሲ ሥርዓት ላይ እምነት ማጣት፣** ሕብረተሰብን የሚጎዱ አብዛኛዎቹ የፍትሕ ጥሰቶችና አድሎአዊ አሰራሮች የሚከሰቱት በመንግሥት ተቋማት ውስጥ ነው፡፡ በነዚህ አካባቢዎች የሚፈፀሙ አድሎአዊ አሰራሮች የዴሞክራሲ ሥርዓት ዋና ምሰሶ የሆኑትን የፍትሐዊነትን፣ የሕግ የበላይነትን እና የእኩ ልነት አሰራሮችን ያዳክማሉ፡፡ በአድሎአዊ አሰራሮች ምክንያት የሚፈፀሙ የመብት ጥሰ ቶች ዜጎች በመንግሥታቸው ላይ አመኔታ እንዳይኖራቸው ያደርጋሉ፡፡

በዚህም የተነሳ ሕዝብ በሥርዓቱ ላይ ጥርጣሬ እንዲኖረው በማድረግ በመንግሥት ላይ እን ዲነሳና አመፅና ብጥብጥ እንዲስፋፉ ምክን ያት ይሆናሉ፡፡ የፍትህ መጓደል ዜጎች በል ማት ሥራዎች ላይ በነፃና በእኩል የመሳተፍ መብታቸውን ስለሚያደናቅፍ በሀገር ልማትና እድገት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት የከፋ ነው፡፡

**የዜግነት ድርሻን ለመወጣት ፈቃደኛ አለመሆን፣**

ፍትሐዊ ሥርዓት መዳከም ለአድሎአዊ ድር ጊቶች መስፋፋት መንስዔ ነው፡፡ በዚህም የተ ነሳ ብዙዎች ሀገር የብዙሀኑ ሕብረተሰብ ሳይሆን የጥቂት "ምርጦች" መኖሪያ ብቻ እን ደሆነች አድርገው ይወስዳሉ፡፡ መልካም አስ ተዳደር እንዳይሰፍን ያደርጋል፡፡ በዚህም ሕዝብም ሀገርም ይጎዳል፡፡

## መልመጃ 4

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

?

1. የፍትሐዊነት መጓደል ያስከትሏቸዋል የምትሏ ቸውን ችግሮች ዘርዝሩ፡፡
2. በአካባቢያችሁ ካሉት ተቋማት መካከል ከፍተኛ የፍትህ በደል ይታይበታል የምትሉትን በመ ለየት ያስከተላቸውን ችግሮች ጥቀሱ፡፡ ለችግሮች መንስዔ ናቸው የምትሏቸውን ነጥቦች ዘርዝሩ፡፡

## 4.3 የፍትሕ አካላት

### 4.3.1 የፍትህ አካላት አሰራር




ሥዕል 4.1 ፍርድ ቤቶች ፍትሕን በማስፈን በኩል ሰፊ ሚና ይጫወታሉ

✓ የፍትሕ አካላት አሰራር ምን መሆን አለበት ትላላችሁ?

ፍርድ ቤቶች ፍትሐዊ አሰራርን የማስፈን ከፍተኛ ኃላፊነትና ስልጣን አላቸው፡፡ ፍርድ ቤቶች ፍትሕን በማስፈኑ ሂደት የተጣለባቸውን ኃላፊነት በብቃት መወጣት የሚችሉት የሚከተሉትን መሠረታዊ መርሆዎች ሲከተሉ ነው፡፡ እነዚህም **የዳኝነት ነጻነትና ከማንም ወገን ጣልቃ ገብነት ነፃ** መሆን የሚሉት ናቸው፡፡

**የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ነጻነት፣**

ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሲሰጡ ከማንም ወገን ተፅእኖ ነፃ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በፍርድ ቤቶች አሰራር ማንም አካል ጣልቃ ሊገባ አይገባም፡፡ በሌላ አነጋገር ዳኞች ከሕግ በስተቀር በሌላ መንገድ መመራት የለባቸውም፡፡ ስለዚህ በማንኛውም የፍትሕ አሰጣጥ ሂደት ፍርድ ቤቶች ተቋማዊ ነፃነታቸው የተከበረ ሊሆን ይገባል። ፍርድ ቤቶች ይህን የሚያረጋግጥ የዳኝነት አሰራር ከተከተሉ የፍትሕ ሥርዓቱ የተስተካከለ ይሆናል ማለት ነው፡፡

**ፍትሕ አሰጣጥ ከወገንተኝነት የፀዳ መሆን፣**

ፍርድ ቤቶች በፍርድ አሰጣጥ ሂደታቸው በዜጎች መካከል ልዩነት ማሳየት የለባቸውም፡፡ ከፍተኛ ባለሥልጣንም ሆነ ማንኛውም ዜጋ በሕግ ፊት እኩል ስለሆኑ ይህንኑ አሰራር ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ፍርድ ቤቶች ከፖለቲካ፣ ከዘር፣ ከቋንቋ፣ ከሃይማኖት ወገንተኝነት መራቅ አለባቸው፡፡ ውሳኔም ሲሰጡ ሕግንና ደንብን እንዲሁም ሙያዊ ሥነምግባርን መሠረት አድርገው መሆን ይኖርበታል፡፡

በዚህ ረገድ የፌደራል ሕገመንግሥት በአንቀጽ 79 የዳኝነት ነፃነትን በሚከተለው መልኩ ያብራራል፡፡ "በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፡፡ በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማንኛውም የመንግሥት አካል፣ ከማንኛውም ባለሥልጣንም ሆነ ከማንኛውም ሌላ ተጽእኖ ነጻ ነው፡፡ ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነጻነት ያከናውናሉ፡፡ ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም፡፡"

**መልመጃ 5**

? *በሚከተሉት ሁለት ፍርድ ቤቶች አሰራር ላይ በመመርኮዝ ከታች ያሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

| ፍርድ ቤት /ሀ/ | ፍርድ ቤት /ለ/ |
|---|---|
| • ከውሳኔ በፊት የተለያዩ ባለሙያዎችንና የሃይማኖት አባቶችን ሀሳብ ይቀበላል፡፡<br>• አስፈላጊ ሲሆን የፖለቲካ መሪዎችን ትእዛዝ ይቀበላል፡፡<br>• ፍርድ የሚሰጠው በሕብረተሰቡ በተመረጡ በተወሰኑ ዳኞች ብቻ ነው፡፡<br>• የተለያዩ የወንጀል ድርጊቶችን በማቻቻል መፍትሄ ይሰጣል፡፡<br>• ዜጎች የተሰጠውን ውሳኔ እንዲቀበሉ ይገደዳሉ፡፡ | • መመሪያና ደንቦችን አገናዝቦ ይሠራል፡፡<br>• በሙያው በሰለጠኑ ዳኞች ውሳኔ ይሰጣል፡፡<br>• በመረጃና በምስክር አሰራሮችን ይከተላል፡፡<br>• ይግባኝና ቅሬታዎችን ይሰማል፡፡<br>• በሀገሪቱ ሕግ ወንጀል ተብለው የተደነገጉትን ድርጊቶች በወንጀልነታቸው መዝኖ ውሣኔ ይሰጣል፡፡<br>• በሕግ ቁጥጥር ሥር ላሉ የሀገሪቱ ፕሬዝዳንት ምህረት ያደርጋሉ፡፡ |

1. *በየትኛው ፍርድ ቤት ነው የዳኝነት ነፃነት የሚታየው? የዳኝነት ነፃነትስ የማይታይበት እንዴት ነው?*
2. *የትኛው ፍርድ ቤት ለዴሞክራሲ ሥርዓትና ለሀገር እድገት ጠቃሚ ነው ትላላችሁ?*

### 4.3.2 ፍትሕ የማግኘት መብት፣

✓ የፍትሕ አካላትን አሰራር ፍትሐዊ እንዲሆን በማድረጉ ሂደት ዜጎች ምን ዓይነት ሚና ሊወጡ ይገባል ትላላችሁ?

ፍትሕን የማስከበሩ ሂደት የመንግሥት ዋና ኃላፊነት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ መንግሥት በዚህ በኩል ሕጎችን ያወጣል፡፡

የፍትሕ አካላትን ያዋቅራል:: አስፈላጊ ባለሙያዎችን ይመድባል:: አሰራራቸውን ይከታተላል:: ሆኖም ግን ይህ ሁሉ ቢደረግም የፍትሕ ተቋማት አሰራር በዜጎች የነቃ ተሳትፎ ካልተደገፈ ውጤታማ አይሆንም:: ዜጎች ፍትሕን በማስከበሩ ሂደት የሚኖራቸው ሚና ምንድን ነው? የሚለውን ሀሳብ በሚገባ ማጤን ያስፈልጋል:: በአጠቃላይ ዜጎች ፍትሕን በማስፈኑ ሂደት ከሚያበረክቷቸው አስተዋፅኦዎች መካከል የሚከተሉት የሚጠቀሱ ናቸው::

### ትክክለኛ ዳኝነት ለማግኘት መታገል፣

በዴሞክራሲ ሥርዓት ተቋማት ህዝቡን ለማገልገል የሚቋቋሙ አካላት ናቸው:: ስለዚህ ዜጎች በየትኛውም ወቅትና ቦታ የሚያጋጥማቸውን የፍትህ ጥሰቶች በዝምታ አለመመልከት፣ መብት ሲጣስ እድልን ወይም ፈጣሪን ማማረር ሳይሆን፣ መብት የጣሰው አካል አሰራሩን እንዲያስተካክልና የመብት ጥሰቱን እንዲያስወግድ መሟገት፣ መታገል፣ ሳይሰለቹ ደጋግሞ በመጠየቅ ሠላማዊ ተፅእኖ ማድረግ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ የመብት ጥሰት ያደረሰውን አካልና ድርጊቱን በመገናኛ ብዙሀን እንዲነገር ማድረግ አጥፊው እንዲታረም ማድረጊያ መንገድ ነው::

### ፍትሕ ሲጣስ መብትን በሕግ ማስከበር፣

በራስ ጥረት መብትን ለማስከበር የሚደረገው ጥረት ካልተሳካ ዜጎች የተነፈጉትን ወይም የደረሰባቸውን በደል በጉልበት፣ በገንዘብ፣ በዘመድ፣ ወዘተ ለማስጠበቅ መሞከር የለባቸውም:: የተዛባ ፍትህን ለማስተካከል ጉዳዩን ለተገቢ የፍትሕ አካል ማሳወቅ፣ አቤቱታ ማቅረብ፣ እንዲሁም የይግባኝ የፍትሕ አሰራር ሂደትን በአግባቡ መጠቀም ነው የሚኖርባቸው:: ሕጋዊ የመፍትሄ መፈለጊያ መንገድ ሁልጊዜም ተመራጭና ውጤታማ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

**መልመጃ 6**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. በተለያዩ አካባቢዎች ለሚያጋጥማችሁ የፍትሕ ጥሰት ልትወስዷቸው የምትችሏቸውን እርምጃዎች አብራሩ::
2. ፍርድ ቤቶች ከማንም አካል ተፅእኖ ነጻ መሆናቸው ያለውን ጥቅም ዘርዝሩ::
3. የዳኝነት ነፃነት ማለት ምን ማለት ነው?

## 4.4 ማሕበራዊ አገልግሎቶች፤

### 4.4.1 ማሕበራዊ አገልግሎቶችና አስፈላጊነት፣

✓ ማሕበራዊ አገልግሎት ለህዝቡ ምን ምን ዓይነት አገልግሎቶች ይሰጣሉ?

### የዋንዛ ማሕበረሰብና ማሕበራዊ ተቋማት፣

የዋንዛ ማሕበረሰብ በተለያዩ ጊዜያት በአካባቢያቸው ሊገነቡ የተሞከሩ የማሕበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ሲያደናቅፉ ኖረዋል:: የነበሩትም ቢሆኑ ተገቢውን አገልግሎት እየሰጡ አልነበረም:: ማሕበረሰቡ ትምህርት ቤት ልጆቻችንን ያባልጋል፣ ባህላችንን ያቆሽሻል በሚል ለማሕበራዊ አገልግሎቶች ጥልቅ ጥላቻ ነበራቸው:: ዘመናዊ ህክምናም ዘራችንን ለማጥፋት የሚደረግ ሴራ ነው ብለው ያምኑ ነበር:: መንገድና ሌሎች መሰረተልማቶች ከተዘረጉ ኑሮ ይወደዳል፣ የፍቅርና የመደጋገፍ ባህላችንን ያጠፋል ይሉም ነበር:: በነዚህ አመለካከቶች የተነሳ ማሕበረሰቡ ለረጅም ዓመታት ከሌሎች ማሕበረሰቦች ወደ ኋላ የቀሩ ነበሩ::

ከጊዜ በኋላ ግን በሌሎች አካባቢዎች በሚያዩት ለውጥና እድገት መቆጨት ጀምረዋል:: ሌሎች ጤናቸው የተጠበቀ፣ ልጆቻቸው እየተማሩ በከፍተኛ ኃላፊነትና ቦታዎች ላይ ሲመደቡ፣ እነሱ ግን በከፍተኛ በሽታ የሚሰቃዩ፣ ልጆቻቸው ያልተማሩና በረባ ኃላፊነት ላይ የማይመደቡ መሆኑ እያሳፈራቸው ነው:: በአካባቢያቸው የመንገድ፤ የውኃ፣ የመብራት፣ ወዘተ አቅርቦት አለመኖሩ ከጊዜ ጊዜ እየተሰማቸው ነው:: ዋንዛዎች በነዚህ ጉዳዮች ላይ እየተነጋገሩ ነው:: ምን ለማድረግ አስበው ይሆን?

**መልመጃ 7**

*በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. የማሕበራዊ አገልግሎቶች ሕብረተሰብን ለማሳደግ ያላቸውን ጠቀሜታ ዘርዝሩ::
2. ማሕበራዊ ተቋማትን ለማስፋፋት እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮችን ዘርዝሩ::

የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርና ውጤቶችንና ሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ተቋማት ማሕበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በመባል ይታወቃሉ፡፡ እነዚህም ተቋማት በመንግሥት ወይም በሕብረተሰቡ የሚገነቡ ሲሆን በነፃ ወይም በዝቅተኛ ዋጋ ለሕብረተሰቡ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፡፡ ማሕበራዊ ተቋማት ለሕብረተሰብ እድገት አስፈላጊና መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ማሕበራዊ ተቋማት የሕብረተሰቡን ህይወትና ኑሮ በማሻሻል ለሀገር እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡ ለምሳሌ ትምህርት ዜጎችን ከመሀይምነትና ከኋላቀርነት በማላቀቅ የእድገት መሳሪያ የሆነውን የተማረ ዜጋን ማፍራት ያስችላል፡፡ እንደዚሁም የህክምና ተቋማት በበቂ ደረጃ ሲስፋፉ ጤናማ እና አምራች ዜጎች መገንባት ይቻላል፡፡

### 4.4.2 ማሕበራዊ አገልግሎቶች ያለ አድሎ አገልግሎት መስጠታቸው ያለው ጥቅም፤

- ✓ በአካባቢያችሁ የሚገኙ ማሕበራዊ አገልግሎቶች ለሕብረተሰቡ የሚሰጡት ግልጋሎት ከአድሎ የፀዳ ነው?

**የአገልግሎት አሰጣጥ መሰረታዊ መርህ፣**

የዋንዛ ማሕበረሰብ የማሕበራዊ አገልግሎቶችን አስፈላጊነትንና ጥቅማቸውን በሚገባ ተረዳ፡፡ ተቋማትን ለመገንባት በተለያዩ ኃላፊነቶች ላይ የሚገኙ የማሕበረሰቡ አባላት ህብረተሰቡን የማስተማርና የማሳመን ሥራዎችን ሠሩ፡፡ በተጨማሪም የማሕበራዊ ተቋማቱ የሚመሩበትን ሕግና ደንብ አዘጋጁ፡፡ ህሕብረተሰቡም እንዲያውቃቸው ተደረገ፡፡ ከደንቦቹም መካከል ተቋማቱ ሕብረተሰቡን ሁሉ ያለምንም ልዩነት በእኩል እና ያለአድሎ እንዲያስተናግዱ የሚሉ ይገኙበታል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በመጀመሪያ ዙር የሚገነቡ ተቋማት ብዙ ሕዝብ ባለባቸውና በማእከላዊ ቦታዎች እንዲሆኑ ተወሰነ፡፡ ቀስ በቀስም ተቋሞቹን በሌሎች ቦታዎች የማዳረስ ሥራዎች እንደሚሠሩም ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡ በጊዜያዊነትም ተገቢ አገልግሎቶቹ የሚዳረሱበት ሥልትም ተቀየሰ፡፡ በመጨረሻም አፋጣኝ መፍትሄ የሚፈልግ ጥያቄም ተነሳ፡፡ ይኸውም አገልግሎት ሰጪ ተቋማቱን የመሥራት ኃላፊነት የማን ነው? የሚለው ነበር፡፡

**መልመጃ ፰**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. ከላይ ካለው ትረካ ፍትሐዊ አሠራሮችን የሚገልፁ ድርጊቶችን ዘርዝሩ፡፡
2. ከአድሎ የፀዳ አሠራር ምን ጠቀሜታ እንዳለው ዘርዝሩ፡፡
3. ማሕበራዊ አገልግሎቶች ለሁሉም ያለ አድሎ መሰጠታቸው የሚሰጠውን ጥቅም ዘርዝሩ፡፡

ዜጎች ተገቢውን አገልግሎት ማግኘት የሚችሉት በተቋማቱ ውስጥ ከአድሎ የፀዳ አሠራር ሲሰፍን ነው፡፡ ከአድሎ የፀዳ አገልግሎት አሰጣጥ የዴሞክራሲ ሥርዓት መገለጫ የሆነውን የእኩልነት መብትን ያረጋግጣል፡፡ በዚህም የዜጎችን የባለቤትነት የተቆርቋሪነት ስሜትን ያጎለብታል፡፡ ከአድሎ የፀዳ አሰራር መንግሥትና ሕዝብን በማቀራረብ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ያጎለብታል፡፡

### 4.4.3 መንግሥትና ህብረተሰብ ማህበራዊ አገልግሎቶችን በማዳረስ ያላቸው ሚና፣

- ✓ መንግሥትና ሕብረተሰብ ማሕበራዊ አገልግሎቶችን ለማዳረስ ያላቸው ሚና ምንድነው ትላላችሁ?

**“ድር ቢያብር አንበሳ ያስር”**

የዋንዛ ማሕበረሰብ ማሕበራዊ ተቋማትን የማስፋፋቱ ኃላፊነት የማን መሆን አለበት በሚለው ሀሳብ ላይ ውዝግብ ውስጥ መግባታቸው አልቀረም፡፡ አንዳንዶች “ተቋማቱን የማስፋፋት ኃላፊነት የመንግሥት መሆን አለበት፡፡ መንግሥት እስካሁን በእኛ አካባቢ ይህ ነው የሚባል ስራዎችን ስላልሰራ ኃላፊነቱን ሊወስድ ይገባል” የሚል ሀሳብ አላቸው፡፡

በሌላ በኩል ግን “መንግሥት አገልግሎቶችን የማዳረስ ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለበት ይታወቃል፡፡ ነገር ግን እኛም የገንዘብ፣ የጉልበትና የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ የነቃ ተሳትፎ ማበርከት አለብን” የሚለው ሀሳብ የአብዛኛውን ድጋፍ አገኘ፡፡ ለስራውም የተለያየ የድጋፍ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀትም ተስማሙ፡፡ ይህንኑ የሚያስተባብር ኮሚቴም ተዋቀረ፡፡ በዚህም በጋራ ትብብርና መደጋገፍ በጥቂት ዓመታት ውስጥ በአካባቢው ትምህርት ቤቶች፣ ክሊኒኮች ተገነቡ፤ መንገድ የመብራትና የስልክ መስመሮች ተዘረጉ፡፡ ሕብረተሰቡም ከተቋሞቹ ተገቢ አገልግሎቶችን ለማግኘት ቻለ፡፡ የተሻለ ሕይወት ለመኖር የማሕበራዊ አገልግሎት ተቋማትን ጠቀሜታ በሚገባ ተረዳ፡፡

**መልመጃ 9**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

?

1. በምንባቡ ውስጥ ከተመለከቱት ሁለት አመለካከቶች የትኛውን ትደግፋላችሁ? ስምን?
2. በማሕበራዊ አገልግሎቶች ግንባታ ላይ የሕብረተሰብ ተሳትፎ ያለውን ጥቅም ዘርዝሩ፡፡

ማሕበራዊ አገልግሎቶችን የማስፋፋት ከፍተኛ ኃላፊነት ካላቸው አካላት መካከል መንግሥት በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳል፡፡ መንግሥት የዜጎችን ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶችን የማሟላት ግዴታ አለበት፡፡ ሆኖም ግን መንግሥት ብቻውን እነዚህን ሁሉ ሥራዎች ሊያስፋፋና ሊገነባ አይችልም፡፡ የመንግሥት እንቅስቃሴ በሕብረተሰቡ የነቃ ተሳትፎ መታገዝ አለበት፡፡ ስለዚህ ተቋማቱን በማስፋፋቱ ሂደት ሕብረተሰቡ በግልም ሆነ በጋራ የጉልበት፣ የገንዘብ ወዘተ ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

***የቡድን ሥራ፣***

በአካባቢያችሁ ከሚታዩት ማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ ምልከታ በማድረግ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ለክፍላችሁ ሪፖርት አቅርቡ፡።

ሀ/ አስፈላጊ ናቸው የምትሏቸውን አገልግሎት ተቋማት፣

ለ/ በሥራው ሊሳተፉ የሚችሉ አካላትን፣

ሐ/ ሊያከናውኗቸው የሚችሉ ተግባራት፣

## 4.5. ግብር፤

✓ ግብር ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ምንድነው?

**የእውቀት ፋና የሥነ ዜጋና ሥነምግባር ክበብ የውይይት ፕሮግራም፣**

የእውቀት ፋና ትምህርት ቤት የሥነዜጋና ሥነምግባር ክበብ ከሚያከናውናቸው ተግባራት አንዱ በተለያዩ ርእሶች ዙሪያ የውይይት ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት ነው። የዛሬው የውይይት ፕሮግራም የሚያተኩረው በግብርና ልማት፣ *በፌደራል መንግሥት እና በክልሎች የግብር ሥልጣንና* ክፍፍል ላይ ይሆናል፡፡ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችና የትምህርት ቤቱ ማሕበረሰብ የፕሮግራሙ ዋና ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡ በሐሳቦቹ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ በተጋበዙ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የሚከተሉት ማብራሪያዎች ቀርበዋል፡፡

**«ግብርና ኢንቨስትመንት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ»፣ /*ክፍል አንድ*/**

“ግብር ኢንቨስትመንትን በማስፋፋቱ ሂደት የላቀ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ ይህም የሚሆነው መንግሥት ከግብር በሚያገኘው ገቢ መሠረተ ልማትን ማለትም መንገዶችንና መብራትን ይዘረጋል፤ ድልድዮችን፣ የውሃ እና የኃይል ማመንጫዎችን ወዘተ...ይገነባል፡፡ እነዚህ መሰረተ ልማቶች በተስፋፉ መጠን ሁኔታዎች ስለሚመቻቹላቸው የሀገር ውስጥም ሆኑ የውጪ ባለሀብቶች በተለያዩ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ላይ ይሰማራሉ፡፡ በሌላ በኩል ኢንቨስትመንት ሲስፋፋ፣ የግብር ምንጭም በዚያው መጠን ያድጋል፡፡ ስለዚህ ግብርና ኢንቨስትመንት ተደጋጋፊ ሥራዎች ናቸው ማለት ነው፡፡”

**መልመጃ 10**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።***

?

1. የኢንቨስትመንት መስፋፋት ምን ፋይዳ አለው፡፡

© MoE-FDRE Not to be republished

### «ግብር በክልሎች ፍትሐዊ እድገት ላይ ያለው ከፍተኛ ሚና»፣ /ክፍል ሁለት/

“በፌደራላዊ የመንግሥት አወቃቀር ክልሎች ያላቸው የሀብት መጠንና የግብር ምንጮች፣ ተመሳሳይ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ሁሉም በአንድ የጋራ ሕገ መንግሥት የሚተዳደሩ አካላት ከመሆናቸውም በላይ በሁሉም ክልሎች የሚኖሩ ሕዝቦች የአንድ ሀገር ዜጎች ናቸው፡፡ ዜጎች ደግሞ በሀገራቸው የሚገኙ ሀብቶችን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የመጠቀም ወይም የመካፈል መብት አላቸው፡፡

በክልሎች መካከል የሚታየው ልዩነት በግብር ገቢ መጠን ብቻ ሳይሆን በልማት ደረጃም ጭምር ነው፡፡ በተለይ ከመሀል ሀገር በጣም ርቀው የሚገኙ አካባቢዎች ያሉባቸው ችግሮች ስር የሰደዱና የተባባሱ ናቸው፡፡

ስለዚህ በሀገር ደረጃ የተመጣጠነ እድገት ለመፍጠር ግብርን ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ለክልሎች ማከፋፈል ተገቢ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ብዙ የግብር ገቢ ያላቸው ክልሎች አነስተኛ የገቢ ምንጭ ላላቸው ማከፋፈል የሚያስችል አሰራር ተግባራዊ ማድረግ የፌደራላዊ የመንግሥት ሥርዓት መለያ ነው፡፡ ይህ አሰራር በክልሎች መካከል የመተሳሰብና የመረዳዳት ባህልን በማጎልበት በሀገር ደረጃ የተቀራረበ እድገትን ማረጋገጥ ያስችላል፡፡”

በሰባት ክልሎች የተከፋፈለ የፌደራላዊ ሀገር የግብር አሰባሰብ ሥርዓት የሚከተለው መልክ ነበረው፡፡

ሁለት ክልሎች ፌደራል መንግሥቱ ከሌሎች ክልሎች ከሚሰበስበው ገቢ በአማካኝ ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር ዓመታዊ ድጎማ ይደረግላቸዋል፡፡ ማእከላዊ መንግሥት ከሶስቱ ክልሎች ከእያንዳንዳቸው አንድ ቢሊዮን ብር በየዓመቱ ግብር ይሰበስባል፡፡ ሌሎቹ ሁለቱ ክልሎች ደግሞ ራሳቸውን የቻሉ በመሆናቸው ምንም ዓይነት ድጎማ አይደረግላቸውም። ሆኖም ከራሳቸውም ተርፈው ለማእከላዊ መንግሥት የሚሰጡት የለም፡፡ አልፎ አልፎ ይህ የግብር አሰባሰብና አከፋፈል ሁኔታ ቅሬታና ፀብ ሲያስነሳ ይስተዋላል፡፡ የሚነሱ የሀሳቦቹ ልዩነቶች የሚከተለው ይዘት ነበራቸው፡፡ ሶስቱ ክልሎች በክልላችን የሚሰበሰበው ገቢ ለእኛ ጥቅም ብቻ መዋል አለበት የሚል አስተሳሰብ ያራምዳሉ፡፡ ራሳቸውን የቻሉት ሁለት ክልሎች ደግሞ ምንም እንኳን ራሳችንን የቻልን ብንሆንም ለሌሎቹ እንደሚደረገው ለእኛም ፌደራል መንግሥቱ ድጎማ ሊያደርግልን ይገባል ይላሉ፡፡ ማእከላዊ መንግሥት የምንከተለው አሰራር ትክክለኛ ነው ብሎ ያምናል፡፡

**መልመጃ 11**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

1. ከላይ ከሰፈሩት ሶስት ሀሳቦች በየትኛው ትስማማላችሁ? ምክንያታችሁን ዘርዝሩ፡፡
2. ትክክለኛውን ሀሳብ በሕብረተሰቡ ውስጥ ለማስረፅ ምን ዓይነት ስራዎች ቢሰሩ ይበጃል ትላላችሁ? ዘርዝሯቸው፡፡

### “የፌደራል እና ክልል ገቢ ዓይነቶች”፣ /ክፍል ሶስት/

የፌደራል የመንግሥት አስተዳደር ዋና መለያ ባህሪ ሥልጣን በፌደራል መንግሥቱና በክልሎች መካከል የተከፋፈለ መሆኑ ነው፡፡ በዚህ የስልጣን ክፍፍል መሰረት ሁለቱም አካላት ግብር የሚሰበስቡባቸው አካባቢዎች ተለይተው ይዘረዘራሉ፡፡ ሁለቱም አካላት በየፊናቸው የተሰጧቸው የግብር አካባቢዎች እንዳሉ ሁሉ የሚጋሯቸው የጋራ የግብር ዓይነቶችም አሉ፡፡ እነዚህ በጋራ የሚሰበሰቡ የግብር ዓይነቶች የጋራ ገቢዎች ተብለው ይታወቃሉ፡፡ በዚህ መሠረት በሀገራችን የፌደራሉ መንግሥትና ክልሎች በተናጠልና በጋራ የተሰጣቸው የገቢ ዓይነቶች በሕገመንግሥቱ ውስጥ በሚከተለው መልኩ ተዘርዝረው ተቀምጠዋል፡፡

| የፌደራል መንግሥት ዋና የገቢ ምንጮች፣/ አንቀፅ 96 / | የክልል መስተዳድሮች ዋና የገቢ ምንጮች፣ /አንቀፅ 97/ | የፌደራልና የክልሎች የጋራ የግብ ዋና የገቢ ምንጮች፣/ አንቀፅ 98/ |
|---|---|---|
| • ከሀገር በሚወጡና በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚጣል ቀረጥ፣ ግብር፤<br>• ከፌዴራል መንግሥትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተቀጣሪዎች የሚሰበሰብ የሥራ ግብር፣<br>• በፌዴራል መንግሥት ባለቤት ነት በሚተዳደሩ ድርጅቶች ላይ የገቢ፣ የትርፍ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስና የኤክሳይዝ ታክስ፣<br>• ከብሔራዊ ሎተሪ እና ሌሎች የዕድል ሙከራ ገቢዎች ላይ የሚሰበሰብ ታክስ፣<br>• ከአየር፣ ከባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የሚሰበሰብ ታክስ፣ ወዘተ:: | • ከክልል መንግሥታት ተቀጣሪዎች ላይ የሚሰበሰብ፣<br>• ከመሬት መጠቀሚያ የሚሰበሰብ፣<br>• በክልል ከሚገኙ ግለሰብ ነጋዴዎች ላይ የሚሰበሰብ፣<br>• በክልል መስተዳድር በግል ባለቤትነት ሥር ካሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች የሚሰበሰብ፣<br>• በክልል መስተዳድር ባለቤ ትነት ሥር ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች የሚሰበሰብ፣<br>• በክልል መስተዳድር አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግ ሎቶች ከሚመነጩ ክፍያዎች የሚሰበሰብ፣ | • የፌዴራል መንግሥትና ክልሎች በጋራ ከሚያቋቁ ማቸው የልማት ድርጅቶች ላይ የሚሰበሰብ፣<br>• ከግል ድርጅቶች የንግድ ትርፍ ላይ እና ከባለ አክሲ ዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ የሚሰበሰብ ግብር፣<br>• በከፍተኛ የማዕድን ሥራዎ ችና ከማናቸውም የፔትሮ ሊየምና የጋዝ ሥራዎች ላይ ከሚጣል የሮያሊቲ ክፍያዎች የሚሰበሰብ፣ |

***የቡድን ሥራ፣***

***በአካባቢያችሁ ወደሚገኙ ግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤቶች በመሄድ፤***

*ሀ) ዋና ዋና የግብር ዓይነቶችና የሚሰበሰብባቸው መንገዶች፣*

*ለ) በግብር አሠባሰቡ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን፣*

*ሐ) የሚሰበሰበው ግብር ለምን ተግባር እንደሚውል በመጠየቅ ሪፖርት አቅርቡ፡፡*

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በአንድ ሕብረተሰብ እና ሀገር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ከሚያደርሱ ጉዳዮች መካከል አድሎአዊ አሰራሮች በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳሉ። አድሎአዊ አሰራሮች የተለያዩ ችግሮችን ያስከትላሉ። ለምሣሌ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታን ያደናቅፋሉ። ዜጐች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በተገቢው ደረጃ እንዳይወጡ ያደርጋሉ። ስለዚህ በማንኛውም ሁኔታ የሚፈፀሙ አድሎአዊ ተግባራትን ለመከላከል ባለሥልጣንም ይሁን ማንኛውም ዜጋ ለሕግ ተገዢ መሆን፣ ሕግን የሚያከብር እና የማያስከብር፣ ሁሉን በእኩል የሚያስተናግድ እና ስራውም ቅንና የሚታመን ሲሆን ይገባል።

ፍትሐዊነት እንዲሰፍን ከሚያደርጉ የፍትሕ ተቋማት መካከል ፍርድ ቤቶች በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። እነዚህ አካላት ከማንም ተፅዕኖ ነፃ የመሆን የዳኝነት ነፃነታቸው ሊከበር ይገባል። ከዚህም በላይ የፍትሕ አካላት ውሳኔ ሕግን መሠረት የሚያደርጉ፣ ከወገንተኝነትና ከአድሎ የፀዱ አሰራሮችን የሚከተሉ መሆን አለባቸው። በሌላ በኩል አድሎአዊነትን በመከላከል ረገድ ዜጎች የጎላ ድርሻ አላቸው። ዜጎች ትክክለኛ ዳኝነት ለማግኘት በግላቸው መጣርም ይህም ሳይሳካ ቢቀር መብታቸውን በሕግ ብቻ ማስከበር እንዳለባቸው በውል ሊገነዘቡ ይገባል።

የማሕበራዊ አገልግሎት ተቋማት የዜጎች ሕይወት የተሻለ እንዲሆን ለማድረግ አስፈላጊ ናቸው። በዚህም የተነሳ ከአድሎ የፀዳ አገልግሎት ማዳረስ ይኖርባቸዋል። ተቋማቱን የማስፋፋቱ ጉዳይ የመንግሥት ኃላፊነት ብቻ ሆኖ መታየት የለበትም። በተጨማሪም ዜጎች ማህበራዊ ተቋማትን በማስፋፋቱ እንቅስቃሴ ላይ የላቀ ድጋፍ ማበርከት ይጠበቅባቸዋል። ግብር ለኢንቨስትመንት መስፋፋትና የክልሎችን እድገት ፍትሐዊ በማድረጉ ሂደት ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው።

ስለዚህ ከግብር የሚሰበሰበውን ገቢ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ለሁሉም ክልሎች ማከፋፈል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ከአንድ በፌደራላዊ ሥርዓት ከሚተዳደር ሀገር የሚጠበቅ አሠራር ነው። በፌደራል መንግሥቱና በክልሎች መካከል የሚደረገው ግብር የመሰብሰብና የማከፋፈል አሠራር በዘፈቀደ የሚሆን ሳይሆን ሕግን የተከተለ እና ሕገ መንግሥትን መሠረት ያደረገ ነው። ዞሮ ዞሮ ግን ዜጎች የግብርን ሁለንተናዊ ጥቅም በሚገባ ተረድተው ግብርን በወቅቱ መክፈልና በግብር አሰባሰብ ሂደትም ተገቢውን ትብብር ማድረግ ይገባቸዋል።

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**ታክስ፣** በመንግስት የሚሰበሰብ ማንኛውም ዓይነት ግብር::
**ተጨማሪ እሴት ታክስ፣** ከተወሰኑ የንግድ እንቅስቃሴ ገቢ ከመቶ አስራ አምስት እጅ ለመንግሥት የሚከፈል ተጨማሪ ክፍያ::
**ቀረጥ፣** በየእለቱ ከሚደረጉ የተለያዩ የንግድ ዝውውር ወይም ልውውጥ በመንግሥት የሚሰበሰብ ገቢ::
**እሴት፣** ስህተትና ትክክል ባህሪየትን መለኪያዎች ወይም አመለካከቶች::
**መርህ፣** የአሠራር ሥርዓት::

© MoE, FDR Ethiopia
Not to be republished

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

## I የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ፡፡

1. አድሎአዊ አሠራሮችን መከላከል እንጂ ሙሉ በሙሉ ማስወገድ አይቻልም፡፡
2. አንዳንድ ጊዜ አድሎአዊ አሠራሮችን ለማስወገድ ጉልበት መጠቀም ተገቢ ነው፡፡
3. አልፎ አልፎ የሚፈፀሙ የፍትሕ ጉድለቶች ለዴሞክራሲ እና ለልማት መጠናከር አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡
4. ማሕበራዊ ተቋማትን በማስፋፋቱ ሂደት የሕብረተሰቡ ተሳትፎ የሚፈለገው መንግሥት መስራት ካልቻለ ነው፡፡
5. ግብር በክልሎች መካከል ያለውን የእድገት ሂደት ለማቀራረብ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡

## II በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. በክልሎችና በፌደራል መንግሥት የሚሰበሰቡ ግብሮች፣ | ሀ. ትምህርት ቤት። |
| 2. በክልሎች መካከል የተመጣጠነ እድገትን መገንቢያ፣ | ለ. የጋራ ገቢ። |
| 3. አድሎአዊነትን ለማስወገድ ዜጎች መውሰድ ያለባቸው እርምጃ፣ | ሐ. ሕግን ማክበር። |
| 4. ማህበራዊ ተቋማት፣ | መ. ፍትሐዊ የግብር ክፍፍል። |
| 5. ከማንም አካላት ተፅእኖ ነፃ መሆን ያለበት፣ | ሠ. ፍርድ ቤቶች። |

## III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ አድሎአዊ አሠራሮችን ማስወገጃ መንገድ አይደለም፣
   - ሀ. በሕግ መጠቀም ፣
   - ለ. የደረሰን በደል በዝምታ ማለፍ፣
   - ሐ. ክስ ማቅረብ፣
   - መ. ሀ እና ለ መልሶች ናቸው፡፡
2. የፍትሕ አካላት መከተል ያለባቸው መርህ፣
   - ሀ. በራሳቸው ስሜትና ፍላጎት አለመመራት፣
   - ለ. ከወገናዊነት ነፃ መሆን፣
   - ሐ. መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣
   - መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡
3. ከሌሎች የበለጠ አድሎአዊ አሠራርን የመከላከል ኃላፊነት ያለበት አካል የቱ ነው?
   - ሀ. መንግሥት፣
   - ለ. የሃይማኖት ተቋማት፣
   - ሐ. ሲቪል ማህበራት፣
   - መ. ማህበራት።
4. ማሕበራዊ ተቋማት፣
   - ሀ. ለህብረተሰብ እድገት አስፈላጊ ናቸው፣
   - ለ. ከአድሎ የፀዳ አሰራር ሊከተሉ ይገባል፣
   - ሐ. በመንግሥት ብቻ ይሰራሉ፣
   - መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው፡፡
5. የአድሏዊ አሰራሮች ውጤት ያልሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. የተነሳሽነት ስሜት መቀዝቀዝ፣
   - ለ. የዲሞክራሲ ሥርዓት መዳከም፣
   - ሐ. ፍትሕን ማስከበር፣
   - መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

## IV የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ፡፡

1. በፌደራል መንግሥት አወቃቀር የግብር ክፍፍል በ_______እና_______መካከል የሚከናወን ነው፡፡
2. የፍርድ ቤት አሠራር መሠረታዊ መርሆዎች_______እና _______ ናቸው፡፡
3. ዜጎች በታችኛው ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎችን በመቃወም ለበላይ ፍርድ ቤቶች አቤቱታ የሚያቀርቡበት ሥርዓት_______በመባል ይታወቃል፡፡

## V የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. ከሚከተሉት አንዱን በመምረጥ የፍትሐዊነት መጓደል ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ዘርዝሩ፡፡
2. ግብር ለሀገር ልማት እና ለክልሎች ፍትሐዊ እድገት ያለውን ጠቀሜታ ዘርዝሩ፡፡

© FDRE Ethiopia Not to be republished

# ምዕራፍ አምስት
# የሀገር ፍቅር

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤**

- የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ታሪክ ማወቅ የሚሰጠውን ጥቅም ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ::
- የጋራ መገልገያ መሣሪያዎችን ለምን በጥንቃቄ መያዝ እንደሚገባ ታውቃለህ/ታውቂያለሽ::
- ድህነትና ኋላቀርነትን መዋጋት አስፈላጊ መሆኑን ትረዳለህ/ትረጂያለሽ::
- የዜግነት መብት መከበር የሀገር ፍቅር ስሜትን እንደሚያዳብር ትረዳለህ/ትረጂያለሽ::
- ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና ብሔራዊ መዝሙር ለሀገር ፍቅር መጎልበት የሚኖራቸውን አስተዋፅኦ ትረዳለህ/ትረጃለሽ::

## 5.1 ትክክለኛ የሆኑ የሀገርን፣ የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ታሪክና ባህል ማወቅ ለአዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት ግንባታ የሚኖረው ጠቀሜታ፤

✓ *የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ታሪኮችና ባህሎች ማወቅ ምን ጠቀሜታ አለው?*

### የእነ እጅጋየሁ ሠፈር ወጣቶች፤

[1] የእነ እጅጋየሁ ሠፈር ወጣቶች በአርአያነት የሚጠቀሱባቸው በርካታ ተግባራትን ያከናውናሉ። በቀበሌአቸው የወጣቶች ማኅበር አማካይነት ልዩ ልዩ ክበቦችን አቋቁመዋል። ከክበቦቹ መካከልም "የብሔረሰቦች ሙዚዬምና የሀገርህን ዕወቅ ፕሮግራም ማስተባበሪያ" በሚል ስያሜ የሚታወቀው ክበብ አንዱ ነው። እጅጋየሁና ጓደኞቿ የዚህ ክበብ አባላት ናቸው። ክበባቸው የሀገራችንን ሕዝቦች ባህልና ታሪክ ሊያሳዩ የሚችሉ ልዩ ልዩ ባህላዊ አልባሳትንና በርካታ ቁሳቁሶችን አሰባስቧል። በተደጋጋሚ ጊዜያት የሀገርህን እወቅ የጉዞ ፕሮግራም ለአባላቱ አዘጋጅቷል። እጅጋየሁ የክበቡ ተጠሪ ስትሆን በየጊዜው ከክበቡ አስተባባሪ ኰሚቴ አባላት ጋር ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን በማስተባበር የምትታወቅ ወጣት ናት። በተለይ በክበባቸው አባላት አማካይነት የሚቀርበው የተለያዩ ሕዝቦች ባህልና ታሪክ ገለፃ የአካባቢው ሕዝብ በጉጉት የሚጠብቀው ፕሮግራም ነው። የሕዝቦቹ ባህልና ታሪክ ገለፃ የሚካሄደው በቡድን የተደራጁ ወጣቶች የሚወክሉትን ብሔር ወይም ብሔረሰብ አልባሳት በመልበስ፣ ባህላዊ ቁሳቁሶችን በማሰባሰብና የብሔሩን ወይንም የብሔረሰቡን ታሪክ በሚገባ በመግለጽ ነው። ይህ ፕሮግራም በቀጨኔና በተጐራባች አካባቢዎች ሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነት በማትረፉ ብዙ ሰዎች አድናቆታቸውን ገልፀውላቸዋል።

**መልመጃ 1**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. የእነ እጅጋየሁ ክበብ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ምን ተረዳችሁ?
2. የተለያዩ ሕዝቦችን ታሪኮችና ባህሎችን ማወቅ በዜጐች ሕይወት ውስጥ የሚያመጣው ለውጥ ምንድን ነው?
3. በአካባቢያችሁና በቤታችሁ ውስጥ የሚገኙ የባህል መገለጫ ቁሳቁሶችን በመዘርዘር የትኛውን ብሔርና ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ እንደሚወክሉ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው::

ኢትዮጵያ የብዙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መገኛ ሀገር ነች። ብዙ ምሁራን ሀገራችንን የሚጠሯት፤ "የብሔረሰቦች ሙዚየም" በማለት ነው። የሀገራችንን ውበት ያፈኩት እነዚህ በርካታ ሕዝቦች የራሳቸው የሆኑ ባህሎችና ከ80 በላይ የሆኑ ቋንቋዎች ባለቤት ናቸው። ሀገራችን የነፃነቷን ክብር ጠብቃ የኖረችው ብሔሮቿ፣ ብሔረሰቦቿና ሕዝቦቿ በከፈሉት ታላቅ መስዋዕትነት ነው። ይህ ታላቅ የሕዝቦች የጋራ ታሪክ አንዳንዴ በውጭ ሀገርና በሀገራችን የታሪክ ጸሐፊዎች ተዛብቶ ሲቀርብ ይስተዋላል።

ባህሎቻቸውም እንዲሁ ተገቢው ትኩረት ሳይ ሠጠው ኖሯል። ነገር ግን አሁን ሀገራችን በተያያዘችው የዴሞክራሲ ሥርዓት ትክክለ ኛው የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና ሕዝቦች ታሪክ ያለአድልዎ እየተጻፈና ባህላቸውም ተገቢውን አክብሮት በማግኘት ላይ ይገኛል።

ይሄው አካሄድ ተጠናክሮ ቀጠለ ማለት በእያ ንዳንዱ ዜጋ ውስጥ አዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት በሚገባ ይሠርጻል ማለት ነው። የብሔ ሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ታሪኰ ችና ባህሎች በሚገባ ማወቅና ማጥናት ብሔ ራዊ የሀገር ፍቅርን ስሜት ያጐለብታል።

በብሔራዊ የሀገር ፍቅር ስሜት የታነጸ ትው ልድ ደግሞ የሀገሩን ሉዓላዊ ክብር ያስጠ ብቃል፣ ሀገሩ በዓለም ማኅበረሰብ ፊት የታወ ቀችበትን የርሃብ ታሪክም እንዲለወጥ ይጥ ራል።

**መልመጃ 2**

***የሚከተሉትን ጥይቄዎች ሥሩ።***

1. ከሀገራችን ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከል ምን ያህሉን እንደምታውቁ ለማ ሳየት የሚከተለውን የንጠረዥ በደብተራችሁ ሠርታችሁ በቀረበው ምሳሌ መሠረት ባዶ ቦታ ዎችን ሙሉ::

| ተራ ቁጥር | የብሔሩ፣ የብሔረሰቡና የሕዝቡ ስም | የሚናገረው ቋንቋ | የሚገኝበት ክልል |
|---|---|---|---|
| 1 | ሜሎ | ሜሎኛ | በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ ክልል |

2. ሀገራችን የነበራትን አኩሪ ታሪክ ጠብቃ እን ድትቆይ ከእያንዳንዱ ዜጋ ምን ይጠብቃል?
3. አዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት ይበልጥ እንዲጐለ ብት የእናንተ ድርሻ ምን መሆን ይገባዋል?
4. በአዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት ሲወገዱ ይገባቸዋል የምትሉትን ብሔራዊ ችግሮቻችንን ዘርዝሩ?

## 5.2 የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች መብቶች በእኩልነት መከበር ለሀገር ፍቅር ግንባታ ያለው አስተዋጽኦ፤



ሥዕል 5.1 የሕዝቦች የዕኩልነት መብቶች መከበር ውጤት

- *ከፎቶግራፉ ምን ተገነዘባችሁ?*

### አርአያነት ያለው የሕዝብ ግንኙነት፤

ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የመጡ ተማ ሪዎች በአንድ የከፍተኛ የትምህርት ተቋም ውስጥ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ነበሩ። የሕይወት እጣ ፈንታ ሆነና ከእነዚህ ተማሪዎች መካከል ከደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረ ሰቦችና ሕዝቦች ክልል ከካፋቾና ሸካቾ እና ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከቦሮ ሺናሻ ብሔ ረሰብ የመጡት ተማሪዎች ተቀራረቡ። ቅርር ባቸው እየተጠናከረ ሄዶ ስለተለያዩ ጉዳዮች በመወያየት አንዱ ለአንዱ ምስጢራቸውን ማካፈል ጀመሩ።

በውይይቶቻቸው መሃል አንድ ቀን ስለ ማንነ ታቸው፣ ባህልና ቋንቋ ታሪካቸው እየተወያዩ ሳሉ ያልታሰበና አስገራሚ የሆነ ነገር ተፈ ጠረ። ነገሩ እንዲህ ነው። ከዛሬ አራት መቶ ዓመታት በፊት በጥቅሉ የጐንጋ ሕዝቦች በሚል ይታወቁ ከነበሩት ከፋቾና ሸኮቾ፣ ቦሮ ሽናሻ፣ ሂናሪያ፣ ቦሾ እና ቡሻሼ ተብለው ይታወቁ ከነበሩት መካከል የካፋቾና ሸካቾ በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሚገኙ ሲሆን የቦሮ ሽናሻ ሕዝቦች ደግሞ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሰፍረው ይገኛሉ።

እነዚህ ሕዝቦች ባለፉት መንግሥታት ተገፍተው የትምህርት እድል ተነፍጓቸው ይኖሩ ነበር። በአሁኑ ወቅት የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት ባረጋገጠላቸው የእኩልነት መብት ተጠቅመው ከሌሎች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር ይኖራሉ። የከፍተኛ ትምህርት እድል ያገኙት እነዚህ ልጆቻቸው በታሪክ አጋጣሚ ተበታትነው የነበሩትን የሕዝቦቻቸውን የባህል፣ የቋንቋና የታሪክ አንድነት በማወቃቸው እጅግ ይደሰታሉ። ይህንኑ አጋጣሚ በመጠቀምም ወደፊት ጥልቅ ጥናት ለማድረግና ትስስራቸውን ይበልጥ ለማጎልበት ስምምነት አደረጉ። የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱንም አጠናክረው ለመቀጠል ሁሉም ቃል ገቡ።

*ምንጭ (ኅብረብሔር መጽሔት፣ በፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚታተም፣ ኅዳር 2000 ዓ.ም ገጽ 33፣ ለዚህ ክፍል እንዲመጥን ተሻሽሎ የተወሰደ)*

**መልመጃ 3**

***ከላይ የቀረበውን ታሪክ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ብሔረሰቦቹን የሚያመሳስሏቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?
2. ተማሪዎቹ ተቀራርበው መወያየት ባይችሉ ኖሮ የጋራ ታሪካቸውን ማወቅ ይችሉ ነበር? ታሪኩን መነሻ በማድረግ በጋራ ሀገራዊ አጀንዳዎች ላይ ውይይት ማድረግ ስለሚኖረው ጠቀሜታ በቡድን ተወያዩ፡፡

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባለፉት ሥርዓቶች ታሪካቸውና፣ ባህላቸው ተገቢው ትኩረት የተሰጠው አልነበረም፡፡ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሥርዓቱም አድሎአዊና ጭቆና የነገሠበት ነበር። ያም ሆኖ ግን ሕዝቦቹ ሀገራዊ ነፃነታቸውንና ሉዓላዊነታቸውን ለመድፈር የመጡ ቅኝ ገገርዎችንና ወራሪዎችን በጋራ በመመከት አኩሪ የትግል ታሪክ አስመዝግበዋል።

በአሁኑ ወቅት የሀገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ማንነታቸው ተከብሮ ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር ችለዋል። ባህላቸውን የማሳደግና በቋንቋቸው የመጠቀም መብታቸው ተከብሮላቸዋል፡፡ የሠላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ተጠቃሚነታቸውም ስለተረጋገጠ በእኩልነትና በመከባበር ላይ የተመሠረተ አንድ ጠንካራ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ማኅበረሰብ ለመፍጠርም ቃል ገብተዋል።

ይህን መሰሉ የዴሞክራሲ ትሩፋት ተጠናክሮ እንዲቀጥልም እያንዳንዱ ዜጋ ድርሻና ኃላፊነት አለበት። የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች መብቶች በእኩልነት ሲከበሩ ዜጎች ለሀገራቸው የጠለቀ ፍቅር ይኖራቸዋል። የሀገር ፍቅሩ የጐለበተ ዜጋ ደግሞ የረሃብ፣ የጦርነትና የእልቂት ምሳሌ ሆና በውጭው ዓለም በመጥፎ ገጽታዋ ብቻ የምትታወቀውን ሀገሩን ተባብሮ በመሥራት ታሪኳን ይለውጣል።

የተጀመሩት የልማት፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ሥራዎች እንዲጎለብቱና ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን የማድረግ፣ ሀገራዊ ተልዕኮና ራዕይ እንዲሳካ ወሳኙን ሚና ለመጫወትም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ትልቅ ድርሻ ይኖራቸዋል።

**መልመጃ 4**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።***

1. የሕዝቦች መብቶች ሳይከበሩ ስለሀገር ፍቅር መናገር ይቻላል? ለምን?
2. የሀገራችን ዕድገት ከብሔሮች ከብሔረሰቦችና ከሕዝቦች መብቶች መከበር ጋር የተያያዘ ነው የሚባለው ስለምንድን ነው?

## 5.3 የጋራ መገልገያ መሣሪያዎችን በጥንቃቄ አለመያዝ በሀገር ደረጃ የሚያስከትለው ጉዳት፤



ሥዕል 5.2 በጥንቃቄ ጉድለት ምክንያት የተጐዱ መገልገያ መሣሪያዎች

- ከስዕሉ ምን ተገነዘባችሁ?
- ከስዕሉ ለተገነዘባችሁት ችግር መፍትሔው ምንድን ነው ትላላችሁ?

## እሳትና ውሃ

እሳትና ውሃ አንድ በሬና የእርሻ መሳሪያዎችን ለጋራ መገልገያነት ገዝተው እየተረዳዱ ይጠቀሙበት ነበር ይባላል። ከዕለታት አንድ ቀን በሬያቸውን ሌቦች ሠርቀው አረዱባቸው። በዚህ ጊዜ አቶ እሳት እጅግ ተቆጥቶ ውሃን እንዲህ አለው "አቶ ውሃ የጋራ ንብረታችን የሆነው በሬ በመሠረቁ በጣም ተናድጃለሁ:: ጠላታችንን ለመበቀልም ስለወሰንኩ ደኑንም፣ ሣሩንም፣ ቤቱንም፣ ሁሉንም ነገር አቃጥዬ የበሬአችንን ሌባ አንድ ላይ አጠፋዋለሁ" ብሎ አማከረው።

ውሃውም "ወንድሜ አቶ እሳት ምነው እንደዚህ ማሰብህ? የሠረቀውንም ሰው ደህነኛውንም አንድ ላይ ማቃጠል አግባብ ነውን? ደግሞስ እነዚህ አቃጥዬና አውድሜ አጠፋቸዋለሁ የምትላቸው ነገሮች ፍጥረትን ሁሉ በጋራ ያለአድልዎ የሚያገለግሉ የጋራ መገልገያዎች አይደሉምን? ለአንድ አጥፊ ሲባልስ ፍጥረታት ሁሉ በጋራ የሚጠቀሙባቸውን መገልገያዎች ማጥፋት አግባብ ነውን? ሌባውን በዘዴ መያዝስ ይቻልየለ? ግዴለም ሌባውን በጥበባችን በቁጥጥር ሥር እናውለዋለን።

ለመሆኑ ምግብ ለማብሰል የሚፈልግ ከአንተ ዘንድ፣ ልብስና ዕቃ ማጠብ የፈለገ ደግሞ ከእኔ ዘንድ መምጣቱ ይቀራልን? ያንጊዜ ሌባውን በዘዴ ይዘን ለሕግ እናቀርበዋለን እንጂ በጋራ መገልገያዎቻችን ላይ ተገቢ ያልሆነና ማስተዋል የጎደለውን እርምጃ መውሰድ አይገባንም" ብሎ እሣትን አረጋጋው።

እውነትም ይህንን ተነጋግረው ጥቂትም ሳይቆዩ አንደኛው ሌባ የሠረቀውን የበሬ ሥጋ ጠብሶ ለመብላት ስለጎመጀ እየተጣደፈ እሳት ፍለጋ መጣ። ሁለተኛው ሌባ ደግሞ የበሬ ጨንጓራ ይዞ ሊያጥብ ወደ ወንዝ ወረደ። ይሄን ጊዜ ውሃና እሳት ተጠቃቅሰው ሌቦቹ እነሱ መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ በቁጥጥር ሥር አውለው በሕግ ፊት አቀረቧቸው።

እሳትም በውሃ ጥበብ እየተደነቀና ቀደም ሲል የወሰነው ያልተገባ ውሳኔ መሆኑን በመረዳት ጓደኛውን ይቅርታ ጠየቀ። የጋራ መገልገያ የሆኑትንም ነገሮች በችኮላ ለማውደም መወሰኑ ፀፅቶት ዳግመኛ ይህንን መሰሉን የችኮላ ስህተት ላለመድገም ውሳኔ አደረገ::

*ምንጭ (እንቅልፍ ለምኔ፣ ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ 1952 ዓ.ም ገጽ 63 ተሻሽሎ የተወሰደ።)*

### መልመጃ 5

***ከላይ የቀረበውን ታሪክ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. ከእሳትና ከውሃ ባህርያት ምን ተገነዘባችሁ::
2. እንደፎከረው እሳት የአካባቢውን የጋራ መገልገያ ሁሉ በንዴት ቢያጠፋ ኖሮ ውጤቱ ምን ይሆን ነበር?
3. የተለያዩ ምክንያቶች የጋራ መገልገያ መሣሪያዎችን የሚያወድሙ ሰዎችን ከዚህ ታሪክ አንፃር እንዴት ታዩታላችሁ?
4. ከታሪኩ ምን ጠቃሚ ትምህርት እንዳገኛችሁ ተወያዩ::

የመንግሥትና የሕዝብ የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች ለምሳሌ፣ ድልድዮች፣ መንገዶች፣ የኃይል ማመንጫ ተቋማት፣ የመንገድ መብራቶች፣ የውሃ መስመሮችና፣ የሕዝብ ስልኮች የአንድ አካል ሀብት ሳይሆኑ የዜጎች ሁሉ የጋራ ሀብት ናቸው። የተገነቡትም ከዜጎች በተሰበሰበ ገንዘብ ነው። የአገልግሎታቸው ተጠቃሚም ራሱ ሕዝቡ ነው። ስለዚህም እያንዳንዱ ዜጋ የመንግሥትና የሕዝብ መገልገያ መሳሪያዎች የዜጎች ሁሉ የጋራ ንብረት መሆኑን አውቆ ለደህንነታቸው ጥበቃ ሊያደርግ ይገባል። ለመንግሥትና ለሕዝብ ሀብት ጥንቃቄ አለማ ድረግ የሚጎዳው እያንዳንዱን ዜጋ ነው። የጋራ መገልገያ መሳሪያዎች የሁሉም ዜጎች ንብረት ስለሆኑ እንዳይባክኑ፣ እንዳይጠፉና፣ እንዳይሠረቁ ሊጠበቁ ይገባል። ለምሳሌ የስልክ መስመሮች በግሰቦች ሲቆረጡና ሲበላሹ፣ የውሃ ቧንቧዎች ተሰብረው ውሃ ያላግባብ ሲፈስ ወዘተ እያዩ ለሚመለከተው ክፍል ያለማሳወቅና ርምጃ አለመውሰድ ከአንድ ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር አይደለም።

© MoE FDRE Not to be republished

የጋራ መገልገያ መሳሪያዎችን በጥንቃቄ ጉድለት የሚያበላሽ፣ የሚያወድም ወይንም የሚያባክን ሰው በሕግ ፊት ተጠያቂ እንደሆነም ግንዛቤ ሊኖር ይገባል።

**መልመጃ 6**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።***

1. የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች የሕዝብ ሀብት ናቸው የሚባለው ለምንድን ነው?
2. የጋራ መገልገያ ሀብቶች ሲባክኑ እየተመለከትን አያገባኝም ብንል ከተጠያቂነት ማምለጥ እንችላለን?
3. በአካባቢያችሁ ሕዝቡ በጋራ የሚገለገልባቸውን ንብረቶች በመዘርዘር ሲደረግላቸው ስለሚገባው ጥንቃቄ አጭር ማብራሪያ ስጡ።

## 5.4 የሕዝብን ሰላምና የጋራ ደህንነትን ሥጋት ላይ የሚጥሉ አፍራሽ ተግባራት፤

### 5.4.1 የሕዝብን ሠላምና የጋራ ደህንነትን ሥጋት ላይ የሚጥሉ አፍራሽ ተግባራትን ለማስወገድ ሲደረጉ የሚገቡ ጥረቶች፣

✓ አፍራሽ ተግባራትን ለማስወገድ ከእናንተ ምን ይጠበቃል?

**"ለጋራ ደህንነት ዘብ መቆም"**

በመላው ዓለም የእርስ በእርስ ብጥብጥና ሁከት እየተነሳ በዜጎች ሕይወት፣ በሀገር ኢኮኖሚና ፀጥታ ላይ ብዙ ጉዳት ሲያስከትል እያስተዋልን ነው። የግል መብቴ አልተከበረልኝም ብሎ የሚያኮርፈው፣ የሀገሩ አስተዳደር የማያረካው፣ በጐሳው፣ በሃይማኖቱና በዘሩ ወይም በፍልስፍናው ያፈነገጠው ሁሉ በሀገር ላይ ሁከት፣ ሽብርና ብጥብጥ እንዲነሣሣ ምክንያት ሲሆን ይስተዋላል።

ብጥብጥ፣ ሁከትና ጦርነት ተመልሰው እነርሱኑ ራሳቸውን ይፈጥራሉ እንጂ ሰላምን አያመጡም። ያለንበት ዘመን የተራቀቀ የተንኰል ዘዴ ሊፈፀምበት የሚያስችለውን አቅጣጫ ሁሉ ፈጥሯል። የተራቀቁ የስውርና የግልፅ የጦርነት መሣሪያዎች ተፈልስፈዋል። በየትኛውም ቦታ ቢሆን ጥፋትና ተንኰል የሚፈፀመው በቀላሉ ነው። በፈንጅ የሰውን ሕይወትንና ንብረት ማውደም ቀላል እየሆነ መጥቷል። ለጉዳትና ለጥፋት ነገሮች ሁሉ የተመቻቹ ይመስላሉ።

የግል ኩርፊያም ሆነ የመንግሥት አስተዳደርን ጠልቶ በእልህ፣ በኃይልና በተንኰል ርምጃዎች በመፈፀም ሕዝብን መጉዳት የሚያስገኘው ውጤት የለም። እንዲያውም ድርጊቱ ችግርና ውድቀትን የሚያባብስ ሊሆን ይችላል።

በሀገር ላይ ለሚቃጣ ማንኛውም የተንኮል ተግባር እያንዳንዱ ዜጋ የመከላከል ኃላፊነት አለበት። ለሀገር ደኅንነትና ለሕዝብ ብልፅግናና ዕድገት የሚያስቡ ዜጎች እንዲህ ዓይነቶችን ለልማት ፀር የሆኑ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ሊቃወሙና ሊከላከሉ ይገባል።

*(የደረስኩበት ግለ ታሪክና ትዝታዎች፣ ማሞ ውድነህ፣ 1997፣ገጽ 524 ተሻሽሎ የተወሰደ)*

**መልመጃ 7**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. ከላይ የቀረበው ጽሑፍ ለማስተላለፍ የፈለገው ዋና መልዕክት ምንድን ነው?
2. «ብጥብጥ ሁከትና ጦርነት ተመልሰው እነርሱኑ ራሳቸውን ይፈጥራሉ እንጂ ሠላምን አያመጡም» በሚለው አገላለጽ ላይ በቡድን ተወያዩ።
3. በሀገር ላይ ለሚቃጣ ማንኛውም የተንኮል ተግባር እያንዳንዱ ዜጋ የመከላከል ኃላፊነት አለበት ሲባል ምን ማለት አለበት?

የሕዝብን ሠላምና የጋራ ደኅንነት ሊያናጉ የሚችሉ የተለያዩ አፍራሽ ተግባሮች በማናቸውም ጊዜ ሊከሰቱ ይችላሉ። ለምሳሌ በሕዝብ መካከል አሉባልታ መንዛት፣ ብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ማጋጨት፣ ርካሽ የፖለቲካ ዓላማን ለማራመድ በሕዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይና ተሽከርካሪዎች ላይ ፈንጂዎችን ማፈንዳት፣ ሠላማዊ የመማር ማስተማር ሂደትን ማሰናከል አፍራሽ ከሆኑ ተግባራት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። አፍራሽ ተግባራት ውጤታቸው ሕዝብን ይጐዳል እንጂ አንዳችም ጠቀሜታ አይኖረውም። ስለዚህም በየደረጃው ሊከሰቱ የሚችሉ ማናቸውንም የጋራ ደኅንነት ሥጋቶችን ለይቶ ማወቅና መከላከል ከብቁ ዜጋ የሚጠበቁ የመልካም ሥነምግባርና የኃላፊነት ስሜት መገለጫዎች ናቸው።

በሀገርና በሕዝብ ላይ የሚደርሱ አፍራሽ ተግባራት ጉዳታቸው ጊዜያዊ ብቻ ሳይሆን በዘላቂነት ሊቀጥል የሚችልም ነው። ስለዚህም እያንዳንዱ ዜጋ እነዚህን መሰል አፍራሽ ተግባራት ራሱን ሊያርቅ ይገባል። ራስን ከጥፋት ማራቅ ብቻም ሳይሆን አፍራሽ ተግባራትንም ያለ ይሉኝታ መታገል ከእያንዳንዱ ሀገሬንና ሕዝቤን እወዳለሁ ከሚል ዜጋ የሚጠበቅ ነው።

**መልመጃ ፰**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።***

1. በሀገርና በሕዝብ ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ የምትሏቸውን አፍራሽ ተግባራት በመዘርዘር በቡድን ተወያዩባቸው?
2. የጋራ ደህንነትን ሥጋት ላይ ሊጥሉ የሚችሉ አፍራሽ ተግባራትን ለማስወገድ ከእያንዳንዱ ዜጋ የሚጠበቁ ኃላፊነቶችን ዘርዝሩ::
3. በሀገርና በሕዝብ ላይ የሚደርሱ አፍራሽ ተግባራት ጊዜያዊ ብቻ ሳይሆኑ ዘላቂነትም አላቸው የሚለውን አገላለፅ እንዴት ትረዳላችሁ?

## 5.5 ድህነትና ኋላቀርነትን መዋጋት፤

### 5.5.1 ድህነትና ኋላቀርነትን ለማጥፋት የታቀዱ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ለመተግበር ከመንግስትና ከዜጐች የሚጠበቁ ግዴታዎች

- ✓ ለሀገራችን ዕድገት በመንግሥት የተነደፉ ዋና ዋና የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ዘርዝሩ::

***የልማት ስትራቴጂ ትክክለኛነት በተግባር ሲረጋገጥ፤***

በሀገራችን የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና ድኅነትን ለማሸነፍ የግብርናው ዘርፍ በቀዳሚ መፍትሔነት ይጠቀሳል:: መንግሥት በአርሶ አደሩ ተቀባይነቱ የተረጋገጠ የግብርና ልማት ስትራቴጂና ፖሊሲ በመንደፍ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረጉ ለሀገራችን ኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ ድርሻ እንዲኖረው አስችሏል። የዚህም ማረጋገጫው የአርሶ አደሩ ሕይወት በከፍተኛ ሁኔታ መለወጥ መቻል ነው::

የሀገራችን አርሶ አደሮች በመንግሥት የተነደፈውን የኤክስቴንሽን ፓኬጅን በተግባር በማዋል በአነስተኛ ማሳዎች ውስጥ የልዩ ልዩ ምርቶች ተጠቃሚ ሆነዋል። በዚህም ምክንያት ከዓመት ፍጆታቸው አልፎ ሕይወታቸው በከፍተኛ ሁኔታ ሊለወጥ ችሏል። መንግሥት የነደፈው የግብርና ልማት ስትራቴጂ ተግባራዊነት የገበሬውን ሕይወት ከመለወጥም አልፎ ዕድገቱ በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ ሀገራችን በአጭር ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ልትሰለፍ እንደምትችል ጥናቶች ያረጋግጣሉ::

ከዚሁ ጐን ለጐንም ተግባራዊ እየሆኑ ያሉት ሌሎች የልማት ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች ለሀገራችን ዕድገት አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛሉ::

*(ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ሚያዝያ 21/2000 ዓ.ም.ገጽ 3 ዕትም ተሻሽሎ የተወሰደ)*

**መልመጃ ፱**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።***

1. የግብርና ልማት ፖሊሲው በአርሶ አደሩ ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ውጤት ሊያስመዘግብ የቻለው ለምንድን ነው?
2. አርሶ አደሩን ይበልጥ ተጠቃሚ ስላደረገው የኤክስቴንሽን ፓኬጅ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ::

ሀገራችን የምትታወቅበትን ድህነትና ኋላቀርነት ለማስወገድ መንግሥት በተለያዩ ዘርፎች ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ነድፎ በተግባር ላይ አውሏል። ለምሳሌ የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ፣ የአቅም ግንባታ ስትራቴጂ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ:: እነዚህ የልማት ስትራቴጂዎች፣ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ተግባራዊነታቸው ቀጣይነት ከሌለው የታቀደው ዕቅድ የሚፈለገውን ውጤት ላያመጣ ይችላል። በተለይም ዜጐች ለድኅነታችንና ለጉስቁልናችን እንቅፋት የሆኑ ችግሮችን ለማስወገድ ለፖሊሲዎቹና ለልማት ስትራቴጂዎቹ ተፈፃሚነት እጅ ለእጅ ተያይዘው ካልቆሙ ድኅነት በንግግርና በምኞት ብቻ ሊወገድ አይችልም።

ለፖሊሲዎቹና ለስትራቴጂዎቹ ተፈጻሚነትና ውጤታማነት በቅድሚያ የሥራ ባህላችን ሊዳብር ይገባል። እያንዳንዱ ዜጋ ድህነትን ለማስወገድ በተሰማራበት የሥራ መስክ ሁሉ ውጤታማ መሆን አለበት። ለሀገራችን ድህነትና ኋላቀርነት የሚጠቀሱ በርካታ ታሪካዊ ምክንያቶች ቢኖሩም እነዚያን ስህተቶች ላለመድገም እያንዳንዱ ዜጋ በግሉ መወሰን ይገባዋል።

**መልመጃ 10**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።***

1. ለሀገራችን ድህነትና ኋላቀርነት መንስዔዎችና ችግሮችን ለማስወገድ መፍትሄ በምትሏቸው ነጥቦች ላይ ተወያዩ::
2. በሀገራችን የተነደፉት የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ከመንግስትና ከሕዝብ ምን ይጠበቃል? ተወያዩበት::

### 5.5.2 ድህነትና ኋላቀርነትን ለመዋጋት በአካባቢ የበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት ላይ መሳተፍ አስፈላጊ ነው፣



ሥዕል 5.3 ወጣቶች በችግኝ ተከላ

- ከሥዕሉ ምን ተገነዘባችሁ?

**የዘመን ፍልሚያ በድህ ጉያ**

ከአሥር ዓመቷ ጀምሮ ድሆችን በፍቅር እየቀረበች ታገለግል ነበር። ለምሳሌ አቡሌ የሚባል ማየት የተሳነው ወጣት ከሚያድርበት የጐዳና ዳር እየሄደች ምግብና ሣንቲም ትሰጠዋለች፣ እየመራች መንገድ ታሻግረዋለች። አንድ ቀን አቡሌ ለምኖ ምንም ሳንቲም ባለማግኘቱ በርሃብ አንጀቱ እጥፍ ብሎ የወደቀበት ሥፍራ ድረስ በመሄድ እንዲህ አለችው፣

"አቡሌ ዛሬ አልቀናህም?"
"አዎ ዛሬ አልቀናኝም።"

እጇን ወደ ቦርሳዋ ሰድዳ ሳንቲም አወጣች፣ እናም ሳንቲሙን በአቡሌ እጅ ላይ ዘረገፈችለት። አቡሌ ቀኑን ሙሉ ቢደክምም የማያገኘውን ሣንቲሞች እንደጨበጠ፣ "ከየት አመጣሽው?" ብሎ ህፃኗን ይጠይቃል። እርሷም፣ "እናቴ የሰጠችኝ የኪስ ገንዘብ ነው። እኔ ብገዛበት ከረሜላ ነው። ለአንተ ግን ራት መቀመሻ ይሆንሃል።" አቡሌ የዚህችን ልበ ብርሃንና አስተዋይ ልጅ በሳል አስተሳሰብ አደነቀ::

ያቺ የአሥር ዓመቷ ህፃን ዛሬ አድጋ የእርጅናን ፀጋ በመጐናጸፍ አንቱ የመባል ክብር አግኝታለች። የያኔዋ ርሁሩህ ህፃን የዛሬዋ ዶ/ር ጀምበር ተፈራ የተባሉት እናት ናቸው።

ዶ/ር ጀምበር ተፈራ በአሥር ዓመታቸው የጀመሩት የበጐ አድራጐት አገልግሎት ፍሬ አፍርቶ ዛሬ በመልካም አርአያነታቸው ከሚጠቀሱ የሀገራችን ሰዎች መካከል አንዱ ለመሆን በቅተዋል። በሙሉ በተቀነባበረ ዘዴ የከተማ ልማት ፕሮጀክት ተብሎ በሚጠራው ድርጅታቸው አማካይነትም በአዲስ አበባ አካባቢ የተለያዩ ቦታዎች በርካታ ተግባራትን እያከናወኑ ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል የአረጋውያን ማቆያ ማዕከላት፣ የማኅበረሰብ ዕድገት፣ የመሠረተ ጤና እንክብካቤና የአካባቢ የልማት ዘርፎች ጥቂቶቹ ናቸው።

ዶ/ር ጀምበር ተፈራ እስከዛሬ ካከናወኗቸው በጎ ተግባራት መካከል በተለይ የወጣቶች ሙያ ማዕከልና ንባብ ቤቶች፣ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ የጤና ኬላ ግንባታዎች፣ የውሃ ቦኖ፣ እጅግ የተጐሳቆሉና ለሰው ልጆች መኖሪያ የማይሆኑ ቤቶችን አፍርሶ በአዲስ የመተካት ተግባሮች፣ የጋራ መጠቀሚያ የሆኑ የማዕድ ቤቶችና የመፀዳጃ ቤቶች ግንባታዎች በምሳሌነታቸው የሚጠቀሱ ናቸው።

ይህንን የዶ/ር ጀምበር ተፈራ የበጐ ፈቃደ ኝነት ተግባራት የተመለከቱ የአካባቢው ነዋሪ ዎችም "የድሃ ጉያ" እያሉ ይጠሯቸዋል። ዛሬ የዶ/ር ጀምበር ተፈራ ዕድሜ ስልሣ አምስት ዓመት ደርሷል። የበጎ ፈቃድ አገልገሎታ ቸውን ለመፈፀምም ዛሬም ድረስ ዕድሜአቸው አልገደባቸውም፡፡

*(ደማቆቹ ፀሐያት ሊሊት፣ በሰለሞን ጥላሁንና ሥምረት ገብረ ማርያም፣ 2000 ዓ.ም ተመጥኖና ተሻሽሎ የተወሰደ።)*

**መልመጃ 11**

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መነሻ በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. የዕድሜ ማነስና መተለቅ የበጐ ፈቃደኛነት አገልግሎት ከመስጠት እንደማያግድ ከዶክተር ጀምበር ተፈራ ታሪክ ምን ተገነዘ ባችሁ?
2. የመንግስት የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ተግ ባራዊ እየሆኑ እያሉ እንደ ዶክተር ጀምበር የመሳሰሉ ዜጐች የሚሳተፉበት የበጐ ፈቃደ ኝነት አገልግሎት በተጨማሪነት ለምን ያስፈ ልጋል?
3. «ድህነትንና ኋላቀርነትን በበጐ ፈቃድ አገ ልግሎት ለማሸነፍ ከእኔ የሚጠበቅ ድርሻ በሚል ርዕስ አጭር ጽሑፍ ጽፋችሁ ለንደኞ ቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

የዜጐች የበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት ያልታ ከለበት ማንኛውም የመንግሥት እንቅስቃሴ የተጠበቀውን ውጤት ላያስገኝ ይችላል። በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ድኽነትን በማሸነፍ ብልፅግናን ለማምጣት የሚጥሩ ሀገሮች ዜጎቻቸው በበጐ ፈቃደኝነት አገልግ ሎት በስፋት ሊሳተፉ ይገባል።

የበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት በጉትጎታና በትዕዛዝ የሚከናወን ሳይሆን በራስ ተነሳሽ ነት የሚፈፀም ተግባር ነው። ለምሣሌ፣ ወጣ ቶች በአካባቢያቸው ያሉ ታናናሾቻቸውን ሰብ ስበው በማስጠናት በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት እንዲያመጡ ቢረዷቸው እህትና ወንድሞቻቸውን ከመርዳት ጐን ለጐን ውጤ ታማ ተማሪዎች ለማፍራት ለሚያስችለው የትምህርት ፖሊሲ ድጋፍ ሰጡ ማለት ነው፡፡

የአንድ አካባቢ ሰዎችም በቡድን ተደራጅተው በበጐ ፈቃደኝነት በሠፈራቸው ውስጥ የሚ ገኙ ጧሪ አልባ አረጋዊያንን፣ የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በሽታ ታማሚዎችን፣ የአእምሮ ህሙማ ንንና በተለያየ ምክንያት አሳዳጊ ያጡ ህፃና ትን ቢንከባከቡ፣ የአካባቢያቸውን ንፅህና ቢጠ ብቁ፣ በማምረቻና በማከፋፈያ ተቋማት በመገ ኘት ነጻ የጉልበት አገልግሎት ቢሰጡ፣ ሙስናን በጋራ ቢከላከሉ የሀገሪቱን ማኅበራዊ ችግሮች በጥቂቱም ቢሆን ለመቅረፍ አስተዋፅኦ እያደ ረጉ ነው ማለት ይቻላል። ይህን መሰሉን የበጐ ፈቃድ አገልግሎት የሚፈጽሙ ዜጐች ለሀገር ዕድገት ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ጐን ለጐን በሥነምግባራቸውም አርአያ ሊሆኑ እንደሚችሉ ማሰብ አግባብ ይሆናል፡፡

**መልመጃ 12**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን በመሆን ተወያዩባቸው።***

1. በዜጐች የበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት ያልተ ደገፈ የልማት ዕቅድ የተፈለገውን ውጤት አያመጣም የሚባለው ለምንድን ነው?
2. የበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት በመንግስት ትዕ ዛዝ የማይከናወነው ለምንድን ነው?
3. የበጐ ፈቃድ አገልግሎት የውዴታ ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ግዴታም ነው የሚባ ለው ለምንድን ነው?
4. በአካባቢያችሁ ማከናወን ስለሚገባችሁ የበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት በቡድን ተወያይ ታችሁ ሪፖርት አቅርቡ፡፡

## 5.6 ዜግነት፤

### 5.6.1 የዜጐችን መብት ማክበር ለሀገር ፍቅር መዳበር ያለው ጠቀሜታ፣

✓ *የዜጐችን መብት ማክበር ለሀገር ፍቅር መዳበር ምን ጠቀሜታ ይኖረ ዋል?*

**የዜግነት ድርሻን መወጣት**

ዜጎች ሁሉ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶ ቻቸው ተከብረውላቸው በሀገራቸው በነፃነት የመኖር መብት አላቸው፡፡ እያንዳንዱ ሰው የራሱ አመለካከት፣ የፖለቲካ አቋም፣ እምነትና ፍልስፍና ሊኖረው ይችላል፡፡ ማንም ሰው የሌላ ውን መብት እስካልነካና የእኔን ሃሳብ ብቻ

ተቀበሉኝ ብሎ እስካላስገደደ ድረስ በሠላ ማዊና ገንቢ በሆነ መልኩ አስተሳሰቡንና አቋ ሙን በነፃነት ለመግለፅ አይከለከልም፡፡ በአን ፃሩ ግን እያንዳንዱ ዜጋ የራሱ ሰብዓዊና ዴሞክ ራሲያዊ መብቶቹ እንዲከበሩለት የሚፈልገውን ያህል የሌላውንም መብት እንዲሁ ሊያከብር ይገባል፡፡

ሀገራችን የብዙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝ ቦች ሀገር ነች፡፡ እነዚህ ብሔሮች፣ ብሔረሰ ቦችና ሕዝቦች ደግሞ የየራሳቸው ቋንቋ፣ ባህልና እምነት አላቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ማንኛውም ሰው ከራሱ ብሔር ባህልና ቋንቋ ጋር ልዩ ትሥሥር ስላለውና የማንነቱም መገለጫ ስለሆነ መብቱ ሳይሸራረፍ ሊከበርለት ይገባል፡፡ የዜጎች ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች በርግጠኝነት የሚከበሩ ከሆነ በሀገራ ቸውና በሕዝባቸው ሊኮሩና የዜግነት ድርሻ ቸውን በሚገባ ሊወጡ ይችላሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ የሀገር ፍቅርን ስሜት ለማዳበር ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡

**መልመጃ 13**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሥሩ።***

1. ከላይ የቀረበው ፅሁፍ ስለ ዜጎች መብት አጠባበቅ ምን መልዕክት ያስተላልፋል?
2. የዜጎች ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶቻ ቸው የማይከበሩላቸው ከሆነ በዜግነታቸው ሊኮሩ ይችላሉ?
3. የዜጎች መብት መከበር ከሀገር ፍቅር ጋር ያለው ቁርኝት እንዴት ይገለፃል?

የአንድ ሀገር ውበቷ ዜጎቿ ናቸው። መብ ታቸው በሕገመንግሥት ተረጋግጦ የተከበ ረላቸው ዜጎች ሀገራቸውን ለማልማትና ለሀገራቸው ልዕልና ዘብ ለመቆም ሁሌም ዝግጁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ የዜግነት መብቱ ያልተከበረለት ሰው የሀገር ፍቅር ስሜቱ የጠነከረ አይሆንም። በዜግነቱ የሚሸ ማቀቅ ሰው የህሊና ርካታና እረፍት አይኖ ረውም። በሀገሩ ልማት ተሳትፎ ድህነትን ለማስወገድ በሚደረገው ጥረትም ንቁ ተሳታፊ አይሆንም፡፡

የሀገራችን ሕገመንግሥት የእያንዳንዱን ዜጋ መብት የሚያስጠብቅ ዋስትና ስለሰጠ በርካታ ሰዎች በሀገራቸው ጉዳይ በንቃት ሲሳተፉ ይስተዋላል። ሀብት ያለው መዋዕለ ነዋዩን እያፈሰሰ ሀገሩን በልማት በመገንባት ላይ ይገኛል። በተለያዩ ምክንያቶች በሌሎች ሀገ ሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአሁኑ ወቅት ወደ ሀገራቸው ተመልሰው በልማት ሥራዎች ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። በርካታ ምሁራንና ባለ ሀብቶችም በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ ተጠቅመው ወደ ሀገራቸው በመመለስ በሠለጠኑበት ልዩ ልዩ ሙያዎች ሀገራቸውን በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ይህ ሁኔታ የሚያመ ለክተው የዜጎች መብቶች ሳይሸራረፉ ሲከበሩ የሀገር ፍቅር ስሜቱም የዚያኑ ያህል እየዳበረ መሄዱን ነው፡፡ የሀገር ፍቅር ስሜት መዳበር ከሚገለጽባቸው መካከልም ጥቂቶቹ፤

- ✓ በጠንካራ የሥራ መንፈስ ውጤታማ ተግባር ማስመዝገብ፣
- ✓ ለዴሞክራሲና ለመልካም አስተዳደር መስፈን የድርሻን መወጣት፣
- ✓ በአካባቢና በሀገር አቀፍ ጉዳዮች ላይ ያለ ማንም ጉትጎታ መሣተፍ፣
- ✓ ለጋራ ደኅንነት መረጋገጥ ብሔራዊ የዜግነት ኃላፊነትን መወጣት፣

የሚሉት በዋነኛነት ይጠቀሳሉ። እነዚህ ተግባ ራት ሲከናወኑ የሀገር ብልፅግና ዕውን ይሆ ናል፡፡ የሀገራችን የድህነት ታሪክም ይለወጣል፡፡

**መልመጃ 14**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።***

1. የዜግነት መብቱ ያልተከበረለት ሰው ሀገሩን ከልብ እያፈቀረ የድርሻውን ሊወጣ ይችላል፡፡
2. ሀገሩን የሚወድ ዜጋ ሊያከናውናቸው ከሚ ገቡ ተግባራት መካከል ሦስቱን ዘርዝሩ፡፡

## 5.7 ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ፤

### 5.7.1 ሰንደቅ ዓላማና ብሔራዊ መዝሙር የሀገርን ፍቅር ስማዳበር የሚኖራቸው አስተዋጽዖ፣



ሥዕል 5.4 ጀግኖች አትሌቶች

- *ከዚህ በላይ ካለው ሥዕል ምን ትገነዘባላችሁ?*

### የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ መዝሙር፤

የዜግነት ክብር በኢትዮጵያችን ፀንቶ፣
ታየ ሕዝባዊነት ዳር እስከ ዳር በርቶ፤
ለሠላም ለፍትሕ ለሕዝቦች ነፃነት፣
ለእኩልነት ፍትህ ቆመናል በአንድነት፤
መሠረተ ፅኑ ስዕብናን ያልሻርን፣
ሕዝቦች ነን ለሰላም ለስራ የቆምን፤
ድንቅ የባህል መድረክ የአኩሪ ቅርስ ባለቤት፣
የተፈጥሮ ፀጋ የጀግና ሕዝብ እናት፣
እንጠብቅሻለን አለብን አደራ፣
ኢትዮጵያችን ኑሪ እኛም በአንቺ እንኩራ!!!

**መልመጃ 15**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።***

1. በብሔራዊ መዝሙሩ ውስጥ የተካተቱ ዋና ዋና መልዕክቶች ምንድን ናቸው፡፡
2. «ድንቅ የባህል መድረክ» የሚለው ሀረግ ምንን ይገልፃል?
3. ዜጐች ሀገራቸውን በክብር እንዲጠብቁ የሚያሳስበው ሀረግ የትኛው ነው?

ሰንደቅ ዓላማ የአንድን መንግሥትና ሕዝብ ሉዓላዊነት፣ ነፃነትና ሥልጣን የሚያሳይ ምልክት ነው፡፡ በመሆኑም ለሰንደቅ ዓላማ ክብር መስጠት ማለት ለሀገራችንና ለሕዝባችን ያለንን ፍቅርና አክብሮት መግለፅ ማለት ነው፡፡

ሰንደቅ ዓላማና ብሔራዊ መዝሙር ከሀገር ፍቅር ጋር እጅግ የተሳሰሩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የሀገራችን ስፖርተኞች በዓለም የስፖርት አደባባይ አሸናፊነታቸውን ተከትሎ ሰንደቅ ዓላማችን ከፍ ብሎ ሲውለበለብ የደስታ ስሜት እየተናነቃቸው እንባቸውን ያፈሳሉ፡፡

ከታሪካችን እንደምንገነዘበው ሕዝባችን ለሰንደቅ ዓላማውና ለሀገሩ ፍቅር ሲል በተለያዩ የጦር ግምባሮች ሕይወቱን መስዋዕት በማድረግ ሉዓላዊነቱን አስጠብቆ ኖሯል፡፡

ዛሬም ቢሆን ሀገሬን እወዳለሁ የሚል ዜጋ ፍቅሩን የሚገልፀው ሀገሩን በሚወክለው ሰንደቅ ዓላማና ከሰንደቅ ዓላማው ጋር ተያይዞ በሚዘምረው ብሔራዊ መዝሙሩ አማካይነት ነው፡፡ ቀደም ባሉት መንግሥታት ይታመን እንደነበረው ሰንደቅ ዓላማ ሊከበርና ሕዝብን ሊያንቀሳቅስ የሚገባው ወራሪ ሠራዊትን ለመመከት ብቻ መሆን የለበትም፡፡

ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በድህነት ላይ ዘምቶ አሸናፊ ለመሆንም በብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማችን ዙሪያ ተሰባስበን ሀገራችንን ወደ ብልፅግና ማሸጋገር ይጠበቅብናል፡፡ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ መፈቃቀርንና መከባበርን ለማጉልበት በሰንደቅ ዓላማ ዙሪያ መወያየት አግባብ ይሆናል፡፡ ለሰንደቅ ዓላማችን ፍቅር ሲኖረን ብሔራዊ የሀገር ፍቅራችንም ከፍ ይላል፣ የዜግነት ድርሻንም በብቃት ለመወጣት የፅናት አቅም ይሆነናል፡፡

**መልመጃ 16**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።***

1. ለሀገራችንና ለሕዝባችን ያለንን ፍቅር እንዴት በሰንደቅ ዓላማችንና በብሔራዊ መዝሙራችን መግለፅ እንደሚቻል በቡድን ተወያዩ?
2. ሰንደቅ ዓላማውንና ብሔራዊ መዝሙሩን የማይወድ ዜጋ ሀገሬን እወዳለሁ ማለት ይችላል? ተወያዩበት፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

አዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት በእያንዳንዱ ዜጋ ስሜት ውስጥ ለመስረጽ የሚችለው የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ታሪኮችና ባህሎች ማክበር ሲቻል ነው፡፡ ለሀገሩ ታሪክና ባህል እንግዳ የሆነ ሰው ለብሔራዊ የሀገር ፍቅር ስሜት የሚኖረው ስፍራ አነስተኛ ነው፡፡

የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች ታሪክና ባህሎች ማወቅ ብቻ በራሱ በቂ አይደለም፡፡ የሕዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በእኩልነት ተከብረው ሁሉም ዜጋ በሀገሩ ጉዳይ በእኩል ደረጃ ተሳታፊ ሲሆን የሀገር ብልፅግና ዕውን ይሆናል፡፡ ለሀገሩ ጉዳይ ባይተዋር የሆነን ዜጋ ሀገርን አፍቅር ቢባል ትርጉም አይኖረውም፡፡

የዜጎች መብት በተግባር ከተረጋገጠ ብሔራዊ የጋራ መግባባት ይኖራል፡፡ የጋራ መግባባትና መተሳሰብ ሲኖር የሀገሪቱ ውስን ሀብት ተገዝተው ለጋራ መገልገያነት በጥቅም ላይ የዋሉ መሣሪያዎችና ንብረቶች በጥንቃቄ ይያዛሉ።

አዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት በልቡ ውስጥ ሠርፃ የገባ ዜጋ ለሕዝብ ደህንነት ሥጋት ከሆኑ አፍራሽና የጥፋት ተግባራት እንዳይከሰቱ ይታገላል፣ ተከስተው ሲገኙም ያለምንም ይሉኝታ ለፍትሕ አካላት አሳልፎ ይሠጣል፡፡

ሀገሬን እወዳለሁ የሚል ሁሉ የሀገሩን ብሔራዊ ክብር ለማስጠበቅ ይጥራል ሰብአዊ ሰንደቅ ዓላማውና ለብሔራዊ መዝሙሩ ልዩ አክብሮትና ፍቅር ይኖረዋል፡፡ የሀገሩ ክብር መገለጫ በሆነው ሰንደቅ ዓላማ ሥር በመሰለፍ ሀገሩን አኩሪ ታሪክ አስጠብቆ ሁልጊዜ ቃሉን ማደስ አለበት፡፡

ሀገራችን ከምትገኝበት ድህነት ኋላቀርነት ተላቃ ወደ ተሻለ ዕድገት ከፍ እንድትል ዜጐች ሁሉ መንግሥት ለነደፋቸው የልማት ፖለሲዎችና ስትራቴጂዎች ተግባራዊነት የድርሻቸውን ሲወጡ ይገባል፡፡ ድህነትን ለማጥፋት በመንግስት የሚነደፉ የልማት ስትራቴጂዎችና ዕቅዶች በዜጐች የበጐ ፈቃደኝነት ተሳትፎ ካልተደገፉ የሚጠበቀው ውጤት ሳይመዘገብ ይችላል፡፡

የሀገራችንን የድህነት ታሪክ ለመለወጥ በአዲሱ የሃገር ፍቅር ስሜት እጅ ለእጅ ተያይዘን ድህነትን ተረት በማድረግ ዘላቂ ልማት ለማምጣት መረባረቡ የዜጎች ሁሉ ኃላፊነት ነው፡፡

© MoE, Not to be reprinted

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**ሉዓላዊ ሀገር፡-** ብሔራዊ ነፃነቱና ክብሩ በየትኛውም የውጭ ኃይል ያልተደፈረ ነፃ ሀገር።
**የዲሞክራሲ ትሩፋት፡-** ዴሞክራሲ ያስገኛቸው ጠቃሚ ውጤቶች።
**መልካም አስተዳደር፡-** ፍትሐዊና አድልዎ የሌለበት አስተዳደር።
**አፍራሽ ተግባራት፡-** የሀገርንና የሕዝብን ደህንነት ሊያናጉ የሚችሉ የጥፋት ተግባራት።
**መዋዕለ ንዋይ፡-** ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ቋሚ ሀብት።

© MoE, FDR Ethiopia
Not to be republished

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

### I የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ::

1. ሀገራችን፤ "የብሔረሰቦች ሙዚየም" ተብላ የምትጠራው ብዙ ባህሎችና ቋንቋዎች ስላሏት ነው።
2. የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ታሪክ ማወቅ የሚቻለው መልክዓ ምድሩን በማጥናት ብቻ ነው።
3. ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና ብሔራዊ መዝሙር የሀገር ፍቅር መገለጫዎች ናቸው።
4. የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት በመንግሥት የሚከናወኑ የልማት እንቅስቃሴዎችን አይደግፍም።
5. የሰንደቅ ዓላማችን ብሔራዊ ዓርማ የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች የዕኩልነት መገለጫ ነው::

### II በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. በራስ ተነሳሽነት የሚፈፀም ተግባር፣ | ሀ. ብሔራዊ መዝሙር:: |
| 2. ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ፣ | ለ. ብሔራዊ ምልክት:: |
| 3. ብሔራዊ ዓርማ፣ | ሐ. የሕዝቦች መገለጫ |
| 4. ዴሞክራሲ፣ | መ. የሀገርን ገጽታና ሀብት የሚጎዱ ድርጊቶች:: |
| 5. የዜጎች የቃል ኪዳን መግለጫ፣ | ሠ. ሃሣብን በነፃ የመግለጽ መብት:: |
| 6. አፍራሽ ተግባራት፣ | ረ. የአንድ ሉዓላዊ መንግሥት ዓርማ:: |
| 7. ባህልና ቋንቋ፣ | ሰ. የበጎ ፈቃድ አገልግሎት:: |

### III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ::

1. ሀገራችን ነፃነቷን አስከብራ የኖረችው፤
   ሀ. በጦር ኃይሏ ጥንካሬ ነው፣
   ለ. በስትራቴጂያዊ አቀማመጧ ነው፣
   ሐ. በጀግኖች ልጆቿ የተጋደሎ ጀግንነት ነው፣
   መ. ሁሉም መልስ ሊሆኑ ይችላሉ።
2. የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አንዳንድ ታሪኮች ሊዛቡ የቻሉት፤
   ሀ. ሁሉም ታሪኮች የተፃፉት በውጭ ሀገር ሰዎች ስለሆኑ ብቻ ነው ፣
   ለ. በሀገር ውስጥ ታሪክ ጸሐፊዎች ስላልተጻፉ ነው፣
   ሐ. የተዛቡ ታሪኮች የሉም፣
   መ. በአንዳንድ የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ ጸሐፊዎች ሲጻፉ በበቂ መረጃ ባለመደገፋቸው ነው።
3. ለመንግሥትና ለሕዝብ ሀብት ጥበቃ ማድረግ ያለበት፤
   ሀ. እያንዳንዱ ዜጋ በተመቸው ጊዜ ብቻ ከጠበቀ በቂ ነው፣
   ለ. የፖሊስ ኃይል ብቻ ነው፣
   ሐ. አንዳንዴ መንግሥት አልፎ አልፎ የአካባቢው ሕዝብ ከጠበቀ በቂ ነው፣
   መ. መንግሥትና ሕዝብ በመተባበር ሊጠብቁ ይገባል።
4. ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ፤
   ሀ. የነፃነት ምልክት ነው፣
   ለ. የአንድነት ማረጋገጫ ነው፣
   ሐ. የሉዓላዊ መንግሥት መለያ ምልክት ነው፣
   መ. ሁሉም መልስ ሊሆኑ ይችላሉ።

©MoE FDRE Ethiopia Not to be republished

5. ሀገሬን እወዳለሁ የሚል ዜጋ ሁሉ፤
   ሀ. በሀገሩ ጉዳይ ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆን ይገባዋል፣
   ለ. ለሀገሩ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና ብሔራዊ መዝሙር ተገቢውን አክብሮት ይሰጣል፣
   ሐ. ለጋራ መገልገያ መሣሪያዎች ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፣
   መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ።

## IV *የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::*

1. የአንድ አካባቢ ሕዝብ በእኩልነት የሚጠቀምባቸው ነገሮች ___________ ይባላሉ።
2. እያንዳንዱ ዜጋ___________አገልግሎት ቢሳተፍ የህሊና እርካታ ያገኛል።

## V *የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ::*

1. ሀገራችንን ከድህነት ለማላቀቅ ከእያንዳንዱ ዜጋ ምን ይጠበቃል?
2. ዜጎች የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት እንዲሰጡ የሚበረታቱት ለምንድን ነው?
3. የዜጐች መብት በእኩልነት ሲከበር የሀገር ፍቅር ስሜት ይዳብራል የሚባለው ለምንድን ነው?
4. ለሀገራችን ብሄራዊ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር ያለንን ክብር የምንገልፀው እንዴት ነው?

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

# ምዕራፍ ስድስት
# የኃላፊነት ስሜት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤**

- ቃል ኪዳንን ማክበር አስፈላጊ መሆኑን ትገነዘ ቢያለሽ/ ትገነዘባለህ::
- የኃላፊነት ድርሻን በብቃት መወጣት እንደ ሚገባ ታምናለህ/ ታምኛለሽ::
- የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን መጠበ ቅና መንከባከብ ተገቢ መሆኑን ትገነዘቢያለሽ/ ትገነዘባለህ::
- ኤች.አይ. ቪ/ኤድስ በሀገር ላይ የሚያስከትላቸ ውን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮችን ትረዳ ለህ/ ትረጃለሽ::

## 6.1 የኃላፊነት ድርሻን በብቃት ስለመወጣት፤

### 6.1.1 የኃላፊነት ድርሻን በብቃት መወጣት ያለው ጠቀሜታ፣



ሥዕል 6.1 የእሳት አደጋ መከላከያ ሠራተኞች የእሣት ቃጠሎን ሲከላከሉና ሕይወትና ንብረትን ከጥፋት ሲታደጉ( ሲያድኑ)

- የእሳት አደጋ መከላከያ ሠራተኞች በድፍ ረትና በቆራጥነት እሳቱን ለማጥፋት የሚታገሉት ለምንድነው?
- በሥዕሉ እንደሚታየው ሠራተኞቹ እሳ ቱን ባይቆጣጠሩት ኖሮ የሚከተለው አደጋ ምን ሊሆን ይችላል?

**ቢዛነት**

ጠያቂዎቻቸው የሁሉም ዕድሜ እርከን አባላት ነበሩ:: ሁሉም የአክብሮትና የፍቅር መግለጫዎ ቻቸውን ይዘው መጥተዋል:: አቶ ታመነ በቃሉ ግን በብዙ ዐይኖች ቢዳሰሱም እሳቸው ማንንም አላዩም:: ምንም አልተናገሩም:: በአልጋቸው ዙሪያ ከበው በሐዘኔታና በማድነቅ ስሜት ተይ ዘው የነበሩት ተማሪዎችና ሌሎችም ብዙ ሰዎች የታጨቁበት ክፍል ዝምታ ነግሶበት እርጭ ብሎ ነበር::

አቶ ታመነ እጆቻቸውና እግሮቻቸው እንዲሁም ጭንቅላታቸው በፋሻ ተጠምጥሞ ማንነታቸውን ለመለየት ከማይቻልበት ሁኔታ ውስጥ ገብተ ዋል:: በተለይ ፊታቸው አብጦ የተጠቀለሉበት ፋሻ ደም ስለሠረገው ይሰቀጥጣል::

አቶ ታመነ ከሞት አደጋ ቢተርፉም ዐይኖቻ ቸውን ገልጠው ሳያዩና ሳይናገሩ ብዙ ቀናት ተቆጥረዋል:: በዚያ ቀን ግን ድንገት አንደበታ ቸውን ሸብቦት የነበረውን ዝምታ ሰበሩት:: ዐይኖቻቸውንም ገለጧቸው:: የመጀመሪያ ጥያቄ ያቸውም "እነዚያ ሕጻናት ተርፈዋል?" የሚል ነበር:: ከመቅጽበት፣ በሚያንቃጭል የፈንጠዝያና የደስታ ቅላጼ በተሞላ ድምጻቸው "ተርፈ ናል....ድነናል...እናመሰግናለን::" አሉ ተማሪዎቹ:: ድምጻቸውም ከክፍሉ አልፎ ተሰማ:: ወዲያው በአቶ ታመነ አልጋ ላይ የአበባ ነዶ ተነሰነሰ:: በእልልታና በጭብጨባም የቀዘቀ ዘው የክፍሉ አየር ሞቀ::

የቃጠሎው መነሻ የፀደይ ቡቃያ ትምህርት ቤት የጽዳት ሠራተኛው ካቻ፣ የወረወራት የሲጋራ ቁራጭ ያስነሳችው እሳት ነበር:: ብዙ ክፍሎች ጣራቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ በእሳት ተያያዘ:: በስልክ የተጠሩት የእሳት አደጋ መከላከያ ሠራተኞች ተማሪዎችንና ንብረትን አተረፉ:: ከሁሉም በበለጠ አቶ ታመነ ከሚንቦገቦገው እሳት ውስጥ በመግባት ወደኋላ ቀርተው የነበ ሩትን የ7ኛ ክፍል ተማሪዎችን በማውጣት የቤ ዛነት ሥራ ሠርተዋል:: እሳቸውም በደረሰባቸው ቃጠሎና የጪስ አፈና ራሳቸውን ስተው ሲወድቁ

በሰዎች እርዳታ ተረፈው ለሕክምና በቅተዋል።

ካቻም በንዝህላልነት በፈጠረው አስከፊ አደጋ በቁጥጥር ሥር ውሎ ቅጣቱን ተቀበለ። ሱሰኛ በመሆኑ የቋጠረው ጥሪት ባለመኖሩም፣ እሱ ሲታሰር ወዲያውኑ ቤተሰቡ ተበተነ። ታማሚ ሚስቱ ወደ ልመና ስትገባ፣ ልጆቹም ከትምህርት ገበታ ተለይተው ለጐዳና ኑሮ ተዳረጉ። አቶ ታመነ ግን ለሙያቸው ታማኝ በመሆናቸው ኃላፊነታቸውን በብቃት ተወጡ።

የበርካታ ሀገር ተረካቢ ተማሪዎችን ሕይወት በማትረፋቸውም በጣም ተመሰገኑ። ከሕዝቡና ከልዩ ልዩ ድርጅቶች ምስጋና አድናቆትና፣ ሽልማት ተበረከተላቸው። ባሳዩት ተጋድሎ አቶ ታመነ በቤዛነታቸው ክብርና መወደድን አተረፉ።

**መልመጃ 1**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. ቤዛነት ምንድነው?
2. የአቶ ታመነ ተግባር ምንን ያመለክታል?
3. ኃላፊነትን በብቃት መወጣትን በተመለከተ የአቶ ታመነንና የካቻ ቦሩን ድርጊት በማነጻጸር ልዩነቶቻቸውን ግለፁ።

***የኃላፊነት ድርሻን በብቃት መወጣት*** ግላዊና ማኅበራዊ ብልጽግናን ከማስገኘቱም በላይ ለሀገር ዕድገት ወሳኝ መሠረት ነው። ማንኛውም ዜጋ የኃላፊነት ድርሻውን በብቃት ሲወጣ በቀዳሚያ የሚያገኘው የሥነ ልቦና እርካታ ነው። ጠንቃቃ ሠራተኛ በመሆኑም በሚያገኘው ገቢ በኑሮው ላይ ተጨባጭ በጐ ለውጥን ያመጣል። በአጠቃላይ ኃላፊነታቸውን የሚወጡ ዜጎች ከራሳቸው አልፈው የኅብረተሰቡን ሁለንተናዊ ዕድገት ያጐለብታሉ።

የኃላፊነትን ድርሻ በብቃት የሚወጡ ዜጐች ተአማኒነት አላቸው። መታመናቸውን በተግባራቸው ያረጋግጣሉ። በማኅበረሰቡ ዘንድም ይወደዳሉ። በዚህ ጽኑ የኃላፊነትን ድርሻ በብቃት የመወጣት የዜግነት ዓላማቸውና ውጤታቸው የተከበሩና በአርአያነት የሚጠቀሱ ይሆናሉ። እንደነዚህ ያሉ የተግባር ሰዎች የራሳቸውን ኑሮ በጥረታቸውና በውጤታቸው ያበለጽጋሉ። በተጨማሪም የሀገርን ልማት ለማፋጠን እንደ አራማጅ ኃይል ሆነው ያገለግላሉ።

**መልመጃ 2**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. የኃላፊነት ድርሻን በብቃት መወጣት ማለት ምን ማለት ነው?
2. ኃላፊነትን በብቃት መወጣት የሚያስገኘውን ጥቅም ዘርዝሩ።

### 6.1.2 የኃላፊነትን ድርሻን በብቃት አለመወጣት የሚያስከትለው ችግር

✓ የኃላፊነት ድርሻን በብቃት አለመወጣት ምን ችግር ያስከትላል?

የተጣለበትን የሥራ ኃላፊነት በቅንነትና በታማኝነት የማይወጣ ግለሰብ ራሱንና ቤተሰቡን ያደኸያል። ሥራውንም በመበደሉ የልማትና የዕድገት እንቅፋት በመሆን የሕረተሰቡን ዕድገት ያጓትታል። ኅብረተሰቡም እምነት ሊጥልበትና ለልዩ ልዩ ጉዳዮቹ የማይወክለው ይሆናል። በቤተሰቡም ሕይወት ላይ ለውጥና ዕድገት ለማምጣት አይችልም። የሚያፈራቸውም ልጆች ከሥርዓት ውጭ ስለሚያድጉ የኅብረተሰብ ጠንቅና ሸክም ይሆናሉ። በመሆኑም ማንኛውም ሰው የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃትና በትጋት መወጣት አለበት።

**መልመጃ 3**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. ኃላፊነትን በብቃት አለመወጣት በግል ኑሮ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ግለጪ/ግለፁ።
2. ኃላፊነት የማይሰማው ሰነፍ ሰው ግላዊና ማኅበራዊ ሕይወቱ ምን ይመስላል?

## 6.2 ቃል ኪዳንን ማክበር፤

✓ ቃል ኪዳን ምንድነው?

✓ ቃልኪዳንን ማክበር ምን ጥቅም አለው?

**የታጠፈ ቃል፤**

“እፎይታ ወላጅ አልባ ሕጻናት ማሳደጊያ” ድርጅት በጐ ሥራ ለመሥራት የተቋቋመ መንግሥታዊ ያልሆነ አካል ነው። ባቀረባቸው ዕቅዶችና የተግባር እንቅስቃሴ ስልቶች፣ እንዲሁም ለዜጎች ድጋፍ ለመስጠት ቃልኪዳን በመግባቱ ከመንግሥት ፈቃድ አግኝቷል። በኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸው የሞቱባቸውን ከሁለት መቶ በላይ ሕጻናት ሰብስቦ ሥራውን ከጀመረ

©MoE FDRE not to be republished

ሰባት ዓመታትን አስቆጥሯል:: በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ካሉ በጎ አድራጊ ድርጅቶች ጋር በፈጠረው ግንኙነት ስለ ሕጻናቱ እንክብካቤና ዕድገት ሲባል በርካታ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ያገኛል::

ሆኖም ከድርጅቱ አስተዳዳሪዎችና ሠራተኞች በስተቀር፣ በድርጅቱ የሚረዱት ሕጻናት ገጽታ ላይ የፈገግታ ፀዳል የለም:: በባዶነት ስሜት ቅሬታ ተላብሰው ይታያሉ:: ከፍ ከፍ ያሉትም በሀዘን ተውጠው ድርጅቱ በጫነባቸው ሥራ ላይ ተሰማርተዋል:: በአካልና በሞራል አድገው በትምህርት ታንፀው የሀገር ተረካቢ ይሆናሉ የተባሉት ወጣቶች የትምህርት ዕድል ሳያገኙ ዓመታት አልፈዋል::

ድርጅቱ በወገንና በመንግሥት ፊት የገባውን ቃልኪዳን ባለመጠበቁ ከተረጂዎች መካከል ማገናዘብና ማስተዋል የቻሉ ወጣቶች በደላቸውን ለማሰማት አቀዱ:: በመጀመሪያ በድርጅቱ ውስጥ የታቀፉትን ልጆች እየተፈጸመባቸው ያለውን በደል እንዲገነዘቡት አደረጉ:: በመቀጠልም የአካባቢው የቀበሌ አስተዳደርና የወጣቶች ማኅበር ሁኔታውን እንዲረዱላቸው አሳወቁ:: በተጨማሪም ጥያቄአቸውን በሚያቀርቡበት ዕለት እንዲገኙም ጋበዙአቸው:: ከዚያ በኋላ በወሰኑት ቀን ከድርጅቱ አስተዳደር ጽ/ቤት ፊትለፊት በመሰለፍ፣ ተገቢ የትምህርት ዕድል፣ ተመጣጣኝ የሥራ ድርሻ፣ ደረጃውን የጠበቀ ምግብና ልብስ፣ እንዲሁም የጥናት ጊዜ እንዲሰጣቸው ጠየቁ::

የድርጅቱ አስተዳዳሪዎች በሁኔታው በመበሳጨት መሪ የሆኑትን ወጣቶች በማባረር ቀሪዎቹን ለመቅጣት አቀዱ:: ሆኖም ቀበሌውና የሚመለከታቸው ድርጅቶች ባደረጉት ትብብርና ማጣራት ድርጅቱ "ቃሉን ያፈረሰ" መሆኑን በማጋለጥ ቃልኪዳናቸውን ያልጠበቁትን አስተዳዳሪዎች አስወገዱ:: በምትካቸውም ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች ተመድበው ወጣቶቹ ተገቢውን ድጋፍ በማግኘት የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ አደረጉ::

## መልመጃ 4

*ከላይ በቀረበው ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. በቃልኪዳኑ መሠረት ያልሠራው ድርጅት ምን ችግር አስከተለ?
2. ይህ ድርጅት ኃላፊነቱን በትክክል ቢወጣ ኖሮ የሚያስገኘው ጥቅም ምን ነበር?

ቃል ኪዳንን ማክበር፣ ኃላፊነትን የመወጣት ችሎታንና የመንፈስ ጥንካሬን የሚያሳይ ብቃት ነው:: በመሠረቱ ቃል ኪዳን የእምነት ማረጋገጫ የሆነ ክቡር ቃል ነው:: ቃል ኪዳን በእያንዳንዱ ዜጋ፣ በድርጅቶችና በመንግሥት የሚሰጥ የተስፋ መተማመኛ ሲሆን፣ ቃል የገባው አካል ቃሉን ማክበሩን ማረጋገጫው ደግሞ ተግባርና ውጤት ነው::

ኃላፊነትን በብቃት መወጣትና ቃልኪዳንን ማክበር ከማንኛውም ዓይነት ሥራ፣ በማንኛውም የኃላፊነት ደረጃ ከሚገኝ ሰው የሚጠበቅ ወሳኝ እንቅስቃሴ ነው:: የግለሰቦች፣ የተቋሞች፣ የመንግሥትና የመንግሥት ያልሆኑ ድርጅቶች የተግባር ውጤቶች ድምር፣ ለኅብረተሰቡ ኑሮ ዕድገትና ለሀገር ብልጽግና መሠረት መሆኑ ግልጽ ነው:: በመሆኑም ዜጎችም ሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም መንግሥት፣ ለገቡት ቃልኪዳን መፈፀም ኃላፊነትን የመውሰድ ብቃታቸውንና ጥረታቸውን በማጠናከር ለሁለንተናዊ ለውጥ አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅ ባቸዋል::

ቃል ኪዳንን አለማክበር ሌብነት ነው:: ጊዜንና አደራን ማባከንም ወንጀል ሆኖ ይቆጠራል:: ይህ ኢ-ተአማኒነትና ውጤት አልባነት በቅድሚያ ኃላፊነቱን ያልተወጣውን ግለሰብ፣ ድርጅት፣ ወይም መንግሥታዊ አመራር እንዲናቅና እንዲጠላ ያደርጋል:: ሊከናወን የሚገባው ተግባር በወቅቱና በተገቢ ውጤት ባለመገኘቱ ደግሞ በማኅበረሰቡ ጥቅምና ሕልውና ላይ ጉዳ ሁኔታን ይፈጥራል:: ይህም የሀገርን ዕድገት ያጓትታል::

## መልመጃ 5

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

1. ቃል ኪዳንን ማክበርና ኃላፊነትን መውሰድ ጠቀሚታው ምንድነው?
2. ቃልኪዳንን ማክበር በግለሰብ ደረጃ ምን ያስገኛል?

## 6.3 የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች፤

### 6.3.1 የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶችን አለመጠበቅ የሚያስከትለው ጉዳት፣



ሥዕል 6.2 ደኖች አደውደሙ

- ከሥዕሉ ምን ተገነዘባችሁ?

**የሁሉም ሰው ጉዳይ፤**

ሀገራችን በተፈጥሮ ሀብቷ የበለፀገችና መሬቷም በደን የተሸፈነ ስለነበር ድንቅና ብርቅ የሆኑ የዱር አራዊት በብዛትና በዓይነት ይገኙባት ነበር:: ዛሬ ግን በሚያስደነግጥ ሁኔታ የተፈጥሮ ሀብቷ በመመናመኑ የአካባቢ አየር መዛባትና የሚያስከትለው ችግር እየታየ ነው::

የተፈጥሮ ሀብቶችን አለመጠበቅ የእርሻ ምርትን ይቀንሳል፣ የተፈጥሮን የአየር ሚዛን ያዛባል፣ አፈር በንፋስና በውሀ እንዲጠረግ ያደርጋል:: ይህም ለብዙ ሰዎችና እንስሳት ሕይወት መጥፋት መሠረታዊ ምክንያት ይሆናል:: ይህን አደጋ ለማስቀረትና የተፈጥሮ ሀብትን በማበልፀግ በጥቅም ላይ ለማዋል፣ ደንን ማልማት፣ መንከባከብና መጠበቅ አማራጭ የሌለው ተግባር ነው:: የደን አለመኖር የአፈርን መጠረግና መታጠብ ስለሚያስከትል የምግብ እህል ምርታማነት በእጅጉ ይቀንሳል::

በዱርና በደን የሚጠለሉ አራዊትና አእዋፋት ያልቃሉ ወይም ይሰደዳሉ ይህም የቱሪዝምን ሥራ ያዳክማል:: የአየር ሚዛን ስለሚያዛባ ድርቅና በረሃማነት ይከሰታል:: የተፈጥሮ ሀብትን አለመጠበቅና አለመንከባከብ በዓለም ዙሪያ ለሰዎችና ለእንስሳት በረሀብ ማለቅና ለስደት መዳረግ ዋነኛው መንስኤ መሆኑ እየታየ ነው:: ስለዚህ እንዚህን አለአግባብ የጠፉና የተመናመኑ ሀብቶችን እንደገና ለማበልፀግ እያንዳንዱ ዜጋ ባለው አቅምና እውቀት መረባረብ አለበት::

የደንን መጨፍጨፍ መከላከል፣ ችግኞችን መትከልና መንከባከብ፣ የሰዎችን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ ስለተፈጥሮ ሀብት ጥቅም ማስተማር፣ በቀጣይነት ሊሠራበት የሚገባ ግዴታ ነው:: የሀገርን ኤኮኖሚ የሚደግፈው የተፈጥሮ ሀብት መዳበር የእያንዳንዱ ሰው ጉዳይ በመሆኑ ለልማትና ለለውጥ መነሳት አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም::

**መልመጃ 6**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

1. የሀገራችን የተፈጥሮ ሀብት በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል?
2. የደን ውድመት ምንን ያስከትላል?
3. የተፈጥሮ ሀብት መበልፀግ ለቱሪዝም ዕድገት የሚጠቅመው እንዴት ነው?

የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች፣ የአንድ ሕዝብ የሕልውናው መሠረቶችና የማንነቱ መግለጫ ናቸው:: የተፈጥሮ ሀብቶች በተፈጥሮ የተገኙ አራዊት፣ አእዋፋት፣ እንስሳት፣ ዕፅዋት፣ አፈርና ማዕድናት፣ ውሀና የውሀ ውስጥ እንስሳትና እጽዋት ሲሆኑ ከአያያዝና ከአጠቃቀም ጉድለት ሊቀንሱ ወይም ሊጠፉ የሚችሉ ናቸው::

የደን ሀብቶች መመናመንና መጥፋት የዓለምን የአየር ንብረት በማዛባት በረሃማነትን እያሰፈነ ይገኛል::የዚህ ሁኔታ መከሰት የሰዎችን ኑሮ አስቸጋሪና አሳሳቢ እያደረገው ነው:: ድህነት፣ ስደት፣ ረሀብ፣ ግጭትና እልቂት በማስከተል ሰዎችን በመፈታተን ላይ ያለው የበረሃማነት መስፋፋት መሠረታዊ መንስኤው የደን መጨፍጨፍ ነው:: በተጨማሪም ደንን ተጠልለው የሚኖሩ አራዊት፣ አእዋፋትና እንስሳት መኖሪያ ፍለጋ ከስፍራ ስፍራ እየተሰደዱ ስለሚሄዱና ስለሚያልቁም በቱሪዝም የሚያስገኙት ገቢ ይቀራል:: ይህም በሀገር ኤኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል:: ያለፉት ወገኖቻችን በጊዜያቸው በነበረው ጥበብና እውቀት የሠሯቸውን ልዩ ልዩ ቅርሶች በማስተላለፍ ዛሬ ሀገራችንን ታዋቂና

ተደናቂ እንደትሆን አድርገዋል:: እነዚህን የማንነት መለያ ቅርሶች አለመጠበቅና አለመንከባከብ የዜግነት ግዴታን አለመወጣት ነው:: ታሪካዊ ቅርሶች ሲጐሳቆሉ፣ ሲበላሹና ሲወድሙ ወይም ሲሰረቁ የሀገር ታሪክ ይጎደላል:: የጐብኝዎችንም ትኩረት ለመሳብና ቱሪዝምን ለማካሄድ አይቻልም:: ታሪካዊ ቅርሶች ካልተጠበቁና እንክብካቤ ካልተደረገላቸው በታሪክና በኢኮኖሚ ላይ ጉድለት ያስከትላሉ:: እንደ ተፈጥሮ ሀብቶች ሁሉ ታሪካዊ ቅርሶችም ፈርጀ ብዙ ጥቅም ስላሉዋቸው ማንኛውም ዜጋ ጥበቃና እንክብካቤ ሊያደረግላቸው ይገባል::

**መልመጃ 7**

? *በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

1. የበረሃማነት ምክንያት ምንድነው?
2. ታሪካዊ ቅርሶችን አለመጠበቅ የሚያስከትለውን ጉዳት ግለጪ/ ግለጽ::
3. የሕዝብ ታሪክ መገለጫ ምንድነው?

## 6.4 ኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ፤

- ✓ ኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ አምራቹን ዜጋ ሲያጠቃ የሚደርሰውን ጉዳት ግለፁ::
- ✓ በሽታው በፍጥነት የሚስፋፋበትን ምክንያት ግለፁ::

**ማንነትን ማወቅ**

አንድ የእንጀራ ማምረቻ ፋብሪካ ሶስት ሺህ ሠራተኞችን በደሞዝ በማሳተፍ በአማካይ ዘጠኝ ሺህ ቤተሰቦቻቸውን ጭምር ይረዳል:: ተፈላጊነቱ የማያቋርጠውን የእንጀራ ምርት በማቅረብ፣ በአንድ ዓመት ሥራው በአስር ሚሊዮን ብር ትርፍ የኤኮኖሚ እመርታ አሳየ:: ሆኖም በቀጣዩ ዓመት ውስጥ በኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ ሁለት መቶ ሃምሳ ቁልፍ የሙያ ሠራተኞች በመሞታቸው የሥራው ሂደት በመታወኩ የፋብሪካው ገቢ በሶስት ሚሊዮን ብር ቀነሰ::

የበሽታው ስርጭት እየሰፋ በመሄዱ በሕመም ምክንያት ከሥራ ገበታቸው ላይ የማይገኙት ሠራተኞችም ቁጥር ጨመረ::

ስለዚህ ፋብሪካው ለችግሩ መፍትሔ ለመፈለግ ጥረት ጀመረ:: በቅድሚያ ሠራተኞቹ ሁሉ ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተከታታይ ትምህርት እንዲያገኙና በመቀጠልም ሁሉም ተመርምረው ያሉበትን ሁኔታ እንዲያውቁ አደረገ:: ቫይረሱ ያለባቸው ተገቢ ሕክምናን በመከታተል፣ የሌለባቸውም ጥንቃቄ በማድረግ ቀጣይ ኑሮዋቸውን በሥርዓት መኖር በመጀመራቸው የፋብሪካው ሥራና ውጤት በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደነበረበት የዕድገት ደረጃ ተመለሰ::

**መልመጃ 8**

? *ከላይ በቀረበው ታሪክ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. በታሪኩ መሠረት የኤች. አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭት በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል?
2. የሠለጠኑ አምራች ኃይላት በበሽታው መሞታቸው ያስከተለውን ጉዳት ግለጪ/ ግለጽ::
3. በአሁኑ ወቅት ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የተገኘ ለት መፍትሔ ምንድነው?

ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ በዓለም ላይ በፍጥነት በመዛመት ላይ ያለ የሰው ልጆች ሕልውና ጠንቅ ነው:: በጠበብቶች ያላሰለሰ ጥረትና ሙከራ ቢደረግም መድኃኒት አልተገኘለትም:: እስካሁን በኤድስ ምክንያት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ሕይወታቸው ተቀስፏል::

አሁንም በቫይረሱ ከተጠቁት የዓለም ሰዎች ሰባ ከመቶው የሚገኙት በአፍሪካ በተለይም ከሰሀራ በታች ባሉ ሀገራት ውስጥ ሲሆን ኢትዮጵያም በሕመሙ ተጠቂዎች ሰፊውን ድርሻ ይዛለች:: እነዚህ ሀገራት ስለበሽታው ጠንቅና መተላለፊያ መንገዶች በቂ ትምህርትና ግንዛቤ ለሕዝቦቻቸው ማስጨበጥ ያልቻሉ መሆናቸው ይነገራል:: ጥናቶች እንደሚያረጋግጡት በሀገራችን በይበልጥ ከ15 ዓመት ዕድሜ በላይ ያሉት ዜጐች በቫይረሱ እየተያዙና በሕመሙ እየተጠቁ ናቸው:: ይህ የዕድሜ ክልል የሚያጠቃልለው ለሀገር ግንባታና ለማኀበራዊ ኑሮ ለውጥ አንቀሳቃሽ የሆኑትን አምራችና በልዩ ልዩ ሙያ የሰለጠኑ እንዲሁም በመማርና በመሰልጠን ላይ ያሉ ዜጐችን ነው:: የእነዚህ ዜጐች መሞት ጉዳቱ ዘርፈ ብዙ ነው:: ጐላ ጐላ ያሉት ችግሮች የሚከተሉት ናቸው::

**1. ማኅበራዊ ችግሮች፣**

ሀ. ሕመምተኛውን ለማስታመም በቤተሰብ ላይ የኃላፊነት ጫና ይወድቃል፣

ለ. ወላጆች ከሞቱ ልጆች ያለአሳዳጊ ይቀራሉ፣ ይጉሳቆላሉ፣ ይበተናሉ፣ የማኅበራዊ ኑሮ ቀውስ ፈጣሪዎችም ይሆናሉ::

ሐ. ልጆቻቸውን በኤድስ ያጡ አረጋውያን ጧሪ አልባ ይሆናሉ::

መ. ዕድሮች ይዳከማሉ የቀብር ቦታዎች ጥበትም ይከሰታል::

**2. ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በሀገር ደረጃ፣**

ሀ. ለሕመምተኞች ብዛት ያላቸው የሆስፒታል አልጋዎች እንዲዘጋጁና የሕክምና ወጪ እንዲመደብ ያስገድዳል:: ይህም በሀገር ኤኮኖሚ ላይ ጫና ይፈጥራል::

ለ. ኤድስ ለሚያስከትላቸው ተዛማጅ በሽታዎች ተጨማሪ ወጪን ያስከትላል::

ሐ. በፋብሪካና ኢንዱስትሪዎች በኩል በሰለጠኑ አምራቾች ሞት የምርት ሥራ ይዳከማል ውጤቱም ይቀንሳል::

መ. በገጠሩ የአርሶ አደሮች ሞት የግብርናውን ሥራ ሲያዳክም ለፋብሪካዎች የሚሆነው ግብዓትና ለከተማ ነዋሪው ሕዝብ የምግብ ምርት አቅርቦት ይቀንሳል::

ሠ. ሰፊ እውቀትና የዳበረ የሥራ ልምድ ያላቸው የሀገር ሀብት ዜጎች (መምህራን፣ ሀኪሞች፣ መሀንዲሶች፣ ወዘተ) ዕውቀታቸውና ውጤታቸው በከንቱ ይቀራል::

ስለዚህም ተፈላጊው እውቀት፤ ክህሎትና ዝንባሌ ያላቸውን ዜጎች ለማፍራት አዳጋች ይሆናል:: ምን መደረግ አለበት?

የመጀመሪያው ዋነኛ ጉዳይ፣ የበሽታውን ምንነትና መተላለፊያውን ሁኔታ ጠንቅቆ በማወቅ ራስን ለኑሮ ሥርዓት ተገዢ ማድረግ ነው:: በቫይረሱ የተያዘ ሰው በምንም ዓይነት ሁኔታ መዳኛ የለውም:: ራስን ከበሽታው ከመጠበቅ ባሻገር ሌሎችም ችግሩን እንዲገነዘቡ ማድረግ የበሽታውን መስፋፋት ለመግታት የዜግነትን ግዴታን መወጣት ነው:: መንግሥትም ሆነ ሌሎች ድርጅቶች በሚያዘጋጁት የማስተማርና የማንቃት ሂደት ውስጥ በመሳተፍ የድርሻን መወጣት ያስፈልጋል:: ይህ የጋራ ጥረት በተቀናጀ መልኩ ከተሰራበት ስርጭቱ በእርግጥ ሊቀንስ ይችላል::

በአብዛኛው በሽታው የሚተላለፈው በወሲባዊ ግንኙነትና ከእናት ወደ ፅንስ በሚተላለፈው ሂደት ነው:: ስለዚህ የቫይረሱን ስርጭት ለመግታት፣

ሀ. ከጋብቻ በፊት ወሲባዊ ግንኙነት አለማድረግ (መታቀብ)፣

ለ. ጋብቻ ከመፈፀም በፊት ትክክለኛ የሀኪም ምርመራ ማድረግ፣

ሐ. በጋብቻ ሕይወት (ባል ለሚስት፤ ሚስት ለባል) ታማኝ ሆኖ መኖር፣

መ. ቫይረሱ ያለባቸው ባለትዳሮችም ቫይረሱ ወደ ፅንሱ እንዳይተላለፍ የሀኪም ምክርና የሕክምና እርዳታ ለማግኘት በግልጽነት መቅረብ፣

እላይ ከተጠቀሱት ዋነኛ መተላለፊያ መንገዶች በተጨማሪ በኋላቀር ልማዶች ሳቢያ የበሽታው ሰለባ ከመሆን መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው:: በባህላዊ ሕክምና ሴት ልጅን መግረዝ፣ እንጥል መቁረጥ፣ ግግ ማውለቅ፣ ንቅሳት መንቀስ ወዘተ አደገኛ መተላለፊያዎች በመሆናቸው እነዚህን ድርጊቶች ማስወገድ ስርጭቱን ይቀንሰዋል:: የጥርስ መፋቂያ፣ ማበጠሪያ፣ ምላጭ፣ መርፌ፣ የጥፍር መቁረጫ፣ ወረንጦና የመሳሰሉ ስለታም እቃዎችን በጋራ መጠቀም በንዝህላልነት ራስን ለመከራ መጋበዝ ነው::

ስለዚህ ጊዜው የሚጠይቀውን ጥንቁቅነትን፣ ታማኝነትንና ጽናትን ይዞ የዜግነትን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ማቀድ ጊዜው ዛሬ፣ አሁን መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው:: አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ ኤድስ ልናሸንፈው የምንችል ክፉ ጠላታችን ነውና በርትተን እንዋጋው::

**መልመጃ ፱**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

1. ከሰሀራ በታች ከሚገኙ ሀገራት ቢያንስ ሁለቱን በመጥቀስ ለምን ኤች.አይ.ቪ በፍጥነት እንደሚዛመትባቸው ግለፁ::
2. የኤድስ ጥቃት ድህነትን እንዴት ያስፋፋል?
3. የምሁራንና የሰለጠኑ አምራቾች በገፍ መሞት የሚያስከትለውን ጉዳት በመዘርዘር ግለፁ::

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ዕድገትና ብልጽግና መሠረታቸው ሥራ ሲሆን፤ ሥራ ውጤታማ ሆኖ ለውጥ የሚያመጣው ዜጐች በየተሰማሩበት መስክ ኃላፊነትን በብቃት መወጣት ሲችሉ ነው፡፡ ለልማትና ለማኅበራዊ ዕድገት አንቀሳቃሽ ሞተር የሆኑ ጠንካራ ዜጐች ቃልኪዳናቸውን በማክበር በሚያሳዩት ውጤት በማኅበረሰቡ ዘንድ የታመኑ፣ የተከበሩ በመሆን በአርአያነት ይጠቀሳሉ፡፡ የተሰጣቸውን ኃላፊነት መወጣት ያልቻሉ ደግሞ ራሳቸውንና ማኅበረሰቡን ሲጐዱ ይታያል፡፡

የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን በመጠበቅና በአግባቡ ለጥቅም እንዲውሉ በማድረግ ኃላፊነትን በብቃት መወጣትና ቃልኪዳንን ማክበር ከእያንዳንዱ ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡ የሕልውና መሠረትና የታሪክ አሻራ የሆኑት እነዚህ ሀብቶች የሁሉም ትኩረት እንክብካቤና ጥበቃ ካልተደረገላቸው የሚደርሰው ጥፋት ከፍተኛ ነው፡፡

ቃልኪዳንን ማክበርና ኃላፊነትን በብቃት መወጣት የሚጀምረው ራስን ለቁም ነገር ለማብቃት ፈታኝ ከሆኑ እንደ ኤድስ ካሉ ችግሮች በመጠንቀቅ ነው፡፡ በወረርሽኝ መልክ በመዛመት ላይ ያለው ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ መድኃኒት ያልተገኘለት በመሆኑ ከገዳዩ ቫይረስ ራስን መጠበቅ የዜግነትን ግዴታ ከመወጣት ውስጥ አንዱ ድርጊት መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ የአንድ ሀገር ዋንኛ ሀብት ዜጐቿ በመሆናቸው ለራስም ሆነ ለሀገር አለኝታ ሆኖ ለመገኘት በተለይ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን መዋጋት አማራጭ የሌለው ተግባር ነው፡፡ ስለበሽታው መተላለፊያ ሁኔታዎች ማወቅና መጠንቀቅ፣ ሌሎችም እንዲያውቁና እንዲጠነቀቁ ማድረግ ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ ተግባር መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ ይህን ኃላፊነትና አደራ በሀቀኝነት ለመወጣት ዛሬውኑ ቃልኪዳን ልንገባ ይገባል፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

| | |
|---|---|
| **የእሳት አደጋ፤** | በእሳት ቃጠሎ ምክንያት የሚደርስ ጉዳት፡፡ |
| **ቅላጼ፤** | ዜማ። |
| **ቢዛነት፤** | ስለሌሎች ጥቅም ችግርንና መከራን መቀበል። |
| **ሥነ ልቦና፤** | አዕምሮአዊ ስሜት። |
| **ሁለንተናዊ፤** | ዘርፈ ብዙ፣ ልዩ ልዩ፡፡ |
| **ኢተአማኒነት፤** | አለመታመን። |
| **ቃለአባይ፤** | ውሸታም፣ ቃሉን የማያከብር። |

© MoE, FDR Et... Not to be republi...

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

**I የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ::**

1. ኃላፊነትን በብቃት መወጣት የሚችሉ ዜጎች ታማኝ ሊሆኑም ላይሆኑም ይችላሉ::
2. የልማትና የለውጥ አራማጅ ለመሆን ትምህርትና የኑሮ ሥርዓት ያስፈልጋል::
3. የቃልኪዳን እውን መሆን የሚመዘነው በተግባርና በውጤት ነው::
4. የተፈጥሮ ሀብቶች እንክብካቤና ጥበቃ ባይደረግላቸውም ከገጸ ምድር አይጠፉም::
5. ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ በሰዎች ላይ እንጂ በሀገር ላይ የሚያመጣው ጉዳት እምብዛም ነው::

**II በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ፡፡**

| ሀ | | ለ |
|---|---|---|
| 1. ኢተአማኒነት፣ | ሀ. | በታማኝነት ፍሬያማ ውጤት ማሳየት:: |
| 2. የመንፈስ ጥንካሬና፣ የሥራ ብቃት፣ | ለ. | ስለ ሰዎች ጥቅምና በጎነት ራስን አሳልፎ መስጠት:: |
| | ሐ. | ኃላፊነትን አለመወጣት:: |
| 3. በረሃማነት፣ | መ. | እጽዋትን፣ ደኖችን ማጉልበትና መስኖን መጠቀም |
| 4. ታሪካዊ ቅርስ፣ | ሠ. | የቀደምት ሥልጣኔ አሻራ:: |
| 5. ቤዛነት፣ | ረ. | አሸዋማነት:: |
| 6. ቃልን አለማክበር፣ | | |

**III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ::**

1. በንዝህላልነት አደጋ የሚያደርሱ ሰዎች፤
   ሀ. ፈጣኖች ናቸው፣　　ሐ. የኃላፊነት ድርሻቸውን መወጣት ያልቻሉ ናቸው፣
   ለ. ያልተማሩ ናቸው፣　　መ. ኃላፊነታቸውን የማያውቁ ናቸው።
2. ኃላፊነትን በብቃት መወጣት፤
   ሀ. ግላዊ ጥቅም የለውም፣　　ሐ. ከቃል ኪዳን ጋር አይገናኝም፣
   ለ. የመንፈስ እርካታና የኑሮ ለውጥ ያስገኛል፣　　መ. ለአርአያነት አይጠቅምም::
3. የቱሪዝም ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ፤
   ሀ. ቅርሶችን መሸጥ፣　　ሐ. ደንን አስወግዶ መንገድ መስራት፣
   ለ. የተፈጥሮ ሀብትንና ታሪካዊ ቅርሶችን ጠንቅቆ ማወቅ፣　　መ. የተፈጥሮ ሀብትንና ቀደምት ንብረቶችን ከጥፋት ማዳን::
4. ኤች.አይ.ቪ ቫይረስን ሊያስተላልፉ ይችላሉ የሚባሉት ባህላዊ የሕክምና ድርጊቶች፤
   ሀ. ውልቃት አሽቶ ማስገባት፣　　ሐ. ስብራት መጠገን፣
   ለ. ግርዛትና ግግ መንቀል፣　　መ. ዳማከሴ ማሽተት።
5. የኤድስ ስርጭት ከሰሀራ በታች ባሉ ሀገራት የተስፋፋው፤
   ሀ. ስለ በሽታው ሁኔታ ግንዛቤና ጥንቃቄ ባለመኖሩ፣
   ለ. ሀገራቱ በረሃማነት ስለሚያጠቃቸው፣
   ሐ. የአየር ንብረቱ ለቫይረሱ ተስማሚ በመሆኑ፣
   መ. የተመጣጠነ የምግብ አቅርቦት ባለመኖሩ።

**IV የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::**

1. ሰው ለሀገሩና ለወገኑ ጥቅም የሚከፍለው መስዋዕትነት __________ ተብሎ ይታወቃል::
2. የኤኮኖሚ ዕድገትና የኑሮ ለውጥ የሚመጣው ሁሉም የሥራ ድርሻውን በ__________ሲወጣ ነው::
3. አፈርን ለመጠበቅ፣ የአየር ጠባይ መዛባትን ለማስቀረት__________ወሳኝነት አለው::
4. ዋነኞቹ የኤድስ ቫይረስ መተላለፊያ መንገዶች __________ እና __________ ናቸው::
5. ታሪክ የሌለው ኅብረተሰብ ላለመሆን __________ መንከባከብ ግዴታ ነው::

**V የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡**

1. የኃላፊነት ድርሻን በብቃት መወጣት፣ በግል፣ በማኅበረሰቡ መካከል፣ ሀገርን በተመለከተ የሚያስገኘው ጥቅም ምንድነው ?
2. ታሪካዊነት እንዲቀጥልና በኢትዮጵያዊነት መኩራት እንዲቻል የዜጎች ድርሻ ምን መሆን አለበት?
3. ለሕይወት ዋጋና ክብር የሚሰጠው እንዴት ነው?



© FDRE Ethiopia. Not to be republished

# ምዕራፍ ሰባት

# ጠንካራ የስራ ባህል

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤**

- የሥራንና የጊዜን ክቡርነት ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ/፤
- ስሥራ ዕቅድ አውጥቶ መንቀሳቀስ ተገቢ መሆኑን ታውቃለህ/ታውቂያለሽ፤
- ሕገመንግሥታዊ የልማትና የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎችን ትረዳለህ/ትረጃለሽ፤
- የሙያ ችሎታንና የሙያ ሥነምግባርን ማዳበር ለምርታማነትና ለዕድገት መሠረት መሆኑን ታውቃለህ/ታውቂያለሽ::

## 7.1 ውጤታማ ሥራ፤

### 7.1.1 ጊዜን ሳያባክኑ ጠንክሮ መሥራት፣

✓ ጊዜን ሳያባክኑ ጠንክሮ መሥራት ለሀገር ልማት ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው?

**ጋዜጣ አዟሪው ደራሲ**

ታዋቂው ብዕረኛ ጠንክር ቢርቢራ ከግቢው ውስጥ መኪናውን እያጠበ ባለበት ሰዓት በልጅነቱ የደንበኞቹን መኪኖች እንደምን አሳምሮ ያጥብ እንደነበረና በአጠቃላይም ያለፈበትን ጊዜና እዚህ ደረጃ ለመድረስ ያጋጠመውን ውጣ ውረድ አስታወሰ:: ሁሌም የሚያነበው መጽሐፍ ከእጁ አያጣም:: እናቱ በጧት ተነስተው የሚያቀርቡለትን የስንዴ ዳቦና ትኩስ ሻይ ቀማምሶ ወላጆቹን በመሰናበት ይወጣል:: ማንም ጠንክርን የፈለገ ሰው በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት በር ላይ በየቀኑ ጧት ከሚኮለኮሉት ወጣቶች ተርታ ሊያገኘው ይችላል:: አልፎ አልፎ ከሚቀድሙት ጥቂት ልጆች በስተቀር ወደ ማተሚያ ቤቱ በር ቀድሞ በመድረስ የጀመረውን መጽሐፍ እያነበበ በአንደኛነት ይሰለፋል:: ከመጽሐፍ በስተቀር ብዙም ጓደኛ የሌለው ጠንክር ህይወቱ ከንባብ ጋር በእጅጉ ተቆራኘ:: በዚያች የተራ ጥበቃ ጊዜ እንኳን የሚያጠፋት የጊዜ ሽራፊ አልነበረችም::

በየቀኑ ታትሞ የሚወጣውን አዲስ ዘመን ጋዜጣን፣ ልዩ ልዩ መጽሔቶችንና ሌሎች ጋዜጦችን ይረከባል:: ከዚያም የቋሚ ደንበኞቹ ሱቆችና መስሪያ ቤቶች እስኪከፈቱ ድረስ አራት ኪሎ በሚገኘው ቱሪስት ሆቴል አካባቢ እየተዘዋወረ ሻይ ለሚጠጡ፣ ጫማ ለሚያስጠርጉና ትራንስፖርት ለሚጠብቁ ሰዎች ጋዜጦችንም ሆነ መጽሔቶችን ለአጭር ጊዜ ንባብ ያከራያል:: በመጨረሻም የሥራ ሰዓት ሲደርስ ወደ ደንበኞቹ በመሄድ ጋዜጦችንም ሆነ መጽሔቶችን በጊዜ ያስረክባል:: ከዚያ በኋላ ቀኑን ሙሉ የሚውለው እዚያው አራት ኪሎ አካባቢ ፖስት ካርዶችንና ፖስታዎችን እያዞረ በመሸጥ ነበር::

ቢርቢራ ቢራቢሮ በማለት አብረውት በሚውሉ ጓደኞቹ የወጣለትና በአራት ኪሎ አካባቢ የሚጠራበት ስም ነው። በትምህርት ቤት አብረውት ከሚማሩ ጓደኞቹ በስተቀር ዋና ስሙ ጠንክር እንደሆነ የሚያውቅ አልነበረም:: ጠንክር እንደ ስሙ ሁሉ ስንፍናን የማይወድ ጠንካራ ሠራተኛ በመሆኑ በልጅነት ዕድሜው ደህና ሥራ ለመሥራት የሚያስችለውን ገንዘብ ለማጠራቀም ቻለ:: መቼ ምን መሥራት እንዳለበት የሚያውቀውና የጊዜ ጥቅም የገባው ጠንክር የሥራ ዕቅዱን በጊዜ በመከፋፈል ስለሚጠቀም ያባከነው ጊዜ አልነበረም:: ሥራውን ሠራርቶ የማታ ትምህርቱን ወደሚከታተልበት ትምህርት ቤት ይሔዳል:: ጥቂት ጊዜ ሲያገኝ አይቦዝንም፣ ያነባል::

በእጁ ከሚገቡት ጋዜጦችና መጽሔቶች በተጨማሪ ከመምህራኖቹና ከደንበኞቹ እየተዋሰና እየገዛም የሚያነባቸው መጽሐፍት ቀስ በቀስ ልዩ ስሜት አሳደሩበት። ጠንክር አንድ ቀን ታዋቂ ደራሲ እሆናለሁ ብሎ ተስፋ አደረገ:: እርግጥ ህይወቱ ውጣ ውረድ የበዛበትና ምቾት የጎደለው ቢሆንም ደከመኝ ታከተኝ ሳይል ጠንክሮ በመሥራቱ በእርግጥ ወደተመኘው ቦታ ለመድረስ ቻለ:: "ሥራና ጊዜ" በሚል በመጀመሪያ ካወጣው መጽሐፍ በተጨማሪ ከአራት ያላነሱ ልቦለድና ኢ-ልቦለድ መጽሐፍትን ለንባብ አብቅቷል::

**መልመጃ 1**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ***

1. ጠንክር በልጅነቱ ያሳየው ጥንካሬ በምን በምን ሁኔታ በህይወቱ ላይ ተንፀባርቋል?
2. የጠንክርን የጊዜ አጠቃቀም በአጭሩ ጽፋችሁ ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡
3. ጠንክር ቢርቢራን ዛሬ ለደረሰበት ትልቅ ደረጃ ያበቁትን ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ግለፁ፡፡
4. የጠንክር የልጅነት ጊዜ ውጣ ውረድ የበዛበት ነበር ሲል ምንን ለመግለጽ ነው?

***ጊዜን ሳያባክኑ ጠንክሮ መሥራት*** በግልም ሆነ በጋራ ያለው ጠቀሜታ የጎላ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ ከተለመደው ባነሰ ጊዜ ውስጥ በጥራት ተሠርቶ የሚጠናቀቅ ሥራ ውጤታማ ነው ለማለት ይቻ ላል፡፡ ለጊዜ ልዩ ግምትና ክበሬታ ያለው ሕዝብና ሀገር ጠንክሮ ሠርቶ ለመበልፀግና ካደጉ ሀገሮች ተርታ ለመሰለፍ የሚያግደው ምንም ኃይል አይኖርም፡፡ ሁሉም የሥራ ዓይነት ሊከናወን የሚችለው በጊዜ ውስጥ ስለሆነ ለእያንዳንዷ ደቂቃ ተገቢ ግምት በመስጠት በአግባቡ መጠ ቀም ለግልም ሆነ ለሀገር ታላቅ ባለውለታ መሆን ነው፡፡

አያሌ ብልህ ሰዎች የወጣትነትና የጉልምስና ጊዜ አቸውን በከንቱ ሳያባክኑ በጥንቃቄ ሥራ ላይ በማዋላቸው ራሳቸውንም ሆነ ወገንን የሚጠቅም ታላላቅ ተግባር ለማከናወን ችለዋል፡፡ ጊዜአቸውን በሚገባ በቁምነገር ላይ አውለውታልና በእርጅና ዘመናቸው ህሊናቸውን የሚቆረቁረው አንዳችም ነገር አይኖርም፡፡ ስለዚህ ጊዜን ሳያባክኑ ጠንክሮ መሥራት ራስን ወገንንና ሀገርንም መጥቀምና ማሳደግ ነው፡፡

**መልመጃ 2**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ***

1. ጊዜን ማባከን በምን በምን ሁኔታ ሊገለጽ ይችላል?
2. ለጊዜ የሚሰጥ ልዩ ግምት ከሀገር ብልጽግና ጋር የሚያያዘው እንዴት ነው?

### 7.1.2 አርአያነት ያለውና ለምስጋና የሚያበቃ ሥራ መሥራት ለሀገር ዕድገት የሚኖረው ፋይዳ፣

- ✓ አርአያነት ያለው ሥራ ሲባል ምንን ለመግለጽ ነው?
- ✓ ለምሥጋና የሚያበቃ ተግባር የፈፀሙ ሰዎች በሕዝብ ዘንድ የሚሰጣቸውን ክበሬታ ግለፁ፡፡



ሥዕል 7.1 ከውጤታማ ሯጮቻችን መካከል አንዷ መሠረት ደፋር

**እርጥብ አሩስ፤**

ሕዝብና ሀገርን ወክለው በሩጫ ሜዳ ተከታታይ ድልን ከተቀዳጁት ኢትዮጵያውያን ሯጮች አንዷ ጃለቴ ናት፡፡ በአንድ ወቅት የዓለም አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ታላቅ የሩጫ ውድድር ባዘጋጀበት ጊዜ የበኩር ልጇን ወልዳ አሥራ አምስተኛ ቀኗ ላይ የምትገኝ ርጥብ አራስ ነበረች፡፡ ብዙ መሥራትን እንጂ ብዙ ዕረፍትን የማትሻው ጃለቴ ይህን ለዓለም ታላላቅ ሯጮች የቀረበ ጥሪ በድህረ ገጽ እንዳነበበች ለአሰልጣኛ ስልክ በመደወል የአራስ ቤት ረፍቷን አቋርጣ በውድድሩ ለመሳተፍ እንደምትሻ ነገረቻቸው፡፡

ቦነስ አይረስ ላይ ታሪክ ያስመዘገበችው ጀግናዋ ሯጭ ኪባኪ ላይ በሚደረገው ውድድር የእናት ሀገሯን ስምና ባንዲራ ዳግም ለማስጠራት ጠንክራ ሠራች፡፡ አትሌቷ "አንዲት ሴት ከወሊድ በኋላ ቢያንስ ለሠላሣ ቀናት አልጋ ላይ ማረፍ ይኖርባታል፡፡" የሚለውን አባባል አትደግፍም፡፡ አሰልጣኛም በመገረም የወሊድ ፈቃድ ላይ መሆኗንና ገና አሥራ አምስት ቀኗ በመሆኑ ውድድሩን ችላ መሳተፍ ትችል እንደሆነ ጠየ ቋት፡፡ እሷም በአስቸኳይ ልምምዷን በመጀመር በውድድሩ መሳተፍ እንዳለባት ውሳኔዋን ደግማ አረጋገጠችላቸው፡፡

አሰልጣኛም የአትሌቷን ጊዜ የማይሽረው ጥንካሬ በማድነቅ ስሟ ለውድድር እንዲመዘገብ አደረጉ:: በዚህም መሠረት የጀግናዋ አትሌት የጃለቴ ቦንሳ ስም ከኢትዮጵያውያንና ከዓለም የሩጫ ተወዳዳሪዎች ተርታ ሠፈረ:: ቀጥሎም አሰልጣኛ ባወጡላት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ልምምዷን ጀመረች::

"አራስ ሴት ውጪ ብቻዋን ብዙ መንገድ መጓዝ የለባትም" የሚለውን ልማዳዊ አስተሳሰብ ሰብራ በመውጣት በዓለም የሩጫ መንደር በአሸናፊነት ድል ዳግም ኀልታ ታየች:: እልህ፣ የአሸናፊነት ወኔና የሀገር ክብር ተጣምረው በሰጧት ጥንካሬ ልማደኛዋ አትሌት በዚህ ውድድርም ደረጃዋን አስጠብቃ ማጠናቀቋ ለዓለም ሕዝብ እንደገና ተበሰረ:: ሕዝቧና የሀገሯ መንግሥትም ከፍተኛውን የላቀ ምሥጋና አቀረቡላት::

## ጠልጠያ 3

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ***

1. ከራስ ጥቅም ይልቅ የሀገርን ጥቅም ማስቀደም ሲባል ምን ማለት ነው?
2. ጃለቴ ቦንሣን ታዋቂ ጀግና እንድትሆን ያበቋት ነጥቦች ምን ምን ናቸው?
3. የጃለቴ አሰልጣኝ ያስገረማቸው ጉዳይ ምን ነበር?

**አርአያነት ያለውና ለምሥጋና የሚያበቃ ሥራ መሥራት ለሀገር ዕድገት የሚኖረው ፋይዳ** ከፍተኛ ነው:: የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ በሚያከናውናቸው ተግባራት ራሱን ብቻ ሳይሆን ሀገሩንና ወገኑን የሚጠቅም የሥራ ውጤት ማስመዝገብ አለበት:: በሀገራችንም ሆነ በዓለም ላይ በሠሩት ሥራ ስማቸው ከመቃብር በላይ ህያው ሆኖ የሚኖር ግለቦች በርካታ ናቸው:: እነዚህ ሰዎች ለትውልድ የሚተርፍ በጎ ተግባር በማከናወናቸው አርአያ ለመሆንና በሕዝብና በመንግሥት ዘንድ ምሥጋናና ከበሬታን ለመቀዳጀት ችለዋል:: አርአያነት ያለው ሥራ ለመሥራት ቆርጠን በተነሳን ቁጥር ሀገራችንን ለማገልገል በቂ ጊዜ እናገኛለን::

አንድ ዜጋ ሀገር ከምትጠብቅበት ድርሻና መሥራት ከሚገባው መልካም ተግባር አንፃር ሲታይ በህይወት የሚኖረው ጊዜ አጭር ነው ለማለት ይቻላል:: ይሁን እንጂ ይህን አጭር ጊዜ ሳያባክን በአግባቡ በመጠቀም ታሪክ የማይረሳውና የሚያስመሰግን አኩሪ ሥራ ለመሥራት ካሰበ ውጤታማ የማይሆንበት አንዳችም ምክንያት የለም::

## ጠልጠያ 4

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩባቸው***

1. አንድ ሰው ለአካባቢውም ሆነ ለሀገሩ የሚበጅ ተግባር ሊሠራ የሚችለው እንዴት ነው?
2. አንድ ሥራ አርአያነት ያለውና የሚያስመሰግን ተግባር ነው የሚባለው መቼ ነው?

## 7.2 ሥራን ዕቅድ አውጥቶ መሥራት፤

### 7.2.1 ለሚያከናውኑት ሥራ የጊዜ ሰሌዳ አዘጋጅቶ የመጠቀም አስፈላጊነት፤

- ✓ የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት ለምን ይጠቅማል?
- ✓ የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት ለተማሪ ያለውን ፋይዳ ግለፁ::
- ✓ ሥራን በዕቅድ ከፋፍሎ መሥራት ሲባል ምን ማለት ነው?

**የሻሸቱ ጎጆ**

የጣርማ በር ትምህርት ቤት ተማሪዎች እንደ ሁልጊዜው በዕረፍት ጊዜያቸው የሚያከናውኑት የቤት ጥገናና የቦይ ጠረጋ ዝርዝር ወጥቷል:: መምህር አለማየሁ ተማሪዎቻቸው ዘንድሮም የአንዲትን የዕድሜ ባለፀጋ መኖሪያ ቤት እንዲጠግኑ በመጀመሪያው ዙር ስማቸው ተለጥፎ ነበር:: መምህር አለማየሁ አስቀድመው በተመለከቱት ጥናት መሠረት የእማማ ሻሸቱ ቤት በየዓመቱ ክረምት ላይ ኀርፍና ፍሳሽ እየሔደበት ነዋሪዋን የዕድሜ ባለፀጋ ሲያስቸግሯቸው ቆይቷል:: መምህር አለማየሁ የእማማ ሻሸቱ ቤት ለመጠገን የሚያስችለውን የጊዜ ሰሌዳ ካወጡ በኋላ እያንዳንዱ የቡድን አባል የሚያከናውነው የሥራ ዝርዝርና ተጠሪ ተመድቦለት ውይይት ተደረገ:: የቤቱ ጥገና ክረምት ከመድረሱ በፊት መጠናቀቅ እንዳለበት ከውሣኔ ሀሳብ ላይ ተደረሰ:: ሥራው በተያዘለት ኘሮግራም መሠረት ተጀመረ:: እያንዳንዱ ቡድን በተቻለ መጠን ከታቀደለት የጊዜ ሠሌዳ ባነሰ ጊዜ ሥራውን ለማጠናቀቅ እንደሚጥር ቃል ገባ:: የሥራ ድልድልም ወጣ:: ግማሹ ቦይ ይጠርጋል፣ ግማሹ ድንጋይ ያመላልሳል፣ ግማሹ የቤቱን የጥገና ሥራ ያከናውናል::

ቤት በአጭር ጊዜ ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ጠግነው አስረከቡ፡፡ የትምህርት ቤቱ ገምጋሚ ቡድን በሥፍራው ደርሶ እንደተመለከተው የቤቱ ጥገና የሚያዳግም አልነበረም፡፡ የእማማ ሻሽቱ ቤት የጣራው ክዳን በሚገባ ተስተካክሎ የጎርፍ መውረጃ ቱቦዎች ተጠርገው መግቢያ መውጫቸው በድንጋይ ተደልድሎ የተመለከተው ገምጋሚ አካል በእርግጥም ይህ ቡድን ባወጣው ዕቅድ በመመራትና ጠንክሮ በመሥራት ከተያዘው ጊዜ ቀድሞ ሥራውን ማጠናቀቁ የሚያስመሰግነው እንደሆነ አረጋገጠለት፡፡

## መልመጃ 5

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ***

1. ስለአንድ ሥራ ዕቅድ አውጥቶ መንቀሳቀስ ለምን ይጠቅማል?
2. የጊዜን፣ የዕቅድን የሥራንና የውጤትን ግንኙነት አብራሩ፡፡

**ለሚያከናውኑት ሥራ የጊዜ ሰሌዳ አዘጋጅቶ መጠቀም** ጊዜን ሳያባክኑ ጠንክሮ ለመሥራትና ለጥሩ ውጤት ከማብቃቱም በላይ በሌሎች ዘንድ አክብሮትንና አድናቆትን ያስገኛል፡፡ ሰው ዕውቀቱን፣ ጉልበቱንና ገንዘቡን በአግባቡ ተጠቅሞ በመሥራት ለአካባቢውም ሆነ ለሀገሩ የሚበጅ ተግባር የሚያከናውነው ጊዜውን በአግባቡ ለመጠቀም በዕቅድ ሲመራ ነው፡፡ ጊዜ ሀብታም ና ድሃ ወይም ጥቁርና ነጭ ብሎ ሳይመርጥ ሁሉንም የሰው ልጆች በእኩል የሚያገለግል በተፈጥሮ የተቸረው ሀብት ነው፡፡

ስለጊዜ የሚነገሩ ብዙ ምሳሌአዊ አነጋገሮች ቢኖሩም በተለይ "ጊዜ ወርቅ ነው" የሚለው አባባል ትልቅ መልዕክት ያለውና በሁሉም ዘንድ የተለመደ አባባል ነው፡፡ ወርቅ ምንጊዜም ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው የማዕድኖች ሁሉ ቁንጮ የሆነ በየትኛውም የዓለም ገበያ ዋስትና ያለው የማዕድን ዓይነት ነው፡፡ እንደዚሁ ሁሉ ጊዜ እንደወርቅ ክብር ያለው አክባሪውን የሚያከብር በአንፃሩ ደግሞ ካልተጠቀሙበት ከእጅ የሚያመልጥና የማይመለስ ውድ ነገር ነው፡፡ ሁሉም ነገር የሚሆነው በጊዜ ስለሆነ ስለጊዜ ጠቃሚነት ጥሩ አመለካከት በኖረን ቁጥር እንቅስቃሴአችንን በጊዜ ዑደትና በዕቅድ በመከፋፈል ልንገለገልበት እንችላለን፡፡ አንድ ተግባር በመልካም ውጤት ይጠናቀቅ ዘንድ ሰው ላቀደው ዕቅድ ራሱን በማስገዛት ጊዜን ሳያባክን ጠንክሮ መሥራት ይኖርበታል፡፡

## መልመጃ 6

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ***

1. ጊዜና ወርቅ የተመሳሰሉበት ምክንያት ምንድን ነው?
2. ዕቅድ የሌለው ሥራ ውጤቱ ምን ይሆናል?
3. በትክክል በታቀደ ሥራና ባልታቀደ ሥራ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

## 7.3 ሥራን መናቅና ሳይሰሩ መኖር፤

### 7.3.1 ሥራን መናቅና ሳይሰሩ መኖር በግልና በሀገር ዕድገት ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖ፤

- ✓ *ሥራን መናቅና ሳይሠሩ መኖር ጉዳቱ ምንድን ነው?*
- ✓ *ሥራን መናቅ በግልና በሀገር ዕድገት ላይ ያለው ጎጂ ገጽታ ምን ይመስላችኋል?*

**ጓደኛሞቹ**

ስዩም አዳፍሬ በአንድ የማምረቻ ድርጅት ተቀጥረው የሚሠሩ አብሮ አደግ ጓደኛሞች ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ወጣቶች በዕድሜ ከመቀራረባቸውም በላይ በዚህ ድርጅት ውስጥ ሥራ የጀመሩት በተመሳሳይ ጊዜ ስለነበር በሚገባ ለመተዋወቅ ምቹ ሁኔታን ፈጥሮላቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በሥራ ባህሪ አይቀራረቡም፡፡ ስዩም ሥራ ወዳድ፣ ሰዓት አክባሪና በሥራ ባልደረቦቹ ዘንድ እንደ አርአያ የሚቆጠር ጠንካራ ሠራተኛ ሲሆን አዳፍሬ በተቃራኒው ሥራ የማይወድ፣ ለሥንፍናው አያሌ ምክንያት የሚደረድርና ሳይሠሩ መኖርን የሚመርጥ ደካማ አስተሳሰብ ነበረው፡፡ ስዩም የጓደኛውን ደካማ ጎን ለመቅረፍ የተለያዩ ሙከራዎችን አድርጓል፡፡ አንድ ቀን አጋጣሚው ረዳቸውና በዚህ ልዩነታቸው ላይ ሰፊ ጊዜ ወስደው ተወያዩ፡፡ በውይይታቸው መጨረሻ ስዩም የተገነዘበው ነገር ቢኖር ሁለቱም የሚኖሩት ከቤተሰቦቻቸው ጋር ስለሆነ ሥራ መሥራት እንደማይገደዱ አዳፍሬ አጥብቆ የሚያምን ሰው መሆኑን ነበር፡፡

ይህ አመለካከት ግን ፈጽሞ የተሳሳተ መሆኑን ስዩም ለጓደኛው በምሳሌ አስረዳው፡፡ በዚህም ወጣቱ ለማምረት በሚያስችለው የሥራ መስክ ተሠማርቶ ሀገሩንና ወገኑን በሥራ ማለማት እንደሚጠበቅበትና እንዲያውም ከየትኛውም ዜጋ በበለጠ ወጣቱ ሳይሠሩ መኖርን አጥብቆ ማውገዝና ሠርቶ በማሠራት አርአያ መሆን እንደሚጠበቅበት ተንትኖ አስረዳው፡፡

በጓደኛው ምክር የተመሰጠው ቤሌቻ ቀስ በቀስ ከዚያ የተሳሳተ አስተሳሰብ ራሱን ለማውጣት ታገለ:: ሥራን የመናቅና ሳይሠሩ የመብላት ስህተቱን ለማረም የህሊና ዝግጅት አደረገ:: ወጣቱ ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ ዜጋ የአቅምና የችሎታውን በመሥራት ሀገሩን በማልማት ተግባር ላይ የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንደሚገባው በማመን የበኩሉን ሚና ለመጫወት ታጥቆ ተነሳ::

**መልመጃ 7**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. በአንዳንድ ወጣቶች ላይ የሚታየው ሳይሠሩ የመብላት አስተሳሰብ ከምን የመነጨ ነው?
2. ሳይሠሩ መኖርን ለመገታት መወሰድ በሚገባቸው ነጥቦች ዙሪያ አንድ አንገዳ ጋብዛችሁ ተወያዩ::

*ሥራን መናቅና ሳይሠሩ መኖር በግልና በሀገር ዕድገት ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ* በቀላሉ የሚታይ አይደለም:: በዓለም ደረጃ በድህነታቸው ከሚታወቁት ሀገራት አንዷ ሀገራችን ኢትዮጵያ ናት:: ለዚህ እውነታ አያሌ ምክንያቶችን ለመደርደር ቢቻልም አንዱና ዋናው እንቅፋት ግን ጠንካራ የሥራ ባህል አለመዳበር ነው:: በእያንዳንዱ ዜጋ አዕምሮ ሠርቶ የመኖር ባህል ካልዳበረ በስተቀር ሀገር ከልጆቿ ልታገኝ የሚገባትን የሥራ አስተዋጽኦ ስለምታጣ በዕድገት ልትገሰግስ አትችልም::



ሥዕል 7.2 ማንኛውም ሥራ ለራስና ለሀገር ጠቀሜታ አለው

በእያንዳንዱ ሰው አስተሳሰብ የጠንካራ የሥራ ፍላጎት ሲኖር ሁሉም ዜጋ ሠርቶ ለማደግ ይጣጣራል:: በዚህም በሥራው ሀገሩንና ወገኑን አገልጋይ የሆነ ሕብረተሰብ ይፈጠራል:: ሳይሠሩ የመኖር ጥገኛ አስተሳሰብ ለግለሰብ ህይወትም ሆነ ለሀገር ልማት አደገኛ የሆነ አዝማሚያ ነው:: ሥራን እየናቁና አንዱን ሥራ ከሌላው እያማረጡ ሳይሠሩ ለመኖር መሞከር ያልደከሙበትን የሌሎችን የድካም ዋጋ ነጥቆ እንደ መብላት የሚቆጠር ጎጂ ተግባር ነው::

በየትኛውም የሥራ መስክ በመሠማራት ከራስና ከቤተሰብ አልፎ ሀገርንና ወገንን ማገልገል እየተቻለ አንዳንድ ግለሰቦች አቅም እያላቸው ሳይሠሩ መኖርን በመምረጥ በልመናና በመሳሰሉት አስፀያፊ ተግባራት ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ:: ከዚህም በተጨማሪ አካል ጉዳተኝነትን ከልመና ጋር በማያያዝ መሥራት የሚችሉ እጆችን ለልመና የሚዘረጉ በርካታ ናቸው:: ይህ ሁኔታ ራስንም ሆነ ሀገርን ለከፍተኛ የኢኮኖሚ ውድቀት የሚዳርግ ስለሆነ በጥብቅ ሊወገዝ ይገባዋል:: በምትኩም የሕብረተሰቡን ሠርቶ የመኖር ባህል ከጊዜ ወደጊዜ ይበልጥ ማሳደግ ያስፈልጋል::

**መልመጃ 8**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው::***

1. ሥራን ሳይንቁ ሠርቶ የመኖርን ጠንካራ አስተሳሰብ ለመገንባት ምን መደረግ ይኖርበታል?
2. ሳይሠሩ መኖር ለሀገር ልማት እንቅፋት የሚሆነው እንዴት ነው?
3. የሌሎችን የድካም ዋጋ ነጥቆ መብላት ሲል ምን ማለቱ ነው?

## 7.4 የልማትና የኢኮኖሚ ዓላማዎች፤

### 7.4.1 በሕገመንግሥት የተደነገጉ የልማት፣ የኢኮኖሚና የባህል ነክ ዓላማዎች ለሀገር ዕድገት ያላቸው ጠቀሜታ፣

- ✓ የልማትና የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች ለሀገር ዕድገት ምን ጠቀሜታ አላቸው?
- ✓ የልማትና የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች በሕገ መንግሥት መደንገጋቸው ምን ጠቀሜታ አለው?

የማንኛውም የልማት እንቅስቃሴ ዋና ዓላማና ግብ የዜጎችን መሠረታዊ ፍላጎት ማሟላትና የኑሮ ደረጃቸውን ከፍ ማድረግ መሆን አለበት::

ሀገራችን በየትኛውም መመዘኛ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ስትነፃፀር በአብዛኛው ጥገኛ የሆኑ ኋላቀር አስተሳሰቦች የነገሱባትና አስከፊ ድህነት የሚታይባት ናት:: በዚህም ምክንያት በዕድገት ኋላቀር ከተባሉት ሕዝቦች መካከል በመጨረሻው ተርታ ላይ እንገኛለን:: ይሁን እንጂ ይህን ኋላቀር የዕድገት አቅጣጫ በመለወጥ ወደ ተሻለ ዕድገት ሊያሸጋግሩ የሚችሉ የልማት፣ የኢኮኖሚና ባሕል ነክ ዓላማዎች በፌዴራል ሕገ መንግሥት ውስጥ ተኩረት ተሰጥቷቸዋል:: እነዚህ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች የሚባሉት በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 89 ላይ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል::

1. መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያውያን የሀገሪቱ የተጠራቀመ ዕውቀትና ሀብት ተጠቃሚዎች የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ኃላፊነት አለበት::
2. መንግሥት የኢትዮጵያውያንን የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ለማሻሻል እኩል ዕድል እንዲኖራቸው ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት::
3. የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ እንዳይደርስ መከላከልና አደጋው ሲደርስም ለተጎጂው ዕርዳታ በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ::
4. በዕድገት ወደኋላ ለቀሩ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች መንግሥት ልዩ ድጋፍ ያደርጋል::
5. መንግሥት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን በሕዝብ ስም በይዞታው ሥር በማድረግ ለሕዝቡ የጋራ ጥቅምና ዕድገት እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት::
6. የሀገር ልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በሚዘጋጁበት ወቅት መንግሥት ሕዝቡን በየደረጃው ማሳተፍ አለበት:: የሕዝብንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት::
7. መንግሥት በሀገር ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት የሚሳተፉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት::
8. መንግሥት የሠራተኛውን ሕዝብ ጤንነት፣ ደህንነትና የኑሮ ደረጃ ለመጠበቅ መጣር አለበት::

በኢ.ፌዲ.ሪ ሕገመንግሥት የወጡትን እነዚህን የልማት ነክ አቅጣጫዎች በመከተል ሕዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት፣ ሀገራችን ከተመጽዋችነት የምትላቀቅበትና ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ዕውን የሚሆንበትን የዳበረ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓትን ለመገንባት ይቻላል::

**መልመጃ 9**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው::***

1.የሀገር እድገት እውን የሚሆነው እንዴት ነው?
2.ሀገራችን በዕድገት ኋላቀር ናት የሚባለው ለምንድን ነው?
3.በሕገመንግሥቱ የወጡትን እነዚህን የልማት ነክ ዓላማዎች ዕውን ለማድረግ ከመንግሥትና ከሕዝቡ ምን ይጠበቃል?

በኢ.ፌዲ.ሪ ሕገመንግሥት የወጡት የልማት፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ነክ ዓላማዎች ዋነኛ ግብ ሕዝቡን ለተሻለ የኑሮ ደረጃ ማብቃትና የውጤቱ ተጠቃሚ ማድረግ ነው:: መቼም የሀገሩን እድገትና የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ መሻሻል ለማየት የማይፈልግ ዜጋ የለም:: ሕዝቡ በእነዚህ የልማትና የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች እየተመራ የሚጠበቅበትን ድርሻ ከተወጣ ወደሚታሰበው የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ ይቻላል:: ጠንካራ የሥራ ባህልን በማዳበር ሥራን ባለመናቅና ሳይሠሩ መብላትን በመፀየፍ ሁሉም ጠንክሮ ከሠራ ኢትዮጵያ በልማትና በዕድገት ሌሎች ሀገራት ከደረሱበት ተርታ ለመሰለፍ የሚያግዳት አንዳችም ምክንያት አይኖርም::

**መልመጃ 10**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመሥራት ለክፍላችሁ አቅርቡ***

1. በኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች ምንነት ላይ አንድ የኢኮኖሚ ባለሙያ ጠይቃችሁ አጭር ጽሑፍ አቅርቡ::
2. የልማትና የኢኮኖሚ ዓላማዎችን ሕገመንግሥታዊ ጠቀሜታ አብራሩ::
3. የግለሰቦች ጠንካራ የሥራ ባህል መዳበር ከሀገር ልማት ጋር ያለውን ቁርኝት ግለፁ::

## 7.5 ጠንካራ የሥራ ባህል፤

### 7.5.1 ለጠንካራ የሥራ ባህል መዳበር የሙያ ችሎታና የሙያ ሥነምግባር መዳበር ተገቢነት፣

✓ የሙያ ችሎታና የሙያ ሥነ ምግባር መዳበር ለጠንካራ የሥራ ባህል መዳበር ያለውን አስተዋጽኦ አብራሩ::

**የኩሬ ጠንካራ የሥራ ባህል፤**

አደይ መንደር ዘመናዊ የአበባ ተክልና ምርት የሚከናወንበት ስፍራ ነው::

በዚህ የአበባ እርሻ ተቀጥረው የሚሠሩ በርካታ ሠራተኞች አሉ፡፡ ኩሪ ከእለታት አንድ ቀን በአንድ አጋጣሚ በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የማስታወቂያ ሠሌዳ ላይ አንድ ማስታወቂያ ታነባለች፡፡ ማስታወቂያው በአደይ መንደር አካባቢ እየተስፋፋ በመጣው የአበባ ተክል ሥራ ላይ ለመቀጠር የሚፈልጉ ግለሰቦችን የሚጋብዝ ነበር፡፡ ኩሪ ሥራ ለመፈለግ ወደ ውጭ ሀገር የመሔዱን ሃሳብ እርግፍ አድርጋ በመተው በዚህ ሥራ ተወዳድራ ተቀጠረለች፡፡

ቀድሞውንም ቢሆን ጠንካራ የሥራ ባህል የገነባች፣ ሥራዋን አክባሪ የነበረችው ኩሪ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከጠንካራ ሠራተኞች አንዷ ለመሆን በቃች፡፡ በዚህ ዘርፍ በየወቅቱ የሚሠጣት የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ደግሞ የበለጠ እንድትሠራ ረዳት፡፡ የሙያ ሥነምግባሯን በማዳበር በምትሠራው ሥራ የመንፈስ ብርታትና በራስ የመተማመን ስሜትን ለማጎልበት ቻለች፡፡ ኩሪ በውጤታማ ሥራዋና በሙያ ሥነምግባሯ በዙሪያዋ ላሉት የሥራ ባልደረቦቿ ጥሩ ምሣሌ በመሆን ስሟ በመልካም አርአያነት ለመጠቀስ በቃ፡፡

በአሁኑ ወቅት እሷን የመሳሰሉ ከአራት መቶ ሃምሳ በላይ ሠራተኞችን የሚያስተዳድረው የአደይ መንደር አካባቢ የአበባ ምርት ጣቢያ ይህችን አርአያ የሆነች ሴት ባላት የሙያ ሥነምግባርና የሥራ ፍቅር በብሔራዊ ደረጃ በምርት ጀግንነት እንድትሸለም ማድረጉም ለሌላ ተጨማሪ ድል አነሳሳት፡፡ ጣቢያው ውብ የተባሉ የአበባ ምርቶችን አምርቶ ወደተለያዩ የአውሮፓ ሀገሮች በመላክ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ለማስመዝገብ የበቃው እንደሷ ባሉና ጥሩ የሙያ ሥነ ምግባር ባላቸው ሠራተኞች አማካኝነት ነው፡፡ ኩሪም ሆነች ሌሎች የአበባ ምርቱ ሠራተኞች ጥሩ የሥራ ሞራል ያላቸው መልካም የሙያ ሥነ ምግባርን የተላበሱና ሠርተው መጠቀምን የሚሹ በመሆናቸው የድርጅቱም ሆነ የእነሱ የዕድገት ደረጃ አስተማማኝ በሆነ ጠንካራ የሥራ ባህል ላይ ሊገነባ በቅቷል፡፡

## መልመጃ 11

**በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. የሙያ ሥነምግባር ለሥራ ውጤታማነት ያለው ሚና ምንድን ነው?
2. ኩሪን ለሽልማት ያበቃት ምክንያት ምን ይመስላችኋል?
3. ጠንካራ የሥራ ባህል እንዴት ይገነባል?

የአንድን ሀገር የኢኮኖሚ ዕድገትና የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሳደግ ከሚቻልባቸው መሠረታዊ ነጥቦች አንዱ የህብረተሰቡ **ጠንካራ የሥራ ባህል መዳበርና የሙያ ችሎታና የሙያ ሥነምግባር** የመላበስ አቅም መጎልበት ዋነኞቹ ናቸው፡፡ የሠራተኛውን የሙያ ችሎታና የሙያ ሥነምግባር ሳያዳብሩ ጠንካራ የሥራ ባህልን ለመገንባት የማይቻል ሲሆን፣ ጠንካራ የሥራ ባህል ሳይኖርም ከኋላቀርነትና ከድህነት በመውጣት ወደተሻለችና በኢኮኖሚዋ ወደበለፀገች ሀገር ለመድረስ በፍፁም አይቻልም፡፡ ስለዚህ በየጊዜው የሙያ ደረጃንና ዕውቀትን በማሻሻል በአዳዲስ የማምረቻ መሣሪያዎች ለመጠቀም ሁልጊዜ መማርና መመራመር እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ሁሉም ዜጎች በተሰማሩበት የሥራ መስክ ጠንክረው በማምረት በሙያ ውጤታቸው ሀገራቸውንና ተገልጋዩን ሕብረተሰብ በተገቢው መልክ ለመጠቀም ይችሉ ዘንድ በመጀመሪያ የሙያ ሥነምግባርን ሊላበሱ ይገባል፡፡

ጠንካራ የሥራ ባህልን ከሙያ ችሎታና ከሙያ ሥነምግባር ጋር አጣምሮ የሚጓዝ ሕብረተሰብ የሀገሩን ኢኮኖሚ የማሳደግ አቅም ስለሚኖረው ወደተሻለ የኑሮ ደረጃ ለመድረስ አጋጣሚው ሰፊ ይሆንለታል፡፡

## መልመጃ 12

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ**

1. ጠንካራ የሥራ ባህል መዳበር ከሙያ ሥነምግባር መላበስ ጋር የሚኖረውን ዝምድና አብራሩ፡፡
2. የሙያ ደረጃን ማሻሻል የሚቻለው እንዴት ነው?
3. የሙያ ሥነምግባርን ለማዳበር ከእያንዳንዱ ዜጋ የሚጠበቀው ድርሻ ምንድን ነው?

### 7.5.2 ከሌሎች ለመማር ዝግጁ መሆንና የሌሎችን የሙያ ውጤት ማድነቅ፣



ሥዕል 7.3 የምርት ቦታ ሲጎበኝ

- *ከሥዕሉ ምን ተገነዘባችሁ?*
- *የሌሎችን የሙያ ውጤት ማድነቅ በሥራ ላይ ምን ጠቀሜታ አለው?*

## መምህር ሱልማን እና መምህርት አሰገደች

መምህር ሱልማን እና መምህርት አሰገደች በተለያዩ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ናቸው:: በአንድ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ላይ ከመገናኘታቸው በፊት አይተዋወቁም ነበር:: የሙያ ማሻሻያውን በጋራ ተካፍለው ከጨረሱ በኋላ ተማሪዎቻቸውን ልምድ ለማለዋወጥ ቀጠሮ ይዘው ነበር:: በዚህ መሠረት መምህር ሱልማን አንድ ቀን ተማሪዎቻቸውን በመያዝ ወደ መምህርት አሰገደች ትምህርት ቤት ለጉብኝት ሄዱ:: በጉብኝቱና በገለፃው ብዙ ልምድ አገኙ:: ትምህርት ቤቱ የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ስለነበር ብዙ ተማሪዎችን በእንጨት ሥራ፣ በብረታ ብረት ሥራ፣ በልብስ ስፌት፣ በኤሌክትሪክና በሌሎችም እያሰለጠነ ያስመርቃል::

በትምህርት ቤቱ ውስጥ በእነዚህ የተለያዩ ሙያዎች የሚሰለጥኑ ተማሪዎች ለተሻለ የሥራ ልምድ ወደ ከፍተኛ የማሠልጠኛ ኮሌጆች ይላካሉ:: በዚያም ተገቢውን የሙያ ሥልጠናና የሙያ ሥነምግባር ከተላበሱ በኋላ የየራሳቸውን ሥራ ለማደራጀት የሚችሉበት ሁኔታ እንደሚመቻች ከጉብኙቱ ግንዛቤ አገኙ::

አቶ ሱልማን ተማሪዎቻቸው የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት ማብራሪያ ተሰጣቸው:: እነ አቶ ሱልማን ከተማሪዎች ጋር በመወያየት የራሳቸውም ሙያ በማካፈልና ልምድ በመቅሰም ጥሩ ጊዜ አሳለፉ:: ከዚያም መምህር ሱልማን በእሳቸውና በተማሪዎቻቸው ስም የተሰማቸውን አድናቆት በመግለጽ ስለተደረገላቸው መልካም አቀባበል አመሰገኑ:: በቀጣዩ ጊዜም መምህርት አሰገደችና ተማሪዎቻቸው በእነሱ ትምህርት ቤት ጉብኝት እንዲያደርጉ በመጋበዝ ወደ ትምህርት ቤታቸው ተመለሱ::

**ከሌሎች ለመማር ዝግጁ መሆንና የሌሎችን የሙያ ውጤት የማድነቅ** ባህል መዳበር ያለበት የጠንካራ ሥራ ባህል መሠረት ነው:: ብዙ ሰዎች ሌሎች በሠሩት ሥራ ቢደነቁም እነዚህን ሰዎች በግልጽ የማድነቅና በሥራቸው ይበልጥ እንዲበረታቱ የማደፋፈር ብርታት የላቸውም:: ከዚህም በቀር ወደ ባለሙያዎቹ ቀርበው ለመማር ያላቸውን ፍላጎትና ዝግጁነት በመግለጽ ከነዚህ ግለሰቦች የሙያ ትሩፋት ጥቂት ለመካፈል እንኳን አይፈቅዱም:: እርግጥ ይህ ሁኔታ የሁሉም ሰዎች ባህሪ ነው ለማለት ባይቻልም የብዙ ሰው አመለካከት ስለሆነ መወገዝና መቅረት ያለበት ኋላቀር አስተሳሰብ ነው::

መቼም ሁሉም ሰው ተመሳሳይ ሙያና ችሎታ ሊኖረው አይችልም:: አንዱ መምህር ቢሆን ሌላው አናፂ ሌላው ግምበኛ ወይም የቢሮ ሠራተኛ ሊሆን ይችላል:: እንዲሁም አንዱ ነጋዴ ሌላው መሐንዲስ ቢሆን ሌላው ደግሞ ገበሬ ወይም የሕክምና ባለሙያ ይሆናል:: ሀገር በሥራ ለማደግ የምትችለው የዜጎቿ የተለያየ የሙያ ህብረት ተጋግዞ ለልማቷና ለብልጽግናዋ የዋለ እንደሆነ ብቻ ነው:: እያንዳንዱ ዜጋና የተሠማራበትም ሙያ ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት የሚያበረክተው የጎላ ድርሻ አለ:: ስለሆነም የልማት ድርሻን ይበልጥ ፍሬአማ ለማድረግ ማንኛውም ሙያ ሊከበርና ሊደነቅ ይገባዋል:: ዜጎችም ከባለሙያዎች ትምህርት በመቅሰም ሙያቸውን ሊያሻሽሉና ራሳቸውን ጠቅመው ሀገራቸውን መጥቀም ይጠበቅባቸዋል:: የነቀፌታም ሆነ የማድነቅ አስተያየት ገንቢነት ባለው ሁኔታ ከተሰነዘረ ነገ ያንን ሙያ የበለጠ ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል:: በዚህ ረገድ መንግሥትና ሕብረተሰቡ ሙያንና ባለሙያውን ማበረታታት፣ ተገቢውን ከበሬታ መስጠትና አንዱ ከሌላው የሚማርበትን መንገድ ማመቻቸት አለባቸው::

### መልመጃ 13

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. ሁለቱ መምህራን የጉብኝት ቀጠሮ የያዙት ለምን ነበር?
2. መምህር ሱልማንና ተማሪዎቻቸው ከጉብኝቱ ምን ይጠቀማሉ?
3. አንዱ የሌላውን ሙያ ማየትና ማድነቅ ጥቅሙ ምንድን ነው?

### መልመጃ 14

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ***

1. አንድ ሀገር በሥራ ልታድግ የምትችለው እንዴት ነው?
2. አንድን ሙያ ማድነቅና ከሌሎች ለመማር ዝግጁ መሆን የሚያስገኘው ጠቀሜታ ምንድን ነው?
3. ሙያንና ባለሙያን ከማድነቅ አልፎ ለተሻለ ደረጃ እንዲበቁ መንግሥት ምን ማድረግ አለበት ትላላችሁ?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ጠንካራ የሥራ ባህል፣ የሙያ ችሎታና ሥነምግባር ከሀገር እድገት ጋር አይነጣጠሉም፡፡ የአንድን ሀገር ኢኮኖሚ በጽኑ መሠረት ላይ በመገንባት ሕብረተሰቡ የተሻለ ሕይወት ተቋዳሽ ለመሆን ይችል ዘንድ የዳበረ ጠንካራ የሥራ ባህልና የሙያ ሥነምግባር ያለው ሠራተኛ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ጠንካራ የሥራ ባህል የተላበሰ ሕብረተሰብ ለሙያውና ሙያውን ለሚያከናውንበት የሥራ ጊዜ ከፍተኛ ግምት ስለሚሰጥ በየዘርፉ በሚያበረክተው አስተዋጽኦ ውጤታማ ይሆናል፡፡ ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀምና በሥራ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ሌላው አስፈላጊ ነገር ሥራን በዕቅድ መምራትና ቢቻልም ከተ ወሰነው ባነሰ ጊዜ ውስጥ ውጤታማ ሥራ ማስመዝገብ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች ቀዳሚ ትኩረትም ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ጠንክሮ በመሥራት ራሱንና አካባቢውን እንዲያለማ ሲሆን በተጨማሪም የሀገሩን ሀብት እኩል ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሥርዓት እንዲገነባ ነው፡፡

ጠንካራ የሥራ ባህል ለመገንባት ሌላው አቢይ እርምጃ ሳይሠሩ መኖርን በመፀየፍ መቃወምና ያገኙትን ሥራ ሳይንቁ መሥራት ነው፡፡ የሥራ ትንሽ ወይም ትልቅ የለውም፡፡ አንዱ የሥራ ዘርፍ ከሌላው ጋር ሲነፃፀር በእኩል የሥራ ጊዜና በተ መሣሣይ የዕውቀት ደረጃ ይከናወናል ባይባልም ሥራ በየትኛውም መመዘኛ ለሀገርም ሆነ ለሕዝብ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ የአንድ ሀገር ዜጎች ጠንካራ የሥራ ባህል እያዳበሩ ሥራቸውን ይበልጥ እያጠናከሩና ሙያቸውን እያሻሻሉ በሄዱ መጠን ወደተሻለ የሥራ ደረጃ በመድረስ ከተለመደው የበለጠ ለምሥጋና የሚያበቃና አርአያነት ያለው ሥራ ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡

እንደዚህ ዓይነት የላቀ የሥራ ውጤት የሚያስመዘግቡ ዜጎችን ማበረታታትና ማድነቅ አስፈላጊ ሲሆን ከእነዚህ ባለሙያ ዎች ለመማር ዝግጁ መሆን ሌላው የጠንካራ የሥራ ባህል ገጽታ ነው፡፡ የሰው ልጅ ዛሬ ለሚገኝበት የስልጣኔ ደረጃ ለመድረስ ያበቃውና ቀዳሚውን ጉልህ ድርሻ የሚይዘው በሥራ ያሳየው ከፍተኛ ትጋት ነው፡፡ በዚህም መሠረት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት የተደነገጉትን የልማትና የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች በተግባር ለመተርጎምና ለጠንካራ የሥራ ባህል መዳበር ሁሉም ዜጎች ከፍተኛ ርብርብ ማድረግ አለባቸው፡፡

© MoE, Not to be

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**መቦዘን:-** ሥራ መፍታት::

**ውጣውረድ:-** የኑሮ ፈተና፣ ችግር፣ መከራ::

**ፋይዳ:-** ጥቅም፣ ረብ::

© MoE, FDR Ethi... Not to be republis...

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

### I *የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ::*

1. ማንኛውም ሙያና ሙያተኛ እኩል ግምትና ከበሬታን ማግኘት አለባቸው::
2. የሕብረተሰቡ ጠንካራ የሥራ ባህል በዳበረበት ሀገር ውስጥ የሰው ሠራሽ አደጋዎች ተፅዕኖ መለስተኛ ሊሆን ይችላል::
3. የሀገር ዕድገት የሚመጣው በከፍተኛ የሙያ ዘርፎች መዳበር ብቻ ነው::
4. የራስን ሙያ ማሳደግ እንጅ ከሌሎች ባለሙያዎች ለመማርና እነሱንም ለማድነቅ መሞከር ትክክል አይደለም::

### II *በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ፡፡*

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ማድነቅ፣ | ሀ. ከአንድ በጎ ነገር የሚገኝ በረከት። |
| 2. ብቃት፣ | ለ. የሥራ ድርሻን በአግባቡ አለመወጣት። |
| 3. መቆጨት፣ | ሐ. የመጀመሪያ ልጅ። |
| 4. ትሩፋት፣ | መ. ለአንድ የሥራ ውጤት የሚሰጥ ምስጋና። |
| 5. የበኩር ልጅ፣ | ሠ. በልምድም ሆነ በትምህርት በአንድ ሙያ ላይ የሚገኝ የሥራ ችሎታ። |
| | ረ. ስለተፈፀመና ስላለፈ ነገር መቆርቆር። |

### III *ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ::*

1. የሀገርን ዕድገት በተግባር ለማረጋገጥ እንዲቻል፤
   - ሀ. ሳይሠሩ መኖር አስፀያፊ ልማድ መሆኑ ግንዛቤ ማግኘት ይኖርበታል፣
   - ለ. ሁሉም ዜጎች በእኩልነት የሥራ ዕድል ሊያገኙ ይገባል፣
   - ሐ. የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች ወደተግባር መለወጥ አለባቸው፣
   - መ. ሁሉም መልሶች ሊሆኑ ይችላሉ።
2. አንድ ዜጋ አርአያነት ያለው ተግባር ፈፀመ ለማለት፤
   - ሀ. የሀገሩን፣ የሕዝቡንና የባንዲራውን ስም የሚያስጠራና የሚያኮራ ተግባር መፈፀም አለበት፣
   - ለ. የእርዳታ ድርጅት ማቋቋም አለበት፣
   - ሐ. በአትሌቲክስ ውድድር መሳተፍ አለበት፣
   - መ. ስሙ በሬዲዮና በጋዜጣ ቶሎ ቶሎ መጠራት አለበት።
3. በሀገራችን ውስጥ ጠንካራ የሥራ ባህል በፅኑ መሠረት ላይ ይገነባ ዘንድ፤
   - ሀ. ህብረተሰቡ ስለ ሥራ ያለው አስተሳሰብ በተሻለ ደረጃ መገንባት አለበት፣
   - ለ. ሥራን የመናቅ ጎጂ ባህሪና የሴትና የወንድ የሚል የሥራ ክፍፍል መወገድ አለበት፣
   - ሐ. የሙያ ችሎታና የሙያ ሥነምግባር መጣመር አለባቸው፣
   - መ. ሁሉም መልሶች ሊሆኑ ይችላሉ።
4. የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች መነሻ፤
   - ሀ. ሕብረተሰቡን የሀገሪቷ ሀብት እኩል ተጠቃሚ ለማድረግ ነው፣
   - ለ. በእድገት ኋላ ቀር ለሆኑ ብሔር ብሔረሰቦች ልዩ ድጋፍ መስጠት ነው፣
   - ሐ. የኢትዮጵያውያንን የኢኮኖሚ ሁኔታን ማሻሻል ነው፣
   - መ. ሁሉም መልሶች ናቸው።
5. መወገድ ካለባቸው የሀገራችን ማህበራዊ ችግሮች አንዱ፤
   - ሀ. ሳይሰሩ መኖርንና ልመናን እንደገቢ ምንጭ የመቁጠር ጎጂ አስተሳሰብ፣
   - ለ. የሌሎችን ሙያ ማድነቅና ከሌሎች ለመማር ዝግጁ መሆን፣
   - ሐ. የሥራ ትጋት፣
   - መ. ሁሉም መልሶች ሊሆኑ ይችላሉ።

### IV *የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::*

1. __________ ሙያንና ባለሙያን ለተሻለ ውጤት ያበቃል::
2. አንድን ሥራ በታሰበው ጊዜ ለማጠናቀቅ በመጀመሪያ _______ ማዘጋጀት ያስፈልጋል::

### V *የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡*

1. የሥራ ትንሽ /ትልቅ የለውም ሲባል ምን ማለት ነው?
2. ጥገኝነት በምን በምን መልክ ሊገለጽ ይችላል?
3. ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ሲባል ምን ማለት ነው?


# ምዕራፍ ስምንት
# ራስን መቻል

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤**

- ራስን ከማንኛውም ዓይነት ጥገኝነት ማላቀቅና ለራስ ክብር መስጠት የሚኖረውን ጠቀሜታ ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ፣
- የኮንትሮባንድ ንግድን ጉጂነት ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ፣
- በራስ የመተማመን አስፈላጊነትን ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ፣

## 8.1 ከጥገኝነት መላቀቅ፤

### 8.1.1 ከጥገኝነት ለመላቀቅ ለራስ ክብር መስጠት፣



ስዕል 8.1 አካል ጉዳተኝነት ራስን ከመቻል አያግድም

- *ለራስ ክብር መስጠት ከበላይነት ስሜት በምን ይለያል?*

አቶ ስንታየሁ ተሻለ ይባላል፡፡ የአካል ጉዳተኛ ነው፡፡ ሁለት እጆቹ ምንም ነገር መስራት የማይችሉ ናቸው፡፡ ሁለት እግሮቹም ቆመው መራመድ አይችሉም፡፡ ስለዚህ ከቦታ ቦታ ለመዘዋወር እንደተቀመጠ እየተንፏቀቀ ይሄዳል፡፡ ወላጆቹ ለምኖ ከመብላት ሌላ እድል ይኖረዋል ብለው ስላላሰቡ እንዲማር ወደ ትምህርት ቤት አላኩትም፡፡ ከአምስት ዓመቱ ጀምሮ ለልመና ወደ ጐዳና ወጣ፡፡

እድሜው እየጨመረ ሲሄድ ግን “እኔ ሰርቼ ለመብላት ምን ያንሰኛል?” የሚል ጠንካራ እምነት በውስጡ ማንሰራራት ጀመረ፡፡ ጤነኛ የሆኑ ሰዎች እንኳ አካላቸውን እያቀሳሰሉ ለልመና በሚወጡባት በዚችው ሀገራችን ውስጥ ስንታየሁ ግን ራሱን አከበረና ልመናን እና ጥገኝነትን ተጸየፈ፡፡ መራመድ እንኳ የማይችሉ እግሮቹን አሰልጥኖ እንደ እጅ እየተጠቀመ ቤተሰቦቹን በስራ ማገዝ ጀመረ፡፡ ከአደገበት መንደሩ ወጥቶ የተሻለ እድል ያስገኙልኛል ወደሚላቸው ከተሞች ኮበለለ፡፡

በመጀመሪያ ሬዲዮና ስዓት ይጠግን ከነበረ አንድ ሰው አጠገብ እየተቀመጠ በማስተዋል ሬዲዮና ስዓት የመጠገን ችሎታ አዳበረ፡፡ ከዚያም በመጀመሪያ ሰውየውን እያገዘ መኖር ጀመረ፡፡ ቀጥሎም በራሱ እየሰራ ገንዘብ ማግኘት ችሎ ነበር፡፡ ሆኖም የረባ መጠለያ ስላልነበረው የመስሪያ እቃዎቹን ሌቦች ዘረፉበት፡፡ እሱ ግን ተስፋ ሳይቆርጥ ጣውላ እየገዛና መንገድ ላይ የወዳደቁ ምስማሮችን እየሰበሰበ አካል ጉዳተኞች ከቦታ ቦታ የሚዘዋወሩበት ኩሽኔታ መስራት ጀመረ፡፡

አሁን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለስራ የተመቻቸ ቦታ ሳይኖረው በጥረቱ ከጥገኝነት በመላቀቅ ትዳር መስርቶ አራት ልጆችን አፍርቶ በተጨማሪም አንዲት የዘመድ ልጅ ጨምሮ በድምሩ ሰባት ቤተሰብ ያስተዳድራል፡፡

**መልመጃ 1**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ስንታየሁ ከጥገኝነት ለመላቀቅ ያነሳሳው ምክንያት ምንድን ነው?
2. በአካባቢያችሁ አካል ጉዳተኛ ሆነው ግን ራሳቸውን ለመቻል ጥረት የሚያደርጉ ሰዎችን በመፈለግ ከጥገኝነት መላቀቅ የሚፈጥረውን ስሜት ለማወቅ ተወያዩ፡፡
3. እናንተስ ለራሳችሁ ክብር ትሰጣላችሁ? በምን ድርጊቶቻችሁ ይገለጻል?

ለራስ ክብር መስጠት ማለት በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ራስን አሳንሶ አለማየት እና የራስን ተገቢ ቦታ ማወቅ ነው፡፡ ማንነትን አውቆ ያንኑ ማንነት ተቀብሎ በትምህርትና ከሌሎች ጋር በሚኖር ግንኙነት ራስን በማሻሻል አቅምን ሙሉ በሙሉ መጠቀም እና የበለጠ ብቁ ለመሆን ጥረት ማድረግ ለራስ ክብር የመስጠት መገለጫ ነው፡፡ ለራሳቸው ክብር የሚሰጡ ሰዎች ሀሳባቸውን በነጻነት ይገልጻሉ፡፡

ብዙ ጊዜ የሚያውቁትን ለማሳወቅም ዝግጁ ናቸው፡፡ በዚህ መሠረት በኢኮኖሚና በማህበራዊ ግንኙነታቸው ራሳቸውን የቻሉ እና በራሳቸው የሚተማመኑ ናቸው፡፡ ለራሳቸው ክብር የሚሰጡ ሰዎች ጥገኛ እና ተመጽዋች መሆንን አጥብቀው ይጠላሉ፡፡ ምክንያቱም የሚያከብሩትን ማንነታቸውን ዝቅ ያደርግባቸዋል፡፡ ከላይ ያነበባችሁት የስንታየሁ ታሪክም ይኼንን ሁኔታ በግልጽ የሚያሳይ አብነት ነው፡፡

**መልመጃ 2**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ለራሳቸው ክብር የሚሰጡ ሰዎችን ባህሪ ግለጹ፡፡
2. ለራሱ ክብር የሚሰጥ ሰው ስህተት ቢሰራና ቢነገረው ምን የሚያደርግ ይመስላችኋል? ለራሳቸው ክብር የሚሰጡ ሰዎች ልመናን እና ምጽዋትን ለምን ይጠላሉ?

### 8.1.2 ከጥገኝነት በመላቀቅ ራስን መቻል፣

- ✓ ከጥገኝነት መላቀቅ ማለት ምን ማለት ነው?
- ✓ ራስን መቻል ማለት ምን ማለት ነው?

**በድሉ**

አምሳለ ገነት በምትባል መንደር ውስጥ በድሉ የሚባል ልጅ ይኖር ነበር፡፡ ወላጆቹ በልጅነቱ ስለሞቱበት አንድ ባለፀጋ ወደ ቤታቸው ወሰዱት፡፡ ከዚያ በኋላ በድሉ ሌሎች በልተው ያስተረፉት ምግብ እየተሰጠው እና መኝታውም ማድቤት ውስጥ ወለል ላይ ሰሌን ተነጥፎለት መኖር ጀመረ፡፡ በድሉም የጥገኝነት ስሜት ስለሚሰማው የሰጡትን ተቀብሎ ይበላል ሲመቱት እንኳን አልቅሶ ዝም ይላል፡፡

አንዳንድ በጎረቤት ያሉ ሰዎች ይኸንን በበድሉ ላይ እየደረሰ ያለውን በደል ሲያዩ "ለምን ከቤት ወጥተህ አትጠፋም?" እያሉ ይመክሩት ነበር፡፡ እሱ ግን "ከዚህ ቤት ወጥቼ ብጠፋ በረንዳ አዳሪ ሆኜ ልቀር እችላለሁ፡፡ ትምህርቴም ይቋረጥብኛል፡፡ ስለዚህ ያለሁበትን ችግር በትዕግስት ተቋቁሜ ጎበዝ ተማሪ መሆን አለብኝ፡፡ ከተማርኩ ከጥገኝነት በመላቀቅ ራሴን እችላለሁ" እያለ ያስብ ነበር፡፡ እንዳሰበው ትምህርቱን ጠንክሮ ተማረ፡፡ ዩኒቨርስቲ ገብቶ በከፍተኛ ውጤት ተመረቀና ሀኪም ሆነ፡፡ ስራ ይዞ ወደሌላ ራቅ ወዳለ አካባቢ ሄደ፡፡

ከዚያ በኋላ ለእረፍት ወደ አምሳለ ገነት መንደር ሲሄድ ንፁህ መኝታ ቤት ይዘጋጅለት ጀመር፡፡ ምግብም የሚፈልገው ዓይነት ይሠራለታል፡፡

በራሱ ስለሚተማመን ለአሳዳጊዎቹ የሚሰጣቸውን ክብር ሳያጓድል ትክክል የሆነውን ነገር ግን ያለፍርሀት ይገልጽ ጀመር፡፡ በእኩልነት ስሜት አብሮዋቸው ቁጭ ብሎ ይወያያል፡፡

**መልመጃ 3**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. አንድ አወያይና አንድ ፀሀፊ ምረጡ፡፡ በመቀጠልም በድሉ እንዴት እራሱን እንደ ቻለና ከጥገኝነት ስሜት እንደተላቀቀ ተወያዩ፡፡
2. በድሉ አንዳንድ ጉረቤቶቹ እንደመከሩት ከአሳዳጊዎቹ ቤት ወጥቶ ቢጠፋ ሊያጋጥሙት ይችሉ የነበሩትን ችግሮች በምሳሌ በማስደገፍ እየገለፃችሁ ተወያዩ፡፡

ራስን መቻል እና ከጥገኝነት መላቀቅ፣ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው፡፡ ማንኛውም ሰው ያለውን አቅም እና ያገኘውን አጋጣሚ ተጠቅሞ በመስራት ራሱን ለመቻል ከወሰነ የሚያቅተው ነገር አይኖርም፡፡ እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባ ነገር አቅምን እና አጋጣሚዎችን ማወቅ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው ድንገት ተነስቶ ዛሬ በዓለም የማራቶን የሩጫ ውድድር አሸናፊ መሆን እችላለሁ ወይም ምህንድስና ስራ ላይ መስራት እችላለሁ ብሎ ቢወስን ጉም እንደመዝገን ይሆንበታል፡፡ ምክንያቱም በዓለም የማራቶን የሩጫ ውድድር ለማሸነፍ ሆነ የምህንድስና ስራን ለመስራት በቅድሚያ የሚያስፈልጉት ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ በሩጫ ውድድር ለማሸነፍ ሰውነትን ማጠንከር፣ ጤንነትን ማረጋገጥ፣ ስልጠና መውሰድ እና ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ መሀንዲስ ለመሆንም በቅድሚያ በሙያው ተገቢውን ትምህርት መማር እና የትምህርት ማስረጃ መያዝ ያስፈልጋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ማንም ሰው ጥረት ካደረገ፣ ያገኘውን አጋጣሚ ከተጠቀመ እና የሚያጋጥሙትን ችግሮች በዘዴ እና በትእግስት ከተወጣ ካሰበው ነገር ላይ መድረሱ አይቀርም፡፡ በድሉ ከጥገኝነት ተላቆ ራሱን ለመቻል ባለፀጋ አሳዳጊ የማግኘቱን አጋጣሚ በአግባቡ ተጠቅሞበታል፡፡ ብዙ ችግሮችንም በትዕግስት አሳልፎ አል፡፡ ስለዚህም ከጥገኝነት ተላቆ ራሱን ቻለ፡፡

ከጥገኝነት የተላቀቀ ሰው ነፃ አስተሳሰብ ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ የበለጠ ለመስራት እና የተሻለ ህይወትን ለመኖርም ይነሳሳል፡፡ ተሸማቃቂ ስለማይሆንና በሌሎችም ይሁንታ ስር ስለማይኖር አዳዲስ ሀሳቦች ለማፍለቅ አቅም ያለው መልካም ዜጋ ይሆናል፡፡

**መልመጃ 4**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ራስን ለመቻል የሚያስፈልጉትን ነገሮች በዝርዝር ግለፁ፡፡
2. ራስን መቻል እና ከጥገኝነት መላቀቅ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው ማለት ምን ማለት ነው?
3. አቅምን እና ችሎታን ማወቅ ማለት ምን ማለት ነው? በምሳሌ አያስደገፋችሁ ግለፁ፡፡

### 8.1.3 ከጥገኝነት መላቀቅ ለኢኮኖሚያዊ፣ ለማህበራዊ ዕድገትና ለመልካም ዜጋ ግንባታ የሚያደርገው እገዛ፣

✓ ከጥገኝነት መላቀቅ ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ዕድገት ምን ያግዛል?

**ጀርመን ከወደቀችበት አዘቅት እንዴት መውጣት ቻለች?**

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከተሳተፉ ሀገሮች መካከል አንዷ ጀርመን ነበረች፡፡

በዚህ የጦርነት ወቅት ሀገሪቱ በከፍተኛ ደረጃ ወድቃ ነበር፡፡ የፀረ ናዚ ኃይሎች ድብደባና የናዚዎች የራሳቸው "ከኛ በኋላ ሰርዶ አይብቀል" ፈሊጥ ተደማምረው የሀገሪቱን መሠረተ ልማት አውታሮች፣ ፋብሪካዎች ህንፃዎች እና ቤቶች በአብዛኛው አውድሞት ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት በጦርነቱ መገባደጃ ላይ በርካታ ህዝብ በእርዳታ እና በምፅዋት የሚኖርበት ሁኔታ ላይ ሊወድቅ ችሏል፡፡

ሆኖም በዚህ ወቅት ከጥገኛነት አስተሳሰብ የተላቀቁ እና ራሳቸውን የመቻል ከፍተኛ ፅናት ያላቸው ዜጎች ብቅ ማለት ቻሉ፡፡ የሀገራቸውን አጠቃላይ ዕድገት ለማፋጠን በከፍተኛ ስሜት መንቀሳቀስ ጀመሩ፡፡

ስለዚህም ጦርነቱ ባለቀ በአስር አመት ውስጥ ጀርመን በነዚህ ዜጎቿ ጥረት ከነበረችበት

ጠቅላላ ውድመት በመላቀቅ ጠንካራ ኢኮኖሚ ያዊና ማህበራዊ ህይወት ለመመስረትና በአውሮፖ ውስጥ ከፍተኛ ኢኮኖሚ ያላት ሀገር ለመሆን በቃች፡፡ ይህ የጀርመኖች ተአምር እየተባለ የሚገለፀው ሁኔታ ሊከሰት ከቻለባቸው መንገዶች አንዱና ዋናው ከጥገኝነት አስተሳሰብ የተላቀቁ እና ለራሳቸው ክብር የሚሰጡ ጠንካራ ዜጐች ስለነበሯት ነው፡፡

**ጠይጠቓ 5**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. የጀርመን ዜጎች ሀገራቸው ገብታበት ከነበረው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ውድቀት ማውጣት የቻሉት እንዴት ነው? ከጥገኝነት መላቀቅ ለዜጐች ለራሳቸውም ሆነ ለሀገር የሚኖረውን ፋይዳ እየገለጻችሁ ተወያዩ፡፡
2. እኛስ ኢትዮጵያውያን ሀገራችንን በዓለም ደረጃ ከፍተኛ ቦታ እንዲኖራት ለማስቻል ምን ማድረግ ይጠበቅብናል? አንድ አወያይና አንድ ፀሀፊ ምረጡና በጥልቀት ተወያዩና የተነሱ ነጥቦችን በማስታወሻ ደብተራችሁ ጻፉ፡፡

የአንድ ሀገር ዕድገትና ብልጽግና የሀገሪቱ ዜጐች የአስተሳሰብ እና የአሰራር ድምር ውጤት ነው፡፡ ስለዚህ ከጥገኝነት አስተሳሰብ ተላቀው በራሳቸው የሚተማመኑ ጠንካራ እና ታታሪ ዜጐች ያሏት ሀገር በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ህይወት የላቀ ደረጃ ላይ መድረስ ትችላለች፡፡ እነዚህ ዜጐች ከጥገኝነት በመላቀቅ ራሳቸውን ለመቻል የሚኖራቸው ቁርጠኝነትና ፅናት ራሳቸውን ከኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ጥገኝነት ነፃ ያደርጋቸዋል፡፡ ድምር ውጤቱም ለሀገሪቷ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገትን ያመጣል፡፡

አንድ ሀገር ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ስላላት ብቻ መልማት አትችልም፡፡ ለልማት መሠረታዊ ነገር ከጥገኝነት አስተሳሰብ የተላቀቁ ዜጐች መኖራቸው ነው፡፡ ከጥገኝነት ተላቀው ራሳቸውን ለመቻል የሚጥሩ ሰዎች በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥም እንኳ አሸንፈው በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ጉዳዮች ደረጃቸውን ማሳደግ ይችላሉ፡፡ የጀርመን ዜጐች የሰሩት ተአምርም የዚህ እውነታ አብይ መገለጫ ነው፡፡

በሌላ በኩል በሀገር ደረጃ ከጥገኝነት መላቀቅ ለሉአላዊነት መከበር ዋና መሠረት ነው፡፡ በሌሎች ሀገራት ብድርና እርዳታ ወይም በጥገኝነት የሚኖር ሀገር ሉአላዊነቱ አደጋ ላይ የወደቀ ነው፡፡ ምክንያቱም ብድሩንና እርዳታውን በማቆም ሀሣባቸውን ለመጫን ሊንቀሳቀሱ ስለሚችሉ ብዙ ጊዜ ሉዐላዊነትን ሊፈታተኑ ይችላሉ፡፡

ባጠቃላይ ከጥገኝነት አስተሳሰብ የተላቀቀ ህብረተሰብ ራሳቸውን የቻሉና በራሳቸው የሚተማመኑ፣ ጥገኝነትን የሚፀየፉ መልካም ዜጐችን ማፍራት ይችላል፡፡

በምላሹም መልካም ዜጐች የሀገራቸውን ኢኮኖሚና ማህበራዊ ደረጃ ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

### 8.1.4 ኮንትሮባንድ እና የጥገኝነት ስሜት፣

✓ **የኮንትሮባንድ ንግድ በሀገር ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ህይወት ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ምንድን ነው?**



ሥዕል 8.2 የኮንትሮባንድ ንግድ የሀገር እድገት ፀር ነው

### ኮንትሮባንዲስቱ ፈለቀ

ፈለቀ በኮንትሮባንድ ንግድ ላይ ተሰማርቶ ሁልጊዜ በስጋት እና በጭንቀት ይኖራል፡፡ ዕቃዎችን ደብቆ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የጉምሩክ ኬላ ላይ ለሚሠሩ ሠራተኞች ጉቦ ይከፍላል፡፡ ሆኖም አንድ ቀን ዕቃውን ደብቆ ለማሳለፍ የሚያደርገው ጥንቃቄ ሁሉ ከሽፎ እጅ ከፍንጅ ከተያዘ ከፍተኛ የገንዘብ እና የእስር ቅጣት እንደሚያስከትልበት ስለሚያውቅ ይሰጋል፡፡ ባለቤቱ ወ/ሮ አለምነሽ እና ልጆቻቸው በጭንቀት ውስጥ ይኖራሉ፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን ወ/ሮ አለምነሽ እና ልጆቻቸው ተመካከሩና ፈለቀን ለውይይት ጠሩት፡፡ በውይይቱ ላይ በተለይም ልጆቹ በሥነዜጋ እና ሥነምግባር ትምህርታቸው ላይ የተማሩትን በማገናዘብ ኮንትሮባንድ የጥገኝነት አስተሳሰብ ውጤት መሆኑን ገለጹለት፡፡ ፈለቀም በኮንትሮባንድ ንግድ ላይ በመሰማራቱ ሀገርን እና ህዝብን እየጐዳ መሆኑን በመግለጽ አምርረው ነገሩት፡፡ ቤተሰቡም በጭንቀት እና በስጋት ውስጥ መኖራቸውን፣ እሱም ጉቦ በመክፈል እና ዕቃዎች ሲወረሱበትም ብዙ ገንዘብ በመክሰር ቤተሰቡ የተሻለ ህይወት መኖር እንዳልቻለ በግልጽ ተወያዩ፡፡ በውይይታቸው ሂደት የኮንትሮባንድ ንግድ ኮንትሮባንዲስቱን፣ መንግሥትንና ህዝቡን የሚጐዳ እንጂ ማንንም ተጠቃሚ የማያደርግ መሆኑን ተግባቡ፡፡ በመጨረሻም አቶ ፈለቀ ይኼንን የወንጀል ድርጊት እንደሚያቆም ቃል ገባ፡፡

የኮንትሮባንድ ንግድ በዓለም አቀፍ ደረጃ የህዝቦችን ሰላም፣ ጤና እና ማህበራዊ ህይወት በማናጋት ላይ ይገኛል፡፡ በተለይም በአደጉት ሀገራት የአደንዛዥ እፅና የረቀቁ የጦር መሣሪያዎች ዝውውር ላይ በማተኮር በሀገራት ላይ ከፍተኛ ስጋትን በማስከተል ላይ ነው፡፡

በሀገራችንም የኮንትሮባንድ ንግድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ ይገኛል፡፡ ኮንትሮባንዲስቶችም በዘመናዊ የጦር መሳሪያ እና የመገናኛ ዘዴዎች እየታገዙ ሀይላቸውን በማጠናከር በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው፡፡ ከዚህም ባሻገር ስለ ኮንትሮባንድ ንግድ በቂ ግንዛቤ የሌለውን የህብረተሰብ ክፍል በማሳሳት በትንሽ ጥቅም እየደለሉ በስፋት በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው፡፡ በዚህ ሁኔታም ሀገራችንን ካለችበት የድህነት አዘቅት ለማውጣት በሚደረገው የልማት ስራ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማሳደር ላይ ይገኛሉ፡፡

የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ በሀገራችን የምስራቅ አካባቢዎች በከፍተኛ ደረጃ ይካሄዳል፡፡ አብዛኛው የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች፣ የተለያዩ አዳዲስ አልባሳት፣ ሽቶዎች፣ የተለያዩ የመዋቢያ እቃዎች ወዘተ በዚህ መስመር የሚገቡ ናቸው፡፡ በወጪ ኮንትሮባንድም በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ እንስሳት፣ ጫት፣ ቡና፣ ጥራጥሬ፣ እህል፣ ቆዳና ሌጦ ወዘተ ወደ ውጪ እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ ሌላው ኮንትሮባንድ ንግድ በስፋት የሚካሄድባቸው ቦታዎች ሰሜን እና ደቡብ ምስራቅ የሀገራችን አካባቢዎች ናቸው፡፡ መጠኑ አነስተኛ ቢሆንም ይህ ህገወጥ ተግባር በሌሎችም የሀገራችን ክፍሎች ይካሄዳል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ለሀገር እድገት እንቅፋት የሆኑትን ኮንትሮባንድንና የንግድ ማጭበርበርን በተጠናከረ ሁኔታ ለመከላከልና ግብር እና ታክስን በአግባቡ ለመሰብሰብ እንዲቻል በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው፡፡ ከነዚህ ስራዎች መካከል የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ሀገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣንና የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን አንድ ላይ እንዲዋሀዱ ተደርገው የገቢዎችና የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን መስሪያ ቤት በአዋጅ ተቋቁሟል፡፡

**መልመጃ ፮**

? ***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. አንድ አወያይ እና አንድ ፀሐፊ ምረጡ እና በኮንትሮባንድ ንግድ ማንም ተጠቃሚ አይሆንም በሚለው ሀሳብ ላይ ተወያዩ እና ድምዳሜ ላይ ድረሱ፡፡
2. በአቅራቢያችሁ የሚገኝ ኮንትሮባንድን በመከላከል ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ወደክፍላችሁ ጋብዙ እና ስለኮንትሮባንድ አጠቃላይ ሁኔታ ተወያዩ፡፡

በዚህ መስሪያ ቤት ውስጥ ኮንትሮባንድን መከላከል የሚያስችል "ብሔራዊ የፀረ ኮንትሮ ባንድ እና የጉምሩክ ንግድ ማጭበርበር ስት ራቴጂ" ተነድፏል፡፡ የዚህ ስትራቴጂ ዋና ግቦች ኮንትሮባንድንና የንግድ ማጭበርበርን በማስወገድና ህገወጥ ንግድን በመግታት ኢኮኖሚው ሊያመነጨው የሚችለውን የጉም ሩክ ቀረጥና ታክስ በመሰብሰብ የሀገራችንን ልማት መደገፍ ነው፡፡

## መልመጃ 7

❓ ***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡ አንድ አወያይና አንድ ፀሀፊ ምረጡ፡፡ በመቀጠልም፣***

1. ኮንትርባንድ ንግድ በአንድ ሀገር ህዝብ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ህይወት ላይ የሚያደ ርሰውን ጉዳት ግለጹ፡፡
2. ኮንትሮባንድን ስመከላከል በበኩላችሁ ማድረግ የሚጠበቅባችሁን እየዘረዘራችሁ ተወያዩ እና ድምዳሜ ላይ ድረሱ፡፡

## 8.2 በራስ መተማመን፣

### 8.2.1 በራስ የመተማመን ስሜትን የማዳበር አስፈላጊነት፣

- ✓ በራስ መተማመን ምን ይጠቅማል?
- ✓ በራስ የመተማመን ስሜትን ለማዳበር ምን ማድረግ ይገባል?

**አይን አፋር**

ጉበዝ በርቺ ማለት መጥቀሙን ሳያውቁ፣
አሳደጉኝና ስህተቴን አጉልተው እያሸማቀቁ፡፡
ስናገር ብሳሳት ስሰራ ቢበላሽ፣
የሚል ፍርሃት ሰብሮኝ እድገቴ ሲኮላሽ፣
ቀና ብየ ሳላይ መንፈሴን አንቅቼ፣
ራሴን ሳልችል ቀረሁ በማውቀው ሰርቼ፡፡
እየተሸማቀቅሁ መድፈር እያቃተኝ አንገት በደፋሁኝ፣
ይጠቅመኝ ይመስል ጨዋ ዝምተኛ አይን አፋር ተባልኩኝ፡፡
አይን አፋር መሆኑ ኋላ አስቀርቶኛል አስወግ ደዋለሁ፣
በራሴ ዕምነት ኖሮኝ ደፋር እሆናለሁ፡፡

## መልመጃ 8

❓ ***በግጥሙ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ዐይን አፋር የሚያሰኙ ባህሪያትን ግለጹ፡፡
2. አይን አፋር በመሆን የሚደርሰውን ጉዳት እየዘረዘራችሁ ተወያዩ እና ድምዳሜ ላይ ድረሱ፡፡

በራስ የሚተማመን ሰው ለመሆን ተወስኖ የተቀመጠና የተመረጠ አንድ ልዩ ወይም ብቸኛ እና ስኬታማ መንገድ የለም፡፡ እንደ ምንኖርበት ህብረተሰብ ባህል፣ አመለካከት፣ የትምህርት ደረጃና ጊዜ ወዘተ ይወሰናል፡፡ ከዚህም ባሻገር በራስ መተማመን በየጊዜው እየዳበረ የሚሄድ እንጂ በተወሰነ ጊዜ ተከና ውኖ የሚያበቃ የአንድ ወቅት ስራ አይደ ለም፡፡ ለአዳዲስ ነገሮች በተጋለጥን ጊዜ ሁሉ ያለማወቅ ስጋት በራሳችን የመተማመን ስሜታችንን መፈታተኑ አይቀርም፡፡ ባልችል ውስ፣ ቢበላሽስ፣ ተቀባይነት ባላገኝስ የሚሉ አፍራሽ ስሜቶች ይረብሹናል፡፡

ሆኖም በህይወታችን ውስጥ የሚያጋጥሙንን አዳዲስ ሁኔታዎች እያሸነፍን በራስ መተማ መናችንን ለማጉልበት ቀጥሎ የቀረቡት ነጥ ቦች በእጅጉ ጠቃሚ ናቸው፡፡

**የራስን ችሎታ ማወቅ እና ማበልፀግ፣** አንድ ሰው የሁሉም ዕውቀት ባለቤት መሆን አይቻለውም፡፡ በአንፃሩ ግን እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ ችሎታ አለው፡፡ ስለዚህ ማንኛ ውም ሰው ያለውን ችሎታ ለይቶ ማወቅ፣ ያለበትንም የዕውቀት ክፍተት በመረዳት መማር፣ ልዩ ልዩ መጻህፍትን ማንበብ እንዲ ሁም ከሌሎች ሰዎች ጋር በመወያየት ዕው ቀትን ማበልፀግ ይጠቅማል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ያሉ ሁኔታዎች በፍጥነት እየተለ ዋወጡ በመሄድ ላይ ናቸው፡፡ ስለዚህ ሁል ጊዜ አዳዲስ የሚነሱ ሁኔታዎችን መከታተል እና ራሳችንን ከነዚህ ሁኔታዎች አንጻር ማብ ቃት አስፈላጊ ነው፡፡

ከሌሎች ሰዎች ለመማር በቅድሚያ የሌሎችን ሀሳብ ማክበር መቻል ጥሩ መሰረት ነው፡፡

ለሌሎች ሀሳብ ክብር ሰጥተን ስናዳምጥ ከእኛ ሀሳብ ጋር ያላቸውን ተቀራራቢነትና ልዩነት እንገነዘባለን፡፡ ከዚያም ልዩነታችንን በግልጽ ማስረዳት እና አቋማችንን ማሳየት እንችላለን፡፡

***እውነታን በፅናት መቀበል፣*** እውነታን በፅናት መቀበል ማለት ደካማና ጠንካራ ጐናችንን ለይተን ማወቅ ማለት ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሌሎች ስለእኛ የሚኖራቸውን እይታ እና ስለ እኛ የሚሰጡትን አስተያየት በነፃ ስሜት መቀበል እንችላለን፡፡ ከምናገኛቸው አስተያየቶች መካከልም የሚጠቅመንን በመውሰድ ራሳችንን ለማሳደግ መጠቀም፣ የማይጠቅመንን ደግሞ መተው ተገቢ ነው፡፡ ጠንካራ እና ደካማ ጐናችንን ለይተን ካወቅን ሌሎች ስለእኛ በሚሰጡት የተሳሳተ አስተያየት አንደናገርም፣ ችግሮች ሲያጋጥሙንም በመሸበር የተሳሳቱ ውሳኔዎችን አናሳልፍም፡፡

***እቅድ ማውጣትና ስራን መገምገም፣*** እቅድ ማውጣትና ስራን መገምገም በራስ ለመተማመን መሠረታዊ ከሆኑ ነገሮች አንዱ ነው፡፡ ለምሳሌ አንዲት ተማሪ በዚህ ዓመት ከክፍል ተማሪዎች አንደኛ እወጣለሁ ብላ ማቀድ ትችላለች፡፡ ይኼንን ዕቅድ አስባው ወይም ወረቀት ላይ ጽፋ ከተወችው ምኞት ነው እንጂ እቅድ አይባልም፡፡ ስለዚህ ይኼንን ዕቅዷን ሊያሳኩላት የሚችሉ ነገሮችን ዘርዝራ መፃፍ ይኖርባታል፡፡ ለምሳሌ የየቀኑን የጥናት ፕሮግራም ማውጣት፣ ከትምህርት ቤት አለመቅረት፣ መምህራን ሲያስተምሩ በፅሞና ማዳመጥ፣ ቤተ መፃህፍት በመግባት መፃህፍትን ማንበብ ወዘተ የሚሉ ለእቅዷ መሳካት መሣሪያ የሆኑትን ነገሮች መንደፍ አለባት፡፡

ድርጊቶችንም በቀን፣ በሳምንት፣ በወር፣ በዓመት እየተመነች የድርጊት መርሀ- ግብር ማውጣት ይኖርባታል፡፡ ባወጣችው መርሀ-ግብር መሠረት መፈፀምና በየጊዜው የተሰራውን ስራ እና ውጤትን መገምገም ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዋ እንዲህ ስታደርግ በራስ የመተማመን ስሜቷ እየዳበረ ይሄዳል፡፡

**መልመጃ ፱**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. በዕቅድ መመሪት እንዴት በራስ ለመተማመን ይጠቅማል?
2. ዕውነትን በፅናት መቀበል ማለት ምን ማለት ነው?

***የቡድን ሥራ፣***

ተማሪዎች አንድ አወያይና አንድ ፀሐፊ ምረጡ፡፡ ከዚያም በራስ የመተማመንን እና የበላይነት ስሜትን መገለጫ ባህሪዎች እየዘረ ዘራችሁ ተወያዩ፡፡ ፍሬሀሳቦችን በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ጻፉ፡፡

### 8.2.2 በራስ መተማመን ለራስ፣ ለቤተሰብና ለሀገር እድገት ያለው ጠቀሜታ፣

- ✓ በራስ መተማመን ለራስ፣ ለቤተሰብና ለሀገር እድገት ምን ጥቅም ይሰጣል?

**የወይዘሮ ዘምዘም ስኬት፤**

ወይዘሮ ዘምዘም የአንድ የግንባታ ዕቃዎች አምራች ድርጅት ስራ አስኪያጅ ናቸው፡፡ ድርጅቱ የተለያዩ የፈጠራ ውጤቶችን በማበርከቱ ተሸላሚ ሆኗል፡፡ በዚህ ምክንያት አንድ ጋዜጣ ስለ ድርጅቱ ስራ አስኪያጅ የስራ አመራር ችሎታ እና ስለግል ህይወታቸው ከተለያዩ ሰዎች ጋር ውይይት አካሂዷል፡፡ ከነዚህ መካከል ከቤተሰባቸው ውስጥ ባለቤታቸው እና ከስራ ባልደረባቸውም በከፊል የሰጡት አስተያየት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

***የወይዘሮ ዘምዘም ባለቤት፣*** "ዘምዘም ራሳችንን እና ልጆቻችንን ባጠቃላይ ቤተሰባችንን በተመ ለከተ በጋራ እንድንወስን ሀሳቦች ታቀርባለች፡፡ እንወያይባቸውና የሚጠቅመን ከሆነ ተግባራዊ እናደርገዋለን፣ ካልሆነ ግን እንተወዋለን፡፡ የእኔ ሀሳብ ከሷ ከተሻለ የኔን ተቀብላ ተግባ ራዊ እናደርጋለን፡፡ ቅሬታ ካላት ፊት ለፊት ትናገራለች፡፡ በዚህ ሁኔታ ተግባብተን ስለም ንኖር ልጆቻችንን በስርዓት ማሳደግ ችለ ናል፡፡ ኑሮዋችንም በየጊዜው ወደ ጥሩ የእድ ገት ደረጃ እየተሸጋገረ ነው" በማለት ተናግ ረዋል፡፡

**የስራ ባልደረቦቻቸው፣** “ዘምዘም በመማማር ታምናለች፡፡ ያላትን ዕውቀት በግልጽ ታካፍለናለች፡፡ አዳዲስ ነገሮች እና አሠራሮችን ለመፍጠር እና ለመሞከር ትደፍራለች፡፡ የማታውቀው ነገር ሲያጋጥማት መጽሐፍ ታነባለች፣ ሌሎች ሰዎችንም ትጠይቃለች፡፡ ከእኛም ጋር መመካከር ትወዳለች፡፡ ስንሳሳትም በግልጽ ታርመናለች፡፡ እሷም ስህተቷን ስንነግራት ታርማለች፡፡ ስለዚህ ሁልጊዜ ለስራ የተነሳሳ መንፈስ እንዲኖረን ማድረግ ችላለች፡፡ የመስሪያ ቤታችን የስራ ውጤት ከፍተኛ ነው፡፡ ይኼ ውጤት በሀገራችን ልማት ላይም ጥሩ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ነው፡፡ በቅርቡ ምርቶቻችንን ወደ ውጪ ለመላክ የገበያ ጥናት በማካሄድ ላይ ነን” በማለት በግልጽ አስረድተዋል፡፡

## መልመጃ 10

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ከተሰጡት አስተያየቶች መካከል የወይዘሮ ዘምዘምን በራስ የመተማመን ባህሪ የሚገልጹት ሀሳቦች የትኞቹ ናቸው?
2. ወይዘሮ ዘምዘም በራሳቸው የሚተማመኑ መሆናቸው ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸው እና ለሀገራቸው ያስገኘውን ጥቅም ግለጹ፡፡

በራሱ የሚተማመን ሰው ከጥገኝነት አስተሳሰብ የራቀ ነው፡፡ ሁልጊዜ የተሻለ ሆኖ ለመገኘት ጥረት ስለሚያደርግ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ህይወቱ በእድገት ጐዳና የሚጓዝ ስኬታማ ይሆናል፡፡ የሌሎች ሰዎችን ሀሳብ ስለሚያከብር ችግሮችን በውይይት ለመፍታት ዝግጁነት ይኖረዋል፡፡ ጠቃሚ ሀሳቦችን ከሌሎች ወስዶ ይጠቀማል፡፡ የራሱንም እውቀት ለማካፈል ወደ ኋላ አይልም፡፡

ከዚህም ባሻገር ግለሰቦች የቤተሰብ መሠረት ናቸው፡፡ ቤተሰብ ደግሞ የአንድ ሀገር ህብረተሰብ መሠረት ነው፡፡ ስለዚህም ሀገርን ማልማት መልካም ዜጋን ከማፍራት ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ በዚህ መሠረት በወይዘሮ ዘምዘም ህይወት ውስጥ እንደሆነው ሁሉ ግለሰቦች በራስ የመተማመን ባህሪ እያዳበሩ በሄዱ መጠን ለመልካም ቤተሰብ ግንባታ ጥሩ መሠረት ይሆናሉ፡፡ መልካም ቤተሰብ ደግሞ በተራው ለሀገር እድገት ተግባብተው የሚሠሩና ሥራ ፈጣሪ የሆኑ ዜጐችን ያፈልቃሉ፡፡ በነዚህ ዜጐቿ ሀገር የለማች እና ሉዓላዊነቷ የተከበረ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በያንዳንዱ ሰው ውስጥ የሚዳብር በራስ የመተማመን ባህሪ በቤተሰብ ህይወት እና በሀገር ግንባታ ሂደት ውስጥ ዐቢይ ሚና ይጫወታል፡፡

## መልመጃ 11

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. “ግለሰቦች ለአንድ ሀገር እድገት እና ውድቀት ዋና ምክንያት ናቸው” የሚለውን አባባል በራስ መተማመንን ከማዳበር አንጻር እያገናዘባችሁ ተወያዩ እና ድምዳሜ ላይ ድረሱ፡፡
2. በራስ መተማመን ስኬታማ ከመሆን ጋር የሚያገናኙትን ነጥቦች እየዘረዘራችሁ ግለጹ፡፡

© MoE FDRE Not to be republished

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ከጥገኝነት የተላቀቁ ሰዎች በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወታቸው ውስጥ ራሳቸውን የቻሉ ይሆናሉ፡፡ ራስን የመቻል ፅንሰ ሀሳብ ደግሞ በግለሰብና በሀገር ደረጃ ያሉ የዕድገት ሂደቶችን ይመለከታል፡፡ ከዚህም ባሻገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ራስን የመቻል መገለጫዎች እርስ በርሳቸው ይደጋገፋሉ፡፡ መሠረታዊ ፍላጎቶችን አሟልቶ መኖር መቻል በማንነት ስመኩራት በር ይከፍታል፡፡ ራስን የመቻል ጥንካሬ ለአንድ ሀገር ሉዓላዊነት መከበርም አስተዋጽኦ አለው፡፡ ራስን ለመቻል የሚረዱ ዘዴዎች ከልምድና ከትምህርት እንዲሁም ከባለሙያዎች ምክር ይገኛሉ፡፡

ሀገራችንን ራሷን ለማስቻል ከዜጎች የሚጠበቁ ብዙ ዓይነት ኃላፊነቶችና ግዴታዎችም አሉ፡፡ ለምሳሌ የሀገሪቱን ህግና ደንብ ማክበር፣ በኮንትሮባንድ እና በህገ ወጥ ድርጊቶች ውስጥ አለመሳተፍ፣ ወንጀሎች ሲፈፀሙ ለተገቢው አካል ማሳወቅ እና በወንጀል ተግባሮች አለመተባበር ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከዚህም ባሻገር የሥራ ባህልን በማዳበር፣ አምራች እና ሥራ ፈጣሪ በመሆን የሀገርን ሉዓላዊነት ማስጠበቅ የዜጐች ሁሉ የጋራ ሀላፊነት ነው፡፡

በሌላም በኩል ሰዎች ሁልጊዜ ለመታረም ራሳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ ትምህርት የሚገኘው ከትምህርት ቤት ብቻ አይደለም፡፡ ከጓደኛ፣ ከቤተሰብ፣ ከአካባቢ፣ ከአረጋውያን ልዩ ልዩ ጠቃሚ ዕውቀቶች ይገኛሉ፡፡ ከጥገኝነት አስተሳሰብ የተላቀቀ ህብረተሰብ ብቻ የሀገር እድገት ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ይችላል፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**ሉአሳዊ:-** ነጻነቱ የተከበረ።

**ኬላ:-** ዕቃዎች በህገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ እና እንዳይዘዋወሩ ቁጥጥር የሚደረግበት ቦታ።

**ዐይን አፋር:-** ስለሚያውቁት ጉዳይ፣ ደስታን፣ ሀዘንን፣ ቅሬታን ፊት ለፊት መናገር ወይም መግለጽ መፍራት፡፡

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

***I የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ::***

1. በራስ የመተማመን ስሜት አንድ ጊዜ ከተገነባ በኋላ ዘላለማዊ ነው፡፡
2. የራሳችንን ጠንካራ እና ደካማ ጐኖች ለይተን ካወቅን ሌሎች ሰዎች በእኛ ላይ በሚሰጡት የተሳሳተ አስተያየት አንታለልም፡፡
3. ሀሳብን በግልፅ እና በቀጥተኛ መንገድ መናገር በራስ የመተማመን አንድ ገፅታ ነው፡፡
4. ለራሱ ክብር የሚሰጥ ሰው የበላይነት ስሜት የተጠናወተው ነው፡፡
5. ኮንትሮባንድ ንግድ በዓለም ላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ የጋራ ጠላት ነው፡፡

***II በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ፡፡***

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ከስህተቱ የሚማር ሰው፣ | ሀ. በራስ ያለመተማመን መገለጫ። |
| 2. ራስን ማክበር፣ | ለ. ብልህ። |
| 3. ራስን መቻል፣ | ሐ. ሀሳብን መግለጽ መፍራት። |
| 4.. ዐይን አፋር | መ. በራስ መተማመን። |
| | ሠ. ራስን የመምራት ነፃነት ይሰጣል። |

***III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡***

1. በራስ መተማመንን ለማጐልበት፤
   ሀ. የራስን ችሎታ ማወቅና ማበልጸግ ያስፈልጋል፣
   ለ. እውነታን በጽናት መቀበል ያስፈልጋል፣
   ሐ. እቅድ ማውጣት እና ስራን መገምገም ያስፈልጋል፣
   መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡
2. ራሳቸውን ለመቻል ጥረት የሚያደርጉ ሰዎች፤
   ሀ. ራሳቸውን ብቻ ይጠቅማሉ፣
   ለ. ቤተሰባቸውን ብቻ ይጠቅማሉ፣
   ሐ. ለራሳቸው ለሀገራቸው እና ለቤተሰባቸው ጠቃሚ ዜጐች ናቸው፣
   መ. ምንም ጥቅም የላቸውም፡፡
3. በራስ መተማመን፤
   ሀ. በየጊዜው እውቀትን በማበልፀግ የሚዳብር ነው፣
   ለ. ብዙ ሀብትን በማከማቸት የሚዳብር ነው፣
   ሐ. ሌሎችን መናቅ ነው፣
   መ. ራስን ለመቻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው።
4. ጥገኛ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች፤
   ሀ. የሀገር ሸክም ናቸው፣
   ለ. የቤተሰብ ሸክም ናቸው፣
   ሐ. ተሸማቃቂ ናቸው፣
   መ. ሁሉም መልስ ነው።
5. ኮንትሮባንድ ንግድ፤
   ሀ. ኮንትሮባንዲስቶችን የሚጠቅም ተግባር ነው፣
   ለ. ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ህይወትን ያቃውሳል፣
   ሐ. ሙስናን እንዲስፋፋ ምክንያት ይሆናል፣
   መ. ‹ለ› እና ‹ሐ› መልስ ናቸው፡፡

©MoE Ethiopia Not to be republished

**IV *የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::***

1. ኮንትሮባንድ ወይም ህገ ወጥ ንግድ ሲካሄድ አይተው ለሚመለከተው አካል ለሚጠቁሙ ሰዎች የ____________ አበል ይሰጣል፡፡
2. ____________ የተላቀቀ ሰው ነጻ አስተሳሰብ ይኖረዋል፡፡
3. ____________ማለት በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ራስን አሳንሶ አለማየት እና የራስን ተገቢ ቦታ ማወቅ ነው፡፡

**V *የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡***

1. "ራሱን ያልቻለ ነፃነት የለውም" የሚለው አገላለፅ በግለሰብ እና በሀገር ደረጃ የሚሰጠውን ትርጉም ግለጹ፡፡
2. ለራስ ክብር መስጠት ማለት ምን ማለት ነው?
3. በኮንትሮባንድ ከሀገር ከሚወጡት እቃዎች ውስጥ አምስቱን ጥቀሱ፡፡

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

# ምዕራፍ ዘጠኝ
# የቁጠባ ባህል

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤**

- የቁጠባ ባህልን ማዳበር አስፈላጊነት ትገነዘቢያለሽ/ትገነዘባለህ፡፡
- በእቅድና በአቅም ልክ መመራት ጠቃሚ መሆኑን ትረዳለሽ/ትረዳለህ፡፡

## 9.1 ቁጠባ፤

### 9.1.1 የቁጠባ ባህልን ማዳበር አስፈላጊነት፣

- ✓ የቁጠባ ባህል አስፈላጊ ነው ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?
- ✓ የግለሰቦች የቁጠባ ባህል መዳበር ከራሳቸው አልፎ በሀገር ያለውን ጠቀሜታ ዘርዝሩ፡፡

**ልጅ ያቦካው ለፉት ሲበቃ**

የልጅነት ጊዜዬን ሳስብ ሁልጊዜ ከአእምሮዬ የማይጠፋ አንድ ትውስታ አለ፡፡ የመንደራችን ሰዎች ሁልጊዜ የሚናፍቁት፣ ተዘጋጅተው በጉጉት የሚጠብቁት አንድ አመታዊ ዝግጅት ነበር፡፡

የመንደራችን ሰዎች ተሰብስበው የአድባር በዓልን ያከብሩ ነበር፡፡ ለዚህ በዓል በልመና የሚተዳደሩት እማማ ልኬ ሳይቀሩ አንድ ዶሮ፣ አንድ ድፎ ዳቦና አንድ ጠርሙስ አረቄ ያቀርቡ ነበር፡፡ በቀን ሠራተኛነት የሚተዳደሩት አቶ በላቸውም ሳይቀሩ ለአድባር በዓል ጊዜ ያቀርቡት የነበረው ሙክት መልኩና ትልቅነቱ አይረሳኝም፡፡

የአድባር ክብረ በዓላችን በመብላት፣ በመጠጣት፣ በመስከር፣ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ጥጋብ የሚነግስባት እለት ነበረች፡፡ በዚያ ዝግጅት መጨረሻ ላይ እያንዳንዱ ተሳታፊና ተጋባዥ ለሚቀጥለው ዓመት ምን ማዘጋጀት እንደሚችሉ ስእለት ያደርጋሉ ወይም ቃል ይገባሉ፡፡ ጊዜው ሲደርስ ከእለት ጉርሳቸው ቀንሰው፣ ከባሰም ተበድረው ቃል የገቡትን ወጪ በማድረግ ለአንድ ቀን ምግብና መጠጥ ይደግሳሉ፡፡

በአንድ ወቅት ሁለት ከመንደሩ የወጡ ጎበዝ ተማሪዎች አንድ ሀሳብ አመነጩ፡፡ ብርቱካን የምትባለው ተማሪ የሚከተለውን ሀሳብ አቀረበች፡፡ "እኔና ዮናስ ካዋጣችሁት ገንዘብ ላይ ትንሽ ገንዘብ ሰጥታችሁን ከመንደራችን ልጆች ጎበዝ ለሆኑት በዚህ በእናንተ ፊት ሽልማት ልንሰጣቸው አስበናል" አለች፡፡

ይህን በሰሙ ጊዜ እማማ ልኬ "እዚህ ያለ ውማ ገንዘብ የስእለት ነው፡፡ የአድባር ገንዘብ ስለሆነ አይነካም፡፡ አድባሯ ትቆጣለች" አሉ፡፡ እማማ ልኬን የተከተሉ በርካታ ሰዎች ሀሳባቸውን ሰጡ፡፡ በዚህ ጊዜ አትዬ አስቴር "እኔ ሀሳቡ ደስ ብሎኛል፡፡ ባይሆን እኔ ለዛሬው ሀሳባችሁ የሚሆን ገንዘብ እሰጣለሁ፡፡ ለወደፊቱ ግን ተመካክረን እናስብበታለን" ሲሉ ተናገሩ፡፡ ያች ቀን የተቀደሰች ነበረች፡፡

በሚቀጥለው ዓመት ሽልማት የሚገባቸው ልጆች ቁጥር ጨመረ፡፡ ጎረቤቶችም ለዚህ አይነቱ ተግባር የሚችሉትን ያህል በመመደብ እየቆጠቡ ማጠራቀም ጀመሩ፡፡ በዚህ አጋጣሚ ጋሽ ኃይሉና አትዬ አስቴር ሀሳቡን አዳብረው አመጡት፡፡ ከሽልማት በተጨማሪ እንደእማማ ልኬ ያሉ ረዳት የሌላቸው አረጋውያን፣ ታሞ በአልጋ ላይ ውሎ የነበረው ወንደላጤው ጎረቤታችን መድኃኒት የሚገዛበት ገንዘብ ድጎማ ተደረገላቸው፡፡ የመረዳዳት ጥቅም በሰፊው ጎለበተ፡፡ ለዚህ አይነቱ ወጪ እያንዳንዱ የመንደራችን ሰው እንደአቅሙ በየሁለት ወሩ እንዲያዋጣ ተስማሙ፡፡ አትዬ አስቴር ገንዘብ ያዥ፣ ሁለቱ ተማሪዎች ደግሞ ጸሀፊና ኦዲተር በመሆን እንዲያገለግሉ

ተመረጡ:: አምስተኛው ዓመት ላይ በዚህ መልኩ የሚጠራቀመው ገንዘብ ከፍተኛ በመሆኑ ለጠንካራ ዓላማ መዋል ቀጠለ:: ዛሬ ያ ስብስብ እድርም፣ የብድር አገልግሎት መስጫም ነው::

**መልመጃ 1**

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. ከላይ የቀረበውን አይነት ድርጊት በአካባቢያችሁ ካለ በጽሁፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ::
2. ተመሳሳይ ሁኔታ ከሌለ በምትኖሩበት አካባቢ ሰዎች ለቁጠባ ሲነሳሱ የሚችሉበትን የጋራ ችግርና ጉዳይ በመፈለግ መፍትሔውንም ጭምር በማቅረብ ለክፍል አቅርቡ::

እያንዳንዱ ሰው በእለትም ሆነ በተወሰነ ጊዜ የሚያገኘውን ገቢ ለኑሮው አብቃቅቶ ከመጠቀም ባሻገር ለወደፊት ኑሮው የሚውል ገንዘብ ማጠራቀም አለበት:: ይህን ማድረጉ የየእለት ፍላጎቱን ከማሟላቱም በላይ በዜግነቱ የሚጠበቁበትን ግዴታዎች ለመወጣት ያስችለዋል:: ለዚህ ለምሳሌ ግብር መክፈልን መጥቀስ ይቻላል:: መንግሥት መንገዶችን የሚሰራው፣ የጤና ተቋማትን የሚገነባው፣ ትምህርት ቤቶችን የሚያስፋፋው ከህዝብ በሚሰበሰቡ መዋጮዎች ነው:: ከእነዚህ መካከል የሚሰበሰበው ግብር ከፍተኛ ቦታ አለው:: የመንግሥት ሠራተኞች፣ ነጋዴዎች፣ እንደአቅማቸው ግብር ይከፍላሉ:: ገበሬዎች፣ በአነስተኛ ንግድ የሚተዳደሩ ሰዎችም ግብር ይከፍላሉ:: ይህንን ግብር ጊዜውን እየጠበቁ መክፈል ካልተቻለ፣ ይጠራቀምና ለመክፈል አዳጋች ይሆናል:: ስለዚህ ሁሉም ሰዎች የሚፈለግባቸውን ለመክፈል ተዘጋጅተው ለመጠበቅ የቁጠባ ባህልን ማዳበር ይኖርባቸዋል::

ቁጠባ የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት:: ከእዚህም መካከል አንዱ እራስን ለመቻል ነው:: አንድ ሰው ራሱን ችሏል ወይም ችላለች የሚባለው በግልም ሆነ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ የሚያስፈልጉ ነገሮችን የሌሎችን እጅ ሳይጠብቅ ወይም ሳትጠብቅ መሸፈን ሲችል ወይም ስትችል ነው:: በተለይ ከቁጠባ ጋር የተያያዘው ራስን የመቻል ሁኔታ የሚገለጸው አስፈላጊ ወጪዎችን ያለጭንቀት መሸፈን፣ ቤተሰብን ለችግር ሳያጋልጡ ኑሮን ለመምራት ሲቻል ነው:: ራሱን የቻለ ቤተሰብ ለትምህርት፣ ለምግብና ለልብስ እንዲሁም ለህክምና የሚያስፈልገውን ወጪ በራሱ አቅም መሸፈን ይችላል:: የቤተሰቡ አባላት ለተለያዩ ቁሳዊና ማህበራዊ ጥቅም እጦቶችና ችግሮች አይጋለጡም::

ከላይ እንደተመለከተው ራስን መቻል በብዙ መልክ ይገለጻል:: በትምህርት፣ በምግብ፣ በአጠቃላይ ለኑሮ መሰረታዊ ፍላጎቶች በመሟላታቸው ሊገለጽ ይችላል:: ለዚህ ቁልፉ ግን በኢኮኖሚ ራስን መቻል ነው:: በሀገርም ደረጃ በኢኮኖሚው ራስን መቻል ከረሀብና ከበሽታ ነጻ የሆነ ህዝብ እንዲኖር ያስችላል:: ይህንን ሁኔታ ዛሬ ባደጉ ሀገራት እና ባላደጉ ሀገራት መካከል ያለውን የኑሮ ደረጃ በማነጻጸር መረዳት ይቻላል::

ባደጉ ሀገራት የሚኖሩ ህዝቦች ሙሉ በሙሉ የትምህርት፣ የህክምና እና የሌሎች መሰረታዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች ናቸው:: እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ህዝቦች ደግሞ በኢኮኖሚ አለማደግ የተነሳ ብዙ ችግሮች አሉባቸው:: ለአንድ ሀገር ራስን መቻል ማረጋገጫዎች ተቀማጭ የእህል ክምችት መኖርና የተፈጥሮ ሀብቶች ይዞታ መጠበቅ ወሳኞች ናቸው::

ተቀማጭ የእህል ክምችት ማለት በየአመቱ ከሚገኙ የሰብል ምርቶች ከጊዜው ፍጆታ በማስተረፍ በመንግሥት ጎተራዎችና መጋዘኖች ለወደፊት ጥቅም እንዲሆን ማስቀመጥ ማለት ነው:: በሌላ አገላለጽ መቆጠብ ማለት ነው::

**መልመጃ 2**

***ቀጥሎ የቀረቡትን የክርክር ሀሳቦች መነሻ በማድረግ በቡድን ሆናችሁ ውይይት አድርጉ::***

ሀ. ለቁጠባ ማደግ አስተዋጽኦ ያለው ባህል ነው::

ለ. ለባህል ማደግ አስተዋጽኦ የሚያደርገው ቁጠባ ነው::

## 9.1.2 የቁጠባ ባህል መዳበር ለሀገር እድገት የሚኖረው ጠቀሜታ፣

✓ የቁጠባ ባህል መዳበር ለሀገር ዕድገት እንዴት ጠቀሜታ እንደሚኖረው ግለጹ፡፡

### የዜግነት ድርሻ ስልጣት

ወ/ሮ ዘነበወርቅ አለማየሁ በተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት በትምህርትና በሥራ ለ27 ዓመታት ከኖሩ በኋላ በ1990 ዓ.ም ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ ለትልቅ ተግባር እራሳቸውን አዘጋጅተው ነበር፡፡ ሠርተው ያፈሩትን ንብረት ይዘው በመምጣት በወሊሶ አካባቢ የእንሰሳት ህክምና መስጫ አቋቋሙ፡፡ የዚህ የህክምና መስጫ መቋቋም ለወሊሶና ለአካባቢው ገበሬዎች ትልቅ ጥቅም እየሰጠ ነው፡፡

*ምንጭ፡ አዲስ ዘመን ጋዜጣ የሴቶች አምባ የካቲት 1992*

**መልመጃ 3**

***?*** ***የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ በቀረበው ምንባብ መሠረት መልሱ፡፡***

1. እንደ ወ/ሮ ዘነበወርቅ አለማየሁ በቁጠባ የልማት ሥራ የሠሩ የአንድ ሰውን አስተዋጽኦ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡
2. አንድ ግለሰብ የቁጠባ ባህል ማዳበር ለራሱ፣ ለቤተሰቡና ለአካባቢ ያለውን ጠቀሜታ ግለጹ፡፡

የቁጠባ ባህል መዳበር የሚጠቅመው ለግል ብልጽግና ብቻ አይደለም፡፡ የዳበረ የቁጠባ ባህል ያላቸው ሰዎች ለሀገር ዕድገት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ የሥራ መስክ በመፍጠር የልማት ሥራዎችን በማስፋፋት ሊሰለፉ ይችላሉ፡፡

**መልመጃ 4**

***?*** ***የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩበት፡፡***

1. የቁጠባ ባህል እንዴት ሊዳብር ይችላል?
2. የቁጠባ ባህል መዳበር እንዴት የሀገር ዕድገትን ያፋጥናል?

## 9.1.3 አባካኝና ኋላቀር ልማዶች፣

✓ አባካኝነትና ኋላቀር ልማዶች ምን እንደሆኑ በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ፡፡

ኋላቀር ልማዶች የሚባሉት ከዘመኑ የአኗኗር ስልትና አስተሳሰብ ጋር አብሮ ለመሄድ፣ አዳዲስ አስተሳሰቦችንና ሳይንሳዊ ግኝቶችን ለመቀበል እንቅፋት የሚሆኑ ነባር እምነቶችና አሰራሮች ናቸው፡፡ የቁጠባ ባህላችንን በማሳደግ እራሣችንን ጠቅመን ሀገራችን ለማሳደግ እንድንችል ለብኩንነትና ለድህነት የሚዳርጉ ኋላቀር ልማዶችን ማስወገድ ይገባናል፡፡

### ለብኩንነትና ለድህነት የሚዳርጉ ኋላቀር ልማዶችን ማስወገድ፣

አባካኝነት በአይነትና በገንዘብ ያለን ንብረት ያለአቅድ ማጥፋት ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የቁጠባ ተቃራኒ ነው፡፡ ለብኩንነት የሚዳርጉ ኋላቀር ልማዶች ዘርፈ ብዙ ናቸው፡፡ አባካኝነትና ለድህነት የሚዳርጉ ኋላቀር ልማዶች ከሚባሉት መካከል ድግስ ማብዛት፣ ጊዜን ማባከን፣ የአካባቢ የተፈጥሮ ሀብትን አላግባብ መጠቀም፣ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

አባካኝነትን የሚያስከትሉ ኋላቀር ልማዶች ስለወደፊቱ ከማሰብ ይልቅ የእለት የእለቱን ብቻ በመመልከት እቅድ አልባ የንብረት አጠቃቀምን የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ አባካኝነት ቅድሚያ የሚሰጠውን ቅድሚያ ከማይሰጠው፣ አስፈላጊ የሆነውን አስፈላጊ ካልሆነው መለየት አለመቻል ነው፡፡ ብኩንነት ለአንድ ጊዜ ፍጆታ ከመጠን በላይ ወጪ ማድረግም ነው፡፡ በአጠቃላይ ብኩንነት ለነገ ወይም ለወደፊት ተብሎ መቀመጥና መቆጠብ የሚገባውን ሀብት ከእቅድ ውጪ ለዛሬ ጥቅም ብቻ ማዋል ነው፡፡ በግለሰብ ደረጃ ሰዎች ለአባካኝ የሚዳረጉት በዋናነት ራስን በሥነምግባር ካለማነጽ ነው፡፡ ይህም በመጥፎ ሱሶች በመጠመድ ሊገለጽ ይችላል፡፡

የሰዎች ብኩንነት በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያለው ጫና ከፍተኛ ነው፡፡ ብኩንነት የተጠናወታቸው የህብረተሰብ ዓባላት የሌሎችንም ሰላም ያደፈርሳሉ፡፡ ቢቸገሩ የሌሎችን እርዳታና ድጋፍ ይሻሉ፡፡



© MoE FDRE Not to be republished

ቤተሰብ ላይ ጫናይፈጥራሉ፡፡ የሥራ ሥነም ግባራቸው ጠንካራ ስላልሆነ ይህ ባህርያቸው ምርታማነት ላይ አሉታዊ ውጤት አለው፡፡ ለምሳሌ አንድ የሰራተኞች ማመላለሻ አውቶ ቡስ የሚያሽከረክር ሰው፣ ሰዓት የማያከብር ቢሆን የመስሪያ ቤት ሰዎችን ከቦታ ቦታ ለስራ ጉዳይ የማዘዋወር ሃላፊነቱን ስለማይ ወጣ ስራን በጊዜው እንዳይሰራ ያደናቅፋል፡፡ ራሱም ቢሆን በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ መከበ ርን ያጣል፡፡

***የቡድን ሥራ፤***

**በአካባቢያችሁ ለድህነት ሊዳርጉ የሚችሉ ኋላቀር አሠራሮችን በቡድን ሆናችሁ በማጥ ናት በክፍል ውስጥ ተወያዩባቸው፡፡**

## 9.2 በእቅድና በአቅም ልክ መመራት፤

አንድ ታዋቂ ድምጻዊ በሚጫወተው ዜማ ውስጥ፤

- ✓ የሚሉ ስንኞች አሉ፡፡ ይህ ግጥም ምን አይነት መልእክት እንደሚያስተላልፍ ግለጹ፡፡

  “አቅምን አውቆ መኖር ጥሩ ነው
  ታላቅ ችሎታ ነው”

### ወይ ተበዳሪ ወይ አበዳሪ ይሞታል፤

ፍቅርተ በምትሰራበት መስሪያ ቤት ውስጥ በመሽቀርቀሯ ትታወቃለች፡፡ የአንድ ክፍል ጸሀፊ ሆና ሳለ ከምታገኘው ደመወዝ ጋር በማይመጣጠን ደረጃ ታጌጣለች፡፡ ሁልጊዜ አዳዲስ ፋሽኖችን ትከተላለች፡፡ ይህን የሚመ ለከቱ የመስሪያ ቤቷ ሰዎች የማይነጥፍ የገቢ ምንጭ እንዳላት ይጠረጥራሉ፡፡ ምሥጢሩ ግን ሌላ ነው፡፡ ፍቅርተ የብዙ ሰዎች እዳ አለባት፡፡ አንዳንድ ልብሶቿና እቃዎቿ በዱቤ የተወሰዱ አለያም በብድር የተገዙ ናቸው፡፡

አክሊሉ ሌላው የመስሪያ ቤቱ ሾፌር ነው፡፡ ጠዋት ለስራ ስምሪት ሲፈለግ አይገኝም፡፡ በደመወዝ ሰሞንም ሆነ በሌሎች ባልተጠበቁ ቀናት ከስራ ገበታው በመጥፋት የታወቀ ነው፡፡ በቢሮ አካባቢ የሚስተዋለው የወር ደመወዝ በሚከፈልበትና የደሞዝ ብድር በሚ ሰጥበት ጊዜ ነው፡፡ የሚደበቃቸውም ሰዎች ብዙ ናቸው፡፡ ምክንያቱም “ደመወዜን ስቀበል እከፍላችኋለሁ” በማለት የተበደራቸውን ሰዎች፣ እመልሳለሁ ባለበት ጊዜ ሲጠፋባቸው ማፈላ ለግ ይይዛሉ፡፡ ከፍቅርተ የሚለየው ከመልበ ስና ከማጌጥ ይልቅ በቁማርና በመጠጥ ብኩን ህይወት መምራቱ ነው፡፡

የገንዘብ ክፍል ሹሟ አለሚቱ ብቻ የሁለቱን ሚስጢር ታውቃለች፡፡ ለምን ከዚህ የብድር ሱስ እንደማይወጡ ስትጠይቃቸው ወይ “አበ ዳሪ ወይ ተበዳሪ ይሞታል” የሚል መልስ ይሰጧታል፡፡

እዳው ሳይከፈል ይቀራል ማለታቸው ነው፡፡ በዚህ ጊዜ አንገቷን ነቅንቃ የጠየቋትን ብድር አስፈርማ ትሰጣቸዋለች፡፡ የሚቀጥለው ወር ተመልሰው ይመጣሉ፡፡

**መልመጃ 5**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ በቀረበው ምንባብ መሠረት መልሱ፡፡***

1. ፍቅርተና አክሊሉ ከአቅማቸው በላይ ለመኖር መፈለጋቸው ምን ጉዳት አስከተለባቸው?
2. እንደ ፍቅርተና አክሊሉ በአካባቢያችሁ ከአቅ ማቸው በላይ የሚኖሩ ሰዎች ካሉ ምን ታደር ጋላችሁ?

በእቅድና በአቅም ልክ መመራት ሁለት ጽንሰ ሀሳቦችን የያዘ ጉዳይ ነው። እነሱም፤

### ሀ. በአቅም ልክ መኖር፣

በአቅም ልክ የሚኖር ሰው አስፈላጊ ያልሆኑ ወጪዎችን ስለማያወጣ ለወደፊት ህይወቱ የሚጠቅመውን ገንዘብና ንብረት ለማስቀመጥ ይችላል፡፡ ይህን በማድረጉም ራሱም፣ አካባቢ ውም ሆነ ሀገሩ እንዲጠቀሙ አስተዋጽኦ ያደ ርጋል፡፡ በአንጻሩ በአቅም ልክ የማይኖሩ ሰዎች በእዳ የተዘፈቁና ከገቡበትም እዳ መውጣት የሚከብዳቸው ናቸው፡፡

በአቅም ልክ አለመኖር በብዙ ሁኔታዎች ሊገለጽ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ተበድሮ የቅንጦት እቃዎች ወይም በወቅቱ በጣም አስፈላጊ ያልሆኑ ነገሮችን መግዛት፣ ከሚገኝ ገቢ በላይ የሚያስወጡ ፍላጎቶችን ማስተናገድ፣ ሌሎች

የሚገዙት ወይም የሚያደርጉትን እኔስ ከማን አንሼ በሚል መንፈስ በተመሳሳይ ለመፈጸም መሞከር ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ይህ መጥፎ ልማድ ከመሆኑ የተነሳ ከፍተኛ የሆነ ችግርም ያስከትላል፡፡ ሥነልቦናዊ እርካታ አለማግኘት አንዱና መሠረታዊ ችግር ነው፡፡ በሌላ በኩል በአቅም ልክ አለመኖር የበታችነት ስሜት እንዲሰማ ያደርጋል፡፡ የፈለጉትን ለማሟላት ያላዘጋጁትን ገንዘብ ከሰው መበደርን ያመ ጣል፡፡ ወደዚህ ችግር ላለመግባት በሚገኝ ገቢ ራስን ገድቦ መኖር ብልህነት ነው፡፡

የገንዘብ አጠቃቀምን ማወቅ አንዱ የቁጠባ ጥበብ ነው፡፡ የቁጠባ ማሳደጊያ ዘዴዎች ከግለ ሰብ ግለሰብና ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ይለያ ያሉ፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች ቋሚ ንብረቶችን በመግዛት በእጃቸው ያለ ገንዘብ እንዳይጠፉ ያደርጋሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ያለማቋረጥ በየጊ ዜው ገንዘብ በባንክ ያጠራቅማሉ፡፡ በባንክ አገል ግሎት ይበልጥ በተጠቀሙ ቁጥር ባስቀመጡት የገንዘብ መጠን ልክ ወለድ ያገኛሉ፡፡

### ለ. በእቅድ መመራት

#### የቴዎድሮስ ገጠመኝ

ቴዎድሮስ ከቤተሰቦቹ ስለገንዘብ አጠቃቀም ምንም ልምድ አልቀሰመም፡፡ ከመምህራን ማሰል ጠኛ ኮሌጅ ተመርቆ ሥራ እንደጀመረ የመጀመ ሪያ ደሞዙን እንዴት ሊጠቀምበት እንደሚችል ሲያስብ ከሁለት ቀናት በላይ ፈጅቶበት ነበር፡፡ በምረቃው ላይ ተገኝተው ደስታቸውን በመግለጽ ስጦታዎች ያበረከቱለትን ጓደኞቹን መጋበዝና ለመምህርነት የሚመጥኑ አልባሳትን መግዛት አሰበ፡፡ ደሞዙ ግን አልበቃውም፡፡ በአንድ ጊዜ ተነባብረው የመጡበትን ሀሳቦች በአንድ ጊዜ መፈጸም እንዳለበት ያምናል፡፡ ስለሆነም "ወደፊት ሠርቼ እከፍላለሁ" ብሎ ተበደረና በሙሉ ተጠቀመበት፡፡ የተከታዩ ወር ደሞዙ ከፊሉ ለእዳ ተከፈለ፡፡ ቀሪው ደግሞ እስከሚቀ ጥለው የደሞዝ ጊዜ እንደማይበቃው ተገነዘበ፡፡

በዓመቱ ቴዎድሮስ ሠርቶ ደመወዝ እያገኘ ሳለ ስለችግር ማውራት ጀመረ፡፡ ቤተሰቦቹን እጅግ አስፈላጊ በሆነ ጉዳይ ላይ እንኳዋን መርዳት ስለተሳነው መበሳጨት አዘወተረ፡፡ በመካከሉ አንድ ኑሮውን በእቅድ የሚመራ ጥሩ ጓደኛ አገኘ፡፡ ቴዎድሮስ ግልጽ በመሆኑ የአኗኗሩን ሥልት ለዚህ ጓደኛው ገለጸለት፡፡ ጓደኛውም የራሱን ገንዘብ አጠቃቀም ዘዴ ነገረው፡፡ ዘዴው ማንም ሰው የሚያገኘውን ገንዘብ እንዴት በእቅድ ሊጠቀምበት እንደሚችል የሚያሳይ ነው፡፡

| የወጪ ርእስ | የወጪ መጠን በመቶኛ |
|---|---|
| ለቤት ወጪ | 50 በመቶ |
| ለማህበራዊ ጉዳይ መዋጮ | 7 በመቶ |
| ለትራንስፖርት | 17 በመቶ |
| ለህክምና መጠባበቂያ | 9 በመቶ |
| ለቁጠባ ተቀማጭ | 10 በመቶ |
| መዝናኛ | 2 በመቶ |
| ትምህርት ለማሻሻል | 5 በመቶ |

**መልመጃ 6**

**?** ***ሠንጠረዡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 ከተዘረዘሩት መካከል ተገቢ የሆኑ እና ያልሆኑ ወጪዎች ካሉ አመ ልክቱ፡፡ እንዲሁም መሻሻል ያለባቸውን ወጪዎች ለዩ፡፡
2. የቴዎድሮስ ደመወዝ ብር ሦስት መቶ ሃምሳ (350.00) ነው፡፡ ከላይ ባለው መሰረት ሸንሸ ናችሁ የወጪውን መጠን ለማሳየት ሞክሩ፡፡
3. የምትቀርቡት አንድ የቤተሰብ አባል በመጠ የቅ የቁጠባ ዘዴያቸው እንዴት እንደሆነ አነጋግሩ፡፡ ከዚያም ከቴዎድሮስ የወር ወጪ ስሌት አንጻር ገቢያቸውን ሸንሽኑና አመል ክቱ፡፡ ዘዴው ሳነጋገራችሁት ሰው ይስማማል ወይስ አይስማማም? ለምን?

እቅድ በወደፊት ህይወት የሚከናወኑ ተግባራ ትን አስቀድሞ መተለም፣ እንዲሁም በገን ዘብ፣ በእውቀትና በጊዜ የሚያስፈልጉ ግብአ ቶችን አስቀድሞ መደልደል ነው፡፡ በማንኛውም ደረጃ እቅድ ለሰው ልጆች ህይወት ወሳኝ ነው፡፡ እቅድ በግለሰብም ደረጃ ሆነ በሀገር ደረጃ ሊከተሉት የሚገባ የእድገት ጎዳና ነው፡፡

©MoE FDRE Ethiopia Not to be republished

### መልመጃ 7

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. በመንግሥት ደረጃ እቅድ ላይ የሚደረጉ ስብሰባዎች ወይም ውሳኔዎች ስለመኖራቸው ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
2. እነዚህ እቅዶች በምን በምን ላይ ያተኮሩ ናቸው?

## ሐ. በእቅድና በአቅም ልክ መመራት ለሀገር እድገት የሚኖረው ጠቀሜታ

- የግለሰቦች እድገት ከሀገር እድገት ጋር እንዴት ሊያያዝ እንደሚችል ግለጹ፡፡

### ልጅ በእድሉ ያድጋል

አቶ በድሩ፣ ወ/ሮ ሸምሲያን በሁለተኛ ሚስትነት ባገቡ በአመታቸው ይኸው የስምንተኛ ልጃቸውን መወለድ እየተጠባበቁ ነው፡፡ ለዚህ ዝግጅታቸው ደግሞ ጎረቤታቸው አቶ ኃይለእየሱስና ባለቤታቸው ወ/ሮ አስካለ እየተባበሯቸው ነው፡፡ አቶ በድሩ የመጀመሪያ ባለቤታቸውን ወ/ሮ ኑሪያን ሲያገቡ አቶ ሃይለእየሱስ ሦስተኛ ወር የትዳር ጊዜያቸው ላይ ነበሩ፡፡ ዛሬ ሁለቱም የበርካታ ልጆች ወላጆች ናቸው፡፡

አቶ ኃይለእየሱስ ያለቻቸውን አነስተኛ መሬት እያረሱ የሚያስተዳድሯቸው ልጆች የትምህርት እድል አላገኙም፡፡ አቶ በድሩም ከሁለቱ ሚስቶቻቸው ከወለዷቸው ከስምንቱ ልጆች አራቱ በንግድና በጉልበት ስራ ሰበብ ወደተለያዩ አካባቢዎች ተሰደዋል፡፡

ሁለቱን ቤተሰቦች የሚያመሳስሏቸው ብዙ ነገሮች አሏቸው፡፡ ሁለቱም "ልጅ ፀጋ ነው" በሚለው አባባል ያምናሉ፡፡ ልጆችን አብዝቶ መውለድ ጎጂ ነው የሚለው ሀሳብ የሰይጣን አመለካከት ነው ብለው ያስባሉ፡፡ አራርቆ መውለድ ለእናቲቱም ጤንነት ሆነ ለልጆቹ አስተዳደግ መልካም መሆኑን አስበውት አያውቁም፡፡ ያለእድሜ ጋብቻ የሚያስከትለው ጉዳት፣ ወሊድን የመቆጣጠር ጥቅም፣ ወዘተ የሚሉት አስተሳሰቦች አይገቧቸውም፡፡

ለማህበር ድግስ፣ ለህክምናና ለምግብ የሚያስፈልገው ወጪ አስቀድሞ ሊታሰብበት እንደሚገባ አይረዱም፡፡ የተወለዱትም ልጆቻቸው ሆኑ ገና የሚወለዱት ሲያድጉ እድል እንደምትታደጋቸው አድርገው ያስባሉ፡፡

ሰሞኑን የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትን ጥቅም ለማስተማር ወደ አካባቢው የዘመቱት የጤና ባለሙያዎች በሁለቱ ቤተሰቦች ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ሁለቱ ወላጆች ይህንን ትምህርት ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሄዋን የደረሱትም ሆነ ያልደረሱት ልጆቻቸው እንዲሰሙ አይፈልጉም፡፡

### መልመጃ 8

*ከላይ በቀረቡት ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. ሁለቱን ቤተሰቦች የሚያመሳስላቸው ምንድን ነው?
2. አራርቆ መውለድ ለቤተሰብ ኑሮ መሻሻል የሚሰጣቸው ጥቅሞች ምን ምን ናቸው?

ልጆች የሚያድጉት በእድል ሳይሆን በወለዷቸው ቤተሰቦቻቸው የገቢ መጠንና የአስተዳደግ ብቃት ነው፡፡ በሀገራችን አንዲት ሴት በአማካይ እስከአምስትና ስድስት ልጆችን መውለዷ የተለመደ ነው፡፡ አምስት ስድስት ልጆችን መውለድ ደግሞ የተሟላ የትምህርትና የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ እንደማያስችል የታወቀ ነው፡፡

ለእናቶች ሞት ቁጥር መጨመር፣ ለጎዳና ተዳዳሪነትና ለልመና የሚዳረጉ ሁኔታዎች የሚመነጩት የቤተሰብ ምጣኔን ሥልት ካለመጠቀም ነው፡፡ የቤተሰብ ምጣኔ አለመጠቀም ከፍተኛ የሆነ የህዝብ ብዛትን ያስከትላል፡፡ የህዝብ ብዛት ደግሞ ያልተመጣጣነ የተፈጥሮ ሀብትን ጥቅም ላይ እንዲውልና መጪው ትውልድ ችግር ላይ እንዲወድቅ ያደርጋል፡፡

*የሚከተለውን ተግባር ሥሩ፡፡*

በአካባቢያችሁ ከቤተሰብ ብዛት ጋር በተያያዘ በችግር የሚኖር/የምትኖር አንድ ሰው በማፈላለግ አነጋግራችሁ ታሪኩን በጽሁፍ አቅርቡ፡፡ በጽሁፉ ውስጥ የምትጠቅሱት ወይም የምትጠቅሷት ባለታሪክ ተሞክሮ ለሌሎች ሰዎች የሚሰጠውንም ትህምርት አሳዩ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የቁጠባ ባህል ማደግ ለግላዊም ሆነ ለማህበራዊ ብልጽግና አስፈላጊ ነው፡፡ በሀገር ደረጃ  የቁጠባ ባህል መዳበር የሚኖረውን ጠቀሜታ ብንወስድ ህዝቦች የትምህርትና የህክምና አገልግሎት በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲያገኙ ያስችላል፡፡ የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅም ከቁጠባ ባህል ጋር ይያያዛል፡፡ ይህን ማድረግ ለወደፊቱ ትውልድ ማሰብ ነው፡፡ ለመለምለም ረጅም አመታት የፈጁትን ደኖች መጨፍጨፍ፣ አፈርን ለመሸርሸር ማጋለጥ፣ የመሳሰሉት ድርጊቶች ግን ድህነትን  የሚያስከትሉ ድርጊቶች ናቸው፡፡

በግለሰብ ደረጃ ደግሞ የገንዘብ አያያዝና የንብረት አጠቃቀም ለኑሮ ዋስትና ይሰጣሉ፡፡ ይህም የሚጠቀመው ራስን ለመቻል፣ ለኢንቨስትመንት ወይም ለልማት ስራ፣ እና ለማህበራዊ ተሳትፎ መዳበር ነው፡፡ ለዚህ የሚረዱ የቁጠባ መርሆችም አሉ፡፡ ለምሳሌ ወጪ ከገቢ እንዳይበልጥ ማድረግና ለማይጠበቁ አጋጣሚዎች  ገንዘብ ማስቀመጥ ጥቂቱ ናቸው፡፡

የቁጠባ ባህልን ለማሳደግ የተለያዩ ዘዴዎች አሉ፡፡ ቤተሰብን መመጠን፣ የጊዜን ክቡርነት መረዳትና ማክበር፣ በአቅም ልክ መኖርን ማወቅ ናቸው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ መታወቅ ያለበት የቁጠባ ባህል እንዳይጎለብት የሚያደርጉ ሁኔታዎች መኖራቸውን መገንዘብ ነው፡፡ እነዚህም ቁጠባን የሚጻረሩ ኋላቀርና ጎጂ ልማዶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ አባካኝነት ንብረትን፣ ገንዘብንና የተፈጥሮ ሀብትን አላግባብ መጠቀም፣ ማውደም ማለት ሲሆን ለዚህ የሚያነሳሱ ኋላቀር ልማዶች ደግሞ ዘመናዊ አኗኗር ዘይቤንና አስተሳሰብን ለመቀበል ዝግጁነቱ አለመኖር፣ ሳይንሳዊ ግኝቶችን አለመቀበል፣ አለመማር፣ የግንዛቤ ማነስ ናቸው፡፡ እነዚህን እንከኖች ደግሞ በማስተማር መለወጥ ይቻላል፡፡

© MoE, Not to be

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**ስንኝ:-** የግጥም ነጠላ መስመር።

**የመሰረተ ልማት ተቋማት:-** እንደ የመንገዛና የስልክ የመሳሰሉትን የመገናኛ ዘዴዎች፣ የሃይል ምንጭ የሆነው የኤሌክትሪክ መዘርጋትንም ያጠቃልላል፡፡

**ኢንቨስትመንት:-** ገንዘብን በቋሚ የምርት ወይም የአገልግሎት ስራ ላይ ማዋል፡፡ ኢንዱስትሪና ፋብሪካ የመሳሰሉት።

**አድባር:-** ባህላዊ እምነት፣ ትልቅ ዛፍ ስር አመት እየተጠበቀ የሚደረግ የአምልኮ ሥርዓት።

**ራዕይ:-** ወደፊት የሚመጣን ወይም የሚያጋጥምን ሁኔታ ከወዲሁ አስቀድሞ ማለም፣ ዓላማና ግብን አስቀድሞ ማስቀመጥ፡፡

**ዱቤ:-** በተወሰነ ጊዜ ዋጋውን ለመክፈል ቃል በመግባት እቃን ወይም ሸቀጥን ከሻጮች መውሰድ፡፡

© MoE, FDRE
Not to be republished

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

**I የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ።**

1. አንድ ሰው የቁጠባ ባህል ቢኖረውም ባይኖረውም ተጠቃሚውም ሆነ ተጎጂው ራሱ ነው።
2. አንድ ሰው በማናቸውም መንገድ ሀብታም መሆን እንደሚቻል ካመነ የቁጠባ ባህል ምንነት ገብቶታል ማለት ነው።
3. የተፈጥሮ ሀብት በየጊዜው ራሱን የሚተካና እንደአላቂ እቃዎች ጥቅም ላይ ውሎ የማያልቅ ነው።
4. በአጭር ጊዜ ለሚታይና ከረጅም ጊዜ በኋላ ለሚገኝ ውጤት ያለንን በጀት እኩል አካፍለን መጠቀም ይኖርብናል።
5. ጥሩ የኑሮ ስልት አለ ማለት የሚቻለው የተመጣጠኑ የገቢና የወጪ ስልት ሲኖር ነው።

**II በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የተፈጥሮ ሃብት፣ | ሀ. ማእድናት። |
| 2. የቤተሰብ ምጣኔ፣ | ለ. እቅድ። |
| 3. ኋላቀር አስተሳሰብ፣ | ሐ. ለሌሎች አለማሰብ። |
| 4. ብኩንነት፣ | መ. በአቅም ልክ መኖር። |
| 5. የቁጠባና ብድር ማህበር፣ | ሠ. እኔ የምሞተው ዛሬ ማታ ገብስ የሚደርሰው ለፍልሰታ። |
| | ረ. ገደብ የለሽ ፍላጎትን ማስተናገድ። |

**III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ።**

1. የአንድን ሀገር እድገት ሊያመጡ የሚችሉት ሁኔታዎች፤
   ሀ. የህዝቦች ከኋላ ቀር ልማዶች መላቀቅ፣
   ለ. የረጅም ጊዜ እቅድ፣
   ሐ. የአጭር ጊዜ እቅድ፣
   መ. ሁሉም መልሶች ናቸው።
2. ለወደፊት ትውልድ ማሰብ ማለት ከሚከተሉት ውስጥ ከአንደኛው ሀሳብ ጋር አይስማማም፤
   ሀ. የቁጠባ ባህልን አዳብሮ ማስተላለፍ፣
   ለ. በትምህርትና በእውቀት የታነጸ ትውልድ መቅረጽ፣
   ሐ. የተፈጥሮ ሀብቶችን አሟጦ አለመጠቀም፣
   መ. የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግን አይመለከትም።
3. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ለብክነት የሚዳርግ ድርጊት ነው፤
   ሀ. ፊልም ቤቶችን ማስፋፋት፣
   ለ. በገጠር መንደር ውስጥ የነዳጅ ማደያ ለማቋቋም ኢንቨስት ማድረግ፣
   ሐ. ለሁሉም ዜጎች የትምህርት እድል መፍጠር፣
   መ. የቤተሰብ ምጣኔ መለመድ።
4. ራስን መቻል ማለት፤
   ሀ. ከሰው መነጠል ማለት ነው፣
   ለ. ለሌሎች ራስን መቻል ድጋፍ ማድረግ ነው፣
   ሐ. ከጥገኝነት መላቀቅ ማለት ነው፣
   መ. ከ‹ሀ› በስተቀር ሁሉም መልሶች ናቸው።

**IV የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ።**

1. በአይነትም ሆነ በገንዘብ ያለን ንብረት ማጥፋት __________ ይባላል።
2. የቁጠባ ባህል በግለሰብም ሆነ በአገር ደረጃ ለማጎልበት መለመድ ካለባቸው የኑሮ ስልቶችና ልምዶች መካከል __________ እና__________ ሊጠቀሱ ይችላሉ።

**V የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ።**

1. ለቁጠባ ባህል መዳበር አስፈላጊነት ምሳሌ የሚሆኑ ታሪኮችን በማካተት አስረዱ።
2. የኋላቀር አመለካከቶች በቁጠባ ባህል አለመዳበር ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ አላቸው። ይህንን ከአካባቢያችሁ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት የምታውቁትን ግለጹ።



© FDRE Ethiopia Not to be republished

# ምዕራፍ አስር
# ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤**

- በአካባቢና በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ያለውን ጠቀሜታ ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ፣
- የልዩ ልዩ ህብረተሰብ ክፍሎች መደራጀትና መጠናከር ጠቀሜታ እንዳለው ታውቃለህ/ታውቂያለሽ፣

## 10.1 በአካባቢ የልማት፣ የሰላምና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እንቅስቃሴ ውስጥ የዜጎች ንቁ ተሳትፎ ወሳኝነት፤

### 10.1.1 የዜጎች ንቁ ተሳትፎ ወሳኝነት ለዴሞክራሲ ግንባታ፣ ለጋራ መግባባትና ለመልካም አስተዳደር መስፈን፣



ሥዕል 10.1 ልማታችንን ለማፋጠን በጋራ እንንቀሳቀስ

- *ሥዕሉ ስለምን እንደሚገልጽ አስረዱ::*
- *የሥዕሉ መግለጫ የያዘው ሐሳብ በትክክል ተግባራዊ ከተደረገ ሠልፈኞቹ ምን ምን አከናውነው ሊሆን ይችላል?*



ሥዕል 10.2 ከአቶ አልቃድር አማን ጋር አጭር ቆይታ

**ተውለደሬ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ሰፈር**

**የተውለደሬ ድምፅ፡** በቅድሚያ ራስዎን ቢያስተዋውቁን?

**አልቃድር፡** ስሜ አልቃድር አማን ሲሆን ተወልጄ ያደግሁት መቄት ወረዳ ነው:: ለሃያ ስድስት ዓመት በውጪ ሀገር ኖሬ ከተመለስሁ ሁለተኛ ዓመቴ ነው:: ይዤ በመጣሁት ሀብት ሥራ ከፍቼ ለ750 ሰው የሥራ እድል ፈጥሬያለሁ::

**የተውለደሬ ድምፅ፡** ኑሮዎንና ሥራዎን ተውለደሬ ያደረጉት እንዴት ነው?

**አልቃድር፡** ወደሀገሬ እንደመጣሁ ላለማና ልኖር የፈለግሁት በተወለድኩበት ኩሸሽሌ ወረዳ ነበር:: እዚያ ግን ለመሥራት የማይመቹ ሆኖ ስለአገኘሁት ሥራና ኑሮዬን ወደ ተውለደሬ አደረግሁ::

**የተውለደሬ ድምፅ፡** ኩሸሽሌ ለመኖርና ሀብት ዎንም ለልማት ለማዋል ያልቻሉት ለምንድነው?

**አልቃድር፡** ያለኝን የልማት ራዕይ በመቄት እውን ለማድረግ አልቻልሁም:: የወረዳው ኃላፊዎችና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሌት ተቀን የሚተጉት በየግል ጥቅሞቻቸው ዙሪያ ለሚያደርጉት ሽኩቻ ነው::

የወረዳዋ ልማትም ሆነ የኗሪዎቹ ኑሮ መሻሻል አያስጨንቃቸውም:: ርስበርስ በትንሽ በትልቁ ሲተማሙ፣ ሲነቃቀፉ ሲናቆሩና ሲጣሉ ይውላሉ:: ለጋራ አላማ ተግባብተው መሥራት አልቻሉም:: ባለጉዳዮች አገልግሎትን በቅልጥፍና አያገኙም:: የመንግሥት ግብር እንዲሁም የውሃ፣ የመብራት፣ የስልክና የመሳሰሉ አገልግሎቶች ክፍያዎችን ለመፈፀም እንኳ ነዋሪዎች ብዙ ደጅ መጥናትና መጉላላት ይኖርባቸዋል::

መሥሪያ ቤቶቹ የተቋቋሙለትን ተግባር ለመፈፀም የተመደቡት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ከተገልጋዩ ሕዝብ መደለያ እንዲከፈላቸው የሚፈልጉ ናቸው:: እኔም ለብዙ ዓመታት ደክሜ ያፈራሁትን ሀብት አምጥቼ አካባቢዬን ላልማ፣ ሕዝቤን ልጥቀም በማለት ሥራዎች ልከፍት ብሞክር ትብብር ላገኝ አልቻልኩም:: የምሠራበት ቦታ፣ የሥራ ፈቃድ፣ ወዘተ ለማግኘት ብዙ ተጉላላሁ:: ያም ሆኖ ሊሳካልኝ አልቻለም:: አንድ ዓመት ተጉላልቼ ስላልተሳካልኝ ትቼ ወደ ተውለደሬ መጣሁ::

**የተውለደሬ ድምፅ፣** በተውለደሬስ ይህ ችግር አልገጠመዎትም?

**አልቃድር፣** ስለተውለድሬ ብዙ መልካም ዝና ብሰማም በመጀመሪያ አላመንሁም ነበር:: መጥቼ ስሞክራቸው ግን እንኳንስ ገንዘቤን ሕይወቴን እንድሰጥ የሚያደርጉ ኃላፊዎች፣ መሥሪያ ቤቶችና ህዝብ ያላት ሥፍራ ሆና አገኘኋት:: በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ የመሥሪያ ቦታዎች፣ የሥራና የንግድ ፈቃዶች፣ ልዩ ልዩ ድጋፎችና ለጥቂት ዓመታትም ከታክስ ነጻ የመሆን እድል ሰጡኝ:: እዚህ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሚወቃቀሱት ስህተቶቻቸውን ለመተራረም፣ አሠራራቸውን ይበልጥ ቀልጣፋና ለተገልጋይ ምቹ ለማድረግ፣ በእውነትም ተውለደሬን ለማልማት ነው:: ምክር ይጠይቁሃል፤ ያዳምጡሃል፤ ለመማር ዝግጁ ናቸው፤ እርስ በርስም ይደማመጣሉ:: ከነዚህ ጋር መሥራት ምንኛ ደስይል መሰለህ?

**የተውለደሬ ድምፅ፣** ስለሰጡኝ አስተያየት በጣም አመሰግናለሁ::

**አልቃድር፣** እኔም አመሰግናለሁ::

**መልመጃ 1**

***ከዚህ በላይ የቀረበውን ቃለ ምልልስ መነሻ በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

?

1. የኩሸሽሌና የተውለደሬን ወረዳዎች በዴሞክራሲ ግንባታ፣ በመልካም አስተዳደርና በጋራ መግባባት ረገድ ምን እንደሚመስሉ አነፃፅሩ::
2. እናንተ የተውለደሬ ወረዳ ነዋሪዎች ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?
3. የኩሸሽሌ ወረዳ ነዋሪ ብትሆኑ ኖሮስ?

ዴሞክራሲ ባልሰፈነበት መከባበር፣ መተማመንና መደማመጥ አይኖርም:: ይልቁንም የጥቂቶች አምባገነንነት ስለሚደነድን የብዙሀን መጎዳት የማይቀር ነው:: ብዙሃኑ ለጋራ እድገት የሚያደርጉት መነሳሳት ይቀጫል፤ ማህበራዊ ልማትም ይጠፋል:: በተቃራኒው ግን የዴሞክራሲ ሥርዓት መገንባት፣ ተከትሎትም የጋራ መግባባት መፈጠርና የመልካም አስተዳደር መስፈን ማህበራዊ ፍትህ እንዲመጣና ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲከተል ስለሚያደርግ ሀገር ይበለፅጋል:: የጋራ መግባባትና የመልካም አስተዳደር መስፈንም መልሶ ዴሞክራሲውን ስለሚያጠናክር እድገቱ ቀጣይነት ይኖረዋል::

እኚህ ውጤቶች ግን በራሳቸው የሚመጡ አይደሉም:: በህብረተሰቡ ውስጥ እነዚህ ውጤቶች እውን እንዲሆኑ የሚያደርግ ጠንካራና ንቁ ተሳትፎ ያስፈልጋል:: ያለንቁ ህዝባዊ ተሳትፎ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ ተጠናክሮ አይገነባም፤ መልካም አስተዳደርም በዘላቂነት ሊሰፍን አይችልም:: እነዚህ ባልተሟሉበትም ልማትና ብልፅግና ሊረጋገጡ አይችሉም::


**መልመጃ 2**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

?

1. የዴሞክራሲን መስፈን ተከትለው ሊመጡ ከሚችሉት መልካም ነገሮች መካከል ሁለቱን ጥቀሱ::
2. ህዝቡ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታው ላይ ንቁ ተሳትፎ ባያደርግ ምን ሊከተል ይችላል?

### 10.1.2 የዜጎች ንቁ ተሳትፎ ለድህነት ቅነሳና ለፈጣን ልማት መረጋገጥ፤



ሥዕል 10.3 በመስኖ ሰፋፊ መሬቶችን ማልማት ይቻላል

• *ከሥዕሉ ምን ተገነዘባችሁ?*

#### *መስኖ አስተማማኝ የርሻ ልማት ዘዴ፤*

የሀገራችን የኢኮኖሚ መሠረት የሆነው የግብርና ሥራ ከዝናብ ጋር የተቆራኘ ነው:: የዝናቡ መጠንና ሽፋን ጥሩ ሲሆን ኢኮኖሚያችን መልካም እድገት ያሳያል:: የዝናብ መጠንና ሽፋን ባነሰ ቁጥር ኑሯችን ወደኋስቁልና ያሽቆለቁላል:: ይህ የዝናብ ጥገኝነታችን እስከመቼ እንዲቀጥል እንፈቅድለታለን? በተለይም የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ባለቤቶች ሆነን የዝናቡን ጥገኝነት የሙጥኝ ማለታችን አያስገርምም?

ሰሞኑን ወደ ምዕራብ ጎጃም ዞን የሰማነው ዜና ከዚህ ለመውጣት እንደምንችል የሚያመላክት ምሳሌ ነው:: በዞኑ ያሉ አርሶ አደሮች በራሳቸው ተነሳሽነት በባህላዊ መንገድ ሁለት ወንዞችን ጠልፈው የልማት ሥራዎችን አከናው ነዋል:: በዚህ መልክ ካለሙት 88 ሄክታር መሬትም ከፍተኛ ምርት አግኝተዋል:: ከጓሮ አትክልት ከፍራፍሬዎችና ፈጥነው ከሚደርሱ ሰብሎች ሽያጭ ከፍ ያለ ገቢ በማግኘት ኑሯቸውን እያሻሻሉ ይገኛሉ::

መስኖን በአማራጭነት ተጠቅመው በሕይወታቸው ላይ ለውጥ ማምጣታቸው ሁለት መሠረታዊ የግንዛቤ ለውጦች እንዳደረጉ ያሳያል:: አንደኛው ዝናቡን ብቻ እየጠበቁ መሥራት ከዘለቄታ አንፃር አስተማማኝ እንዳልሆነና ከዚህ ጥገኝነት መላቀቅ እንዳለባቸው ማመናቸው ነው:: ሁለተኛው ደግሞ አስተማማኝ ያልሆነውን ነገር የአመራረት ስልት በሌላ በተሻለ ስልት መተካት እንደሚቻል ርግጠኞች መሆናቸው ነው::

በመስኖ ተጠቃሚ የሆኑት እነዚህ አርሶ አደሮች በራሳቸው ተነሳሽነትና ጥረት በቀላሉ ከተረጂነት ለመላቀቅ የቻሉበትን ጅምር እንቅስቃሴ ልናደንቅ ይገባል:: ይበልጡንም ይህን የመሰለውን ጥረት በባለሙያዎች እገዛና በመንግሥት ድጋፍ ወደአጠቃላይ ግብርናና ወደ ድብልቅነት እንዲሁም ወደ ዘመናዊነት መለወጥ ያስፈልጋል:: በዚህም ከዓመት እስከዓመት የሚመረትበት የግብርና እንቅስቃሴ ማደራጀት አስፈላጊ ይሆናል:: አመራረቱ በግልና በአለት ቤተሰባዊና አካባቢያዊ ፍጆታነት ሳይወሰን ሰፋ ላለ የገበያ ፍላጎት እንዲሆን ሊደረግ ያስፈልጋል:: ይህንን የመሳሰሉ ለውጦች መደረጋቸው ብቻ ሳይሆን ለውጡ ፈጣንና የማያቋርጥ መሆኑን ማረጋገጥም ይገባል:: በቀድሚያ የድህነት ቅነሳ ጥረታችንን የሚያሳካ ሆኖ በቀጣይ ደግሞ ዘላቂ ልማታችንንና ፈጣን እድገታችንን የሚያረጋግጥ ሊሆን ይገባል::

#### መልመጃ ፫

*በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

1. በምዕራብ ጎጃም የተደረገው የአርሶ አደሮች የልማት ሥራ ለድኅነት ቅነሳ እንዴት አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል?
2. ይህን የአርሶ አደሮች መልካም የእድገት እንቅስቃሴ ጅምር እንዴት ወደፈጣንና የማያቋርጥ የልማት እንቅስቃሴ ለማሸጋገር ይቻላል?
3. የምዕራብ ጎጃም አርሶ አደሮች ያደረጉት ለውጥ ምን ያህል ንቁ ተሳትፎ ያካተተ ነው? ወደ ማያቋርጥ ፈጣን እድገት ለመራመድ ተሳትፏቸውን እንዴት ማድረግ ይኖርባቸዋል?

ድህነት በጣም ባጎሳቆላቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት በተለመደ ዓይነት የልማት እንቅስቃሴ ብቻ ከሚገኙበት አዘቅት ለመውጣት አይቻልም:: ጠንካራ የድህነት ቅነሳ ስልትን እየተጠቀሙ ፈጣን ሆኖ ቀጣይነቱ የተረጋገጠ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ ያስፈልጋል:: ይህ ይሆን ዘንድ ደግሞ መላው ህዝብ በቂ ግንዛቤ ጨብጦ በየበኩሉ አቅሙን፣ ገንዘቡንና እውቀቱን ማስተባበር ይገባዋል:: ይህን መሰል ፈጣን ልማት ሊረጋገጥ የሚችለው ሁሉም ዜጋ

በየተሰማራብት ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ውጤት ካስገኘ ነው።

**መልመጃ 4**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. በሀገራችን ፈጣን ልማት ማረጋገጥ ያስፈለገበት ምክንያት ምን ይመስላችኋል?
2. በኢትዮጵያ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ይመጣ ዘንድ በወሳኝነት ሊኖር የሚገባው ምንድነው? ለምን?

### 10.1.3 የዜጎች ንቁ ተሳትፎ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈን፣

✓ የዜጎች ንቁ ተሳትፎ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈን እንዴት ይጠቅማል።

**የርእሰ መምህሩ ዘገባ**

የተከበራችሁ የትምህርት ቤታችን መምህራንና ሠራተኞች፣ ውድ ተማሪዎች፣ ባለፈው ዓመት በትምህርት ቤታችን ግልጽነትና ተጠያቂነት የተረጋገጠበት አሰራር ለመዘርጋት እቅድ አውጥተን በጋራ ማፅደቃችን ይታወሳል፡፡ በዚህም ዓመት ይኸው እቅድ በተግባር ሲተረጎም ቆይቷል፡፡ በዛሬ ስብሰባ ይህንን እቅድ ተግባራዊ በማድረግ የተገኘውን ውጤት አቀርብላችኋለሁ፡፡

እንደምታወቁት በትምህርት ቤቱ የሚሰጡ ብዙ አገልግሎቶች አሉ፡፡ የነዚህንም አገልግሎቶች ምንነት፣ ለነማን እንደሚሰጡ፣ እንዲሁም በምን ዓይነት ሁኔታና በምን ያህል ጊዜ ሊሰጡ እንደሚችሉ ለይተን ዝርዝር አዘጋጅተን እንደነበረ ታስታውሳላችሁ፡፡ ለምሳሌ ለተማሪዎቻችን መልካም ዜጋ የሚያደርጋቸው ተግባራዊ ትምህርት መስጠትና ውጤታቸውን በተከታታይ ምዘና ማረጋገጥ ዋናው አገልግሎት እንደሆነ አስቀምጠናል፡፡ ለተማሪዎቻችን ቅንና ጠቃሚ የምክር አገልግሎት መስጠት ሌላው ተግባር እንደሆነ ለይተናል፡፡ የትምህርት ማስረጃዎቻቸውን በወቅቱ ልንሰጣቸው እንደሚገባም ተስማምተናል፡፡ ተማሪዎቻችን ከክፍል ውጪ በተግባራዊ ትምህርት እንዲታነፁ የተጓዳኝ ትምህርት እድሎች እያመቻቸን ልናሳትፋቸውም አቅደናል፡፡ ለተማሪዎቹ ወላጆች ወይም ለሞግዚቶቻቸው ስለልጆቻቸው የትምህርት አያያዝ ለማወቅ ስለሚሹ ፈጣንና ተገቢ ምላሽ ለመስጠት እቅድ ተይዟል፡፡



ሥዕል 10.4 የትምህርት ቤት አሠራር ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው ለሆን ይገባል

ከትምህርት ቤቱ ልዩ ልዩ መረጃ ለሚፈልጉ አግባብ ላላቸው አካላትና ግለሰቦች እንዲሁም ለጥናትና ምርምር ወይም ለተለያዩ ምክንያቶች መረጃ ለሚሹ ሕጋዊ ለሆኑ ሰዎች ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ሌላው የሚጠበቅብን አገልግሎት እንደሆነም አስቀምጠናል፡፡ ለመምህራንና ለትምህርት ቤቱ ሠራተኞችም ቀልጣፋና አርኪ የአስተዳደር አገልግሎት መስጠት የሚያስፈልግና የሚገባም እንደሆነ በአገልግሎታችን ዝርዝር ውስጥ አስቀምጠናል፡፡ ይህም ሥራችን ግልጽነትን እንዲያረጋግጥ መታመኑን ያሳያል፡፡

እንደምታስታውሱት ማንኛቸውንም የተጠቀሱትን አገልግሎቶች የሚፈልግ ሰው በቅድሚያ ያሉበትን ግዴታዎች ማሟላት እንደሚኖርበት በማመን ለያንዳንዱ ተገልጋይ ይህንኑ ዘርዝረን በግልጽ ቦታ አስተዋውቀናል፡፡ አያይዘንም ግዴታቸውን ላሟሉ ተገልጋዮች ቀልጣፋ፣ ተገቢና በአክብሮት የተሟላ አገልግሎት ባንሰጥ ወይም ምንም ዓይነት እንግልት ብናደርስ ተወቃሽ፣ ተጠያቂና ተከሳሽ ልንሆን ተስማምተናል፡፡ በሌላ አነጋገር የተጠያቂነትን መርህ ልንከተል ወስነናል፡፡

በዓመታዊው ክንውናችን እነዚህን ያስቀመጥናቸውን እቅዶች ተግባራዊ ለማድረግ ጥረናል፡፡ ጥቂት ጉድለቶች በተወሰኑ መምህራንና ሠራተኞች ዘንድ ከመከሰታቸው በቀር በአጠቃላይ መልካም ውጤቶችን አግኝተናል፡፡ ለምሳሌ አንድ መምህር ለተማሪዎች ተከታታይ ምዘና በአግባቡ ባለማካሄዳቸው፣ ውጤቱን መዝግበው ባለመያዛቸውና ለተማሪቹም ባለማሳወቃቸው ተቀጥተዋል፡፡

አንድ የአስተዳደር ሠራተኛም ለአንድ ትምህርት ቤቱን ለለቀቀ ተማሪ የትምህርት መረጃ ለመስጠት ብዙ ስላጉላሉትና በመጨረሻም የተሳሳተ መረጃ ስለሰጡት እንዲቀጡ ተደርገዋል፡፡ ከነዚህ ችግሮች ውጪ በአብዛኛው ጠንካራ ውጤቶች ተመዝግበዋል ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነ

በመሆኑም የዓመቱ ሥራችን ስኬታማ እንደነበር ተገምግሟል::
*ስለአዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ!*

**መልመጃ 5**

***ከዚህ በላይ የቀረበውን ዘገባ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. ርእሰ መምህሩ ከአቀረቡት ዘገባ ምን ተገነዘባችሁ?
2. እስከአሁን ባለው አሠራር ትምህርት ቤታችሁ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያረጋገጠ አሠራር አለው? ተጨባጭ ምሳሌዎችን በማቅረብ አስረዱ::
3. በትምህርት ቤታችሁ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያስፈልጋቸዋል የምትሏቸውን ሁለት ጉዳዮች ከነምክንያታቸው አቅርቡ::

በአንድ ህዝባዊ አገልግሎት በሚሰጥበት ሥራ "የግልጽነትና የተጠያቂነት አሰራር መኖሩ በውጤት ላይ ልዩነት ያመጣል/አያመጣም" በሚል ርእስ በቡድን ተከፋፍላችሁ በክፍል ውስጥ ክርክር አድርጉ:: በክርክሩ መጨረሻም ከሂደቱ ያገኛችሁትን ቁም ነገር ለመምህራችሁ አቅርቡ::

በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ከተገነባ ህዝቡ አስተሳሰቡን በነፃነት ለማራመድ ይችላል:: ይህም መደማመጥን ስለሚያስችል የጋራ መግባባት እንዲፈጠር ያደርጋል:: የመንግሥት አካላትም የህዝብ አገልጋዮች መሆናቸውን በመገንዘብ መልካም አስተዳደርን ያሰፍናሉ:: እንዲህ ያለው ሁኔታ ደግሞ ህዝብ ለልማቱ እንዲተጋ ስለሚያደርግ ልማት ይፋጠናል:: በህዝቡ ዘንድ ግንዛቤ እንዲዳብር ከተደረገ ከሚፈለገው የዕድገት ደረጃ ለመድረስ ፈጣንና የማያቋርጥ ልማት ለማስመዝገብ ከፍ ያለና ንቁ ህዝባዊ ተሳትፎ ለማድረግ ይቻላል::

የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባትና የመልካም አስተዳደር መስፈን ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ በመንግሥት አሠራር የግልጽነትና የተጠያቂነት መርኅ ተግባራዊ ሆኖ መታየት ነው:: ማንኛውም መንግሥታዊ አካል ለህዝብ የሚሰጠውን የአገልግሎት ሁኔታ፣ አገልግሎቱ ሊያስገኝ የሚችለውን ውጤት፣ ለዚሁም የሚከተለውን የአሠራር ስልት፣ ወዘተ ግልጽ በማድረግ በዚሁ መለካት ይኖርበታል::

እነዚህን በግልፅ ያስቀመጣቸውን አሠራሮች በመከተል ካልሠራና ተገቢውንም ውጤት ካላስገኘ የሚጠየቅበት፣ የሚወቀስበትና የሚከሰስበት ሥርዓት መኖር አለበት:: እነዚህ ሁሉ እውን መሆን የሚችሉት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ ከኖረ ነው:: በመሆኑም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ መጠበቅ ይኖርበታል:: ያለንቁ ህዝባዊ ተሳትፎ ዴሞክራሲውም ሆነ ከሱ የሚፈጠሩት የጋራ መግባባት፣ መልካም አስተዳደር እንዲሁም ፈጣን ልማት ሊረጋገጡ አይችሉም::

**መልመጃ 6**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::***

1. ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት አስተዳደር መኖሩ እንዴት ይታወቃል? መልካም አስተዳደር ሰፍኗል ሲባልስ የሚችለው ምን ሲታይ ነው?
2. ፈጣን የኢኮኖሚ ልማት ሲባል ምን ማለት ነው?
3. ለመልካም አስተዳደርና ለፈጣን ልማት መረጋገጥ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ቅድመ ሁኔታ ነው ቢባል ትስማማላችሁ? ለምን?
4. ለመልካም አስተዳደር፣ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ለፈጣን ልማት መረጋገጥ ከህዝብ ምን ይጠበቃል?

| ዓ.ም. | በጥሬ ገንዘብ | በጉልበት | በቁሳቁስ | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 1996 | 9037861.38 | 8254753.58 | 8635715.00 | 25928329.96 |
| 1997 | 39007287.91 | 52868978.92 | 26818768.85 | 118695035.70 |
| 1998 | 16938779.97 | 28753391.95 | 11822624.08 | 57514796.00 |
| 1999 | 10836418.18 | 17408596.31 | 13492739.00 | 41737753.49 |
| 2000 | | | | 59501332.27 |
| *ጠ/ድምር* | *75820347.44* | *107285720.80* | *60769846.93* | *4435414843* |

ሠንጠረዥ 1፣ በአማራ ክልል ህብረተሰቡ በልዩ ልዩ ማህበራት ተደራጅቶ በመሳተፍ ለትምህርት ልማት ያበረከተው አስተዋጽኦ *(ምንጭ ከአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የትምህርት ቢሮ የ15 ዓመት የትምህር እንቅስቃሴ የሚሌኒየም ፌስቲቫል መጽሔት፣ ግንቦት 2000፣ገጽ126 የተወሰደ::)*

## 10.2 የሲቪክ ማህበራት፤

### 10.2.1 በሲቪክ ማህበራት መሳተፍ ለሀገር ልማት የሚኖረው ጠቀሜታ፣

በመረጃው መሠረት ለክልሉ ትምህርት ልማት ህብረተሰቡ ያደረገውን ድጋፍ መንግሥት ከመደበው በድምሩ ብር 2675315103.37 ከሚሆነው ገንዘብ ጋር በማነፃፀር ልዩነቱን ግለጹ፡፡ ህብረተሰቡ በመረጃው የቀረበውን ድጋፍ ለትምህርት ልማት ለማሰባሰብ የቻለው እንዴት ባለ አደረጃጀት ተሰባስቦ ይመስላችኋል?



ሥዕል 10.5 የሴቶች ስብሰባ

#### ቅመሚትና ባልደረቦቿ

ቅመሚት በጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካው የሴት ሠራተኞች ማህበር ውስጥ ከተራ አባልነት እስከ አመራር ደረጃ በንቃት ተሳትፋለች፡፡ ተናግራ የምታሳምን፣ በተግባር የምታምንና ቆራጥና ቁርጠኛ የማህበሩ አባል ስለሆነች ሌሎቹ ቅመሚት የሚል ስም ሰጥተዋታል፡፡ በእውነተኛ ስሟ የሚጠራት የለም፡፡

ከፋብሪካው ሠራተኞች ሁለት ሦስተኛው ሴቶች ናቸው፡፡ በፊት በተመሳሳይ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሴቶች ከወንዶች ያነሰ ክፍያ ነበራቸው፡፡ የሥራ ሁኔታም ሆነ የሰራተኞች ጥቅሞችና መብቶች የሴቶችን ሁኔታ ያላገናዘቡ ነበሩ፡፡ በዚህ ላይ በርካታ ሴቶች በፆታቸው ምክንያት ብቻ ብዙ ችግሮች ይደርሱባቸው ነበር፡፡ ብዙውን ጊዜ ፆታዊ ጥቃቶችም ያጋጥሟቸው ነበር፡፡

ፋብሪካው የሚገኘው ከከተማው ዳርቻ ላይ በመሆኑም ሴት ሠራተኞች ከፋብሪካ ውጪ በርካታ ችግሮች ነበሩባቸው፡፡ ፋብሪካው በቂ የትራንስፖርት አገልግሎት ስለሌለው ሴት ሠራተኞች ረዥም መንገድ ለመሄድ ይገደዱ ነበር፡፡ ከበርካታ ድካም በኋላ ከሥራ ወጥተው የእግር ጉዞ ማድረግ አንዱ ችግር ነበር፡፡ በምሽትም ሆነ በቀን ጭር ባለ መንገድ ሲጓዙ የሚደርሱባቸው የወሮበላ ንጥቂያዎችና ፆታዊ ጥቃቶችም ነበሩ፡፡

ቅመሚት እነዚህን ተጨባጭ የሴት ሠራተኞች ችግሮች ልቅም አድርጋ በማጥናት በሠራተኛ ማህበር እንቅስቃሴ መፍትሔ ለማምጣት ጥረት አድርጋለች፡፡ ማህበሩ ግን እንደምትጠብቀው

የሴቶቹን ችግር በተለየ ትኩረት በማየት ለመፍትሔው መታገል አልቻለም፡፡ በጥረቱም አልረካችም፡፡ በመሆኑም የሴት ሠራተኞች ማህበር እንደቅርንጫፍ መደራጀት እንዳለበት አመነች፡፡ ከብዙ ውጣ ውረድና ትግል በኋላ በብዙኃኑ ሴት ሠራተኞች ጠንካራ ትብብር ተሳካላት፡፡ እሷ በሊቀመንበርትነት ተመረጠች፡፡ እነሆ ከዚያ ወዲህ የሴት ሠራተኞች ማህበር መላውን ሴት ሠራተኞች አነቃንቋል፡፡ በጥሩ እንቅስቃሴዎቻቸውም በፋብሪካ ያሉት የሴት ሠራተኞች ችግሮች እንዲፈቱ አድርጓል፡፡ ዛሬ በሴትና በወንድ ሠራተኞች መካከል የጥቅምና የመብት ልዩነት የለም፡፡ ከፋብሪካ ውጪም ይገጥሙ የነበሩትን ችግሮች ከፋብሪካው አስተዳደር፣ ከፖሊስ፣ ከሌሎችም አግባብ ካላቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት እንዲሁም ከአካባቢው ሕብረተሰብ ጋር በመቀ ናጀት እንዲፈቱ ተደርጓል፡፡

ዛሬ በፋብሪካው ፍጹም ሰላም አለ፡፡ ሴት ሠራተኞች ያለ ሐሳብ በሥራ ቦታና ከፋብሪካም ውጪ መንቀሳቀስ፣ እንደልብ መውጣትና መግባት ችለዋል፡፡ በፋብሪካው አስተዳደር ጥሩ ተሳትፎ አላቸው፡፡ የሠራተኞችን መብትና ጥቅም በማረጋገጥ፣ የሥራን ምርታማነት በሚመለከትና በማናቸውም ውሳኔዎች ጭምር ሴቶቹ እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡ ፋብሪካውም የበለጠ ምርታማ እየሆነ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በደንብ እየደገፈ ይገኛል፡፡ ይህ ሁሉ አባላቱ ባደረጉት ንቁ ተሳትፎ የተቋቋመው የሴት ሠራተኞች ማህበር ከመላው ሠራተኞች ማህበር ጎን ሆኖ በጥንካሬ በመንቀሳቀሱ የተገኘ ውጤት ነው፡፡

**መልመጃ 7**

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. በታሪኩ ውስጥ የጎላ ሚና የተጫወተ የሲቪክ ማህበር አለ? ካለ ምን ሚና ተጫውቶ ምንስ ውጤት አስገኝቷል?
2. በታሪኩ መሰረት በፋብሪካው እንቅስቃሴ በዴሞክራሲ ግንባታ፣ በሰላምና በልማት ረገድ የተገኙትን ውጤቶች በዝርዝር አቅርቡ::
3. በፋብሪካው ለውጥ ላይ የሠራተኞች ንቁ ተሳ ትፎ ነበር? ምን ጠቀሜታ ወይም ጉዳት እን ደነበረው አስረዱ::
4. አንተ/አንቺ የዚህ ፋብሪካ ሠራተኛ ብትሆኑ ኖሮ በዚህ ትግል ወቅት ምን ታደረጉ ነበር? ለምን?

ለአንዲት ሀገር በልማት መገስገስ መሠረቱ የሰላም መስፈንና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገ ንባት ነው:: ይህም እውን ይሆን ዘንድ የመላው ህዝብ ንቁ ተሳትፎ ወሳኝ እንደሆነ ተረጋግ ጧል:: ህዝብም ለሰላም፣ ለዴሞክራሲና ለልማት በተናጠል ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ይልቅ በልዩ ልዩ መልክ እየተደራጀ የሚያከናውነው አስተ ዋጽኦ ከፍ ያለ ውጤት ያስገኛል::

የሲቪክ ማህበራት ሚና ጎልቶ የሚመጣው እዚህ ላይ ነው:: ብርቱ አመራርና ቁርጠኛና ታታሪ አባላት ያሉት፣ ግልጽ የልማት ራዕይ ያነገበ፣ ጠንካራ የሲቪክ ማህበር የማይፈታው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር አይኖርም:: በመሆኑም እንዲህ ያለ የሲቪክ ማህበር ዴሞክ ራሲን ለመገንባት፣ ሰላምን ለማንገስና ኢኮኖሚ ያዊ እድገትን ለማረጋገጥ የማያጠራጥር አቅም አለው::

**መልመጃ 8**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

1. በአንድ ሀገር ሰላም፣ ዴሞክራሲና ልማ ትን በማረጋገጥ እድገትን ለማምጣት ህዝብ በምን መልክ ቢንቀሳቀስ ይሻላል?
2. የሲቪክ ማህበር ሰላምን፣ ዴሞክራሲንና ልማትን በማስፈን ረገድ ያለው ሚና ምን ይመስላል?

### 10.2.3 በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ መንግሥትን ለማትጋትና ለመቆጣጠር በሲቪክ ማህበራት መሳተፍ፣

✓ *በሲቪክ ማህበር በመሳተፍ እንዴት መንግሥትን ማትጋትና መቆጣጠር ይቻላል?*



ሥዕል 10.6 የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ፎረም አጠቃላይ ስብሰባ

**የአዲስ አበባ ከተማ የነዋሪዎች ፎረም**

በአዲስ አበባ ከተማ በ1999 ዓ.ም በተለያዩ የህብ ረተሰብ ክፍሎች ቀደምት አደረጃጀቶች ላይ በመ መሥረት በየቀበሌው የነዋሪዎች የጋራ ፎረሞች ተቋቁመዋል:: ዋናዎቹ የፎረሞች መሠረቶች የወጣቶችና የሴቶች ማህበራት ናቸው:: በኋላም ከተማ አቀፍ ወደ ሆነ የነዋሪዎች ፎረም ተጠቃ ሏል::

ፎረሙ በዋናነት የሴቶችን፣ የወጣቶችን፣ እንዲ ሁም የዝቅተኛውንና የመካከለኛውን የህብረተሰብ ክፍል ችግሮችን ማዕከል በማድረግ መንቀሳቀስ ቀጥሏል:: የሥራ አጥነት፣ የሰላምና የፀጥታ ችግር፣ የመልካም አስተዳደር እጦት፣ የኑሮ ውድነት መባባስ፣ የመሳሰሉትን ችግሮች ዋና መንቀሳቀሻ ጉዳዮቹ አድርጓል:: በአጠቃላይ የአ ዲስ አበባ የልማት እንቅስቃሴዎች መቀዛቀዝም ሌላው ዐቢይ ትኩረቱ ሆኗል:: ፎረሙ ከከተ ማው አስተዳደር ከፍተኛ ኃላፊዎች ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቶ ሒስ በመስጠት የተፋዘዘውን የከተማ አስተዳደር እንቅስቃሴ ለማንቃት ችሏል:: በአስተዳደሩ ልዩ ልዩ መሥሪያ ቤቶች አካባቢ እየጎላ የመጣውን የሙስናና የአድሏዊ አሠራሮችን መስፋፋት ይፋ እያደረገ ታግሏል:: ከፌዴራል መንግሥት ኃላፊዎችም ጋር በመወ ያየት የህዝቡን ተጨባጭ ችግሮች አስተጋብ ቷል:: የመንግሥትንም ድክመቶች ለማሳየት ችሏል:: በጋራ በተካሄዱ ውይይቶችም ጥሩ የመፍትሄ ርምጃዎች እንዲወሰዱ ድርሻውን አበርክቷል:: ችግሮቹ በፍጹም እስኪወገዱ ድረስ ፎረሙ ትግሉን አጠናክሮ መቀጠል ያለበት ቢሆንም በእስከአሁኑ ጥረቱ ግን ችግሮቹ በጎላ መልክ እየቀነሱና የከተማዋም የተቀዛቀዘ እንቅስ ቃሴ ነፍስ እየዘራ መጥቷል::

## መልመጃ ፱

*ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማ ድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. የአዲስ አበባ ከተማ የነዋሪዎች ፎረም የሲ ቪክ ማህበር ነውን? ለምን?
2. ፎረሙ በከተማይቱ ለሰላም፣ ለልማትና ለዴሞክራሲ መጠናከር እንዲሁም መንግ ሥትን ለማትጋትና ለመቆጣጠር ያደረገው አስተዋጽኦ ምን ይመስላል? ምን ውጤትስ አስገኝቷል? በበለጠ ምን ሊያከናውን ይችል ነበር?
3. በፎረሙ ውስጥ ግለሰብ አባላት ምን ዓይ ነት ተሳትፎ ሊያደርጉ ይገባል?
4. ከአዲስ አበባ የነዋሪዎች ፎረም ሌሎች ከተ ሞችና አካባቢዎች ሊያገኙ የሚችሉት መል ካም ተሞክሮና ትምህርት አለ የምትሉ ከሆነ እስቲ ግለጹ፡፡

የሲቪክ ማህበራት ከመንግሥት ቁጥጥር ነፃ የሆኑና ለአትራፊነት የማይሠሩ የህዝብ አደ ረጃጀቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ለህዝቡ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና፣ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አስተዋጽኦ ለማድ ረግ የሚቋቋሙ ማህበራት ገንቢ እንቅስቃሴ ያደርጉ ዘንድ የሕዝቡን ንቁ ተሳትፎ ይሻሉ፡፡ በተለይም በዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ውስጥ የሕዝ ቡን የእለት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግርን በማቃለል በኩል ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡

ሕዝቡ የዴሞክራሲ ባህልን እንዲያዳብር የሚጫ ወቱት ሚናም ከፍተኛ ነው፡፡ በማህበሩ ውስጥ ነጻ ተሳትፎ ማድረግን፣ የአመራር አባላትን መምረጥን፣ እምነት ሲያጡበት ከኃላፊነት ማው ረድን፣ የመሳሰሉ የዴሞክራሲያዊ አሠራሮች ልምምድ ያካሂዱበታል፡፡ ሕዝቡን ከመንግሥት ጋር በማገናኘት መንግሥት ኃላፊነቱንና ግዴታ ውን በአግባቡ እንዲወጣ በማድረግ ረገድ የሚኖራቸው አስተዋጽኦ የማይናቅ ነው፡፡ መንግሥትን ይህን ማድረግ ሲገባህ አላደረግህም እያሉ ለመውቀስና ለመቆጣጠር ስለሚችሉ ያላቸው ህዝባዊ ሚና ወደር የለውም፡፡

## መልመጃ 10

*በሚከሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡*

1. የሲቪክ ማህበራት ከሌሎች ድርጅቶች በምን ይለያሉ?
2. የሲቪክ ማህበራት ምን ጥቅሞችን ያስገ ኛሉ?
3. በሲቪክ ማህበራት በንቃት መሳተፍ ያስፈል ጋልን? ለምን?
4. በትምህርት ቤታችሁ ምን ዓይነት የሲቪክ ማህበራት ሊኖሩ ይችላሉ? በነዚህ ሲቪክ ማህበራት ውስጥ የያንዳንዳችሁ ሚና ምን ሊሆን ይገባል?

© MoE, Not to be republished

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የጋራ መግባባት እንዲኖር፣ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን፣ በመንግሥታዊ አካላት ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሠራር እንዲረጋገጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት እንደሚኖርበት ተመልክተናል፡፡ እነዚህ ፈጣን እድገት እንዲረጋገጥ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ቅድመሁኔታዎች እንደሆኑም ተገንዝበናል፡፡ ሁሉም እውን እንዲሆኑና በዘላቂነትም ለመቀጠል እንዲችሉ የሚንከባከባቸውና የሚጠብቃቸው የማያቋርጥ ንቁ ህዝባዊ ተሳትፎ ሲኖር እንደሚገባ በሰፊው አይተናል፡፡

ታዲያ እንዲህ ያለው የህዝብ ተሳትፎ ውጤታማ የሚሆነው በተናጠል በሚካሄድ እንቅስቃሴ ሳይሆን ህዝቡ በተለያየ መንገድ እየተደራጀ በሚያደርገው እንቅስቃሴ እንደሆነ ጥርጥር የለውም፡፡ የሲቪክ ማህበራት ለሰላም መከበር፣ ለዴሞክራሲ መጎልበትና ለፈጣን እድገት መረጋገጥ ህዝቡ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የሚሳተፍባቸው መድረኮች ናቸው፡፡ እነዚህ ማህበራት አንዳንዴም በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ህዝቡ መንግሥትን ለመቆጣጠርና በወሳኝ ነገሮች ላይ መንግሥት እንዲተጋ ለማሳሰብ የሚረዱ መድረኮች ናቸው፡፡ በመሆኑም በሲቪክ ማህበራት ውስጥ እያንዳንዳችን ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ሰላማችንን በዘለቄታ ለማስፈን፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓታችንን ለማጠናከር፣ እንዲሁም ቀጣይነቱ የተረጋገጠ ፈጣን ልማታችንን ለማረጋገጥ መጣር ይኖርብናል፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**መልካም አስተዳደር:-** አድሎ የሌለበት፣ ከሙስና የፀዳ፣ ቀልጣፋና ተገቢ አገልግሎት የሚገኝበት (የሚንፀባረቅበት) አስተዳደር::

**ግልጽነት:-** የመንግሥት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሕግን ብቻ ተከትለውና አግባብ የሆነ አሰራር መሆኑን የሚያረጋግጡበት፣ የሚፈፅሙትና የሚወስኑበት አሠራር::

**የፆታ ጥቃት:-** ሰዎች በሴቶች ላይ የሚያደርሱት ልዩ ልዩ መልክና ደረጃ ያለው አካላዊና ሥነልቡናዊ ጉዳት የሚያደርስ ችግር::

**የጋራ መግባባት:-** ልዩነት እንደተጠበቀ ተነጋግሮና ተደማምጦ በሚያስማሙ ጉዳዮች ላይ ስዘላቂ የጋራ ግብ አብሮ መሥራት::

**ፎረም:-** የጋራ ዓላማ ያላቸው ቡድኖች በጋራ ለመንቀሳቀስ የሚያቋቁሙት ኅብረት::

**ተጠያቂነት:-** የመንግሥት ኃላፊዎችና ሠራተኞች በሚፈጽሙትና በሚወስኑት ነገር እንደሁኔታው የሚመስገኑበትና የሚሸለሙበት አሊያም የሚጠየቁበት የሚከሰሱበትና የሚቀጡበት ሥርዓት::

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

**I የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ::**

1. የዴሞክራሲያዊ ሁኔታን መጓደል ሊያንፀባርቁ ከሚችሉት ነገሮች መካከል አንዱ የግለሰብ ኃላፊዎች አምባገነንነት ነው::
2. ለድኅነት ቅነሳ አስተዋጽኦ የሚያደርገው ልማትን ማፋጠን ነው::
3. ለፈጣን እድገት መረጋገጥ ወሳኙ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ሳይሆን የተፈጥሮ ሀብት መብዛት ነው::
4. መልካም አስተዳደር እንዲኖር ከግልጽነትና ከተጠያቂነት አንዱ ብቻ መረጋገጡ በቂ ነው::
5. ሲቪክ ማህበራት ለዴሞክራሲና ለሰላም ያላቸው ጠቀሜታ ውስን ቢሆንም ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው ግን እጅግ ከፍተኛ ነው::

**II በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ተጠያቂነት፣ | ሀ. በመረጡት ሰው አማካኝነት መተዳደር/መሥራት። |
| 2. ሲቪክ ማህበር፣ | ለ. ለፈጸሙትና ለወሰኑት ተግባር ኃላፊነትን መውሰድ። |
| 3. ቀጥተኛ ተሳትፎ፣ | ሐ. የሚያከናውኑትን ነገር ምስጢር ያለማድረግ። |
| 4. የውክልና ተሳትፎ፣ | መ. መንግሥትን ማትጋትና መቆጣጠር። |
| 5. የሲቪክ ማህበራት ተግባር፣ | ሠ. በፖለቲካዊ ጉዳይ በየግል መንቀሳቀስ። |
| | ረ. በሚያከናውኑት ተግባር ትርፋማ መሆን። |
| | ሰ. አንድ ዓይነት የህዝብ አደረጃጀት። |

**III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ::**

1. መልካም አስተዳደር ተጓድሏል ሊያሰኙ ከሚችሉት መካከል አንዱ ---------- ነው፤
   ሀ. የሙስና መኖር፣ ሐ. የአድሎ አሠራር፣
   ለ. የባለጉዳዮች መጉላላት፣ መ. ሁሉም ትክክል ናቸው::
2. ሲቪክ ማህበራት ከሚያከናውኗቸው ተግባራት አንዱ፤
   ሀ. የመንግሥትን ፖሊሲዎች ማስፈፀም፣
   ለ. ሕዝብን በልማት፣ በሰላምና በዴሞክራሲ እንቅስቃሴ ማሳተፍ፣
   ሐ. ለመንግሥት ሕዝብን የሚቆጣጠርበት መሣሪያ ሆኖ ማገልገል፣
   መ. ሁሉም ትክክል ናቸው::
3. የያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል ሚና በሌላ ሊተካ አይችልም ሲባል -------ማለት ነው፤
   ሀ. በህብረተሰብ ዘንድ የሥራ ክፍፍል መኖር ይኖርበታል፣
   ለ. አንድ የህብረተሰብ ክፍል በሚያከናውነው ሌላው ጣልቃ መግባት የለበትም፣
   ሐ. እያንዳንዱ ክፍል ካለው ልዩ ባህርይ የተነሳ ሌላው ወገን ሊያሟላ የማይችለው ነገር አለው፣
   መ. ሁሉም ትክክል ናቸው::
4. የዴሞክራሲን መጠናከር ሊያደናቅፉ ከሚችሉት መካከል የሚቆጠረው፤
   ሀ. የርሰበርስ ሽኩቻና መናቆር፣ ሐ. ርስበርስ ያለመደማመጥና ያለመቻቻል፣
   ለ. ገንቢ ትችትን ለመቀበል አለመቻል፣ መ. ሁሉም ትክክል ናቸው::
5. የሲቪክ ማህበራት መንግሥትን ለማትጋትና ለመቆጣጠር እንዲችሉ፤
   ሀ. ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ባለበት ሁኔታ ውስጥ መገኘት አለባቸው፣
   ለ. ከመንግሥት አመራር ማግኘት ይኖርባቸዋል፣
   ሐ. ከመንግሥት ላቅ ያለ ሥልጣን ሊያገኙና ከመንግሥት ቁጥጥር ነፃ ሊሆኑ ይገባል፣
   መ. ሁሉም ትክክል ናቸው::

**IV የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::**

1. አንድ ሕዝብ በማህበረ ኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርግባቸው ሁለት መንገዶች------------ ተሳትፎና ----------------- ተሳትፎ የሚባሉት ናቸው::
2. በንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ታጅቦ መፈፀም ያለበት ልማት ፈጣን ብቻ ሳይሆን-------- መሆንም ይኖርበታል::

**V የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡**

1. ከመልካም አስተዳደር እጦት የተነሳ ሊደርሱ ከሚችሉ ችግሮች ሦስቱን ጥቀሱ::
2. ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ለመልካም አስተዳደር መገኘት ሊያበረክት የሚችላቸውን ሁለት ነገሮች ግለጹ::



© Not to be republished

# ምዕራፍ አስራ አንድ
# እውቀትን መሻት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤**

- ዕውቀት የሚዳብርባቸውን መንገዶች ትረዳለህ/ትረጂያለሽ፡፡
- ዕውቀት አገልግሎት ላይ የሚውልባቸውን መንገዶች ትረዳለህ/ትረጂያለሽ፡፡
- የመረጃን አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ትረዳለህ/ትረጂያለሽ፡፡
- ኋላቀር አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን መዋጋት ተገቢ መሆኑን ትረዳለህ/ትረጂያለሽ፡፡

## 11.1 ዕውቀት የሚዳብርባቸው መንገዶች፤



ሥዕል 11.1 የአፍሪካ ዝሆን



ሥዕል 11.2 አትሌት ጥሩነሽ ዲባባና ቀነኒሳ በቀለ

- *እናንተ ከዚህ በላይ በቀረቡት ሥዕሎች ዙሪያ ዕውቀታችሁን ማዳበር ብትፈልጉ ምን ምን መንገዶችን ልትጠቀሙ እንደምትችሉ ግለጹ፡፡*
- *ዕውቀት ከየት ከየት ከሚገኙ መረጃዎች ሊዳብር ይችል ይመስላችኋል?*


***የቡድን ሥራ፣***


መምህር ኡጁሉ ተማሪዎቻቸው በአራት ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ ዕውቀትን ሊያዳብሩ የሚችሉ ነጥቦችን እንዲያቀርቡ ጠየቋቸው፡፡ ተማሪዎቹም ርእሰ ጉዳዮቹን በቡድን ተከፋፍለው ሊያዳብሯቸው የሚችሉ ነጥቦችን አሰሳ ተሰማሩ፡፡ ሥራቸውንም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አጠናቀው አቀረቡ፡፡

በመምህሩ የተሰጡት ርእሰ ጉዳዮች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

- የዐድዋ ድል እንዴት ሊገኝ ቻለ? (ለከድጃ ቡድን የደረሰ ርእስ)
- የጋምቤላ ብሔራዊ ክልል አቀማመጥና የአየር ጠባይ (ለበርሔ ቡድን የደረሰ ርእስ)
- የንቦች ማኅበራዊ አኗኗር ምን ይመስላል? (ለቦንቱ ቡድን የደረሰ ርእስ)
- የውሃ ብክለት በእርግጥ የጤና ጠንቅ ይሆናል? (ለአዱኛ ቡድን የደረሰ ርእስ)

በሚቀጥለው ክፍለጊዜ ተማሪዎቹ እነዚህን ነጥቦች የሚያዳብሩ በቂ ሐሳቦችን በየቡድናቸው ይዘው ቀረቡ፡፡ ማዳበሪያ ነጥቦቹም ከተለያዩ ምንጮች መገኘታቸው በሚከተለው ሁኔታ ይታያል፡፡





## የሬዲዮ ፕሮግራም

ስለንቦች ማህበራዊ አኗኗር ብታስረዱኝ!







ሥዕል 11.4 ዕውቀት ከሚዳብርባቸው ሁኔታዎች ጥቂቶቹ።

1. *ከሥዕሎቹ እንደምታስተውሉት፣ እያንዳንዱ ቡድን በተሰጡት ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ ያለውን ዕውቀት ሊያዳብሩለት የሚችሉትን ነጥቦች ከምን ከምን ምንጮች አገኘ ማለት ይቻላል?*
2. *በአጠቃላይ ስንመለከተው ካሉት የዕውቀት ምንጮች ሁሉ የበለጠ አስተማማኝና ቋሚ ዕውቀት የሚገኘው ከየትኛው ነው? ለምን ይመስላችኋል?*

የሰው ልጅ አዘውትሮ ዕውቀትን መሻት የተፈጥሮ ባሕርይ ነው። ራሱን የሚያሻሽለውም ሆነ ሀገሩን ሊያለማ የሚችልው በዕውቀት ሲበለጽግ መሆኑን ይገነዘባል። ለዚህም ነው እያንዳንዱ ሰው በዕድሜ ከፍ ሲል ወደ ትምህርት ቤት እንዲገባ የሚመከረው። ሰው ዕውቀት ባገኘ ቁጥር በአስተሳሰቡ እየበሰለ ችግር የመፍታት አቅሙም እየጎለበተ ይሄዳል። የሰው ልጅ ዕውቀቱን የሚያበለጽገው የተለያዩ የዕውቀት ምንጮ ችን እንደመሣሪያ እየተጠቀመ ነው።

የእውቀት ማበልጸጊያ መንገዶቹም ባጠቃላይ በአራት ሊከፈሉ ይችላሉ። እነሱም መደበኛ ትምህርት፣ መደበኛ ያልሆነ ትምህርት፣ መገናኛ ብዙኃንና ንባብ ናቸው። ሰዎች የተጠናከረና ዘላቂነት ያለው ዕውቀት ለማግኘት አስቀድመው የሚመርጡት ትምህርት ቤት ነው። በትምህርት ቤት በየሙያ መስኩ በሚገባ የሰለጠኑ መምህራን ይገኛሉ። የመማሪያ ቁሳቁሶችም በተለየ ሁኔታ ተደራጅተው ይቀርባሉ። የትምህርት አቀራረቡም የተማሪዎችን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ፣ በሳይንሳዊ መንገድ በተቀረጸ ሥርዓተ ትምህርት የተቀየሰ ስለሆነ አስተማማኝነት ያለው ነው።

ከትምህርት ቤት በተጨማሪ ከራሳችንና ከሰዎች ተሞክሮም ብዙ ዕውቀት እንደምናገኝ የታመነ ነው። ይኸውም ነገሮችን በጥልቀት በመመልከት፣ ከሰዎች ጋር በመነጋገር ወይም በመከራከር፣ በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ በመሳተፍ ሊሆን ይች ላል። ለምሳሌ በምንኖርበት ትንሽ ከተማ ውስጥ ያሉ ሕጻናት በተቅማጥ በሽታ ሲሰቃዩ

እንመለከት ይሆናል:: "መነሻው ምንድነው?" ብለን ራሳችንን እንጠይቃለን:: ምናልባት በከተማው ብዙ ሰዎች የወንዝ ውሃን በመጠጥነት ይጠቀሙ ይሆናል:: ይህ ተደጋግሞ የሚከሰት በሽታ መንስኤው የውሃ ብክለት መሆኑን እንረዳለን፣ ግንዛቤ አገኘን ማለት ነው:: ከዚያም ሕዝቡ እንዲነጋገርበት እናደርጋለን:: በመጨረሻም ነዋሪው "ንጽሕናው የተጠበቀ ውሃ በማቅረብ ሕጻናትን ከውሃ ወለድ በሽታዎች መታደግ አለብን!" የሚል አቋም ይይዛል:: ከዚያን ቀን ጀምሮም ንጹሕ ውሃ ለማቅረብ አስፈላጊውን ጥረት ሲያደርግ እናስተውላለን::

ከዚህ ተሞክሮ ቢያንስ ሁለት ነገሮች ተምረናል:: በአንድ በኩል የተበከለ ውሃ ለጤና ጠንቅ መሆኑን ሲሆን፣ በሌላ ወገን ደግሞ ሕዝብ ከተባበረ ለአንድ ትልቅ ኃላፊነት በጋራ ሊነሳ እንደሚችል እንገነዘባለን:: ይህ እንግዲህ መደበኛ ባልሆነ መንገድ ዕውቀት ማዳበርን ያመለክታል::

እንደ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣና መጽሔት የመሳሰሉትን ምንጮች የሚከታተሉ ሰዎች ስለአካባቢያቸው፣ ስለሀገራቸውና በጠቅላላውም ስለዓለም የሰፋ ግንዛቤ ይኖራቸዋል:: እኛም አስፈላጊ ሲሆን፣ ልንረዳ የምንሻቸውን ጉዳዮች ወይም ጥያቄዎች በስልክና በደብዳቤ ለእነዚህ ምንጮች ብናቀርብ የተለያዩ ባለሙያዎችን አማክረው ወይም አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን አንብበው መልሶችን ያቀርቡልናል:: ለምሳሌ ስለንቦች ማኅበራዊ አኗኗር ጥያቄዎች ቢኖሩንና ለኢትዮጵያ ሬዲዮ ብንጽፍ ጋዜጠኞቹ የመስኩን ባለሙያ በማነጋገር ወይም በጉዳዩ ዙሪያ የተጻፉ መረጃዎችን በማቅረብ አጥጋቢ ምላሽ ሊያቀርቡልን ይችላሉ::

የበለጸገ ዕውቀት በማስገኘት ረገድ ሰፊውን ቦታ ከሚይዙት ዘዴዎች አንዱ ንባብ ነው:: ለምሳሌ ስለአድዋ ድል በስፋት ማወቅ ብንፈልግ በጉዳዩ ዙሪያ የተጻፉ በርከት ያሉ መጻሕፍት ስላሉ እነሱን ማንበብ እንችላለን:: በዚሁ ዓይነት በሁሉም የዕውቀት ዘርፎች ዙሪያ በስፋት ማንበብ የጠለቀ ዕውቀት ለመጨበጥ የሚኖረው ድርሻ ተወዳዳሪ የለውም::

**መልመጃ 1**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::***

?

1. በሚከተሉት ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ በቂ ዕውቀት ለማዳበር ከአራቱ ዘዴዎች የትኛው በበለጠ እንደሚረዳ ተወያዩና ወስኑ:: ለእያንዳንዱ ውሳኔያችሁም ዝርዝር ምክንያቶቻችሁን አቅርቡ::
2. የባለፈውና የዚህ ዓመት የኑሮ ውድነት ሲነጻጸር ምን አጠቃላይ መመሳሰልና ልዩነት ይስተዋላል?
3. የሰዎች ንግግር በሬዲዮ ውስጥ ተሳልፎ ወደ አድማጮቹ የሚመጣበት ሳይንሳዊ ሂደት እንዴት ሊከናወን ይችላል?
4. በአካባቢያችን ያለው ወንዝ ስያሜውን እንዴት ሊያገኝ ቻለ?
5. የውሻ በሽታ ከምን የተነሳ ሊከሰት ይችላል? መከላከያውስ ምንድነው?
6. ጨረቃ ስታበራ እየተመለከትን፣ እንዴት የራሷ ብርሃን የላትም ማለት እንችላለን?

## 11.2 ዕውቀት አገልግሎት ላይ የሚውልባቸው መንገዶች፤

- ✓ እናንተ ወደፊት ከፍ ያለ ዕውቀት ሲኖራችሁ ይህን ዕውቀታቸውን ለምን ለምን ዓይነት አገልግሎቶች ልታውሉት ታስባላችሁ?
- ✓ ከእናንተ መካከል አንደኛዋ ተማሪ"ዕውቀቴን ለምርምር ሥራ አውለዋለሁ" ብትልና፣ ሌላው ተማሪ ደግሞ ዕውቀቴን ራሴን ለማሻሻል አውለዋለሁ ቢል ከሁለቱ ተማሪዎች ማነው ትክክል ትላላችሁ? ለምን?
- ✓ መምህራችሁ ዕውቀት የሚከተሉት የአገልግሎት መንገዶች እንዳሉት ቢዘረዝሩላችሁና፣ እንድትወያዩባቸው ቢጋብዟችሁ፣ እያንዳንዱን አገልግሎት እንዴት ታስረዳላችሁ?

ዕውቀት አገልግሎት ላይ የሚሰጥባቸው ዐበይት መንገዶች፣

| | |
|---|---|
| ሀ. ለምርምር፣ | ለ. ለፈጠራ፣ |
| ሐ. ራስን ለማሻሻል፣ | መ. ለሀገር ዕድገት። |

### ሀ. ዕውቀት ለምርምር አገልግሎት፣

ዕውቀታችን እየጨመረ በሄደ ቁጥር የመመራመር ፍላጎታችንም ይጨምራል:: ምንም እንኳን ሌሎች ምሁራን አንድን ነገር ተመራምረን ደርሰንበታል ቢሉን ሙሉ በሙሉ ከማመን ይልቅ ራሳችን ፈትሸን ለማረጋገጥ ያለን ዝንባሌ ከፍ ይላል:: ስለሆነም ዕውቀት በነገሮች ዙሪያ ተጨማሪ ጥናትና ምርምር ለማድረግ በር ይከፍታል ማለት ነው:: ለምሳሌ እናንተ ወደፊት በትምህርታችሁ እየገፋችሁ ስትሄዱ እንደየዝንባሌያችሁ ምርምሮች ልታካሂዱ ትችላላችሁ:: አንዳንዶቻችሁ የእስከዛሬውን የኢትዮጵያን ወይም የአፍሪካን ታሪክ ልትመረምሩ ትፈልጉ ይሆናል::

ሌሎቻችሁ ደግሞ የሀገራችንን የግብርና ምርት ሊያሻሽሉ የሚችሉ ዘዴዎችን በተመለከተ ጥናትና ምርምር ልታካሂዱ ትችላላችሁ:: በዚህ የተነሳ ዕውቀት ለምርምር ሥራ የሚያግዝ ሲሆን፣ ምርምርም ተጨማሪ ዕውቀት ለማገኘት ያግዛል::

**ለ. ዕውቀት ለፈጠራ አገልግሎት፣**

እያንዳንዳችሁ ምን ምን የፈጠራ ዝንባሌ እንዳላችሁ አስቡ:: ብዙዎቻችሁ ከሥዕል፣ ከምሕንድስና፣ ከሙዚቃ፣ ከሥነጽሑፍ፣ ከቅርጻቅርጽ፣ ከጥልፍ፣ ከቆዳ ሙያና ከሸክላ ሥራ ወይም ከሌላ ዓይነት ዝንባሌዎች አንዱን ወይም ከአንድ በላይ ሊኖራችሁ ይችላል:: ከእነዚህም ሌላ የዓለም ሰዎች እንደፈለሰፏቸው እንደ መኪና፣ አውሮፕላን፣ ማምረቻ ማሽን ወይም እንደኮምፒውተር የመሳሰሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችንም አፍልቃችሁ መደነቅ ትፈልጉ ይሆናል:: አሁንም አንዳንድ ነገሮችን እየሞከራችሁ ሊሆን ይችላል:: እነዚህን የመሳሰሉ ጥበቦች የፈጠራ ችሎታ የሚያፈልቃቸው ናቸው::

በዚህ ረገድ ድንቅ የተባሉ ሰዎች በሀገራችንም ሆነ በዓለም ደረጃ አሉ:: በሀገራችን ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌን የመሳሰሉ ሠዓሊያን፣ እንደ ሎሬት ጸጋዬ ገብረመድኅን ያሉ ጸሐፍት ይጠቀሳሉ:: ታዲያ በኪነ ጥበብ ዘርፍ ብቻም ሳይሆን፣ በተፈጥሮ ሳይንስ እንደ ዶክተር አክሊሉ ለማ፣ እንዲሁም በማገዶ ቆጣቢ ቴክኖሎጂ የፈጠራ ባለቤትነት ሕጋዊ ማረጋገጫ ያገኙ ብዙ የፈጠራ ሰዎች አሉን::

ያለን ዕውቀት ሌላ ተጨማሪ ነገር እንድንፈጥር ሊያስችለን ይገባል:: ይህም ዕውቀት በራሱ ግብ ሳይሆን አዲስ ነገር መፍጠሪያ መሆኑን ያሰገነዝባል:: ለምሳሌ የሞባይል ስልክ ፈጠርን ብለን በዚሁ ረግተን አንቀመጥም፤ ደግሞ ከእሱ የተሻለ ሌላ የመገናኛ ዘዴ ለመፈልሰፍ እንጣጣራለን::

**ሐ. ዕውቀት ራስን ለማሻሻል ያለው ድርሻ፣**

የምንማረው ራስን ለመለወጥ መሆኑ አይካድም:: ከአሁኑ ትምህርታችንን በሚገባ ተምረንና አጥንተን እስከመጨረሻው በውጤታማነት ከዘለቅን፣ ወይም የራሳችንን ድርጅት ካቋቋምን የተሻለ ገቢ የምናገኝ ሰዎች እንሆናለን:: ያኔም ለሕይወታችን መሠረታዊ የሆኑ ነገሮችን በቀላሉ ማሟላት እንችላለን:: የተቸገሩ ወገኖቻችንና ያስተማረንን ማኅበረሰብም በተገቢው ሁኔታ ለመርዳት አቅም እናገኛለን:: ስለሆነም ዕውቀት ማግኘት ራስን ለማሻሻል መሠረታዊ ጉዳይ ነው::

***መ. ዕውቀት ሀገርን በማሳደግ ረገድ የሚጫወተው ሚና፣***

ኢትዮጵያ ከምትገኝበትና ሕዝቦቿም ከሚኖሩበት ድህነት መውጣት የሚችሉት ማንኛውም አኗኗር በዕውቀት ላይ ሲመሠረት ነው:: መቼም በእያንዳንዳችሁ ላይ ሀገርን የማሳደግና ከድኅነት የማውጣት ኃላፊነት እንዳለ ሳትገነዘቡ አትቀሩም:: ይህን ከተገነዘባችሁና አደራችሁን ለመወጣት ዓላማ ካላችሁ ደግሞ መሳሪያችሁ ዕውቀት መሆኑን መዘንጋት የለባችሁም:: በየትምህርት ቤቱ የምናገኘው ዕውቀት የሀገርን ችግር ለማስወገድና ዕድገቷን ለማፋጠን የሚረዳ መሆን ይኖርበታል:: በየመስኩ አስተማማኝ ዕውቀት ያላቸው ዜጎች ካልኖሩን ማኅበረሰቡን በተገቢው ሁኔታ ለመርዳት አቅም እናገኝም::

ስለሆነም ዕውቀት ማግኘት ራስን ለማሻሻል መሠረታዊ ጉዳይ ነው፣ የሀገር ችግሮች በሚፈቱበት ዙሪያ መፍትሔ የሚያመላክቱ ምርምሮች ይካሄዳሉ:: አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎችም ይፈልቃሉ:: ሳይንሳዊ አመለካከቶችም ሥር ይሰዳሉ:: እነዚህ ጉዳዮች ደግሞ ከሰፊ ዕውቀት የሚገኙ ሲሆኑ፣ አጠቃላይ ግባቸውም ሀገርን ማልማት ይሆናል:: ባጠቃላይ ማንኛውም ዜጋ ከጋን መብራትነት ወጥቶ፣ ለሀገሩ አኩሪ ተግባር ማከናወን የሚችለው፣ ያለውን ዕውቀት ለሀገር ዕድገት ሲያውል ነው::

**መልመጃ ፪**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. አንድ ሰው ያገኘውን እውቀት ራሱን ለማሻሻል ቢያውለው በተዘዋዋሪ መንገድ ሀገሩን መርዳቱ ነው ቢባል ዕውነት ነው ወይስ ሐሰት? ለምን?
2. ዕውቀት የፈጠራ ሥራን በማጎልበት ረገድ ምን ሚና ሊኖረው ይችላል?
3. ሰዎች በጉዳዮች ዙሪያ ጥልቅ ምርምር ያደርጉ ዘንድ የግድ ዕውቀት ያስፈልጋቸዋል? እንዴት?

## 11.3 በመረጃ ያልተደገፉ ጉዳዮች የሚያስከትሏቸው ችግሮች፤

"ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው::"
"ሳያጣሩ ወሬ፣ ሳይገሉ ጎፈሬ::"

- *ከዚህ በላይ ያሉት አባባሎች በመረጃ ያልተደገፉ ጉዳዮችን በተመለከተ ምን ሊጠቁሙ ይችላሉ?*

## ዋሾ

በድሮ ጊዜ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ አንድ ዋሾ የሚባል አሽከር ይኖር ነበረ፡፡ ይህ ሰው ባልና ሚስቱን ሊያጣላ አሰበ፡፡ ከዚያም አንድ ቀን ሌሊት ባልና ሚስቱ በሠላም አብረው ተኝተው እያለ ውሃ ለብ እስኪል አሞቀና፣ ቀስ ብሎ በሁለቱ መካከል አፈሰሰው፡፡ ውሃው እንደፈሰሰ ሁለቱም በየተራ ነቁ፡፡ ሆኖም በጉዳዩ ላይ አልተነጋገሩም፡፡ ባልዮውም ሚስቱ ሽንቷን የሳተች መስሎት መጠየቅ ስላፈረ ዝም አለ፡፡ ሚስቲቱም "እንዴት ባሌ ዛሬ ሽንቱን ሊስት ቻለ? ጤና አይደለም ይሆን?" በማለት መጠየቁ ስላሳፈራት ርጥበቱን ታግሳ ተኛች፡፡

በማግስቱ ባልዮው ብዙ ገበሬዎችን ደቦ ለምኖ እርሻ እያሳረሰ ነበረ፡፡ ሚስትዮዋም ለአራሾቹ ምግብ ለማዘጋጀት በቤት ውስጥ ከጎረቤት ሰዎች ጋር ደፋ-ቀና እያለች ትገኛለች፡፡ ይህ ዋሾ የተባለው ሰባቂ መጀመሪያ ወደ ሚስቲቱ ሄደና፣ "ዛሬ ባለቤትዎ እያረሱ ላሉት ገበሬዎች ስለእርስዎ በጣም መጥፎ ወሬ እያወሩላቸው ነው፡፡ ወሬውም ሚስቴ ዛሬ ሌሊት ሽንቷን ሸናችብኝ የሚል ነው" በማለት ነገራት፡፡ ሚስትዮዋም ባለቤቷ ለገበሬዎቹ እንዲህ ያለ ነውር ነገር እየተናገረ ስሟን በማጥፋቱ በጣም ተናደደች፡፡ ቶሎ መጥቶላት ለመጣላት ቸኮለች፡፡

ዋሾ እንደገና ወደባልዮው በመሄድ፣ "ባለቤትዎት እቤት ውስጥ ከሴቶቹ ጋር ስምዎትን እያጠፉ ነው፡፡" አለው፡፡

"ምን ብላ?" ሲል ጠየቀ ባልዮው፡፡

"ዛሬ ሌሊት ሽንቱን ስቶ አልጋውን አጥለቅልቆት አደረ እያሉ" በማለት መለሰለት፡፡

ባልዮውም እንዴት ራሷ ሽንታ ስታበቃ የኔን ስም ታጠፋለች በማለት ተናደደ፡፡ ከዚያም በቀጥታ ጠመንጃውን አንስቶ ወደቤቱ ገሰገሰ፡፡ ሚስትዮዋም ስታየው በክፉ ንግግር ተቀበለችው፣ እሱም እጅግ ተናዶ ነበርና ሁኔታውን ሳያጣራ ሚስቱን በጥይት ገደላት ይባላል፡፡

**መልመጃ ३**

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ሁለቱ ሰዎች ወደንዴት ከመግባታቸው በፊት ምን ማድረግ ነበረባቸው?
2. ተረቱ በመረጃ ሳይደገፍ ስለሚቀርቡ ጉዳዮች ምን ያስተምረናል?
3. እናንተ ዘንድሮ የስምንተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና እንደማይሰጥ ተወስኗል" የሚል ወሬ ድንገት ብትሰሙ ነገሩን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ምን ታደርጋላችሁ?

በየአጋጣሚው የተለያዩ መረጃዎች ወደ እኛ ሊመጡ ይችሉ ይሆናል፡፡ ከሚደርሱን ከእነዚህ መረጃዎች መካከል ግን የትኛው እውነት የትኛው ደግሞ ሐሰት እንደሆነ ለማጣራት ሊያስቸግር ይችላል፡፡ በእርግጥ አንዳንዶቹ እውነት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ሐሰት ቢሆኑም ያን ያህል ጉዳት ላያደርሱብን ይችላሉ፡፡ የተወሰኑት ግን በግለሰቦች ወይም በአካባቢ ወይም በሀገር ላይ ከፍ ያለ ችግር ሊፈጥሩ የሚችሉ ዓይነት መሆናቸው አይቀርም፡፡ አንዳንድ ነጋዴዎች አንድን ያልጠፋ ሸቀጥ እንደጠፋና፣ እጥረት እንዳለ በማስወራት በዕቃዎች ላይ ፍትሐዊ ያልሆነ ዋጋ ይጨምራሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ የሽብር ወሬዎችን በማስወራት የሕዝብን መንፈስ ያውካሉ፡፡

ስለሆነም በየአጋጣሚው የሚሠራጩ ወሬዎች ሁሉ እውነተኛ ናቸው ብሎ ከመደምደም በፊት፤

1. ከነጻና ለጉዳዩ ባለቤት ከሆኑ ታማኝ ምንጮች መምጣታቸውን ማረጋገጥ፣
2. ከአንድ ወገን ብቻ ሳይሆን ከእውነተኛ ምንጮች መምጣታቸውን ማወቅ፣
3. መረጃዎቹ አሳማኝ መስለው አልታይ ሲሉ፣ እንዳሉ ተቀብሎ ከማሰራጨት ይልቅ የነገሩን እርግጠኝነት ሊያጣሩ ከሚችሉ ታማኝና ሕጋዊ አካላት ዘንድ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት መጣር፣
4. ከቃላዊ መረጃ ይልቅ በሰነድ ላይ የሰፈሩ ወይም በጽሑፍ የቀረቡ ምንጮችን እንደአማራጭ መውሰድ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ይህ ካልሆነ ግን አንዳንድ ግለሰቦች ወይም ለሠላምና ለሥነልቡናዊ መረጋጋት ጠንቅ ሊሆኑ የሚችሉ አካላት የራሳችንንም ሆነ የአካባቢያችንን ሕዝብ ሠላማዊ እንቅስቃሴ ሊያውኩ ይችላሉ፡፡ አልፎ ተርፎ በሕዝቦችና በቡድኖች መካከልም ግጭቶችንና ሁከትን ሊቀሰቅሱ ይችላሉ፡፡ ይህ ሁሉ ቢቀር፣ ያልተጨበጠ ነገር አቀብለውን እኛም እውነት ነው ብለን እንድናወራና ውሸት ሆኖ ሲገኝ ግን ከትዝብት ላይ እንድንወድቅ ሊያደርጉን ይችላሉ፡፡

**መልመጃ 4**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. አንድ መረጃ አስተማማኝ ነው የሚባለው ምን ሆኖ ሲገኝ ነው?
2. ያልተረጋገጡ መረጃዎችን ለመቀበል መጣደፍ ምን ዓይነት አጉል ገጽታ አለው?
3. እውነትነታቸው የሚያጠራጥር መረጃዎች ሲያጋጥሙን ምን ማድረግ ያስፈልገናል?
4. ያልተረጋገጡ ጉዳዮች በአንድ አካባቢ ላይ ምን ምን ጉዳቶችን ሊያስከትሉ ይችላሉ?
5. የአካባቢያችሁ ሕዝብ ባልተረጋገጡ መረጃዎች እንዳይወናበድ እናንተ ምን ሚና መጫወት ይገባችኋል?

## 11.4 ኋላቀር አስተሳሰቦችና አመለካከቶች፤

- ✓ ኋላቀር አስተሳሰብ ከምን የተነሳ ሊመጣ ይችላል?
- ✓ በአካባቢያችሁ ምን ዓይነት ኋላቀር አመለካከቶች አሉ? እንዴትስ በተራማጅ አስተሳሰቦች ሊተኩ ይችላሉ?
- ✓ እነዚህን ኋላቀር አመለካከቶች በማስወገድ ረገድ ድርሻችሁ ምን መሆን አለበት?

ኋላቀር አስተሳሰቦች ከባህላዊው አመለካከት እንደሁኔታው እየተወረሱ ለትውልድ የሚሸጋገሩ ናቸው። ይህም ማለት ቀደም ሲል የነበሩት ትውልዶች በዘመናቸው ያምኑባቸውና ይመሩባቸው የነበሩት አንዳንድ አመለካከቶችና ማኅበራዊ መርሆዎች በአዲሱ ዘመንም እንዳስፈላጊነቱ ሳይሻሻሉ ወይም ሳይወገዱ የሚቀጥሉበት ሁኔታ ነው። አመለካከቶቹ በጥንቱ ዘመን ተቀባይነት ያገኙ ሊሆኑ ይችላሉ። አሁን ባለው የዕድገት ደረጃ ማዕቀፍ ውስጥ ግን ተቀባይነታቸው ቀንሷል ወይም ቀርቷል።

ለምሳሌ የተለያዩ የዕደጥበብ ባለሙያዎችን ዝቅ አድርጎ መመልከትና ሙያቸውንም ማጣጣል በጥንቱ ዘመን የተዘወተረ ነበር። በአሁኑ ዘመን ግን ባለሙያውም ሆነ ሙያው የሚከበሩ ናቸው። አንዳንድ ሰዎች ራሳቸውን የትልቅ ሰው ዘር አድርገው የሚመለከቱበት ወቅትም ነበር፤ ዛሬም አልፎ አልፎ ይህ አመለካከት ያላቸው አይጠፉም። ዛሬ የሰዎች ንቃተ ሕሊና እየጨመረና አስተሳሰቡም እየተለወጠ ሲመጣ ይህ አመለካከት ፍጹም ኋላቀርና ተራ የመኮፈስ ምልክት ሆኗል። በነባሩ ማኅበረሰብ እምነት ሴት ልጅ ወላጆች መርጠው ያመጡላትንና የማታውቀውን ሰው እንድታገባ ይደረግ ነበር። ባለንበት ዘመን ግን የጋብቻ ሕይወቷን በራሷ ምርጫ ላይ መመሥረት አለባት የሚል አመለካከት መምጣት ብቻም ሳይሆን ሕገመንግሥታዊ መብትም ነው። ስለዚህ የአንዱ ዘመን ማኅበራዊ ፍልስፍና ለሌላውም ይሠራል ማለት አይቻልም፤ ዘመኑ ሲያልፍ አብሮ ያልፋል።

በዚህ የተነሳ ኋላቀር አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን ማስወገድ ያስፈልጋል ማለት ነው። ኋላቀር አመለካከቶችን ለማስወገድ ዋናው መርሕ ደግሞ በምክንያትና በዕውቀት በተደገፈ አመለካከት ላይ መመሥረትን ልማድ ማድረግ ነው። በምክንያት ላይ ተመሥርቶ የሚያስብ ሰው ለነገሮች ጥልቅ አመለካከት ስለሚኖረው በተራ ግምት ከውሳኔ ላይ አይደርስም ወይም በጭፍን እምነት ወደሚያምኑ ሰዎች አመለካከት አይሳብም። ለምሳሌ በጭፍን እምነት ላይ በመመሥረት የሚኖሩ ሰዎች የአንጥረኛ ሙያን የሚያጣጥሉበት ሳይንሳዊ ምክንያት የላቸውም። በምክንያት የሚያምን ሰው ግን የዚህን ሙያ ክቡርነት በምክንያት አስደግፎ ለማስረዳት በቂ ማስረጃ ማቅረብ ይችላል።

እያንዳንዱ ሰው በጌጣጌጦች ተውቦ እንደሚሄድና እነዚህን ጌጣጌጦች በልዩ ልዩ ቅርጽ የሚሠራቸው ደግሞ አንጥረኛው ባለሙያ መሆኑን አብራርቶ ማስረዳት አይሳነውም። ከዚህም አልፎ በዚህ ሙያ የተሠማሩ ሰዎች የተሻለ ገቢ የሚያገኙ በመሆናቸው ራሳቸውን አሻሽለው የሚኖሩና ወገናቸውንም በከፍተኛ ደረጃ የሚደግፉ መሆናቸውን አስረጅዎችን በማቅረብ ለማሳየት አያቅተውም። በዚሁ ሁኔታ እያንዳንዱ ሐሳብ ወይም የሕይወት ፍልስፍና በተጨባጭ ማስረጃ ላይ ተመሥርቶ መቀበል ወይም አለመቀበል እንጂ፣ አባቴ ወይም እናቴ ያምኑበት ነበር በማለት መቀበል ለራስ መሻሻልም ሆነ ለሀገር ዕድገት ሊጠቅም አይችልም።

ባጠቃላይ ሀገራችን እንድትበለጽግ፣ ሕዝባችንም የተሻለ ዕውቀት እንዲኖረው ኋላቀር አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን ማስወገድ ተገቢ ይሆናል።

**መልመጃ 5**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን እየሆናችሁ ተወያዩባቸው።***

1. ኋላቀር አመለካከቶች እንዴት ሊከሰቱ ይችላሉ?
2. ኋላቀር አመለካከቶች በአንድ ሕዝብ ልማት ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ አላቸው?
3. በምክንያት የጐለበተ አመለካከት ማራመድ ከኋላቀር አስተሳሰቦች ለመራቅ እንዴት ይረዳል?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ዕውቀት በአራት ዋና ዋና መንገዶች ሲዳብር ይችላል፡፡ እነሱም መደበኛ ትምህርት፣ መደበኛ ያልሆነ ትምህርት፣ መገናኛ ብዙኃንና ንባብ ናቸው፡፡ አንድ ሰው በአራቱም መንገዶች ወይም ከአራቱ በተወሰኑት መንገዶች ዕውቀቱን ሊያጎለምስ ይችላል፡፡ ይሁንና ዜጎች በማንኛወም ሁኔታ ራስን ለመለወጥና ወገንንና ሀገርን በላቀ ደረጃ ለመጥቀም እንዲችሉ  ትምህርት ቤቶች የጎላ ድርሻ አላቸው፡፡

የሰው ልጅ በዕውቀት እየጎለመሰ ሲሄድ በዚያው ልክ የመመራመር ዝንባሌውም ይጨምራል፡፡ በምርምርም የአካባቢውንና የሀገሩን ችግሮች ለመፍታት ይችላል፡፡ ዕውቀት የፈጠራ ችሎታን ባግባቡ እንድንጠቀምበትም ያግዛል፡፡ የተለያዩ የጥበብ ፈጠራዎች በዕውቀት የታገዙ ናቸው፡፡ የተዋጣለት የሥነጽሑፍ ወይም የምሕንድስና ጥበብ ባለቤት ለመሆን የጠለቀ የሙያው ዕውቀት መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ ዕውቀት ራስን የመለወጥ ፋይዳውም በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ከፍ እስካለ ደረጃ የተማረና በዕውቀቱ የበለጸገ ሰው፣ ተቀጥሮ ለራሱ ሥራ ፈጥሮ በሚያገኘው ገቢ የተሻለ ተጠቃሚ መሆኑ አይካድም፡፡ ከዚህም አልፎ ዜጎች በትምህርታቸው ሲገፉና፣ በሀገሪቱ የተማረ ሰው ሲበረክት ዕውቀታቸው ለሀገር ዕድገት የሚያገለግል ይሆናል፡፡ የተማረ የሰው ኃይል ሳይኖር የሀገርን ብልጽግና ማሰብ አይቻልም፡፡ ለሀገር ብልጽግና የሚያስብ መንግሥት አስቀድሞ በትምህርት መስፋፋት ላይ መሥራት አለበት የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡

© MoE, FDR
Not to be repu

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**አስተማማኝ መረጃ:-** እርግጠኛውን ጉዳይ በትክክል ከሚያውቁ አካላት ወይም ግለሰቦች የሚገኝ ፍትሐዊና ሐቀኛ መረጃ::

**ቃላዊ መረጃ:-** በጽሑፍ ያልተያዘ ወይም በሌሎች መሣሪያዎች ተቀርጾ ያልተያዘ፣ በግለሰቦች ዘንድ በቃል ደረጃ የሚዘዋወር እርግጠኝነቱ የሚያጠራጥር መረጃ::

**ጦር የፈታው:-** በጦር ሜዳ ላይ ተዋግቶ ድል የሆነ ወይም በጦርነቱ የተሸነፈ::

**ወሬ የፈታው:-** በአሉባልታ ወይም ባልተረጋገጠ መረጃ መንፈሱ ተሸብሮ ከዓላማው ያፈገፈገ::

**ሳይንስ:-** ዕውነትነታቸው በተጨባጭ በተፈተኑ መረጃዎችና ዕውቀት ላይ የተመሠረተ የአስተሳሰብና፣ የአኗኗር የሰው ልጆች ዘመናዊ ዘዴ::

**ምርምር:-** ነገሮችን፣ መረጃን፣ ዕውቀትን እየመላለሱ መፈተሽና ምንነቱን መረዳት/ማረጋገጥ::

**ራስን ማሻሻል:-** በኑሮ ውስጥ መሠረታዊ ፍላጎቶችን በበቂ ደረጃ አሟልቶ ለመገኘት መቻል::

© MoE, FDRE Not to be republished

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

## I *የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ::*

1. ከኋላ ቀር አመለካከቶች መካከል አንደኛው በፈጠራ ሥራዎች መጠመድ ነው::
2. ሳይንሳዊ አመለካከት ሲበለጽግ ጎታች አመለካከት እየመነመነ ይሄዳል::
3. ሕይወትን ለማሻሻል ዋናው ተፈላጊ ነገር ከዕውቀት ይልቅ ሀብት ነው::
4. "ከዕውቀት ማዳበሪያ መንገዶች ዋናው መደበኛ ትምህርት ነው" የሚባልበት ምክንያት፣ ትምህርት ቤት ወጥነት ባለው የትምህርት ሥርዓት የሚመራ የእውቀት ማዕከል ስለሆነ ነው::
5. ሁሉም የሬዲዮ ጣቢያዎች አስተማማኝ የመረጃ ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ::

## II *በ "ለ" ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ::*

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የዕውቀት ዋናው ምንጭ፣ | ሀ. ያላጣራ ጆሮ ከጎረቤት ያጣላል። |
| 2. መገናኛ ብዙሃን የሚለው እሳቤ፣ | ለ. ከሕጋዊና ከሐቀኛ ምንጮች ይገኛል። |
| 3. አስተማማኝ መረጃ፣ | ሐ. እንደሬዲዮና ጋዜጣ ያሉትን ያጠቃልላል። |
| 4. የሕዝብን ሠላም ሊያውኩ ይችላሉ፣ | መ. ያልጠረጠረ ተመነጠረ። |
| 5. የተዛባ መረጃን ጉዳት ይጠቁማል፣ | ሠ. በእርግጠኛ መረጃ ላይ ያልተመሠረቱ ጉዳዮች። |
| | ረ. ትምህርት ቤት። |

## III *ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ::*

1. ኋላቀር አስተሳሰቦች ሊቀየሩ የሚችሉት መቼ ነው?
   ሀ. ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ሲስፋፋ፣　　ለ. ለቃል መረጃዎች የበለጠ ትኩረት ሲሰጥ፣
   ሐ. ባሕላዊ ትምህርት ሲስፋፋ፣　　መ. ሁሉም።
2. ስለዕውቀት አገልግሎት ትክክል የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ለምርምር ተግባር ሊውል ይችላል፣
   ለ. ባህላችንን እንድንጠላ የሚያደረግ መንፈስን ይፈጥርብናል፣
   ሐ. ልምዶቻችንንና ትውፊቶቻችንን በሙሉ ማስወገድ የሚያስችለን መሆን አለበት፣
   መ. ሁሉም መልስ ነው።
3. ከሚከተሉት መካከል የተሻለ የዕውቀት ምንጭ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?
   ሀ. ቴሌቪዥን፣　　ለ. ቃላዊ መረጃ፣　　ሐ. የስብሰባ ላይ ውይይት፣　　መ. ትምህርት ቤት
4. ዕውቀት ራስን ለማሻሻል የሚረዳው እንዴት ነው?
   ሀ. ወደውጪ ሀገራት ሄደን እንድንሠራ ዕድል በመክፈት፣
   ለ. ብልጣብልጥ ነጋዴ እንድንሆንና ያልታሰበ ትርፍ እንድናገኝ በማስቻል፣
   ሐ. ለአንድ የሙያ ዘርፍ ብቻ ፍቅር ያላቸው ዜጎች ስንሆን፣
   መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናል::
5. ከሚከተሉት መካከል የኋላቀር አስተሳሰብ የማይስተዋልበት የትኛው ነው?
   ሀ. ሴትን ልጅ ማስተማር ለሁሉም ይጠቅማል፣
   ለ. ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ፣
   ሐ. ልጅና ጦጣ ውሃ ይጠጣ፣
   መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ::

## IV *የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::*

1. በኢትዮጵያ ዝቅተኛ እንደሆኑ ይቆጠሩ ከነበሩ ባለሙያዎች ውስጥ አንዱ----------- ነው።
2. ዕውቀት አገልግሎት ላይ ከሚውልቡቸው መንገድ ውስጥ ---------- እና -------- ይጠቀሳሉ።
3. ------------- በሰዎች ወይም በቡድኖች መካከል አለመግባባቶችን ሊፈጥሩ ይችላሉ።

### V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. የሳይንሳዊ ዕውቀት ዐበይት ምንጮች ምንድናቸው?
2. ንባብ እንደ አንድ የዕውቀት ማዳበሪያ መንገድ የተቆጠረበት ምክንያት ምንድነው?
3. ኋላቀር አስተሳስብ ጎጂ ሊሆን የሚችለው በምን በምን ምክንያቶች ነው?
4. ሁሉም የአበውና የእመው አስተሳሰቦች ኋላቀር ተብለው ሊፈረጁ ይችላሉ? እንዴት?
5. ኋላቀር አመለካከቶችን በማስወገድ ሂደት ውስጥ ወጣት ተማሪዎች ምን ዓይነት ሚና መጫወት ይችላሉ?

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished